
Who is "Mr. 666?"
666 የወደፊቱ ዓለም መመሪያ
Who is Mr. 666?
የንግድ ምልክት
FUTURE WORLD SOSIETY=FWS
ፍካሬ
666
U. S. NAVY
Kerman Scott Ltd.
666
POLYESTER 60% COTTON
PERMANENT PRESS
Close-up of shirt labels from Red China
LEAR SIEGLER INC.
LSI
666
LSI Computers" made in the U.S. and shipped to Israel have on them this inspection seal. (Courtesy of Dr. Jack Van Impe) This depicts the "666 System" in the U.S.
PRESIDENT CARTER'S

# ፍካሬ 666

መጋቢ ተኩ ከበደ

እትም አንድ 1993
እትም ሁለት 1999

መጋቢ ተኩ ከበደ

እትም ሁለት ለጉለሌ አዲስ አበባ መሠረተ
ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠ

ይህንን መጽሐፍ ያለ ደራሲው
ፈቃድ ማባዛትም ሆነ ማሳተም
በሕግ የተከለከለ ነው።

Copy Right © 2000 by Pastor Teku kebede

© 2007

All Rights Resereved

Printed In Ethiopia



## ምስጋና

ይህ ፅሁፍ በዚህ ዓይነት እንዲዘጋጅ ሁኔታዎችን ያመቻቸልኝን ጌታዬንና አምላኬን እግዚአብሔርን ከሁሉ አስቀድሜ አጥብቄ አመሰግነዋለሁ።

ፅሑፉን በኮምፒዩተር በማዘጋጀትና በማደፋፈር ያስማቋረጥም በፀሎት የረዳችኝን ውድ ባለቤቴን ምሥራቅ አበበን እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።

አስፈላጊ ነገሮች ተሟልተው ሳሉ ከ10 ዓመታት በላይ አሳትሜ ለማቅረብ ጋሬጣ ሆኖብኝ የነበረውን የገንዘብ እጥረት መሰናክል በማስወገድ መጽሐፉን ለህትመት ያበቁትን የደቡብ አዲስ አበባና የጉለሌ መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ምዕመናን በክርስቶስ ምህረትና ፍቅር እባርካለሁ።

በመጨረሻም ለዚህ መጽሐፍ ህትመት ቅድመ ዝግጅት ፍፃሜ ማግኘት በፀሎት፣ ሐሳብ በመስጠት፣ በመምከር፣ እንዲሁም በተለያየ መንገድ አብረውኝ የቆሙትን ለዚህ ጽሑፍ እርማት በማድረግ እንዲሁም አስተያየትን በመፃፍ የረዱኝንና ሌሎችንም በየክፍለ ሃገሩ ያሉ ወገኖችን ከልብ አመሰግናለሁ።

የሥራው ባለቤት ጌታ ይባርካችሁ!

መጋቢ ተኩ ከበደ

# መግቢያ

በዘመናት መካከል የእስራኤልንና የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ከእግዘአብሔር ጋር ካላቸው ግንኙነት አኳያ ስንገመግም እግዚአብሔር ያዘነባቸውን ብዙ ነገሮች ማየት እንችላለን:: ከእነዚህም ውስጥ ዋነኛው በነቢያቱ በኩል ለተላለፈው መልዕክት ሕዝቡ ልባዊ ትኩረትና ምላሽ አለመስጠታቸው ነበር:: መሢህ እንደሚወለድ ትንቢት ተነገረ ለትንቢቱ ቃል ሙሉ ሳይሆን ከፊል ማስተዋል ተሰጠው ዘመኑም በግማሽ ልብ ተመረመረና መሢህ በቤተልሔም ይሁዳ መወለዱ ታወቀ:: ሆኖም ከ28 ዓመት በኋላ መሢህ በቤተልሔም ይሁዳ መወለዱ በጥንቃቄ ሳይጤን ቀርቶ ከገሊላ እንደተወለደ ተቆጥሮና እንደ ጠላት ታይቶ በስቀለው ነጐድጓዳዊ ድምጽ ተገደለ::

በአሁኑም ዘመን የክርስቶስ ዳግም ምፅዐት እውነትነቱ በቤተ ክርስቲያን ዘንድ ቢታወቅም ለመቀበል ያለው ዝግጅት ግን በጣም አሳፋሪ ሆኗል:: ቀኑ እንዳልቀረበ ወይም ምፅዐቱ እንዳሌለ በማሰብ ሊሆን ይችላል:: የእስራኤልን ታሪክ ስናስብ አመድ በዱቄት ይስቃል እንደተባለው በእኛም እንዳይሆንብን የዘመኑ ዳግም ልደትን ያገኘን ቤተ ክርስቲያናት ዘመኑን በጥንቃቄ ልንመረምርና ርምጃ ልንወስድ ይገባል::

ስዚህም ይረዳ ዘንድ የፍካሬ-666 መጽሐፍ የጌታ ምፅዐትና የቤተ ክርስቲያን በደመና መነጠቅ ጊዜ በጣም መቅረቡን ለማሳየት በጥቂት ስዕላዊ ማስረጃዎች ተደግፎ ቀርቦልናል:: መጽሐፉ አራት ክፍሎች ያሉት ሲሆን፤

<u>ክፍል አንድ</u> የ666 ትንቢት መሠረትና የመጻህፍት ራስ ስለሆነው መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኝነት፣ ስለመጽሐፍ ቅዱስ ታላላቅ ሰዎች የተናገሩትን ዕንቁ ምሥክርነቶች ይገልጻል:: በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ ከያዛቸው 6208 ትንቢቶች ውስጥ ዋነኛ ስለሆነው ምድራችንም እየሰጠመችበት ያለው የ666 ብቸኛ መንገድ ጠራጊ እንዲሁም የሐጢአት ሙላት መግለጫ የሆነው ክህደት እንዴት ሰዎችን እያጥለቀለቀ መሆኑን ያሳያል::



<u>ክፍል ሁለት</u> ደግሞ ስለ666 አጀማመር፣ ቁጥሩ ከአውሬው ወይም ከሐሰተኛው ክርስቶስ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት፣ አገልግሎት፣ የአውሬውንና የክርስቶስን ተከታዮች እንዴት ተፅዕኖ እንደሚያደርስባቸው እንዲሁም የቁጥሩ ባለቤት አውሬው ከእስራኤል ከቤተ ክርስቲያን፣ ከሰይጣን ስላሴ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነትና በመጨረሻም ስለአውሬው ፍጻሜ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን ትንቢታዊ ይዘት ይገልጻል::

<u>ክፍል ሦስት</u> በክፍል ሁለት ስለ666 የተተነበየው ዕውነት በምድራችን ላይ ያለውን የ666ን ወቅታዊና ታሪካዊ እንቅስቃሴ በዝርዝር የሚያሳይ ነው:: 666 ከኮምፒውተርና ከግለሰብ ስሞች ጋር እንዲሁም ከልዩ ልዩ ዕቃዎችና ከመናፍስት ጋር ስላለው ጥልቅ ግንኙነት ይገልጻል::

በመጨረሻው በ<u>ክፍል አራት</u> የ666 ትንቢታዊና ታሪካዊ እንቅስቃሴ ዕውነት ከሆነ በምድሪቱ የሚኖሩ አማኞችና ከሃዲዎች ሁሉ ተጠያቂዎች መሆናቸውን በማሳየት ከአውሬውም ሆነ ከክርስቶስ ኢየሱስ ለሚቀርብላቸው የስንዱልኝ ጥያቄ ከዚያም የፍርድ ቀን ሃዘን መልስ ለመስጠት እንዲዘጋጁ የሚጋብዝ ነው::

የመጽሐፉ ዐቢይ ዓላማ ስለ666 በትንቢት መልኩ መልዕክትን ያስተላለፈልን መጽሐፍ ቅዱስና ደራሲው መንፈስ ቅዱስ የተናገረው ከ1900 ዓመታት በኋላ ጊዜው ሲደርስ መፈጸሙ የቃሉን እርግጠኝነት እንድናይ ለማድረግ ሲሆን፤ ሁለተኛው ዓላማ ደግሞ የተተነበየው አሁን እንደታየ ሁሉ ገና ያልተፈጸመውም የአውሬው በግልጽ መምጣት፣ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅና የክርስቶስ ኢየሱስ በዚህ ዓለም ላይ ሊፈርድ መመጣቱም ዕውነት መሆኑን በማሳየት ራሳችንን ወደ ክርስቶስ ኢየሱስ በንጽህናና በቅድስና እንድናቀርብ ለማሳሰብ ነው::

አስጀምሮ ያስጨረሰኝ ዕውነተኛው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተመሰገነ ይሁን!!

## መክስተ አርዕስት


**ክፍል አንድ ነገረ ፍጻሜ በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች**

1.1. የመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛነት
1.2. የመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛነት ማረጋገጫዎች
1.3. ታላላቅ ሰዎች ስለመጽሐፍ ቅዱስ የተናገሩት
1.4. በዘመናት ርዝመት ዕንቅልፍ ዕንቅልፍ ሲል
1.5. ዘመን መርማሪው ሰው
1.6. ከ6208 ትንቢቶች ሁለቱ
- ትንቢተ-ክህደት
- የዘመኑ የክህደት ዓይነቶች
  - መሠረታዊ የአውሬውና የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አስተምህሮ
  - የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ዓላማና ትኩረት
  - ፀረ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንቅስቃሴ
  - ክህደትና የአባታችን ሆይ ፀሎት
  - ክህደተ-አሥርቱ ትዕዛዛት
  - ምዕዓተ-ውዳሴ ሰይጣን
  - ነፍስም እንደ ሸቀጥ

**ክፍል ሁለት ፍካሬ 666**

2.1. የ666 አጀማመር
2.2. የአውሬው ስሞች
2.3. የአውሬው ባህሪያትና ዓላማዎች
2.4. የአውሬው የግዛት ክልል
2.5. የአውሬው ተከታዮች
2.6. አውሬው የሚገዛበት ጊዜ (70ኛው ሱባኤ)
2.7. አውሬውና ጋስሞታይቱ
7.8. አውሬውና እስራኤል
2.9. አውሬውና ቤተ ክርስቲያን
2.10. አውሬውና የሰይጣን ሥላሴ
2.11. የአውሬው ፍጻሜ





**ክፍል ሦስት: ዕይታ 666**

3.1. የዓለም ሕዝብ መሪዎች ጩኸት
3.2. 666 የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ መብራት
3.3. 666 በኮምፒዩተር "COMPUTER" ውስጥ
- የኮምፒዩተር አመጣጥና ምንነት ዓይነቶች ጥቅም ቋንቋና አሠራር
- ኮምፒዩተር እንደ እግዚአብሔር፣ ኮምፒዩተር የሰውን አእምሮ ሲቆጣጠር፣ ኮምፒዩተራዊ ኢንተርኔት
- የ"COMPUTER" ስሌት

3.4. 666 የታየባቸው ዕቃዎችና ሁኔታዎች
3.5. የ666 ማንነት
3.6. የ666 ዘመን ማየል
3.7. ስለ 666 የሚነሱ ጥያቄዎች
3.8. የ1997 ዓ.ም መረጃዎች

**ክፍል አራት መጥኔአዊ ዲላማ**

4.1. አረማዊ?
4.2. ከያኒ?
4.3. ተምኔታዊ?
4.4. የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ?
4.5. መሰቃዊ?
4.6. ዘንገሊል?
4.7. መሃል-ሰፋሪ?
4.8. ቅይጣዊ?
4.9. ፈሪ?
4.10. ፖለቲከኛ?
4.11. ኃይማኖታዊ?
4.12. ከሃዲ?
4.13. መናፍስት ጠሪ? ጠንቋይ? ሟርተኛ?
4.14. ቤተ ክርስቲያን

ግርጌ ማስታወሻ
የቃላት መፍቻ
ምህፃረ-ቃላት

"ፍካሬ 666" ስለዘመኑ መጨረሻ በቂ ግንዛቤ ለሌለው ክርስቲያን ቀስቃሽ መልዕክት ያዘለ መጽሐፍ ነው:: ደራሲው ልዩ ልዩ ስዕላዊ ማስረጃዎችን ለመሰብሰብ ያደረጉት ጥረት የሚደነቅ ነው:: የእግዚአብሔር ሰዎች በጥልቀት ሳያረዱ ለአውሬው እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታዎች እየፈጠሩ መሆኑን ደራሲው ስዕላዊ መግለጫዎችን በመጠቀም ፍካሬ 666ን ጽፈዋል:: የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ስለዘመኑ መጨረሻ በማስተማርና በመስበክ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ሲያደርጉ ቆይተው ይህንን መጽሐፍ አዘጋጅተው ለአንባቢ ሊያቀርቡ በመቻላቸው በአገልግሎታቸው እግዚአብሔር አዲስ መገለጥና ራዕይ እንዲሰጣቸው እመኛለሁ::

(ዮሐንስ ገርማሞ:- በመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የወንጌል ስርጭትና ሚሲዮናዊ ተልዕኮ ተጠሪ)

"ፍካሬ 666" ስለዘመናት ለተዘናጋ ክርስቲያን የማንቂያ ደወል ከመሆኑም በላይ ስለመጨረሻው ዘመን ምንም ግንዛቤና እውቀት ለሌላቸው እንዲሁም አለ እንዴ! በማለት ካለማወቅ የዘመኑን ፍጻሜ ወደማወቅ፣ በቂ ግንዛቤን በመጨበጥ በጥንቃቄ ለመኖርና የሕይወት ጉዳናን ለማስተካከልና ለቀጣዩ ትውልድም እጅግ የሚጠቅም መጽሐፍ ሆኖ አግኝቼዋለሁ:: ስዕላዊ መግለጫዎችም በትክክለኛ ቦታ መቀመጣቸው የደራሲውን ብስለት የሚጠቁሙ በመሆናቸው ያነበበ ሁሉ ክዚህ በላይ እስተያየቱን እንደሚቸር እርግጠኛ ነኝ::

መጋቢ አዳነ ኪዳነማርያም
ጉለሌ አዲስ አበባ
መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን



# ክፍል አንድ

## ነገረ ፍጻሜ በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች

### 1.1 የመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛነት

ስለ ነገረ ፍጻሜ ስናስብ በውስጡ ያለውን እውነት ጥርት ባለ ሁኔታ ለመረዳት የሚያስችለንን መጽሐፍ ቅዱስ መቃኘት አማራጭ የሌለው እርምጃ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዓለም አጀማመር፣ ሂደትና ፍጻሜ በዝርዝር ይነግረናል:: የእነዚህንም ነገሮች እርግጠኝነት ለመቀበል የሚቸገሩ ክፍሎች መኖራቸው ይታወቃል:: ይህም ቢሆን በትህትናና በማስተዋል፣ ጊዜንና የጸጥታ ቦታን በማመቻቸት የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ለሚመረምሩ ሁሉ እውነት ራሷን ትገልጥላቸዋለች:: ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ወደ እውነት ለማድረስ መልአኩን፣ ፊልጶስንና መንፈስ ቅዱስን የላከ ጌታ ዛሬም እውነት ፈላጊዎችን ወደ ህይወት ሊያደርሳቸው ፈቃደኛ ነው:: ሰዎችም ፈቃደኞች ሊሆኑ ይገባቸዋል::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታሪኮች፣ ሕግጋት፣ ወንጌላት፣ ቅኔዎችና፣ ትንቢቶች ወዘተ በዝርዝር ተጽፈዋል:: ሁሉም የእግዚአብሔርን፣ የሰይጣንንና የሰዎችን ወዘተ ያለፈ፣ አሁን እየሆነ ያለውንና ሊመጣ ያለውን ትዕይንት ያመለክታሉ:: በተለይ ስለ ወደፊቱ የዓለም ትዕይንቶች በመጽሐፍ ቅዱስ የተተነበዩትን እውነቶች ስንመረምር ብዙ የምናተኩርባቸው ነገሮች ይኖራሉ:: ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የፍጻሜ ዘመን ምልክቶች፣ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ፣ የ70ኛው ሱባኤ (የሰባት ዓመት) መከራ፣ የጌታ ኢየሱስ ከቅዱሳኑ ጋር በምድር ለመንገስ ከሰማይ መምጣት፣ የሺህ ዓመት መንግሥትና የዘላለም መንግሥት (የአዲስ ሰማይና ምድር) ሥርዓት መጀመር ናቸው::

ከላይ ከተዘረዘሩት ዐቢይ የፍጻሜ ዘመን ትዕይንቶች ውስጥ በ70ኛው ሱባኤ (በ7ቱ ዓመታት የመከራ ዘመን) የሚፈጸመው ትዕይንት ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል:: ምክንያቱም በዚህ ዘመን አውሬው በመባል የሚታወቀው ሐሰተኛ ክርስቶስ ስለሚመጣና ወዲያውም የእርሱና የዓለም መንግሥታት ምድራዊ አሰራርና አገዛዝ ማብቂያ ለመቃረቡ ከመጨረሻው ዘመን ምልክቶች ውስጥ ዋነኛው ስለሚሆን ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ ነው:: ምክንያቱም ደራሲው እግዚአብሔር የሆነው መንፈስ ቅዱስ ቅዱሳን በሆኑ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ምሪት እንዲጻፍ በማድረጉ ነው:: ይህንንም «ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ» የሚለው ቃል ያረጋግጥልናል:: 2ኛጴጥ. 1:21 እግዚአብሔር እውነት ነው:: ዮሐ. 14:6፤ እርሱ እውነት ከሆነ ደግሞ ቃሉም እውነት ነው:: ዮሐ. 17:17:: ከቃሎቹም ውስጥ አንዱ በትንቢት መልክ የተገለጸው ነው:: የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ምንጩ መንፈስ ቅዱስ ከሆነ እውነት ነው ማለት ነው:: ትንቢቱን የተናገሩት ሰዎች ቅዱሳን

እንዲሆኑ ያስፈለገበት ምክንያት ርኩሳን የሆኑ ተንባዮችም በአጋንንት መንፈስ ተነድተው ስለመፈለሻው ዘመን መናገራቸው መታወቁ ነው:: ሐሰተኞች ሲተነብዩ ቀድሞ ከተባለው ተነስተው ስለሚሆን ትንቢታቸው እንደ እውነት ተቆጥሮ ዋጋ ሊቀበሉበትና ቦታ ሊሰጣቸው አይገባም:: ሰማይና ምድር ሲያልፉ ቃሌ ግን አያልፍም የተባለለት የእግዚአብሔር ቃል እውነት ግን ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል::

## 1.2 የመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኝነት ማረጋገጫዎች

መንፈሱ በመንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ አሠራር ዳግም ልደትን ያገኘም ሰው ይሁን ያላገኘ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ሲያጠና ስለቃሉ እርግጠኝነት አንዳንድ ጥያቄዎች ሲነሱበት እንደሚችሉ እሙን ነው:: ይህም ሲሆን ደግሞ ሰው ምላሽን ይፈልጋል:: «ይህን ያነበብኩትን በእምነት እውነት ነው ብዬ ብቀበለው ለራሴ አእምሮም ሆነ ለሌሎች ለሚጠይቁኝ ምን ምላሽ ይኖረኛል»? የሚል ጥያቄ በአእምሮው ቢፈጠር ቀጥሎ የተዘረዘሩት መረጃዎች ጠቃሚ መሣሪያዎች ሊሆኑለት ይችላሉ::

በተለያዩ ዘመናት የተነሱ ብዙ የሥነ መለኮት አጥኚዎች መጽሐፍ ቅዱስ በህይወታቸውና በሌሎች ህይወት ያሳየውን ለውጥ በመገምገም ስለትክክለኛነቱ ብዙ ማስረጃዎችን ጠቅሰዋል:: ከእነዚህም ማስረጃዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው::

### ያለው አስደናቂ ቅንብር

66ቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባባት በ1600 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ከ40 በሚበልጡ በመንፈስ ቅዱስ በተመሩ ደራሲያን ተጽፈዋል::[1] መጻሕፍቱ በሙሉ እርስ በርስ የሚጋጭ ሃሣብ ፈጽሞ የላቸውም:: እንኳን በ2 ሺህ ያህል ዓመታት ርቀት ውስጥ ያሉ ደራሲያን ሃሣብ ይቅርና በዚህ ዘመን በተለያዩ ቦታዎች የሚኖሩ ሰዎች በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በአንድ ዓይነት ርዕስ ላይ እንዲጽፉ ትዕዛዝ ቢሰጣቸው የተለያየና እርስ በርሱ የሚጋጭ ሃሣብ እንደሚኖራቸው እየታየ ካለው የዓለም ታሪክ ጽሑፍ እንገነዘባለን:: ይህም የመጽሐፍ ቅዱስ ቅንጅት ደራሲው አንዱ እግዚአብሔር መሆኑን ያሳያል::

### በዓለም ኅብረተሰብ ላይ የሚያመጣው ለውጥ

መጽሐፍ ቅዱስን በመቀበልና በሚሰጣቸውም መመሪያ የኖሩ በየትውልዱ የነበሩና ያሉ ሁሉ በጣም ተደስተውበታል:: ታላቅ የፍጻሜ ተስፋንም ሰጥቷቸዋል:: በተለያዩ ቦታዎች ለተከሰቱትም ሥልጣኔዎች ምንጭ ሆኗል::



### በድጋሚ ሊጻፍ አለመቻሉ

መጽሐፍ ቅዱስ እንደቀሩት መጻሕፍት በተከታታይ ቮሊዩም ተቀንሶለትም ሆነ ተጨምሮበት ሊጻፍ አይችልም:: በውስጡ ስህተት ተገኝቷል ተብሎ አይታረምም:: ምክንያቱም ደራሲው መንፈስ ቅዱስ በመሆኑ ነው::

### አስተምህሮቱ

መጽሐፍ ቅዱስ ከሐይማኖት፣ ከባህሎችና ከህብረተሰብ ግንኙነቶች ጋር በተያያዘ መልኩ የሚሰጣቸው ትምህርቶች በሙሉ ፍጹም ተወዳዳሪ የሌላቸው የህይወት መርሖዎች ናቸው::

### ከራሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኙ ማስረጃዎች

የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲያን ራሱ እግዚአብሔር መልዕክቱን እንዲጽፉ እንደተናገራቸው የሚገልጹ ከ3800 በላይ ማስረጃዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሰዋል::

### ወሰን የማይገኝለት ጥልቅነቱ

መጽሐፍ ቅዱስ እውነቱን እንዲቀበሉት ቅዱስ ጥሪ የሚያቀርበው ለተወሰኑ ጐሳዎችና ዝርያዎች ብቻ ሳይሆን ለዓለም ህዝብ ሁሉ ነው:: ትምህርቶቹ ምክንያታዊ፣ በሚሰጣቸው ተስፋዎች የሚታመን፣ በተቃዋሚነቱ ጽኑ፣ በጠቃሚነቱ ቋሚ፣ ዐረፍተ ነገሮቹ ሁልጊዜ የማይወድቁ፣ በየዘመኑ ለሚመጣው አዳዲስ ትውልድ የሚሆን የማይለዋወጥ ትምህርት መያዙ፣ ማንኛውም ሥልጣኔ ሊጥለው የማይችል እውነት መያዙ፣ ሕግጋቱ ሙሉዎች፣ ዓላማዎቹ በስግብግብነት ላይ ያልተመሰረቱ መሆኑ፣ የሚጠይቃቸው ተግባራት ቅኖችና ትክክል፣ ፍርዶቹ ፍትህ ያለባቸውና አድልዎ የማያደርጉ፣ ጥበባቱ ሁሉ ሕላዌ ምጡቅነትን የተቀዳጁ በመሆናቸው መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ይገልጻሉ::

### ተአምራቶቹ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተዘገቡት ተዐምራት ውሸቶች ወይም ልብ ወለድ ላለመሆናቸው ዛሬም በህዝብ ህይወት መታየታቸው የእግዚአብሔርን እውነተኝነትና የቃሉ ባለቤት ዛሬም መኖሩን መመስከራቸው ያረጋግጣል::

### ፍጹምነቱ

መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ምስክሮች ያሉት ህያው ንባብ ነው:: ሳይንሳዊና ታሪካዊ ይዘቱ ፍጹም እውነት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ስላለፉትና አሁን

ስላሉት የዓለም ታሪኮች፣ ስለ ሥነ ከዋክብት፣ ስለ እትክልቶች ጥናት፣ ስለ ሥነ-ህይወትና ስለ ሌሎች የትምህርት ዘርፎች የሚናገራቸው ከመቶ የሚበልጡ እውነቶችን ይዟል:: ሁሉም ትክክል ናቸው:: እያደገና እየለሰጠነ የመጣው የዓለም ህዝብ ቴክኖሎጂ እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት አይደለም:: እየተሰወጠና እየተሻሻለ የመጣው የሰው ልጆች አስተሳሰብ እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት አይደለም::

ስለአስትሮኖሚ (ስነ ከዋክብት) በቀድሞ ዘመን የነበሩ ሳይንቲስቶች ብዙ ዓይነት መላምቶችን ተናግረው ነበር:: ከተባሉትም ውስጥ ጥቂቶቹ ምድር ተደግፋ ቆማለች፣ የከዋክብቶች ቁጥር ውሱን ነው፣ ምድር ጠፍጣፋ ናት ወዘተ ነበሩ:: ሆኖም ግን ሳይንስ መጠቀ ሥልጣኔ ከፍተኛው ደረጃ ላይ ደረሰ ከመባሉ ከክ. ል. በ. በ1033-975 የኖረው ጠቢቡ ሰለሞንና፣ ምሳሌ 8:27፤ ከ745-695 የኖረው ነቢዩ ኢሳይያስ ምድር ክብ መሆኗን ያለ ረዳት መሣሪያ ሁሉን በሚያይ አይን በእግዚአብሔር ተገልጦላቸው ተናግረዋል:: ኢሳ. 40፣22 ይህንንም እውነት ሳይንስ በተለያዩ ጊዜያት አረጋግጧል::[2]

ስለ ሥነ ውቅያኖስም ዘመናዊ የሆነ ባህር-ጠለቅ-መሣሪያ ሳይኖራቸው በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተው ኢዮብና ዳዊት ውቅያኖስ የነበረውን ጥልቅነት ስለ ባህር-ወለል በባህር ውስጥ ስላሉ ፍጥረታት ጽፈው ነበር::

ስለሜቲዮሮሎጂም ስናነሳ ዝናብ ከሰማይ እንደሚመጣ እንጂ የዝናብ ምንጩ የባህር ትነት መሆኑ በዘመናውያን ተመራማሪዎች ለብዙ ዘመናት አይታወቅም ነበር:: ሆኖም ግን ኢዮብ በ36:27-28 ከክልበ የተረዳው እውነት ነበር::[3]

ስለአርኬዎሎጂም (የምድር ቅርሳ ቅርሦች) ስናነሳ ለመኖራቸው አከራካሪ የነበሩትን ከተማዎች መጽሐፍ ቅዱስ ዘግቦ ይዟቸው ስለነበር የዘመኑ ተመራማሪዎችም ከተሞች ቀድሞ እንደነበሩና የመጽሐፍ ቅዱስ አመልካችነት እውነት መሆኑን አረጋግጠዋል::[4]

ተስማሚነቱ

በዓለም ላይ በየትኛውም ቦታና ጊዜ ለነበሩ ሰዎች ሁሉ ተስማሚ የሆነ መልዕክት ነበረው:: ማለትም እውነቱን በተቀበሉት ሁሉ ላይ ለውጥን ማምጣት ችሏል:: ለምሳሌ ሰው መንፈስ ቅዱስን ሲቀበል በህይወቱ የሚታየው ፀረ-ሥነ ምግባራዊና ፀረ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ አቋም ወደ በጐነት መለወጡ፣ በፊት ሲገፋት የነበሩ ሁሉ በተቀበሉት ጊዜ ግን ፍጹም የተስተካከለ ጤናማና አስደናቂ የህይወት ለውጥን ሰጥቷቸዋል::

የተፈጸሙ ትንቢቶች

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወደ 6208 ትንቢቶች ይገኛሉ:: ከእነዚህ ውስጥ ከ3300 በላይ የሚሆኑት የተፈጸሙ ሲሆኑ ወደ2908 ደግሞ ወደፊት



የሚፈጸሙ ናቸው:: ከተፈጸሙት ውስጥ አንድም ቃል እንኳን አልተሳሳተም:: ይህ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና የሚለውን የ2ኛጴጥ. 1:21 ቃል ምንጭ በትንቢቱ የማይሳሳተው ሁሉን አዋቂ የሆነው ጌታ መሆኑን ያሳየናል:: እነዚህ ሁሉ ትንቢቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መገኘታቸውና መፈጸማቸው መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ያመለክተናል::

አለመጥፋቱ

መጽሐፍ ቅዱስ አሁን ባለበት ሁኔታ እንዳይገኝ ሊያደርጉት የሚችሉ ብዙ ሁኔታዎች ተከስተው ነበር:: ከእነዚህም ሁነቶች ውስጥ ዋነኞቹ የጊዜ፣ የስደቶችና የተለያዩ ትችቶች ናቸው:: መጽሐፍ ቅዱስ መጻፍ ከተጀመረበት እስካሁን በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ሰዎች በተለያዩ የጽሕፈት መሳሪያዎችና ቋንቋዎች ለትውልዶች ለመዳረስ ተገልብጧል:: በዚህ ሁሉ ሁኔታ አልጠፋም፤ አልተበላሸም:: አንድ የሰሜን አሜሪካ የሥነ ጽሑፍ ክፍልም ለእንደነ ሼክስፒር ካሉት የዓለም ጸሐፎች ይልቅ ለመጽሐፍ ቅዱስ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረጉን ገልጿል:: ይህም የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ጥበቃ ነው፤ በተጨማሪም በዓለም ከነበሩ የፖለቲካ፣ የባህልና፣ የሃይማኖት ክፍሎች ከነገስታት፣ ከምሁራንና ከሃይማኖተኞች ስደት ደርሶበታል:: ለምሳሌ ቮልተር በመባል የታወቀው ፈረንሳዊው ፀረ-ክርስቲያናዊ ከሃዲ እርሱ ካለበት ዘመን ጀምሮ ወደፊት ባሉት መቶ ዓመታት ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስና ክርስትና ከታሪክ ተለይተው እንደሚጠፉ ተናግሮ ነበር:: ሆኖም እርሱ ሲሞት መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ክርስትና እስካሁን አሉ:: እንዲያውም የቮልቴርን ትንቢት ተቃራኒ የሆነ ታሪክ ተፈጽሟል:: ይኸውም ቮልቴር ከሞተ ከ50 ዓመታት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ቤቱና ማተሚያው ለመጽሐፍ ቅዱሶች ማምረቻነት ጥቅም መዋሉ ነው::[5] ይህ በእግዚአብሔር እውቀትና ሐሣብ ላይ የሚነሳ እንቅስቃሴ ሁሉ ከንቱ እንደሚሆን የሚያመለክት ነው::

በመጨረሻ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ከደረሱት ተቃውሞዎች ውስጥ ሊጠቀስ የሚገባው ከተለያዩ ግለአማክሉታውያንና ቡድኖች የተሰነዘረው እፍራሽ ሂስ ነው:: ተፀምራቶቹን መቀበል ያልተስማማቸው ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ቅዠት፤ ልብ ወለድ፣ እፈ ታሪክ፣ ውሸት፤ የኢምፔሪያሊስት መጽሐፍ፣ የወጣቱን ትውልድ አእምሮ አደንዛዥ እንደሆነና አሁን ያሉት የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አባላትም «ታላቁ ውሸት» በማለት ታላላቅ እፍራሽ ሂሳቸውን ሰንዝረውበታል:: ሆኖም ግን በእነዚህ ተቃውሞዎች ሁሉ ጸንቷል፣ አልጠፋም:: በተለያዩ ዘመናት የተነሱ ጳጳሳት፣ ቀሳውስት፣ ነገስታት፣ መሳፍንቶችና ገዢዎች ሊያጠፉት የድንጋይ ናዳ አውርደውበታል:: በርናርድ ራም የተባሉት ሰው፣ «እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ጭፍጨፋ የተካሄደበት፣ የተከተፈ፣ የተበጠረ፣ የተጨመቀና ዋጋ እንዲያጣ ሴራ የተዶለተበት መጽሐፍ ፈጽሞ አይገኝም» ብለዋል:: በቀድሞም ሆነ በአሁኑ ዘመን የተጻፉ ሃይማኖት ነክ፣ ሥነ ልቡናዊ፣ ፍልስፍናዊም ሆነ ፖለቲካ ቀመስ መጻሕፍት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ያለ እውዳሚ ሂስ አልደረሰባቸውም::

መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ሁሉ አፍራሽ ሃይል ቢደርስበትም ሊጠፋ አልቻለም። በአንጻሩ ግን እስካሁን በሚሊዮን በሚቆጠሩ ሰዎች ዘንድ ተወዳጅነቱ ጨምሯል። ሁሉም ያነቡታል፣ ያጠኑታል በተጨማሪም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ በጣም አስደናቂ ጽሑፍ ጽፈዋል። የጽሑፉ ዐቢይ ሃሣብ የመጽሐፍ ቅዱስን ሂስንና ስደትን የመቋቋም ኃይሉን ለመግለጽ የተነገረ ነው። ራም «መጽሐፍ ቅዱስና የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በዓለም የተነሱትን የተቃዋሚዎች መዶሻ የሰባበሩ መስፎች ናቸው» በማለት ተናግረዋል።[6] ይህ ሃሣብ በእለቱ በክርስቶስ ላይ የሚወድቅ ሁሉ ይቀጠቀጣል። ዓለቱ ግን የሚወድቅበትን ሁሉ ይፈጨዋል ከሚለው የጌታ ንግግር ጋር ይስማማል። ማቴ. 21:44

## ስርጭቱ

መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ጊዜያት በከፍተኛ ደረጃ ታትሞ እንዲሰራጭ ጥያቄ ቀርቧል። በዓለም ከሚገኙት መጻሕፍት በመነበብና በብዙ ቋንቋዎች በመተርጐም የመጀመሪያውን ደረጃ ይዟል። እ.ኤ.አ. በ1932 ዓ.ም. ብቻ በዓለም ላይ 1,330,213,815 (አንድ ቢሊዮን ሦስት መቶ ሰላሣ ሚሊዮን ሁለት መቶ አሥራ ሦስት ሺህ ስምንት መቶ አሥራ አምስት) መጽሐፍ ቅዱሶች ታትመው ተሰራጭተዋል። ይህም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር መለኮታዊ የሆነው የእግዚአብሔር እጅ መኖሩን ያሳያል።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃልና እውነተኛ መሆኑን ካለፉት ልዩ ልዩ ማስረጃዎች ተመልክተናል። በተጨማሪም ቀጥሎ የተጠቀሱትን ምስክሮች መመልከቱ ይጠቅማል።

## 1.3 ታላላቅ ሰዎች ስለመጽሐፍ ቅዱስ የተናገሩት[7]

ጆርጅ ዋሽንግተን «ያለ መጽሐፍ ቅዱስና ያለ እግዚአብሔር ዓለምን በትክክል መምራት አይቻልም» ብለዋል። ዋሽንግተን ይህንን ሲሉ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ያህል በሰዎች ላይ ለመልካም ነገር ተጽዕኖ ማድረግ እንደሚችል እንደተረዱ ያመለክታል።

### ዮሐንስ ኲዊንሲ አዳምስ

«የመጀመሪያውና ብቸኛው የዓለምን ህዝብ ትኩረት የሳበ መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።»

### ዊድሮው ዊልሰን

«የሰው ልጅ ከዓለም አጣ ቢባል የቀረበት ትልቁ ነገር መጽሐፍ ቅዱስ ነው።»



### ኡሊሴስ ግራንት

«በዓለም ላይ ለተካሄዱት ሥልጣኔዎች መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ስለሆነም ወደፊት ልንመራበት ይገባናል።»

### ኸርበርት ኾቨር

«መጽሐፍ ቅዱስን የሚተካከል የጥበብ መከማቻ መጽሐፍ አይገኝም።»

### ዮሐንስ ባከን

«ያለ መጽሐፍ ቅዱሴ በዓለም ውስጥ መኖር አልችልም።»

### ናፖሊዮን ቦናፓርት

መጽሐፍ ቅዱስ ከመጻሐፍት ሁሉ በላይ ነው። ተግባርን የተሞላ ህያው ኑባሬ ከመሆኑም በላይ ተቃዋሚዎቹን ሁሉ የመውረርና የማሸነፍ ሥልጣን ያለው ኃይል ነው።»

### አሌክሳንደር ክሩዴን

«ሌሎች መጻሕፍት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ሲነጻጸሩ የሚሰጡት ጥቅም እጅግ ጥቂት ነው።»

### ዳንኤል ዌብስተር

«መጽሐፍ ቅዱስ የእምነት፣ የትክክለኛ አስተምህሮ፣ የሥነ ምግባር፣ የትክክለኛ ሐይማኖት ምንጭና የእግዚአብሔር ልዩ መገለጥ ያለበት መጽሐፍ ከመሆኑም በላይ የሰውን ትክክለኛ ኃላፊነት፣ የሰውን ክብርና ከሌላው ሰው ጋር ያለውንም እኩልነት የሚያስተምር መጽሐፍ ነው።»

### 800 የታላቋ ብሪታኒያ ሳይንቲስቶች

«ቀጥሎ ፊርማችን የተመለከተው የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪዎች በዘመናችን የተነሳነው ተመራማሪዎች በመጽሐፍ ቅዱስ እውነትና ትክክለኛ ነት ላይ ስላስቀመጥነው ጥርጥር እንጸጸታለን። የእግዚአብሔር ቃል በተፈጥሮ መጽሐፍ ፈጽሞ ሊጻፍ አይችልም ብለን የተጻፈውም ቢሆን እርስ በርሱ ይቃረናል የሚል ጽንሰ ሃሣብ አምጥተን ነበር። ሆኖም ስህተት ነበርን የተፈጥሮ ሳይንስ ገና በማደግ ላይ የሚገኝ ነው።» (ይህ ምስክርነት በኦክስፎርድ ቦዲሊየን ቤተ መጻህፍት ተዘግቦ ይገኛል)።

*(የትምህርተ ጥቅሱ ንግግሮች በትርጉም የተገኙ ናቸው።)

እግዚአብሔር ራሱን ያስ ምስክር የማይተው እምላክ ነው:: እውነት ለሚሹ ሁሉ ማስረጃ አለው:: ከላይ የተጠቀሱትን የመንፈስ ቅዱስንና የታላላቅ ሰዎችን ምስክርነት ከልብ ማዳመጡ እጅግ ጠቃሚ ነው:: ሰው ሁሉ ይብዛም ይነስ በከፊልና በሙሉ በባርነት ሥር መኖሩ ሐቅ ነው:: ባርነት ደግሞ ሰውን ያሰውዬታው በግዳጅ ኑሮ ውስጥ ያመላልሰዋል:: ባርነት የምንሰው ሰው አንድን ነገር ለመሆንና ለማድረግ እየፈለገ ሳይሆን ቀርቶ በሰቀቀን ሲኖር ነው:: ከባርነትም ነጻ መውጫው ዋነኛ መንገድ በእውነት መንገድ መቆም ብቻ ነው:: ዮሐ. 8:32 እውነትም የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ነው:: እውነት ለሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እነዚህን የሚያህሉ ልዩ ልዩ ምስክሮች ከያዝን ቀጥሎ ሙሉ ልባችንን ሰጥተን እንደ ቤሪያ ክርስቲያኖች ልንመረምረው ይገባል:: ሐዋ.17:10-11:: መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ከሆነ የተናገራቸው ትንቢቶች ሁሉ አንዱም ሳይወድቅ ይፈጸማል ማለት ነው:: ስለሆነም የከፉው ትንቢት ውጤት ተካፋይ ላለመሆን ነገር ግን የበጐው ትንቢት ውጤት ተካፋይ ለመሆን ምን ተተንብዮአል በማለት ክትትል ማድረግ ያሻል::

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ጥርጥር ያለበት ሰው በውስጡ የተጠቀሰውን እውነት ለህይወቱ ብርሃን እድርጐ ለመውሰድ ይቸገራል:: ህግህ ለእግሬ መብራት ነው በተባለበት ቃሉን እንደ ሐሰተኛ ነገር መመልከት ወደ ትክክለኛው መንገድ ለመግባት ትልቅ እንቅፋት መፍጠር ይሆናል:: ይህ እንዳይሆን ገደላገደል በሆነ መንገድ በጨለማ መብራት ይዘው ሲጓዙ ጨለማ እንዳይፈጠር ከፍተኛ ጥንቃቄ እንደሚደረግ እውነተኝነቱ ለተረጋገጠለት የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ህያው ጥንቃቄ ማድረግ ያሻል::

መጽሐፍ ቅዱስ ምትሃታዊ፣ ወይም ዕድል ማምለኪያ የጥንቆላ መጽሐፍ አይደለም:: በቅንነትና በታማኝነት ከታዘዙት በሰው ህይወት ድንቅን የሚሰራ መጽሐፍ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ሃሣብ፣ የሰውን ሁኔታና የሐጢአትን ምንነት የሚገልጽ ነው:: ትምህርቶቹ የተቀደሱ፣ ታሪኮቹም እውነቶች ናቸው:: ስለሆነም ብልህ ለመሆን አንብበው፤ ለመዳን እመነው፤ ለመቀደስ ተሰማመደው፤ መጽሐፍ ቅዱስ ለምሪትህ ብርሃንን፣ ለድጋፍህ ምግብን፣ ለደስታህ መጽናናትን፣ ይዟል:: መጽሐፍ ቅዱስ የመንገደኛ ካርታ፣ የመናኝ ምርኩዝ፣ የአብራሪ ኮምፓስ፣ የወታደር ሰይፍ ነው:: ዘወትር በዝግታ፣ በፀሎት በማሰላሰል ላይ ላዩን ሳይሆን ጠለቅ ብሎ በመመርመር ሊነበብ እንዲሁም ያለማቋረጥ፣ በንጽህና፣ በከፍተኛ ትጋትና ድካም ዋጋም በመክፈል በትህትና ሊጠና ያሻል::

የህይወትን ክፉ ተራሮች ነቅሎ መጣል የሚያስችልን እምነት በህይወት እስኪፈጥር እንዲሁም የህይወት ክፍል እስኪሆን ደጋግሞ ማንበብና ማጥናት ያስፈልጋል:: የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢቶች ለመመርመር ስንነሳ በዚህ መረዳት ልንሞላ የግድ አስፈላጊ ነው:: ለመጽሐፍ ቅዱስ ያለን መረዳት የተዛባ ከሆነ ትንቢቶቹንም በተዛባ መልኩ ልንተረጉማቸው እንችላለን::[8]



## 1.4 በዘመናት ርዝመት እንቅልፍ እንቅልፍ ሲል

ጌታ ኢየሱስ ወደ ዓለም በስጋ ከመምጣቱ በፊት የነበሩ ነቢያት ስለ ምፅዓቱ ተንብየው ነበር:: በስጋ መጥቶ ከሄደም በኋላ ተመልሶ እንደሚመጣ በቅድሚያ ራሱ ክርስቶስ ራዕይ.1:1-3:: ቀጥሎም ቅዱሳን መላዕክቱ ሐዋ. 1:11 ቀጥሎም መንፈስ ቅዱስ ሐዋርያቱና ወንጌላውያኑ ተናግረዋል:: በተለይ ከመንፈስ ቅዱስ መውረድ ጀምሮ ናጌታ ይመጣልን ብለን በጌታ እራት ሥርዓት ሞቱንና ትንሣኤውን በመናገር ስናስታውስ ወደ 2000 ዓመታት ደርሷል::

ትላንት ይመጣል፣ ዛሬም ይመጣል፣ ነገም ይመጣል ሆነ:: ታዲያ ይሄ "ጌታ ይመጣል" መቼ ይሆን ተፈጻሚነት የሚያገኘው? ይመጣል የሚለው ትንቢት ተደጋግሞ በመነገሩና ባለመፈጸሙ ይሆን ሰዎች በመቻከል በ1844 ዓ.ም. በስውር መጥቶ ተመልሶ ወደ ሰማይ መቅደስ ገባ የተባለው? ከመዘግየቱስ የተነሳ ይሆን ዘባቾች የመምጣቱ ተስፋ የታል? ሁሉ እንዳለ ይኖራል (2ኛጴጥ. 3:3) ወደሚል ሃሣብ የተዘነበሉት? ለመንፈሳዊ እንቅልፍ መንስኤው ይኸው ሊሆን ይችላል:: ሆኖም መጠንቀቅ ነው::

"ሙሽራውም በዘገየ ጊዜ ሁሉ እንቅልፍ እንቅልፍ አላቸውና ተኙ" ተብሎ መጻፉ ለትምህርታችን መሆኑ መዘንጋት የለበትም:: ማቴ. 25:5 ምንጊዜም ለእንቅልፍ መንስኤ አለው:: የእንቅልፍ መንስኤ በአብዛኛው ድካም ነው:: ድካምም የሰውነት ወቅታዊውን ሁኔታ መቋቋም ሲያቅተው ነው:: ብዙ መጠበቅ ተስፋን ያቀፋል:: ተስፋ ደግሞ ሳይፈጸም ሲቀር ልብን ያዝላል:: የምትዘገይ ተስፋ ነፍስን ታዝላለች እንደተባለ ከላይ በተጠቀሰው ቃል ለእንቅልፋቸውና ለመኝታቸው መንስኤው የሙሽራው መዘግየት ነበር በመሰረቱ የሙሽራውን መዘግየት የፈጠሩት ቆነጃጅቱ ናቸው እንጂ ሙሽራው አይደለም:: ምክንያቱም በሙሽራው ዘንድ መምጫ ጊዜው የተወሰነ ስለነበር ነው:: የቆነጃጅቱ ልብ መቸኮልና ያለጊዜው ይመጣል ብለው መጠበቃቸው ነው ወደ ተስፋ መቁረጥና መድከም ያስገባቸው ዛሬም ቢሆን ከዚህ የምንማረው ትምህርት የሙሽራውን መምጫ ሰዓት በትዕግስት መጠበቅ እንዳለብን ነው:: በጌታ ኢየሱስ ዘንድ መፍጠንም መዘግየትም ስህተት አይኖርበትም::

ሁለቱም ውሱን ናቸው በጌታ ቀን ሺሁ እንደ አንድ፣ አንዱም እንደ ሺህ ነውና ዘገየ ስንለው ሊፈጥን፤ ፈጠነ ስንለው መዘግየቱ ሊሆን ይችላል:: ለዚህ መድሃኒቱ በጥንቃቄ ዘመኑን መመርመር ነው:: ዘመኑን እንደ ይሳኮር ልጆች ስንመረምር ግልጽ ሆኖ ይታየናል:: ከታየን ደግሞ አንደናቀፍም:: ምክንያቱም ሉቃ. 12:56ትን ከታዘዝን በረከቱን ስለምናገኘው ነው:: ዘመን መርማሪው ሰው ፈጽሞ አያንቀላፋም::

### 1.5 ዘመን መርማሪው ሰው

ጌታ ኢየሱስ በምድር ይኖር በነበረበት ጊዜ ያላዘኑት ብዙ ነገሮች ነበሩ:: የገዛ ወገኖቹ እርሱን አለመቀበላቸውን አጋንንት እንዳለበት መቆጠሩ

ኢየሩሳሌምን ሊሰበስብ መሞቶ መሰብሰብ አለመፈለጋቸው፣ እስራኤላውያን የመጉብኛ ጊዜያቸውን አለማወቃቸው፣ የሰዎች ያለ እረኛ መበተናቸው፣ የመከሩ መብዛትና የመከር ሰብሳቢዎች ማነስ ወዘተ ካሳዘኑት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ነበሩ:: በተለይም መሪዎች ነን ይሉ የነበሩት ጸሐፍት ፈሪሳውያን እርሱን ባለመረዳት እውሮች መሆናቸው አሳዝኖታል:: ጸሐፍት ፈሪሳውያን ተራ በሆነ ነገር ላይ ተመራማሪዎች መሆናቸውና አውራ የሆነውን የምርምር አቅጣጫ ማጣጣላቸው አሳዝኖት እንደነበር ከሉቃስ 12:56 እናነባለን:: ጌታ ኢየሱስ ተቆጥቶ እናንተ ግብዞች... በማለት ይነቅፋቸዋል:: የነቀፈበት ምክንያት ዘመኑን መመርመር ባለመቻላቸው ላይ ያተከረ ነበር::

ጌታ ኢየሱስ ይህንን ዘመን የማትመረምሩ ለምንድነው ያለበት ምክንያት ነበረው:: መሲህ በዓለም መጨረሻ ወደዚህ ዓለም እንደሚመጣ በቀደሙት ዘመናት ተተንብዮ ነበር:: መላው እስራኤልም የመሲህን መነሻና መምጫ በናፍቆት ይጠባበቅ ነበር:: እንደ ጠበቁትም መጣ:: ሆኖም ጌታን በትክክል አላገኙትም:: ጌታ ኢየሱስ አገልግሎት ሲጀምር የተነሳው ከገሊላ ነበር:: ከቤተልሔም ይሁዳ እንደሚመጣ ተረድተው ከገሊላ አይመጣም በማለት ተከራከሩ:: ዮሐ.7:52 ሁሉቱም ልክ ነበሩ:: ሲሳሳቱ የቻሉት ግን 28 ዓመታት ያህል ወደ ኋላ መለስ በማለት ጌታ የተወለደበትን ጊዜና ቦታ ማየት ባለመቻላቸው ነበር:: ይህንን ቢያደርጉ ጌታ በቤተልሔም መወለዱንና ከዚያ የተነሳ መሆኑን ይገነዘቡ ጌታንም ይቀበሉ ነበር:: 28 ዓመታት ያህል ወደኋላ መለስ ብለው ታሪክን ባለመመርመራቸው ከባድ ኃጢአትን ለመስራት አልፈው ተሰጡ::

መላው የኢየሩሳሌም ህዝብ ጌታ እግዚአብሔርን በደለ:: ክርስቶስ ኢየሱስን ሳቱት፤ ላለመቀበል ብዙ መከላከያዎችን አቀረቡ:: እንደ ሃሳዊ መሲህ ቆጠሩት ስቀለው! ስቀለው! ደሙ በእኛና በልጆቻችን ይሁን! እስከማለት በጌታ ላይ የስድብና የርግማን ውርጅብኝ አስተላለፉበት:: ሰባርኮታቸው የመጣውን ጌታ ለመርገም እስከመለወጥ እርምጃ ወሰዱ:: የዚህ ሁሉ መሳት መንስኤ ዘመንን አለመመርመር ነበር:: እስራኤላውያን የነቢያትን ቃል በተለይ ኢሳያስ 35ትን፣ 53ትንና የኢዩኤልን መጸሀፍት መርምረው ቢሆን ኖሮ ጌታ ከ400 ዓመታት የጨለማ ዓመታት በኋላ ከደረቅ ምድር ብቅ ሲል፣ ሙታንን ሲያስነሳ ሽባዎችን ሲተረትርና እንደሚዳቋ ሲያዘልል ቢያስተውሉ ኖሮ በተቀበሉት ነበር:: የጌታም መስቀል በሌላ በኩል በሆነና እነርሱም የመጨረሻውን ወንጌል ሰብዎች በሰበኩ መንግሥትም ከእነርሱ ሳይወሰድ ክህነታቸውን ባጸኑ ነበር::

ዛሬም ቢሆን የተጻፈ ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፏል እንደተባለ ከዚህ አንድን ታላቅ እውነት ልንማር ይገባል:: ይኸውም ዘመንን የመመርመር አስፈላጊነትንና ጠቃሚነትን በተመለከተ ነው:: ጌታ ምልክቶችን የሰጠን ያለ ምክንያት አይደለም:: ምልክቶች ዘመንን እንድንመረምር ይረዱናል:: የምንመረምረውም ለውጤት መሆን አለበት:: ጌታ ኢየሱስ በሉቃስ 21:31 እና በማቴ. 24:33 ላይ «... ይህ ሁሉ መሆኑን ስታዩ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደቀረበች እወቁ፤ ... ይህን ሁሉ ስታዩ በደጅ እንደቀረበ እወቁ» በማለት ሲናገር ያለ ምክንያት አይደለም:: ምልክት



ሲታይ ያነቃል፣ እንቅልፍን ያርቃል፣ ያበረታታል:: ስለሆነም ስቀለው ስቀለው እንዳሉት እስራኤላውያን ዛሬም ጌታ ገና ነው ገና ነው ወደሚል ስህተት ገብተን በመተኛት የ70ኛውን ሰባኤ መከራ እንዳናጭድ ዛሬውኑ ዘመኑን መርምረን ልንነቃና ልንጠነቀቅ ይገባናል::

ዘመንን ለመመርመር መሣሪያ ያስፈልገናል:: ስለ ህክምና ቀምድር ቅርስ፣ሳይንስና ወዘተ በተደረሰበት ደረጃ ሙሉ እውቀት ሊገኝ የቻለው ከብዙ ምርምርና ድካም እንደሆነ ሁሉ ይህም ጊዜ የመጨረሻው ዘመን ለመሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶችና ትንቢቶቹ በሚገለጹበት የዓለም ታሪክ ሊመረመር ያሻል:: ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከ6000 በላይ ትንቢቶች አሉ:: እነዚህ ሁሉ ትንቢቶች በዓለም ታሪክ ውስጥ የግድ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል:: ምክንያቱም ትንቢቶቹ የተነገሩት ከመርገምና ከበረከት ጋር በተያያዘ ለሰይጣን፣ ለወደቁት መላዕክት፣ ለሰዎችና ወዘተ ስለሆነ ነው:: ንቁና እውነተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ሰው የትንቢትን ተስፋዎች ፈጽሞ አይረሳም:: ምን ተተነበየ? ምንስ እየተፈጸመ ነው? የሚለውን ጥያቄ ይዞ ከፍተኛ ክትትል ያደርጋል:: ወደ ላይ አሻቅቦ በመመልከት የመነጠቅንም ሆነ የጌታን ምጽዓት በጉጉት ለመጠበቅ የቅርብ ትንቢት ፍጻሚዎችን ከሁሉ ይልቅ ልብ ማለት ይገባል:: ለምሳሌ ከአመልማሎ፣ ንጣፍና ጥቁር የደመና ዓይነት ውስጥ ጥቁርና ከባድ የሆነው የደመና ዓይነት በሰማይ ከታየ ዝናብ በአስተማማኝ ሁኔታ ሊዘንብ መሆኑ እንደሚታወቅ ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱት ሁለት ተከታታይ ትንቢቶች በዓለማችን ከታዩ ጌታ ኢየሱስ ለቅዱሳኑና ለሺህ ዓመት ንግሥት ሲመጣ መሆኑን መቶ በመቶ እርግጠኞች ያደርገናል:: እነዚህ ፀቢይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች የትኞቹ ይሆኑ ይሆን?

### 1.6 ከ6208 ትንቢቶች ሁለቱ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱትን ትንቢቶች በከፍተኛና በልዩ አክብሮት እናጠናቸዋለን:: የምናጠናበትም ዋነኛ ዓላማ በተስፋ እንድንሞላና ተደላድለን እንድንቆም ነው:: ይህም ተስፋ በቲቶ 2:13 እንደተጠቀሰው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር መገለጥ ነው:: የክብሩንም መገለጥ ስናስብ መቃረቡን አትኩረን እንከታተለዋለን:: የጌታን ክብር መገለጥ መቃረብ ከምንከታተልባቸው ፀቢይ የታሪክ መመርመሪያ መሣሪያዎች ውስጥ ምልክቶች ይገኛሉ:: ምልክቶችን ደግሞ ስናጠና የመጽሐፍ ቅዱስንና የታሪክን ጨምረን ከ73 ያላነሱ የመጨረሻ ዘመን ምልክቶች እናያለን:: እነዚህ ምልክቶች ግማሾቹ የሩቅ ማለትም ባለፉት 2000 ዓመታት ውስጥ በተደጋጋሚ የተፈጸሙ ሲሆኑ የቀሩት ደግሞ የቅርብ (ያልተፈጸሙ ሆኖም ሲፈጸሙ እጅግ በጣም የቀረቡ) ሆነው እናገኛቸዋለን:: የዚህ መጽሐፍ ዓላማ በሩቅ ምልክቶች ላይ ያተከረ ሳይሆን በቅርብ የጌታ መገለጥና የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ምልክቶች ላይ ያተከረ ነው:: እነዚህም ሁለት ፀቢይ ምልክቶች የክህደት መምጣትና ቀጥሎ የአውሬው (የሐሰተኛው ክርስቶስ) መገለጥ ናቸው:: እነዚህንም ምልክቶች ከታሪካዊ ማስረጃዎች ጋር በዝርዝር እንመለከታለን::

## ክህደትና አውሬው በምልክትነት

በ68 ዓ.ም. ገደማ በተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ዘንድ ከፍተኛ መምታታትና ትርምስ እንደነበረ የመጀመሪያው ዘመን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል። የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች በተለያየ ዓይነት ዘዴ ማለትም በመንፈስ በቃልና በጽሑፋዊ መልዕክቶች የጌታ መምጫ በጣም ቀርቧል የሚል ድምጽ የሚሰሙበት ጊዜ ነበር። ከዚህም የተነሳ ቅዱሳኑ ዕለታዊ ሥራቸውን በመተው ጌታን ብቻ ቁጭ ብሎ በመጠበቅ ላይ ለማተኮር የተፈተኑበት ወቅት ነበር። በዚህ ሁኔታ አእምሯቸው ተናውጦ ስለነበር ሐዋርያው ጳውሎስ ጠንካራ መልዕክት ይጽፍላቸዋል። መልዕክቱም፣ «ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና ወደ እርሱ ስለመሰብሰባችን በመንፈስ ወይም በቃል ወይም ከእኛ እንደሚመጣ በመልዕክት የጌታ ቀን ደርሷል ብላችሁ ከአእምሯችሁ ቶሎ እንዳትናወጡ እንዳትደነግጡም እንለምናችኋለን። ማንም በማናቸውም መንገድ አያስታችሁ ክህደቱ አስቀድሞ ሳይመጣና የአመጽ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ አይደርስምና።[9]» በሌላ ትርጉም ደግሞ ቁ. 3 «... ያ ቀን ከመድረሱ አስቀድሞ የመጨረሻው አመጽ ይሆናል። ለጥፋት የተወሰነውም የአመጽ ሰው ይገለጣል»[10] ይላል።

ጳውሎስ በማስረገጥ ሊያስተላልፍ የፈለገው እውነት የክርስቶስ ኢየሱስ መምጣት ከመሆኑ በፊት ሁለት ዐቢይ ተከታታይ ምልክቶች እንደሚፈጸሙ ነው። እነዚህም ምልክቶች የክህደት (የአመጽ፣ ሥርዓተ አልበኝነት) መከሰትና በመቀጠል የአመጽ ሰው (የጥፋት ልጅ) የተባለው አውሬ-ሐሰተኛው ክርስቶስ መገለጡ ናቸው። እነዚህ የጌታ መምጫ ከፍተኛ የቅርብና ግልጽ ምልክቶች ናቸው። በ2ኛ ተሰ. 2፣3 መሠረት የጌታ መምጣት ስንል ከ70ኛው ሱባኤ በኋላ ያለውን በክብር መገለጡን ለማመልከት እንጂ ቅዱሳኑን በአየር ለመቀበል (ለመነጠቅ) የሚመጣውን ማለት እንዳይደለ ልብ ልንል ያሻል። ቅደም ተከተላዊ ሂደቱም ይህንን ይመስላል። የክህደቱ ምልክት ይታያል። ይህ ክህደትና አመጽ ራሱ በከፍተኛ ደረጃ ለሐሰተኛው ክርስቶስ ሁኔታዎችን ያመቻችለታል። ይህ ከሆነ በኋላ ቤተ ክርስቲያን (አሁን ያለችውን ማለትም የመከራውን ዘመን ቤተ ክርስቲያን ሳይጨምር) ትነጠቃለች፤ መነጠቁ ሲሆን ለአውሬው መንገድ ይከፈትለታል። በሃይል ለመስራት ይመጣል። ለ7 ዓመታት (ለአንድ ሱባኤ) በምድር ላይ ይሰለጥናል። ዳን. 9:27፤ ከዚህ በኋላ ነው ክርስቶስ ኢየሱስ በግልጽ በምድር ላይ ለመንገሥ የሚመጣው። እንግዲህ ይህንን ሁኔታ መሠረት በማድረግ መነጠቃችንንም በናፍቆት ለመጠበቅ ወቅታዊውን ክህደት ልንመረምር ይገባናል። አሁን በምድራችን ላይ ለአውሬው ሁኔታዎችን የሚያመቻቸው አመጽ (ክህደት) አለ ወይስ የለም? የሚታወቅባቸውስ መልኮችና ልምምዶች ምን ይመስላሉ? በእነዚህ ጥያቄዎች ላይ በማትኮር ዘመኑን ልንመረምር ይገባናል። ምክንያቱም ኩብራችን ስለሆነ ነው። ቲቶ 2:11-13 የተማረ ክብሩን መረመረ የተሰኘውም አባባል እውነትነቱ የሚፈተነው እዚህ ላይ ነው። ሰው ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ በሆነ ምርምር ላይ ብቻ አትኩሮ ትርፍን ቢያመጣ ለዘላለማዊ ኩብር አይሆንም።



## ትንቢተ ክህደት

ጳውሎስ ስለ መጨረሻው ዘመን ክህደት መምጣት ለተሰሎንቄ ቅዱሳን ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ጽፏል። በ2ኛ ጢሞ. 3:1-9 ባሉት ቁጥሮች ቃል በቃል የመጨረሻው ዘመን ሰዎች «ከዳተኞች» ይሆናሉ ብሏል። በዚሁ ክፍል የተጻፉት ራስን መውደድ፣ ትዕቢት፣ ተሳዳቢነት፣ ለወላጅ አለመታዘዝ፣ አለማመስገን፣ ቅድስና ማጣት፣ ዕርቅን አለመስማት፣ መልካምን አለመውደድ፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን መውደድ፣ የጌታን ኃይል ክዶ የአምልኮት መልክ መያዝ፣ ወዘተ የሰውን እግዚአብሔርንና ለውን መካድ ያሳያሉ። በተጨማሪም ማቴ. 24:4-31 እና ራዕ. 13፣4-6 እንመልከት። ክህደት ብዙ ዓይነት መልክ አለው። ሰው የገባውን የጋብቻ፣ የንብረት ማቆየት፣ የሥራ፣ የቤተሰብ ወዘተ ቃል ኪዳን ሲያፈርስ ከሃዲ ይባላል። ሰው ከአገሩ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ሳይታዘዝና ሳይጠብቅ ሲቀር ከሃዲ ነው። መመለክ የሚገባው አንድ አምላክ እግዚአብሔር ብቻ ሲሆን ሰው በየዛፉ፣ ወንዛ ወንዙ፣ በትላልቅ ድንጋይ (ቋጥኝ) ሥር በመንበርከክ፣ ወይም ታላቅ ነው ለተባለ ሰው ሲንበረከክና ሲሰግድ ይህ ሁሉ ክህደት ነው። በተጨማሪም በአካሉ ውስጥ በመግባትም ሆነ ከውጪ በመሆን ድምጽ የሚያሰሙትን መናፍስት በመከተል ዘውታሪ ሲሆንና ሲያመልካቸው ክህደት ነው። ከዚህ ሌላ ሰው ራሱን በአምላክ ቦታ አስቀምጦ ግለአማክሎታዊነትን ሲያጸንን ይህ ከፍተኛው ክህደት ይሆናል።

ግለሰብም ሆነ አንድ መንፈሳዊ ድርጅት፣ ቡድን ወይም ሃይማኖታዊ መልክ ያለው እንቅስቃሴ መካዱ የሚታወቅበት መንገድ ምንድነው? ለዚህ ጥያቄ መልስ የምናገኘው ከመጽሐፍ ቅዱስና ከመንፈስ ቅዱስ ነው። ማንኛውም ከመጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ አስተምህሮ የማይስማማና ተቃራኒ የሆነ እውቀት፣ መንፈሳዊ ልምምድ፣ ጽሑፍና ሃሣብ በሙሉ ክህደት ነው። በአሁኑ ጊዜ በምድራችን ያለውን የሃይማኖት አስተምህሮና ልምምድ ስንመረምር የመጨረሻው ማለትም የአውሬው (666) መንገድ ጠራጊ የሆነውን ክህደት መጠገዘ በግልጽ እንመለከታለን። ይህንንም ስናይ የአውሬው መገለጥ እጅግ ቅርብ መሆኑን እናረጋግጣለን።

### የዘመኑ የክህደት ዓይነት

ለአውሬው መምጣት መንገድ ጠራጊ የሆኑት የክህደት ዓይነቶች በግልጽ ከሚታዩባቸው መልኮች ውስጥ ዋነኛው የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ነው። ቀጥሎ የተመለከተው ሠንጠረዥ በአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን ከፍተኛና ተቃራራቢ ልዩነት የሚያሳይ ነው።[11]

| የአዲስ ዘመን እንቅስቃሴና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ልዩነት | | |
|---|---|---|
| ቃላትና ስሞች | ትርጉም | |
| | የአዲስ ዘመን እንቅስቃሴ አስተምህሮ | መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክርስትና አስተምህሮ |
| እግዚአብሔር | ስብዕናና ሥነ ምግባራዊነት የሌለው፣ በሁለንታዊ ዓለም በለውጥ /evolutionary/ የመፍጠር ኃይል፣ ሁሉ በአንዱ የሆነ በወንድና በሴቱ (በግዑዝ) ጾታ ሲጠራ የሚችል ፈጣሪም ፍጡርም ሆኖ መለኮታዊ መረዳት ያለው የመፍጠር ኃይል | እግዚአብሔር ከፍጡር ሁሉ የተለየ፣ የሥነ ምግባር አቋምና ስብእዊነት ያለው ሁሉን ቻይ፣ ሁሉን አዋቂና በሁሉ ሥፍራ መገኘት የሚችል የሁሉ ፈጣሪ ነው ሐዋ. 17፣ 28፣ ቆላ. 1፣16-17 1ኛቆሮ. 4፣7፤ ኢሳ. 48፣11-12 |
| ፍጥረት /Creation/ | ግዝፈ-ዓለሙ Universe/ ሁልጊዜ የፈጣሪው ኃይል መገለጫ /manifestation/ ወይም አምላክ ነው:: | እግዚአብሔር ግዝፈ-ዓለሙን ከምንም ፈጥሯል:: እግዚአብሔር ከፍጥረቱ የተለየ ነው:: ፍጥረት እግዚአብሔር ተብሎ ሲጠራ አይችልም |
| እግዚአብሔርና መንፈስ ቅዱስ | ሁለቱም ስብዕና የላቸውም፣ መንፈስ ቅዱስ /እግዚአብሔር/ ማለት የመለኮት፣ የጉልበት /ኃይል/ መርገብገብ /መገኘት/፣ የዓለም አቀፍ ሕግ፣ ሁለንታዊ አእምሮ፣ ዘላለማዊ እውነታ ወዘተ ማለት ነው:: | እግዚአብሔር ስብዕና /ህላዊ/ አለው:: መንፈስ ቢሆንም የማይወሰን፣ ከሰው ውጪ የሆነ፣ በሰው ሊመለክ የሚገባው አምላክ ነው:: ዮሐ. 1፤16፣13-14፤4፣11 |
| ሰው | ሰዎች የምድራዊው ለውጥ የመጨረሻ ደረጃ ናቸው፣ ያልተወሰነ አምቅ ኃይል ያላቸው፣ መለኮታዊ ኃይል እንዳላቸው ያወቁና የግዝፈ ዓለሙን የለውጥ ሂደት መምራት የሚችሉ ናቸው:: በክፉና በበጐ መካከል የማይለዩም ናቸው ይላሉ:: | ሰው ክፉና ደጉን ለመለየት በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረ ነው:: ሰው ከመውደቁ የተነሳ በራሱ ኃይል የሌለው ጥገኛና ነጻነት የሚሻ ፍጡር፣ ሰይጣንም ህላዊ ያለው የክፋ ሞራል ምንጭ እንደሆነ ያስተምራል:: ዮሐ. 3፣16-19፤ 8፣44፤ ሮሜ 3፣23፤ ኤር. 17፣5-9 |



| | የአዲስ ዘመን እንቅስቃሴ አስተምህሮ | መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክርስትና አስተምህሮ |
|---|---|---|
| መገለጥ /Revelation/ | በታሪክ ሂደት ውስጥ የነገሮችን ሁሉ መለኮትነት ማወቅ እንችላለን፤ ከመለኮታዊው የህይወት ኃይል ጋርም ፍጹም ህብረት ማድረግ እንችላለን፣ አሁን ካለንበት የመረዳት ችሎታ ወደ ከፍተኛው እናድጋለን:: | እግዚአብሔር በተፈጥሮ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ፣ በቅዱሳት መጻሕፍትና በሌሎችም ራሱን ገልጧል:: ሮሜ 1:18-19፤ ዮሐ. 1:14 |
| መዋጀት | ክርስቶስ ለዓለም ኃጢአት አልሞተም፣ የደሙ መፍሰስ አሳዛኝ ቢሆንም ዛሬ ለሰዎች መንፈሳዊ ፍላጐቶች ምንም ረብነት የሰውም መቤዠት አያስፈልግም:: ክርስትና የደም ኃይማኖት ነው:: | ክርስቶስ ለዓለም ኃጢአት ማስወገጃ መስዋዕት ሆኗል:: በደሙ እንድናለን፣ በትንሣኤው ብቸኛ ኃይል የዘላለምን ህይወትና በሞት ላይ የድል ዋስትና ይኖረናል:: ዕብ. 9፣22፤ ዮሐ. 3፣16፤ ሮሜ 3፣23፤ ገላ. 1፣1-5 |
| ክርስቶስ | ተወዳዳሪ የሌለው መንፈሳዊ መምህርና መለኮታዊነቱን ያወቀ እኛንም መለኮታዊነት እንዳለን ለመርዳት ራሱን የሰጠ ነው:: የክርስቶስ አምላክነት ከእኛ አምላክነት ፈጽሞ አይለይም:: መለኮትነቱን በማግኘቱ ፍጹም ጌታና ፍጹም ሰው ነው:: | የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ዘላለማዊው ሁለተኛ ው ስላሴ፣ አምላክም ሰውም የሆነ፣ የሰውን ዘርና ፍጥረተ ዓለሙን ሁሉ የሚቤዥ፣ ሁሉን የፈጠረ፣ ሰዎችን ለማዳን የተላከ ብቸኛ መሲህ ነው 1ኛዮሐ.2፣20-25 ዕብ.1፣8፤ ቆላ. 1፣14-19፤ 2፣9-10 |
| ኃጢአት | ኃጢአት የራስን መለኮትነት መረዳት አለመቻል ሲሆን ክፉም ሆነ በጐ ሰውን ወደ ከፍተኛው የንቃተ ህሊና /የህይወት ኃይል/ ደረጃ እንዲደርስ አስተዋጽኦ አላቸው:: | ኃጢአት የሥነ ምግባር ክፋት ነው:: በፍጹም ፈቃደኝነት ላይ የተመረከዘ በእግዘአብሔር ፍጹም የሞራል ህግ ላይ የሚደረግ አመጽ ነው:: ሮሜ 1:18-32፤ ዕብ. 10:26-39 |

| | የአዲስ ዘመን እንቅስቃሴ አስተምህሮ | መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክርስትና አስተምህሮ |
|---|---|---|
| ይቅርታ | ሰው ለችግሮቹ ሁሉ ኃላፊ በመሆን ራሱን ይቅር ሊል ይገባል፤ ከሰው ውጪ ስለ ይቅርታ ሊለመን የሚገባ ማንነት ፈጽሞ የለም፤ ከራሳችን ውጪ ይቅርታን ሊሰጠን የሚችል ምንም የለም:: | አፍቃሪው እግዚአብሔር ብቻ ኃጢአታችንን በማንጻት ይቅርታ ሊያደርግልን ይችላል:: ሰው ሙሉ በሙሉ የኃጢአት ባሪያ ስለሆነ ራሱን ይቅር ማለትና ማንጻት አይችልም:: 1ኛጴጥ. 2፥24፤ 1ዮሐ.1፥2-6፤ያዕ.4፥6-11 |
| ደህንነት | ደህንነት ማለት የራሳችንን መለኮትነት በመገንዘብ ከበደለኝነት ስሜትና ከፍርሃት ነጻ መውጣት ነው:: | በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ከኃጢአት ኃይልና ቅጣት ነጻ መሆን ነው:: ክርስቶስ የኃጢአትን ቅጣት በመስቀል ላይ ሞቶ በመነሳት ከፍሏል:: ኢሳ. 53፤ 1ኛ ዩሐ. 2:1 |
| ፍርድ | ኃጢአትና ክፉ የሰዎች ቅዠት ናቸው:: ሕልውና ያለው ፈራጅ ስለሌለ ፍጻሜ በማይኖረው የነፍስ ደጋግሞ መወለድ /Reincarnation/ ሂደት ወደ ፍጹምነት ደረጃ በመምጣት እንነጻለን፤ ያኔም ወደ ከፍተኛው የንቃተ ህሊና ደረጃ እንደርሳለን | አማኞች ለእግዘአብሔር ቃል ባላቸው ታማኝነት መሠረት በመንግሥተ ሰማይ ሽልማት ይጠብቃቸዋል:: በክርስቶስ ኢየሱስ ያላመኑ ሁሉ ግን በእግዘአብሔር ላይ ባመጹት መጠን በእሳት ባህር ለዘላለም ይቀጣሉ:: ዮሐ. 5:28-29፤ ራዕይ 20:11-15 |
| መላዕክት | እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አባባል መላዕክት የሚባሉ የሉም ሆኖም በሰማይ ውስጥ ከሰው መረዳትና ኃይል እጅግ የላቀ ችሎታ ያላቸውና ሰዎችንም ወደ ከፍተኛ ው የመረዳት ችሎታ ለማድረስ የሚችሉ መንፈሳዊ ኃይላት አሉ:: ያረጉ የሰዎች መንፈሶች ናቸው:: | መላዕክት በእግዘአብሔር የተፈጠሩ መንፈሳዊ ኃይላት ናቸው:: ጥቂቶቹ መላዕክት ከሰይጣን ጋር አምጸዋል:: ስለሆነም የእግዘአብሔርና የሰው ጠላቶች ናቸው:: የቀሩት ለእግዘአብሔር ታማኝ ሆነው ያገለግላሉ:: የሰዎች መንፈሶች መላዕክት አይደሉም:: ይለያያሉ:: ራዕይ 12:3-9 |



| | የአዲስ ዘመን እንቅስቃሴ አስተምህሮ | መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክርስትና አስተምህሮ |
|---|---|---|
| የሰው ህይወት | ሰው ወደ ፍጹም ሙላት እስኪደርስ ድረስ ደጋግሞ በመንፈስና በሥጋ ይወለዳል /Reincarnate/:: በዚህም ሂደት ወደ ፍጹም አምላክነት ደረጃ ይደርሳል:: | ሰው አንድ ጊዜ ብቻ በሥጋ በዚህ ዓለም የመኖር ዕድል አለው:: በመሞት (ከሥጋ በመለየት) ሰው በመንፈሱ ወደሚፈርደው ወደ እግዚአብሔር ይቀርባል:: ቀድሞ በምድር ደህንነት ያገኙ ከቅጣት ሲድኑ የቀሩት ይቀጣሉ:: ዕብ. 9፥27፤ ዮሐ. 3፥16 |
| ሥራ | በመልካም ሥራ ወይም በአብርሆት /enlightenment/ ሰው የመለኮትነት ነገር አውቆ ከእግዚአብሔር ጋርም ፍጹም ተራክቦ (ህብረት) ሊያደርግ ይችላል:: ይህም ሁለንታዊው ህግ ነው /universal law/:: | ሰው በመልካም ተግባሩ ወይም ሕግን በመጠበቅ አይድንም በራሱ ጥረት አብርሆተ ሕሊና ሊኖረው አይችልም:: የሰማዩ መንግሥት ዳግም ለተወለዱና የእግዚአብሔርን ነጻ የፀጋ ስጦታ በእምነት ለተቀበሉ ብቻ ነው:: ቲቶ 3፥5፤ ገላ. 3፥1-4፤ 2፥16፤ ዮሐ. 3፥3 |
| አማላጅነት | በሰማይ ያሉ መንፈሳዊ ኃይላት መንፈሳዊ አብርሆትንና ምሪትን ሊሰጡን፣ ሰውም ወደ መለኮትነት እንዴት እንደሚደርስ ሊያሳዩንና ሊረዱን ይችላሉ:: | በሰዎችና በእግዘአብሔር መካከል ብቸኛው አማላጅ ክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ ነው:: ከመናፍስት ምሪትን መቀበል ከአስማትና ከሟርተኝነት ሥራ ተለይቶ አይታይም በእግዘአብሔር ዘንድ ጥፋት ነው:: እነዚህ መናፍቃንና አሳቶች ከሰይጣን ናቸው:: ለሰው በትክክል የሚያበራው ክርስቶስ ነው:: ዘዳ.18፥10-12፤ ኢሳ.8፥19፤ መዝ.(34)፥5 1ሳሙ. 28፥1-15፤ 1ጢሞ.4፥1፤ 1ቆሮ.10፥13-14፤ ዮሐ. 1፥4-9፤ |

| | የአዲስ ዘመን እንቅስቃሴ አስተምህሮ | መጽሕፍ ቅዱሳዊ የክርስትና አስተምህሮ |
|---|---|---|
| መጽሐፍ ቅዱስ | መጽሐፍ ቅዱስ ለሰው የህይወት መመሪያን ለመስጠት ብቃት የለውም:: ስለሆነም መገለጦች፣ ከሰዎች፣ ከመንፈሳዊ ኃይላትና ከመጻህፍት መጠቀም ወሳኝ ነው:: ስለሆነም ዓለም አቀፍ የአ.ዘ.እ. መጽሐፍ ሁላቀፍ ስለሆነ ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል:: | መጽሐፍ ቅዱስ ስልጣን ያለው፣ ኃይለኛ፣ ሰውን በማናቸውም በጐ የህይወት አቀጣጫ ሊመራ የሚችል፣ ክርስቶስን በመቀበል የሚያነበው ሁሉ የህይወት እርካታና ደስታ ሊያገኝበትና የሰማይን ርስት ሊጨብጥበት የሚችል ስህተት የሌለበት የጌታ ቃል ነው:: ዮሐ.5፣39፤ ራዕይ22፣18-19 2ኛጴጥ. 1፣21፤ ሐዋ. 17፣2፤ 11፤ 18፣28፤ 20፣32 |
| ዳግም ልደት | ግላዊ ለውጥ ወይም ፈውስ ሲሆን ነው:: ይህም የሚከሰተው መንፈሳዊ ኃይላት የሰውን ማንነት ሲቆጣጠሩና ሰውም ከፍተኛውን መንፈሳዊ ኃይል፣ እውቀትና ጥበብ ሊቀበል ነው:: | ሰው አምኖ በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና በክርስቶስ ደም ከኃጢአቱ ሲነጻና ከመንፈስ ቅዱስ ዳግም ተወልዶ የእግዘአብሔር ልጅ ሲሆን:: ቲቶ 3፣5፤ ዮሐ. 3፣3-5 |
| ዳግም ምጽአት | ከመናፍስት ዓለም ስላም ሰጪ የሆነው ክርስቶስ ይመጣል:: ሲመጣም ለሁላችን አምላክ-እኔነት ደረጃ ውስጥ የሚያስገባንን ከፍተኛ ውንና የመጨረሻውን ንቃተ ህሊና ይሰጠናል:: የክርስቶስ ኢየሱስ ንቃተ ህሊና (Christ consciousness) ይኖረናል:: | ክርስቶስ ከአባቱ ዘንድ ከሰማያዊው መንግሥት ለሺህ ዓመት መንግሥት ለመንገስ ይመጣል:: የመናፍስት ሁሉ የበላይና ጌታ ነው:: የቅዱሳንን አካል ወደ ማይሞትና ወደ ተከበረ ማንነት ይለውጣል:: ሰዎችን ወደ አምላክነት ደረጃ አያደርስም:: ፊልጵ. 3:21፤ ራዕይ 19:11-14 |



| | የአዲስ ዘመን እንቅስቃሴ አስተምህሮ | መጽሕፍ ቅዱሳዊ የክርስትና አስተምህሮ |
|---|---|---|
| መንግሥተ ሰማይ | ይህች ምድር በመንፈስ ነጽታ ሰው የክርስቶስን /የባለ 666ቱን/ ንቃተ ህሊና አግኝቶ በምድር አምላክ-እኔነት ወይም የሰው ሉአላዊነት የሚረጋገጥበትና ሁሉም ልዩነት ጠፍቶ አንድ ስንሆን ነው:: | ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ምድር በመምጣት ከተለወጡት ጋር ለሺህ ዓመታት ነግሶ ደግሞም በአዲስ ሰማይና ምድር መኖር ሲጀመር:: ራዕይ 20፣22 |
| ገነት | ማንኛውም ሰው (ሁሉም) ከሞቱ በኋላ መንፈሳቸው ሄዶ የሚያርፍበት ሰማያዊ ከተማ ሻምባላ /Shamballa/ ይባላል:: | በክርስቶስ ያመኑ ቅዱሳን ብቻ በሰማይ እስከ ትንሳኤ መንፈሳቸው የሚያርፍበት የመጠባበቂያ ሥፍራ ገነት ይባላል:: |
| ገሃነም | ገሃነም የሚባል ፈጽሞ የለም | ኃጢአተኞች ሁሉ ለዘላለም የሚሰቃዩበት የቅጣት ሥፍራ:: ራዕይ 20፣13-15 |
| የክርስቶስ ተቃዋሚ | ማንኛውም አምላክ መሆኑን የማይቀበል ሰው:: | የእግዘአብሔር ልጅ የሆነውን፣ በመስቀል ሞቶ ኃጢአትን በደሙ የሚያነጻውን ጌታ ኢየሱስ የማይቀበል፣ ኢየሱስ ከሥጋ የመጣ አምላክ መሆኑን የሚክድ ሁሉ:: 1ዮሐ. 4:2-3፤ 2:18 |
| ደም መፍሰስ | ይህች ምድራችን ንጹህ፣ ሚዛናዊና ፍትህ የሞላበት የምትሆነው ደም ሲፈስላት ነው:: ስለሆነም ለአዲስ ዘመን እንቅስቃሴ የማይገዙ አይሁዶች ክርስቲያኖችና ሌሎች ክፍሎችም መሲሐችን ሲመጣ ለምድራቱ ማጥሪያ ይሰዋሉ:: | ለሰው ልጆች ሁሉ ኃጢአት መንጻት ሊፈስስ የተገባው የክርስቶስ ደም ብቻ ነው:: 1ኛዮሐ. 1፣7-9:: |

| | የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አስተምህሮ | መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክርስትና አስተምህሮ |
|---|---|---|
| የተሰቀለው ሰው | ለሰው ደህንነት የተሰቀለው ክርስቶስ ሳይሆን ክሪሰታ ነች:: የዓለም እናትና ሰላም ሰጪ ተሰቅላ ህያው የሆነችው ሰሰመጣች ደስ ይበላችሁ:: ነይ ብላችሁ ጸልዩ:: | ለሰው ልጆች መዳኛ የተሰቀለው ክርስቶስ ሴት አይደለም:: ከሰማየ ሰማያት የወረደው ከድንግል ማርያም የተወለደውና የተሰቀለው የእግዘአብሔር ልጅ ክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ ነው:: እውነተኛው ሰላም በእርሱ ብቻ ይገኛል:: የሐዋ.4፣12፤ ዮሐ. 14፣27 |
| የሔዋን ረሃብ | ሔዋን እምላክ ሰመሆን የወሰደችውን እርምጃ እኛም ልንወስድ ይገባል:: ሁላችንም ሔዋን ከበላችው የዛፍ ፍሬ ስር ተሰብስበን እንመገባለን:: | ሔዋን የመረጠችው የረሃብ መንገድ የሞት ህይወት ስለሆነ የእርሷን ፍለጋ ልንከተል ፈጽሞ አይገባንም:: ዘፍ. 3!14-20፤ 2ኛ ቆሮ. 11:3 |
| ወሲብ (ሩካቤ) | በሩካቤ እርካታ ጊዜ ኮከብን የሚያንቀሳቅስ ኃይል ሊገኝ ሰለሚችል ወሲብ ፈጽሞ ሊከለከል አይገባም፤ ምክንያቱም ኃይልን ማካፈል ሰለሆነ ነው:: | አንድ ለአንድ ከሆነው ወሲብ ውጪ ልቅ ወሲብ ሁሉ ዝሙትና አመንዝራነት ሰለሆነ ፍርድና ቅጣት ለላሰበት መወሰን ያስፈልጋል:: 1ኛ ተሰ. 4:3-4፤ ሮሜ 1:26-27 |
| ድንግል | በወሲብ እኳያ ለሁሉም የምትሆን ሴት (ወንድ) | ከወንድ ጋር ያልተገናኘች ሴት ወይም ከሴት ጋር ያልተገናኘ ወንድ:: ሉቃ. 1:34 |
| ስግደት | ጊዜው የሴት ስለሆነ እንሰገድላት | ሰግደት ለእውነተኛው እግዘአብሔር ብቻ ነው:: ዘፀ. 20:3-6፤ ሉቃስ 10:27 |
| ከኃጢአት መንጻት | ሰው ወሲብ ሲፈጽም ይነጻል | በክርስቶስ በማመን ብቻ ይነጻል:: 1ኛ ዮሐ. 2:1፤ 1:5 |
| ጨለማ | የኃይል ማግኛ ዋነኛው መንገድ ነው:: | ወደ ዘላለም ጥፋት መሔጃ መንገድ ነው:: 2ኛ ቆሮ. 4:4፤ ዮሐ. 1:5 |



| | የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አስተምህሮ | መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክርስትና አስተምህሮ |
|---|---|---|
| እባብ | የገነቱ እባብ ራሱ አምላክ ሰለነበር እንከተለዋለን:: | ሰይጣን መልኩን ቀይሮ የመጣበት ስለሆነ ነፍስ ገዳይ ጠላት ነው:: 2ኛ ቆሮ.11:3፤ ራዕይ 20:1-2 |

ማንኛውም ስለ አዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ግንዛቤ ማግኘት የሚፈልግ ሰው ከላይ የተዘረዘሩትን መሠረታዊ ትምህርቶቻቸውን ፈጽሞ ሊረዳቸው ያሻል:: በተጨማሪም ማናቸውም የኃይማኖት ክፍሎች የሚያስተላልፏቸው ትምህርቶች በአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አስተምህሮ መለከፍ አለመለከፋቸውም በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ለመለየት ያስችላል:: ትምህርቶቻቸው በእነዚህ አበይት ሃሳቦች ላይ ያተኩራል:: አዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ መንፈሳዊ እብዮት በማካሔድ የሃይማኖት ሰውጥ እናመጣለን የሚሉት በሰንጠረዡ ውስጥ እንደተጠቀሰው ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውንና ወይም ከፊል ተመሳሳይነት ያሰውን አስተምህሮት በማቅረብ ነው:: አዲስ የሚሉትም ይህንኑ ትምህርታቸውን ነው:: ታዲያ ይህ ቀላል ክህደት ነው?!



## ሰባቱ የአውሬው ትምህርቶች ስርጭት

አውሬው በዓለም ላይ ከተለያዩ ቡድኖችና ድርጅቶች የተውጣጡ ከ400 በላይ መምህራን እንዳሉትና እነዚህም ሰባቱን የአውሬውን ትምህርቶች በማሰራጨት ላይ እንዳሉ ይነበባል::

### ሰባቱ የአውሬው (የሐሰተኛው ክርስቶስ) መሠረታዊ ትምህርቶች[12]

1ኛ. የመጽሐፍ ቅዱሱ ክርስቶስ እግዚአብሔር አልነበረም፣ አይደለምም፣ መሲህም ሊሆን አይችልም:: ይህ የአዲሱ ትውልድ እንቅስቃሴ መሪ ሐሰተኛው ክርስቶስ በዚህ ዓይነት ከፍተኛ የተቃውሞ መንፈስ እንደሚመጣ አስቀድሞ ተተንብዮአል:: 1ዮሐ. 2:18፤ 2ተሰ. 2:3-6፤ 1ኛ ዮሐ. 4:3::

2ኛ. እግዚአብሔር ሰብዓዊነት /ሞራላዊነትና-ሥነ ምግባራዊ/ ህላዌ ያለው ሳይሆን ኃይል-ጉልበት ነው:: ይህም አቋማቸው አዲስ ሳይሆን ቀድሞም ነበር:: ለምሳሌ በሮሜ 1:25 ላይ ...በፈጣሪም ፈንታ የተፈጠረውን አመለኩና አገለገሉ ተብሎ ተጽፏል::

3ኛ. ሰው ለህይወቱ ዘላቂ የሆነ መንፈሳዊ ምሪትን ለማግኘት ልዩና ሰማያዊ-ከሆኑ መንፈሳዊ ኃይላት ጋር ተራክቦ (ህብረት) መፍጠር አለበት:: ይህም አስቀድሞ በ1ኛ ጢሞ. 4:1 እና 1ኛ ዮሐ. 4:1-3 ላይ የተጠቀሰው መፈጸሙን ያሳያል::

4ኛ. ሰው ራሱ አምላክ ነው፣ ሰው በውስጡ ያለውን የእምቅ ኃይል ምንነት ቢረዳ ኖሮ አምላክ መሆኑን ያውቅ ነበር:: አሁንም ይህንን ኃይል ለማግኘት ሰው መጣር ይኖርበታል:: የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ተከታዮች «እምቅ ኃይል» የሚሉት መናፍስት ውስጣቸው ከገቡ በኋላ በህይወታቸው የሚፈጽሟቸውን ልዕለ-ተፈጥሯዊ ልምምዶች ነው እንጂ በእርግጥ ለአምላክነት የሚያበቃ ኃይል በውስጣቸው ኖሮ አይደለም:: በ2ኛቆሮ. 4:4 ላይ እንደተጠቀሰው የክርስቶስ የክብር ወንጌል እንዳያበራላቸው ክፉው መንፈስ መንፈሳዊ መረዳታቸውን ስላሳወረው ያላቸው ዕድል በአጋንንት የሚሰበክላቸውን ልዩ ወንጌል (የምስራች መሳይ አጥፊ መልዕክት) አሜን ብለው መቀበል ብቻ ነው::



# የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አመልካች ስዕሎች

JUNE 1990

"Christian Rock Is *Not* Christian!"


**The Dragon's Hot Breath**

**Unmasking The Awful Truth About "Christian" Rock Music**











፭ኛ. በዓለም የሚገኙ ኃይማኖቶችና ትምህርቶቻቸው ሁሉ አኩልና ግባቸውም አንድ ነው። ይህ የአውሬው ትምህርት ኀላማው እውነተኛውን የመዳን ጥበብ ምንጭ የሆነውን የክርስትናን እምነት በሌሎች ለመዋጥ (ለመሸፈንና ለማጥፋት) የተደረገ ጥንስስ ነው የአውሬው ዓላማ ኃይማኖትን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም እንቅስቃሴዎች ሁሉ ወደ አንድነት ማምጣት ነው።

6ኛ. የግሪክ፣ የግብጽና የባቢሎን ጥበብ እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥበብ ብቻ የእውነት መሠረት አይደለም።

በእርግጥ ከላይ የተዘረዘሩት ሦስት አገሮች የእግዚአብሔርን ምርጥ ህዝብ እስራኤልን ካሰቃዩት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ሆኖም የአውሬው ከፍተኛው የትኩረት አቅጣጫ ከሁለቱ አገሮች ይልቅ በባቢሎን ላይ ነው። የባቢሎን ታሪክ ጉላ ብሎ ከዘፍ. 11 ይጀምራል። የትዕቢት ከተማ ናት። የባቢሎን መንፈሳዊና ውጪአዊ ይዘትዋ በራዕይ 17 እና 18 በዝርዝር ተጽፏል። የባቢሎን ጥበብ ማለት የአጋንንት ጥበብ ማለት ነው። ምክንያቱም ልክ በኢሳ. 14:12-14፣ ሰይጣን፣ በዘፍ. 3 እና 11 ሰዎች እንደ እግዚአብሔር ለመሆን ስለጣሩ ነው ዛሬም የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አቢይ ገቢር ይኸው ነው።
ከዓለም ታሪክና ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ እንደተረጋገጠው ኢየሩሳሌም የክርስቶስ ኢየሱስ ከተማ እንደሆነች ሁሉ ባቢሎን ደግሞ የሰይጣንና የአውሬው ዙፋን መቀመጫ ከተማ እንደምትሆን ይታሰባል።

7ኛ. ሰላምና ፍቅር እንጂ ኃጢአትና ክፉ የለም። ይህ ሃሣብ አውሬው በሚነግሥበት ጊዜ በሰባቱ ዓመታት መከራ ሰዎች ሰላምና ደህንነት ነው ሲሉ 1ኛ ተሰ. 5:3 ምጥ እርጉዝን እንደሚይዛት ጥፋት በድንገት እንደሚመጣባቸው የሚያመለክት ነው። ሰዎች ኃጢአት እና ክፉ መኖሩን ካሰቡና ካመኑ ውጤቱ ሞትና የዘላለም ስቃይ (ቅጣት) እንደሆነ አውቀው ይረዳሉ። ከተረዱ ደግሞ የመዳኛውን መፍትሔ ይፈልጋሉ። ክርስቶስ ኢየሱስንም ያገኛሉ። ዮሐ. 3:16 እና የሐዋ. 4:12 ስለሆነም ሰዎች በእውነተኛው አዳኝ በክርስቶስ ኢየሱስ እንዳያምኑና ወደ እርሱ እንዳያስቡ የጥፋት መሠረት የሆኑትን ኃጢአትና ክፉ እንደሌሉና የአእምሮ ቅዠቶች እንደሆኑ ማስተማር አለባቸው። የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ መሪዎችና ተከታዮቻቸው ከላይ የተጠቀሱትን መሠረታዊ የአውሬው ትምህርቶች በከፍተኛ ፍጥነት በማንቀሳቀስ ላይ ናቸው። የትምህርቶቹ መገኘትና መስራጨት አውሬው በቅርብ መኖሩን ያሳያል። እነዚህ ሰባት የአውሬው አስተምህሮት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የእውነተኛውን የክርስትና አስተምህሮ የሚቃወም ነው። ክህደት ለመሆኑ ግልጽ ሆኖ ይታያል።



## የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ዓላማና ትኩረት

የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ስሙ እንደሚያመለክተው አዲስ ይባል እንጂ በመሠረቱ ፍጹም አዲስ አይደለም። ሆኖም ቀድሞ የነበረ አሁን በዘመኑ ፍጻሜ ደግሞ በተጨማሪ መልኮች የመጣ ማለት ነው። የዚህ እንቅስቃሴ መሠረት ሰይጣን ነው። እንቅስቃሴው ለመጀመሪያ ጊዜ የጀመረው በሰማይ ሲሆን ተባባሪ ኃይላት የወደቁ መላዕክት ነበሩ። ከሰው ዘር ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ከዚህ እንቅስቃሴ ጋር የተባበሩት አዳምና ሔዋን ናቸው። ከአዳምና ሔዋን ቀጥሎ በዘፍ. 6 እንደምናነበው ፀረ-ኖሃዊ-እንቅስቃሴ የነበራቸው ኔፊሊማውያን በተጨማሪም በዘፍ. 11 ላይ ታሪካቸው የተጠቀሰው የሰናኦር ምድር ሰዎች (ባቢሎናውያን) ይገኛሉ።

የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ መርህ የወጣው በአብዛኛው ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው። ይህም ማለት «ሰይጣን ለአመሉ መጽሐፍ ቅዱስ ይጠቅሳል አሉ» እንደሚባለው ክፉው ለራሱ ዓላማና ግብ ተስማሚ በሆነ መልኩ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል አጣምሞ በመተርጐም ነው። ለምሳሌ በራዕይ 21:1-6 ላይ እግዚአብሔር ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ እንዳለ ሰይጣንም ሰዎች እግዚአብሔርን እንዳያዩ እርሱን እንዲመለከቱ ለማድረግ አዲስ የሚለውን ሃሣብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ወስዶ ቀድሞ የነበረውን ሆኖም ትውልድ የረሳውን በአዲስ መልክ ያቀርበዋል። ወይም ደግሞ እግዚአብሔር ለሰዎች አዳዲስ እውቀትን ሲገልጥ ያንን ራሱ እንዳደረገ በማስመሰል የሰዎችን ልብ በማሳወር ይጠቀማል። የመጠቀሚያ ዘዴው ደረጃ ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጻጸር ምን ያህል እንደሆነ በውል ባይታወቅም ማጭበርበሩ ተጨምሮበት ሙሉ በሙሉ እስኪጣል ድረስ የሚሰራበት ኃይል እንዳለው ይታወቃል። የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ መርህ ምንጭ አውሬው እንደመሆኑ መጠን የአውሬውን ዓላማ ከፍጻሜ ማድረስ ዕለታዊ ተግባራቸው ነው። የአውሬው (የሐሰተኛው ክርስቶስ) ዓላማዎች ብዙዎች ናቸው። ሆኖም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ይሆናሉ።[13]

ሰው ሁሉ እስከአሁን በከፍተኛ ደረጃ ሊሰቃይ የቻለው ያለውን መለኮታዊ ሥልጣን ባለመረዳቱ መሆኑን አሳውቆ ከማናቸውም ዓይነት ግልጽና ስውር ጭቆና ነጻ እንዲወጣ ማበረታታት ፀቢይ ዓላማቸው ነው። ሰው መለኮታዊ መሆኑን ቢያውቅ ፊት ለፊቱ ሊመጡ ያሉትን ቀውሶች-አሉታዊ ገጠመኞች ያለ ምንም ችግር ማለፍ ስለሚችልበት ልዕለ-ተፈጥሯዊ ልምምድ፣ የሰውን አእምሮ ያለ ችግር ማንበብና መረዳት ስለሚቻልበት፣ ያለ ረዳት መሣሪያ በብዙ ሺህ ማይልስ ርቀት ላይ እየተፈጸመ ያለውን ሁነት በግልጽ ማየት ስለመቻል፤ ቀለማት ላይ በማትኮር፣ አወስቦን በመፈጸም፣ የከበሩ ደንጊያ ጥናቶችን (ጂሞሎጂ) በመለማመድ፣ እጣን በማጨስ፣ ልዩ በሆነና ወሲባዊ ቅላጼ ላይ ባተኮረ ዘፈን (ሙዚቃ)፤ ሓሺሽ በመውሰድ፣ ዮጋን በመለማመድና-እጅ በመጫን ሥርዓት ወዘተ ሰዎች ወደ አምላክነት የሚለወጡባቸውን ዘዴዎች ማሳየት ሌሎች ዓላማዎቻቸው ናቸው። በምድር ገጽ ላይ የሚኖር ማንኛውም እነርሱ ቀርበው የሚያነጋግሩት ሁሉ መለኮት መሆኑን የማይቀበል ከሆነ ሊያጠፉት ውሣኔ አድርገዋል። በዓለም ያለው ሃብትና የሃብት ምንጭ

የሆነው የምድር ክልል በሙሉ በቁጥጥራቸው ሥር መሆን እንዳለበት ያምናሉ:: በእስራኤል ክርስ-ምድር ውስጥ ያለውም ሃብት ለዓለም ህዝብ ጥቅም መዋል እንዳለበት ማሳየት አቋማቸው ነው:: የመጽሐፍ ቅዱሱ ክርስቶስ ኢየሱስ ለዓለም መድኃኒት መሆን እንደማይችል በማስተማር ከፍተኛ ቅስቀሳ ያደርጋሉ:: ያላቸውን ብዙ ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ ፖለቲካን ሃይማኖትንና ህብረተሰባዊ ግንኙነቶች በሙሉ አንድ ወጥ አሠራር እንዲኖራቸው ያደፋፍራሉ:: ለዚህም በኢንተርኔት አማካይነት ዓለም-አቀፋዊ ቁጥጥር እናደርጋለን ይላሉ:: ይህንን የሚቃወሙትን የምድር ወገኖች በሙሉ የማይገጥሙ (ዚ-አንፊት ግሩኘ) በማለት ከዚህ ምድር ሊያጠፉዋቸው አቅደዋል:: እነዚህ (አዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ) የአውሬው ገባሪ ኃይላት እንደመሆናቸው መጠን ብዙ ቅዱሳንን ይገድላሉ:: ራዕ. 6:9-10፤ 17:6፤ 18:24፤ 16:6፤ 13:10:: አዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ቤተ ክርስቲያንን በርዞ ማጥፋት አላማቸው ነው:: ማናቸውንም መጽሐፍ ቅዱሳዊና እውነተኛ የሆኑትን የክርስትና እምነት ተከታዮች በመጀመሪያ ረቂቅ በሆነ ዘዴ ቀጥሎ ከተደራጁና ኃይላቸውን ለዓለም ካሳወቁ በኋላ ደግሞ በግልጽ እውነተኛይቱን ቤተ ክርስቲያን ለማጥፋት ጥረት ያደርጋሉ:: በራዕይ 13:10 እና ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰውም ለጊዜው ይሳካላቸዋል:: ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ብዙ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ:: የመጀመሪያው በ2ኛ ቆሮ. 11:12-15 እንደተጠቀሰው ራስን ከቤተ ክርስቲያን ጋር አመሳስሎ መቅረብና በኋላ ዓላማቸውን መፈጸም ነው:: በቃሉና በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው መናፍስትን በመለየት የሚመላለሱ ቤተ ክርስቲያናት ለአንድ አፍታ እንኳን አይንበረከኩላቸውም:: ሆኖም ለራሳቸው ክብርና ጥቅም ሲሉ እውነትን እየረገጡ የሚመላለሱ ስማውያን ክርስቲያኖች በመረባቸው ይያዛሉ:: ወደ ምርኮኝነትም ይሄዳሉ፣ በአንጻሩ ደግሞ የክርስቶስ ሆነው ስጋን ከክፉ ምኞቱና መሻቱ ጋር የሰቀሉ እንደሁሉቱ ነቢያት ለቅድስና በመኖራቸው ይገደላሉ::

የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አባላት ሆነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስም ያላቸውና ራሳቸውን ቤተ ክርስቲያን ነን ብለው የሚጠሩ የተወሰኑ ሃይማኖተኞች አሉ:: ከእነዚህ ውስጥ የሴት ቤተ መቅደስ፣ ሥነ ሳይንሳዊ ቤተ ክርስቲያን፣ የአምላክ ልጆች፣ የአርማጌዶን፣ የተዋህዶ (ዩኒፊኬሽን)፣ የመለኮተ ሰው ቤተ ክርስቲያንና፣ የያህዌ መሲሃዊ ቤተ ክርስቲያን ወዘተ ይገኛሉ::[14] አዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ በተቻለ መጠን ራሳቸውን መሰወር እንጂ መግለጥ አይፈልጉም:: እነዚህ ሁሉ ሰዎች በሃይማኖት ስም ለማጥመድ የተዘጋጁ መረቦች ናቸው:: ዕቅዳቸውና ተግባራቸው ሊጨነግፍ የማይችልበት ደረጃ ላይ መድረሱን ካላረጋገጡ በስተቀር ገሃድ አይወጡም:: ወደ ቤተ ክርስቲያን ከገቡ በኋላ ቀስ በቀስ አባላትን ይይዛሉ፣ በተለያየ ዘዴ እንደ አቤሴሎም የሰውን ነፍስ ይሰርቃሉ:: ሁኔታ ሲመቻችላቸው የራሳቸውን ዓላማ ያስፈጽማሉ:: 2ኛ ሳሙ. 14-15::

በአሁኑ ጊዜ በምድር ላይ የሰይጣን፣ የአውሬውና፣ የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ (የገሃነም ደጆች) ተፋላሚ ቤተ ክርስቲያን ናት:: ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ወኪል ስለሆነች ነው:: ስለሆነም የአውሬው ስውር መንፈስ ቤተ ክርስቲያን ሳታየው መሥራት ይኖርበታል:: 2ኛተሰ.



2:6-7:: የአውሬው መንፈስ ሥራ በቤተ ክርስቲያን ከታየ ስመፍረሱ ምንም ጥርጥር የለውም:: ለዚህም ነው የአመጽ ሚስጢር አሁን ይሰራልና የተባለው:: በምድር ያለን ቅዱሳን በሙሉ የክርስቶስ ወኪሎች የገሃነም ደጅ ተፋላሚዎች መሆናችንን አበክረን በማወቅ ቤተ ክርስቲያንን ለመበወዝ የተነሳውን ይህንን የአምላክኞነት መንፈስ በጾም በፀሎት፣ መጽሐፍ ቅዱስን በመመርመርና በክርስቶስ የስሙ ሥልጣን መግጠም ያሻል:: የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አስተምህሮ ክርስቶስ ለሌላቸውና መንፈሳዊ አይናቸው እንደ ኒቆዲሞስ ቅድመ-ዳግም ልደት ህይወት ለታወረባቸው ሁሉ ጣፋጭ ነው:: ብዙ ህያው መሳይ ተስፋዎችን ይሰጣሉ:: ህዝቡም ተስፋው እውነት ይመስለውና ይጠማጠምበታል:: የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ከሚሰጧቸው ተስፋዎች ውስጥ ጥቂቶቹ ሰው ራሱን በራሱ ወይም በሌላ አካል በማጥፋትና (በመግደል) ወደ ሌላ ዓለም መለወጥ፤ ደግሞ ደጋግሞ በነፍሱ ትስብዕት ሂደት መወለድና ለዘላለም መኖር፤ ከሰውነቱ ውስጥ በመንፈስ ወጥቶ መብረር፣ ከሰው ወደ እንስሳነት ከእንስሳነት ወደ ሌላ ፍጡር በሉጠት ሂደት መኖር እንደሚችል ማስተማር ወዘተ ናቸው:: 150,000 ተከታዮች ያሏት ማሪያ ዴቪ ክርስቶስ የምትባለዋ ራሺያዊት «ራስን ከቁስ መለየት» በሚል መርህ አባላቶቿን ወደ ሌላ ዓለም ለማሻገር ጥረት አድርጋ ነበር:: ከተከታዮቹ አንዳንዶቹ ዕድሜአቸው 187000 እንደሆነ ተናግረዋል:: ይህ በነፍስ ትስብዕት ዘዴ መሆኑ ነው:: ሆኖም በዚህ ዘዴ ሰው ሲኦል ካልሆነ በቀር ወደ ገነት ፈጽሞ ሊገባ አይችልም::[14.1]

የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ሌላው ዐቢይ ተልዕኮ የወንጌልን መልክ ማጥፋት ነው:: ይህንንም የሚያደርጉት ተመሳሳይ የሆኑ ጣፋጭ መሰል ሆኖም ሰዎችን ጀሜ የሚያወርዱ መጻህፍትን ማሳተምና ማሰራጨት ነው:: እነዚህ መጻህፍት ርዕሦቻቸው በጣም የሚስቡና የሚያመራምሩ፣ ሰውን ከእምነት የሚያፈናቅሉ አቴቴ የተጠናወታቸው ንባባት ናቸው:: የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ እንደተባለ እውነተኛ አማኝ ዘውታሪዎች ቃሉን ሲሰሙ መንፈስ ቅዱስ እንደሚወርድባቸው ሁሉ ሐዋ. 11:44 በአጋንንት ምሪት የተጻፉትንም መጻህፍት የሚያነብቡ ሁሉ ክፉ መንፈስ ሊጠናወታቸው (በመግባት ወይም በማጥቃት) እንደሚችል ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ ልብ ይባላል:: አዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ከሚጠቀሙባቸውና ሰዎችን ከሚስቡባቸው እውቅ መጻሕፍት ውስጥ ጥቂቶቹ፤ የሄኖክ ቁልፍ፣ የተሟላው የአስማትና የጥንቆላ መጽሐፍ፣ የንጋት ልጆች፣ አስትራ፣ የቀስተ ደመናው ድልድይ፣ ራስን የመፈለግ ዘመቻ፣ የዘላለም ዳንስና ወዘተ ይገኛሉ:: በአሁኑ ጊዜ አዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ የተወሰኑ ክርስቲያን መሪዎችንና አገልጋዮችን አድራሻ ፈልጎ በማግኘት ውድ የሆኑ ትላልቅ መጻሕፍቶቻቸውን በነጻ መላክ ጀምረዋል:: የእነዚህም ንባባት አካሄድ እምብዛም ከመጽሐፍ ቅዱስ የራቀ አይደለም:: በጣም ተመሳሳይ ቃላትን ይጠቀማሉ:: አንባቢያን በከፍተኛ ነጽሮት (አትኩሮት) ካልመረመሯቸው በስተቀር ለአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሸሎኪያና መግቢያ ቀዳዳ ሊፈጥሩ ይችላሉ:: የእነዚህ ንባባት ዋነኛ ዓላማ የትክክለኛውን ወንጌል ርቱዕ መልዕክት መበረዝ ነው:: ስለሆነም የወንጌሉ ባለአደራዎች የሆንን ሁሉ ክርስትናችንን አይቶ ማጣት

እንዳይሆንብን ቆመን አናንቀላፋ፤ እዳችንን ለመወጣት ህያው ትግልን እንታገል::

150000 (መቶ ሐምሳ ሺ) ተከታዮቿ ራሳቸውን ከቁሳዊ አካል ይለያሉ ያለችው ሐሰተኛዋ መሲህ ማሪያ ዴቪ ክርስቶስ



ፀረ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንቅስቃሴ

ማንኛውም መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር እንደሆነ የማይቀበል ግለሰብ፣ ቡድንና ሃይማኖታዊ ድርጅት ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም:: በዚህ ላይ መጽሐፍ ቅዱስን በተሻሻለ መልኩ በአዲስ መልክ ጽፎ ለማቅረብ የሚደረግ ሙከራ ሁሉ በራዕይ 22:18-19 እውነት ላይ የሚደረግ አመጽ ይሆናል:: የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ በአሁኑ ጊዜ የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ዓለም አቀፋዊ መጽሐፍ ቅዱስ የተሰኘውን መጽሐፍ በማሰራጨት ላይ ይገኛሉ:: መጽሐፉም መጽሐፍ ቅዱስን በሚተካ መልኩ ሊያገለግል እንደሚችል ይታሰባል:: ህዝቡ ሁሉ ከተቀበለው በኋላ መጽሐፍ ቅዱስን ዋጋ ለማሳጣት የታቀደ እሳቦት ነው:: በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ብዙ ዓይነት ለውጦች እንደተካሄዱ ይነገራል፣ ይነበባል:: ከተደረጉት ዋና ዋና ለውጦች



ውስጥ አንዱ የአባታችን ሰይጣን ሆይ ፀሎት በአባታችን ሆይ ፀሎት መተካቱ ነው:: የትርጉም ቃሉም፣ በሲኦል የምትኖር አባታችን ሰይጣን ሆይ መንግስትህ ትምጣ ፈቃድህ በሲኦል እንደሆነች እንዲሁም በምድር ሆናለችና ወደ ፈተና ምራን ከክፉ አታድነን መንግሥትህ ያንተ ናትና የሚል ነው::[14.2]

ይህ የሚያመለክተን እውነተኛውን የሰማዩ እግዚአብሔር (የክርስቲያኖች አምላክ) ፈጽሞ እንደማያስፈልጋቸው ነው:: ይህ ከፍተኛው ክህደት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ውሸት እንደሆነ በመጻፍ በማውራትና በማስወራት በዓለም ህብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያጣ ብዙ ሴራዎችን በመጠንሰስ ላይ ይገኛሉ:: ይህ እንግዲህ ከእግዚአብሔር ጋር መጣላት ነው:: ከእግዚአብሔር ጋር የሚጣሉ ይደቅቃሉ ተብሎ እንደተጻፈ ሊደርስባቸው እንዳለ ያመለክታል:: ሰው መዳንን (የዘላለም ህይወትን) ማግኘት የሚችለው ወንጌል ሳይጣመም በትክክል ሲደርሰው ብቻ ነው:: የተበረዘና የተለወጠ ወንጌል ልዩ ወንጌል ነው:: ልዩ ወንጌል ደግሞ ሰውን በምድር በትንሹ ጠቅሞ በኋላ የሚከነክን ሃዘንንና ዘላለማዊ ስቃይን የሚያመጣ ነው:: ለምሳሌ የማሪያ ዴቪ ተከታዮች ወደ ዘላለሙ መደነሻ ቦታ እንደርሳለን በማለት ራሳቸውን በመግደል ከዚህ ዓለም ሲለዩ ሞትና ሲኦል ግን ወደ መሰቃያ ስፍራ ሲያስገቧቸው ማየታቸው ምንኛ ይደንቃቸውና ያሳዝናቸው ይሆን? እንግዲህ በዘመኑ ያለን ቅዱሳን ሳያሽ የበላ ዝንጀሮ ሲስል ያድራል የተባለው እንዳይደርስብን፣ መጻህፍትን ስንገዛ፣ ስንቀበል፣ ስናነብብ፣ ስናስነብብ ወደ አገር ለማስገባት ስንጻጻፍም እያጣራን ሊሆን ይገባል:: ሰው ወድዶ አይስትምና::

የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ የመጽሐፍ ቅዱስን መልክ ብቻ ሳይሆን የሰውንም መልክ ማጥፋት አላማቸው ነው:: ሰው የዘላለምን ህይወት መውረስ የሚችለው ሰው መሆኑን ሲቀበል ብቻ ነው:: ካልሆነ ግን ሰውና ወንጌል ይተላለፋሉ:: ወንጌል የመጣው ለሰው ነው:: ሰው ግን ሰው ብቻ መሆኑን በመልቀቅ አንዴ ወደ መንፈስ፣ አንዴ ወደ እንስሳት አንዴ ወደ ተክሎች እንዲሁም ወደ ግዑዝ ፍጥረታት ደረጃ ራሱን በማምጣት ለመቀራረብ ቢሞክር የደህንነት ወንጌል ያልፈዋል:: በአሁኑ ጊዜ የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ሰው በህይወት ሽክርክሪት (ከሰው ወደ እንስሳ ከእንስሳ ወደ ሰው ወዘተ) ሂደት ሰው ወደ እንስሳና አምላክ ደረጃ መለወጥ ይችላል:: በዚህም ለዘላለም ይኖራል፣ የሚሉት አስተምህሮ የዓለምን ህዝብ በመድረስ ላይ ይገኛል:: ሰው አምላክ ነኝ እንስሳም ነኝ ቢል ወንጌል ሊረባው አይችልም:: ምክንያቱም ወንጌል ለእንስሳተ፣ ለባህር ፍጥረታት፣ ለአምላክና ለመላዕክቱም ስላልመጣ ነው:: እንግዲህ ሰው ወደ ዘላለም ጥፋት የሚገባው ከዚህ ነጥብ (ሁኔታ) ላይ ነው:: ስለሆነም ሰው አካሄዱን በጥንቃቄ መመርመር ይኖርበታል::

## ክህደትና የአባታችን ሆይ ፀሎት

የዘመኑ ክህደት ከሚንጸባረቅባቸው መልኮች ውስጥ ሌላው በአባታችን ሆይ ፀሎት ላይ የተነጣጠረው ፌዝ ነው:: ሰዎች ከኃጢአታቸው

የተነሳ እግዚአብሔር ሲርቃቸው ሰይጣን መቅረቡ የማይቀር ነው። ሰይጣን ደግሞ በሰውና በመናፍስቱ አማካይነት ሰውን ይቀርበውና በጊዜያዊ ክብር ደስታና ጥቅማ ጥቅም ይይዘዋል። በዚህ ጊዜ ሰው የሰይጣን አባትነት መልካም መስሎ ይታየውና እውነተኛ አምላኩን ማጣጣል ይጀምራል። በእውነትም ላይ ጨምሮ ያፌዛል። የሰው በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ ከተገለጠባቸው በ1970ዎቹ ማብቂያ ትዕይንቶች ውስጥ አንዱ የአባታችን ሆይን ፀሎት በአባታችን ጆርጅ ቡሽ ሆይ ፀሎት መተካቱ ነበር። ፀሎቱም:

> አሜሪካን በምትገኘው በዋሽንግተን ከተማ የምትኖር አባታችን ጆርጅ ቡሽ ሆይ መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በቡልጋሪያና በሃንጋሪ እንደሆነች ሁሉ እንዲሁም በኢትዮጵያ በአገራችንም ትሁን። የዓመት ቀለባችንንም ስጠን የሚቀጥለውንም ዓመት አስቀምጥልን ብድራችንንም ይቅር በለን የምንከፍለው የለንምና ወደ ኮሚዩኒዝም አታግባን ከሶሻሊዝም አድነን እንጂ ኤምፔሪያሊዝም ያንተ ናትና ለዘላለሙ አሜን። የሚል ነበር።[15]

ጆርጅ ቡሽ ሥልጣን ሲለቅቁ ደግሞ በታይም ጋዜጣ 4ኛ ዓመት ቁ.. ህዳር 6/1991 የሚከተለውን እናነባለን።

> አባታችን ቢል ክሊንተን ሆይ
> በዋሽንግተን የምትኖር
> መንግሥትህ ይጠንክር፤
> መንፈስህም ይጎብኘን
> ፈቃድህ በቦዝንያና በኢራቅ እንደሆነች
> እንዲሁም በኢትዮጵያ ትሁን፤
> በላያችን ላይ የተጫኑትን ቅልቦችህን
> ፈጥነህ አንሳልን
> በደርግ ጊዜ የበደልነውንም ይቅር በለን።
> እኛም ቅልቦችህን ይቅር እንላቸዋለን፤
> ከእንግዲህ ወደ ክፉ ጦርነት አታግባን፤
> ዓለም በብቸኝነት ያንተ ናትና፤
> ኃይልም ሥልጣንም ለዘላለሙ አሜን።
>
> ክላሽንኮፍ ኃይላችን ነው።
> ክላሽንኮፍ ጽናታችን ነው።
> ክላሽንኮፍ መድህናችን ነው።
> ክላሽንኮፍ የነፍሳችን መድሃኒት ነው።
> የመጀመሪያዋ የጳውሎስ መልዕክት ወደ እስጢፋኖስ ሰዎች

እነዚህ በአባታችን ሆይ ፀሎት ላይ በማፌዝ የተሰነዘሩት ንግግሮች ምን ያህል በድርጅት መልክ እንደተደራጁ በውል ባይታወቅም መንፈሱ ግን አዳኚ መሆኑን ልብ ልንል ይገባል። ይህ ስድብ ነው።



የዚህ ጽሑፍ የጀርባ ሃሣብና ዓላማ (ሞቲቭ) ግልጽ ሆኖ ባይታይም አንድን እውነት ግን ያስተላልፋል። ይኸውም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ለእግዚአብሔር አክብሮት መንሳትን ነው።

በተጨማሪም በ1980ዎቹ አጋማሽ ላይ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የወጣ በአባታችን ሆይ ፀሎት ላይ የተጣለ ማሾፍ ተነብቧል። ንባቡም «የጣጤው ፀሎት» የሚል ርዕስ የተሰጠው ሲሆን ቃሉም፣

> በመሸታ ቤት የምትኖር አባታችን አልኮል ሆይ፣ ሽታህ ትቀደስ ስካርህ ትምጣ ፈቃድህ በመለኪያ እንደሆነ ሁሉ እንዲሁም በጠርሙስ ይሁን፤ የዕለት መስከሪያችንን ዛሬ ስጠን የትላንቱንም ዕዳ ይቅር በለን፤ እኛም በአፋችን የጠጣነውን ሁሉ በአፍንጫችን እናስወጣ ዘንድ፣ አቤቱ ከቡና ቤት አታርቀን፤ የተኛ ውሻ ከመርገጥ ከአስፋልት ቱቦ ከገደል አድነን እንጂ፤ ዝሙት የአንተ ናትና መከራና ጉስቁልናም ሳይለየን በጋን ሥር ሆነን ለዘላለሙ አሜን። የሚል ነው።[16]

ይህ ሁሉ ሙልጭ ያለ ክህደትና በአባታችን ሆይ ፀሎትም ላይ ማሻፍ ነው።

ጽሑፉ ለባልተኛ አስቂኝ፣ ለቁም ነገረኛና የእግዚአብሔር ቤት ቅናት ለሚበላው (ለሚቆረቆር) ሰው ደግሞ እጅግ አሳዛኝና አስቆጪ ነው። በመሠረቱ ይህ ንባብ በምሳ. 23:29-35 ሲመዘን እውነት ሆኖ እናገኘዋለን። ይህን ፀሎተኛ ዝሙት መከራና ጉስቁልና ገደል መውደቅ ውሻ ረግጦ መነከስ እያጠቃው ተመልሶ ለአልኮል ልመና ሲያቀርብ ይታያል። ጠቢቡ ሰለሞን «ደግሞ ጨምሬ እሻታለሁ ትላለህ» ይለዋል። ይህ ፀሎት በግለሰቡ ያደረ ረቂቅ መንፈስ ወይም ሥጋው በምፀት ፀሎት በእግዚአብሔር ቃል ላይ እንዲያሾፍ እንዳደረገው መረዳት ይቻላል። ይህ ታላቅ ክህደት ነው። <u>የዳቦ ፀሎት ምላስ አይዝም</u> የተባለው አነጋገር እዚህ ላይ እውነት ሆኖ ይታያል። እንግዲህ የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አባላት አቋምና በኢትዮጵያ ደግሞ በአባታችን ሆይ ፀሎት ላይ የተደረገው ማሾፍ የክህደት መንፈስ ቀስ ብሎ ውስጥ ውስጡን በመስራት ላይ መሆኑን ያሳየናል። ሌሎች ክህደቶችንም መጥቀስ ይቻላል። ለምሳሌ በቀደሙት ዓመታት አንድ ሰው ሌላውን እንደምን አለህ ደህና ነህ ወይ ብሎ ሲጠይቀው በታላቅ ፍርሃትና አክብሮት የፈጣሪውን ስም እየጠራ «እግዚአብሔር ይመስገን» ይል ነበር። በቅርብ ዓመታት ደግሞ ለተመሳሳይ ሰላምታ እግዘአብሔር ተጣለና ደህና ደህና መባል ተጀመረ አሁን ባለንበት ጊዜማ ይባስ ብሎ «ይመችህ ይመችኝ» መባል ተጀመረ። ቀላል ክህደት ነው? አይደለም!

### <u>በአስርቱ ትዕዛዛት ላይ የተደረገ ክህደት</u>

የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ የክህደት አቅጣጫ ከአባታችን ሆይ ፀሎት በተጨማሪ በ10ቱ ትዕዛዛትም ላይ ያተኮረ ነው። ይህ እንቅስቃሴ «<u>ምድር እናታችን</u>» (አወር ማዘር-ኧርዝ) በሚል አምልኮ <u>10ቱ የምድር</u>

ትዕዛዛት እንዲጠበቁ የሚያስገድድ ነው። አስርቱ የምድር ትዕዛዛትም የሚከተሉት ናቸው።[17]

1. ምድር ስለምትባርክህና ህይወትህን ስለምታለመልም ልትወዳትና ልታከብራት ይገባሃል።
2. እያንዳንዱን ቀን ለምድር ልትቀድስና የወራቶቿንም መለወጫ ልታከብር ይገባሃል።
3. ራስህን ከሌሎች ፍጥረታት በላይ አትመልከት ፈጽሞም አታጥፋቸው።
4. ለምትመገባቸው ምግቦች ለሚያለመልሙህ ለፍጥረታትና ለተክሎች ምሥጋና አቅርብ።
5. የሕዝብ ብዛት ለምድሪቱ ስለሚከብዳት መራባትህን ገድብ።
6. በጦር መሣሪያ አማካይነት የምድሪቱን ሃብት በመግደል አታጥፋ።
7. ከምድሪቱ በምታገኘው ጥቅም-ትርፍን አታሳድድ። ሆኖም የጠፋ ክብሯን ለመመለስ ተጣጣር።
8. በምድር ላይ ስትኖር ካገኘኸው የሥራህ ውጤት ከራስህና ከሌሎች አትደብቅ።
9. ምድሪቱን በማደህየትና በመርዝ በመጉዳት ከሚመጣው ትውልድ አትስረቅ።
10. ሁሉም ሊጠቀም በሚችል መልኩ ከምድር ቁሳዊ ነገሮችን ትጠቀማለህ።

በተጨማሪም የእስራኤሉ የተፈጥሮና የአካባቢ ጥበቃ ሚኒስቴር «አስርቱ አረንጓዴ ትዕዛዛት» በሚል የሚከተለውን ጽፏል።[18]

1. አካባቢያችንን ማክበር አለብን።
2. ምድርን ከነሙሉ ክብሯ ለመጠበቅ የግላዊነታችንን፣ የብሔረተኝነታችንን ባህሪ መለወጥ ይኖርብናል።
3. ውሣኔዎቻችን ሁሉ በአካባቢ ጤንነት ላይ ማትኮር ይኖርባቸዋል።
4. አካባቢን የማሻሻል ግዴታ ይጠበቅብናል።
5. ለአካባቢ ውበት የሚሰጡ ሃብቶችን መንከባከብ ይኖርብናል።
6. የፈጠራ በጐነት ያደለንን ሃብቶች ወደ ቀድሞ መልካም ሁኔታቸው ለመመለስ እንነሳ።
7. አካባቢን መዘበራረቅ፣ ማጥፋትና ማቆሸሽ አይገባንም።
8. አካባቢን በማጥናት ሂደትን የሚያበላሸውን ነገር ማስወገድ አለብን።
9. አካባቢያችንን ማገልገል አለብን።
10. ሰብአዊነት የተፈጥሮ አካል መሆኑን መርሳት የለብንም።

ከላይ የተጠቀሱት ሁለቱ 10ቱ ትዕዛዛት ለምን አስር ብቻ ሆኑ የሚለው ዐቢይ ጥያቄአችን ሊሆን ይገባል። ለምን አምስት ወይም ዘጠኝ አልሆኑም? ሰዎቹ በማወቅ ወይም ባለማወቅ ጽፈውት ሊሆን ይችላል። ሆኖም በትዕዛዛቱ ውስጥ ያለው ሐሣብ ወደ እግዚአብሔር ከማትኮር ይልቅ ወደ ተፈጥሮ ማትኮርን ያደፋፍራል። በተለይ 10ቱ የምድር ትዕዛዛት



በቀጥታ የ10ቱ የኦሪት ትዕዛዛት ተቃራኒ ሆኖ የቀረበ ይመስላል። ይህ መጽሐፍ ቅዱስንና ደራሲውን ማናናቅን እውነቱንም አለመቀበልን በአዲስ ነገር መተካትን ያመለክታል። ይህ ሙልጭ ያለና አይን ያወጣ ክህደት ሊሆን ይችላል። ስለምድርና ተፈጥሮ ሃብት ከ10 በላይ ትእዛዞችን ማውጣት ሲቻል ለምን 10 ብቻ ሆነ?

ምጽዐተ ውዳሴ ሰይጣን

በአሁኑ ጊዜ የሰይጣን መወደስና መመለክ ያለ ፍርሃት በየአቅጣጫው በመፍላት ላይ ይገኛል። በቀድሞ ጊዜ ቤተ ሰይጣን በስውርና በፍርሃት ይመሠረትና አምልኮም ይካሄድ ነበር። በአሁኑ ጊዜ ግን በግልጽ መካሄድ ጀምሯል። ሰይጣን ፈጽሞ ሊጠላ እንደማይገባ፣ አስቀድሞ ቬኑስ ላይ ይገዛ እንደነበር በኋላ ግን እግዚአብሔር ተመቅኝቶ ከሰማይ እንደጣለው አንድ ቀን ሰይጣን አሸናፊ ሆኖ ወደ ቀድሞ ክብሩ እንደሚመለስ ቀኑን የሚናፍቁ አሉ። ሰይጣንና ኢየሱስ ወንድማማቾች እንደሆኑ በመናገር ሊያቀራርቧቸው የሚሞክሩ፣ ሰይጣንንና እግዚአብሔርንም ለማስታረቅ የሚጸልዩ እንዳሉ ይሰማል። በአሁኑ ጊዜ ክርስቲያኖች በዝማሬ አምላካችንን እንደምናወድስ ሰይጣንንም የሚያከብሩ መኖሳታቸው እውቅ ነው። ታላቁን ወደ ገሃነም የሚወስደውን አውራ ጐዳና ተያይዘነዋል። ሁላችሁም የእኛን መንገድ ተከተሉ የሚል ጥሪ እንደሚስተጋባ ከአስርት መጽሔት ይነበባል።19

እስከ 1974 ዓ.ም. ታዋቂ ከነበሩት ዘፋኞች አንዱ በንስኮት ናሰይጣን ሆይ የሚገባኝን ክፈለኝን በማለት ይዘፍን ነበር። በ19ኛው ክፍለ ዘመን በክፋቱ ተወዳዳሪ አልነበረውም የሚባለውና በአሰቃቂ የስካር አሟሟት ከዚህ ዓለም የተለየው ጂሚ ፔጅ ራሱን ቢስት-666 (አውሬ-666) በማለት ለይሞ ነበር። ከሰይጣን ጋር ከፍተኛ ቅርበት ነበረው። ዚፔሊን የተባለው ዘፋኝ ደግሞ ከሰይጣን ጋር ስለምኖር እዘፍናለሁ፤ ጌታ ኢየሱስ ገፍቶኛል። ከሰይጣን ማምለጫ የለኝም፣ ሰይጣን ጣፋጭ ነው፣ የኃይሌም ምንጭ እርሱ ነው። ለሰይጣን እኖራለሁ፣ ሰይጣን 666ትን ይሰጣችኋል በማለት ይዘፍን ነበር። እንዲሁም ቬነም በመባል የታወቀውም ዘፋኝ መስዋዕት ለሉሲፈር ለጌታዬ አቅርቡ! አጋንንቶች ደስ ይበላችሁ! ዋጋችሁን ተምኑ! በማለት ይዘፍን ነበር። ይህ ሁሉ የሰው ልጅ ምን ያህል ውድ ፈጣሪውን እንደጣላና አምልኮተ ሰይጣንን እየወደደ እንደሆነ ያመለክተናል። ይህ ክህደት ነው። ይህ ዘፈን ደግሞ በረቀቀ መልኩ ወደ ቤተ ክርስቲያንም እየገባ እንደሆነ የአስርት አዘጋጅ ስታንተር በጽሑፉ ዘርዝሮ ያቀርባል።20 በዘመኑ የተነሱት የሮክና የከባድ መሣሪያ ዘፈኖች (ሮክ ኤንድ ሄቪ ሜታል ሚዩዚክ) ሰይጣንን ለማምለኪያና ራስን ለማጥፊያ ብዙዎች ሲጠቀሙበት ታይቷል። እንግዲህ በዘመናችን ያሉ አንዳንድ በቃል ዘማርያን መንፈሳዊ ዝማሬን ከዘፈን ጋር እንዳይቀላቅሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

ነፍስን ለሰይጣን የመሸጥ ቅስቀሳ

የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ዓለምን ከሚያበረታቱበት ልምምዶች አንዱ ሰዎች ነፍሳቸውን ለሰይጣን እንዲሸጡ ማበረታታት ነው። እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1989 አጋማሽ ከኮምፒውተር የተገኘ ጽሑፍ

እንደሚጠቁመን ሰው ነፍሱን ለሰይጣን እንዲሸጥ የሚያነሳሳ ሃሣብ እንዳለ ያመለክታል። በጽሑፉ ውስጥ «ሰዎች ሆይ ኑ አድርጉት! እያንዳንዱ ሰው እያደረገው ስለሆነ እናንተም አድርጉት! ነፍሳችሁን ለሰይጣን ለመሸጥ እንኳን ደህና መጣችሁ በቀደሙት ዘመናት ነፍስን ለሰይጣን መሸጥ እንደቀልድና አስቸጋሪ ነገር ይታይ ነበር፤ አሁን ግን ልንቀበለው የሚገባና የማይቋረጥ ግልጋሎትን ከሰይጣን ማግኘት እንደሆነ ይገልጻል።

በተጨማሪም ሰይጣን ሰውን ሊያገለግል እንደሚችል ቃል ኪዳኑንም አክባሪ እንደሆነ ሰዎች ራሳቸውን መስጠት እንዳለባቸው ያደፋፍራል። (ስዕሉን ይመልከቱ)



ለሰው ነፍስ አሳቢ የሚመስለው በዘንዶ የተመሰለው ሰይጣን (ከኮምፒዩተር የተገኘ)

እስከአሁን የተመለከትነው በዓለማችን ያለውን የክህደት ሁኔታ ነው። ሰዎች የእግዚአብሔር የሆነውን በጐ እየገፉ የሰይጣንን ክፉ ነገር እየወደዱ መሆኑን በግልጽ እናያለን። ሰይጣን ያልደበላለቀውና ያልበረዘው ምን አለ። አዳምና ሄዋንን ከኤደን ካስወጣ እንኳን ከ6000 ዓመታት በላይ እንዳለ ይገመታል። ከጌታ ልደት ወዲህ እንኳን ባሉት 2000 ዓመታት ህልቆ መሳፍርት የሌላቸው 6000 ያህል ሃይማኖቶች ተፈጥረዋል። ከእነዚህ ሃይማኖቶች ጥቂቶቹ አስቀድመው ቢኖሩም በዘመኑ ግን በልዩ ሁኔታ ለህዝብ በመቅረብ ላይ ናቸው።



ብዙ ዓይነት ክህደቶችን ተመለከትን ከእነዚህ ሁሉ የሚበልጠውና እግዚአብሔር ፈጽሞ ሊታገሰው የማይችለው የክህደት ዓይነት አለ። ይህም ክህደት <u>የኃጢአት ሙላት መግለጫ ክህደት ነው</u>። በዳን. 8:23 ላይ <u>ኃጢአታቸው በተሞላች ጊዜ</u> እንቆቅልሽን የሚያስተውል ፊተ ጨካኝ ንጉሥ ይነሳል ይላል። ይህ የኃጢአት ሙላት የቱ ነው? ፊተ ጨካኙስ ንጉሥ? ኃጢአት ሲሞላ የእግዚአብሔር ቁጣ ይገለጣል። ሮሜ 1:18 ኃጢአት ሞላ የሚባለው ይቅርታ የማይደረግለት ኃጢአት ሲከሰትና ድግግሞሹ ሲበዛ ነው። ከአውሬውና ከአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ህልውና ጋር በተያያዘ ኃጢአት መሙላቱን የምናውቀው ከመካከላቸው <u>እኔ እግዚአብሔር ነኝ</u> የሚል ማንነት መኖሩን ስናረጋግጥ ነው። ታዲያ ከአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አባላት እኔ አምላክ ነኝ የሚል ማንነት ይኖር ይሆን?

ከ875000000 እስከ 1 ቢሊየን የሚደርሱ የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አባላት መመሪያቸው የሰውን አምላካዊና ሉአላዊነት መግለጽ ነው። አምላክ መሆናቸውን ያምናሉ፣ ይቀበላሉም። መሪያቸው አውሬውም ከ7ቱ ትምህርቶቹ ውስጥ አንዱ ሰው አምላክ መሆኑን የሚያስረግጥ ነው። በ2ኛተሰ. 2:4 ላይ ባለ 666ቱ አውሬ እኔ አምላክ ነኝ በማለት ሰዎች ከሚያመልኩት በላይ ራሱን ከፍ ከፍ እንደሚያደርግ ተተንብዮአል። እንግዲህ ቀደም ብሎ ከአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ልምምዶችና ዓላማዎች የተመለከትናቸው አቋሞች በቀጥታ በአሁኑ ጊዜ የአውሬውን መንፈስ በሥራ ላይ መሆን የሚገልጹ ናቸው። ይህም መንፈስ የአምላክ-እኔነት መንፈስ ነው።

እንግዲህ በ2ኛተሰ. 2:3 ላይ የተጠቀሱትን የክህደትንና የአመጸኛውን መምጣት በዘመኑ ዕይታ ስንመረምር ክህደቱ በመፈጸም ላይ እንዳለና እንዲያውም ከፍተኛው ደረጃ ላይ መድረሱን ማረጋገጥ እንችላለን። ክህደቱ ከቀደመ ይህም ክህደት እኔ (እኛ) አምላክ ነኝ (ነን) በሚል እንቅስቃሴ ከተገለጠ በቀጥታ አውሬው በደጅ መሆኑን ያመለክተናል። ይህ ከሆነ ደግሞ አውሬው ከመምጣቱ በፊት በር እንዲከፈትለት የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ መቃረቡን መገንዘብ ይቻላል። በክፍል ሁለት ስለ 666 በመጽሐፍ ቅዱስ የተተነበየውን በግልጽ እንመለከታለን።

## ክፍል ሁለት

## ፍካሬ 666

በክፍል አንድ ውስጥ የአውሬው የ666 ቁጥር መንገድ ጠራጊ ስለሆነው የክህደት መምጣትና በዓለማችን እየተካሄደ ያለውን የክህደት እንቅስቃሴ ይዘት ተመልክተናል:: በዚህ ክፍል ደግሞ ሁለተኛ ደረጃ ከክህደቱ በኋላ ስለሚመጣው ትክክለኛ መጠሪያ ስሙ በውል ስላልታወቀው የአመጽ ሰው ስለ ሐሰተኛው ክርስቶስ በዝርዝር እንመለከታለን::

### 2.1 የ666 አጀማመር

ስለ 666 ፊት ለፊት በትንቢት መልኩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎ የሚገኘው በራዕይ 13:18 ብቻ ነው:: ቃሉም፣

ጥበብ በዚህ አለ አእምሮ ያለው የአውሬውን ቁጥር ይቁጠረው:: ቁጥሩ የሰው ቁጥር ነውና ቁጥሩም ስድስት መቶ ስድሣ ስድስት ነው የሚል ነው::


### የአውሬው ማስገበሪያዎች

ሐሰተኛው ክርስቶስ ወደ ምድር ሲመጣና ሲገዛ በግዛቱ ሥር ያሉ የምድር ነዋሪዎች እንዲንበረከኩለት የሚያደርገው በሦስት ዋና ዋና መንገዶች ነው:: ይኸውም በምልክቱ (በምስሉ)፣ በቁጥሩና፣ በስሙ ነው:: ራዕይ 13:16-17::

### የግምባርና የቀኝ እጅ ምልክት


አውሬው ሰዎችን ለራሱ የሚያንበረክከው በቀኝ ወይም በግራ እጃቸው ላይ በአውሬው የተዘጋጀውን ምልክት እንዲቀበሉ በማድረግ ነው:: ይህ ምልክት ምን እንደሆነ ግልጽ ሆኖ በመጽሐፍ ቅዱስ አልተጻፈም:: ሆኖም የአውሬው አርማ፣ የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ልዩ ልዩ የአምልኮ ምልክቶች እንደ ስዋስቲካ፣ የመስቀሉ በሦስት አንግልና በክብ ውስጥ ሆኖ መሳል፣ የዮጋ ልዩ ልዩ እንቅስቃሴ፣ የእባብና የዘንዶ ስዕል፣ የሦስተኛው ዓይን መብራት የሰማይና የምድር እንዲሁም የባህር ፍጥረታት ስዕላዊ መልክ ሲሆን እንደሚችል ይታሰባል:: በአውሬው ግዛት ሥር የሚኖሩና በፈቃዳቸው የተቀበሉት ሁሉ የሚያዘጋጅላቸውን ምልክቶች ይቀበላሉ::ራዕይ14:9-11፤ 16:2፤ 20:4-6






How this event may occur. These illustrations are from 666 Pictorial by Salem Kirban If you wish this book, send $4 to: Salem Kirban, Inc. Kent Road, Huntingdon Valley Penna. 19006. Price includes postage and handling

ሰዎችን ሁሉ ለመቆጣጠር በሰዎች አካል ውስጥ የምትቀበረው ከአስፐሪን የምታንሰዋ




**Chips:** Computer technology already exists to control every human being on Earth.

### የአውሬው ስም

ሁለተኛው አውሬው ሰዎችን የራሱ እንዲሆኑ የሚያደርግበት ዘዴ ስሙን እንዲቀበሉ ማድረግ ነው:: ራዕይ 13:17፤ 14:11 ስሙ ማን እንደሚሆን መጽሐፍ ቅዱስ አይነግረንም:: በዓለማችን ብዙ ሰዎች የአውሬውን ማንነት በስም ለይቶ ለመጥራት በማሰብ ከ35 ያላነሱ መጠሪያዎች ተሰንዝረዋል::[1] ለምሳሌ አንዳንዶች በዘፍ. 10 የተጠቀሰው የባቢሎን መስራች ናምሩድ ትንሳኤ አግኝቶ ይመጣል ሲሉ ሌሎች ደግሞ ሙሶሊኒን፣ ሂትለርን፣ ስታሊንን፣ ጐርባቾቭን፣ ኪሲንጀርንና ወዘተ እንደሆኑ አመልክተዋል:: ይህንንም ሊሉ የቻሉት የእነዚህ ሰዎች ስም በግሪክና በእንግሊዘኛው (የአልፋ ቤት) ስም ትንታኔ የስማቸው ቁጥር ተደምሮ 666 ስለሰጣቸው ነው:: በዚህ የቀደም ተከተል ዓይነት ሁኔታ ሌሎችም ስሞች ሊጠቀሱ ይችላሉ:: ሆኖም የታሪክ እውነትነቱ 100% የሚረጋገጠው ጌታ ሲመጣ ወይም ራሱ አውሬው ሲመጣ ስለሆነ እስከዚያው ነገርን ሳንንቅ አክርረንም ሳንቀበል በመመርመር መንፈስ በልብ መያዙ አይከፋም::

### የአውሬው ቁጥር

ሦስተኛው ሐሰተኛው ክርስቶስ ተከታዮቹን በባርነት የሚገዛበት ዘዴ የስሙን ቁጥር 666ትን እንዲቀበሉ በማድረግ ነው:: ራዕይ 15:2:: ስለ 666 ቁጥር ስናስብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱትን ቁጥሮችና አተረጓጐማቸውን መረዳቱ ጠቃሚ ይሆናል:: በዕብራይስጥ ቋንቋ የፊደላት ቅደም ተከተል ከቁጥር ጋር የተያያዘ ዋጋ አለው:: በተለይም አዲስ ኪዳን በተጻፈበት ጊዜ የነበረውም የግሪክ ቋንቋ እንዲሁ ነበር:: የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱትን ቁጥሮች ከክንዋኔአቸው ጋር በማያያዝ ይተረጉሟቸዋል:: የእግዚአብሔር ትክክለኛ

መሃንዲስ መሆን በቁጥሮች ውስጥ እንደሚታይና ቁጥሮች የእግዚአብሔር ቃል ምስጢራዊ ኮድ (መለያ) እንደሆኑ ይነገራል::[2] ለምሳሌ አንድ የአንድነት፣ ሁለት የምስክርነትና የመተባበር፣ ሦስት የትንሣኤ፣ የመለኮት ምልዐትና ፍጹምነት፣ ስድስት የኃጢአት መገለጥ፣ የሰይጣን ክፋትና የሰው ድክመት፣ ዘጠኝ የመንፈስ ፍሬ፣ አሥራ ሁለት የአገዛት ፍጹምነት፣ ሃያ አራት የክህነት፣ ሰላሣ የክርስቶስ ኢየሱስ ደም፣ ሃምሣ የመንፈስ ቅዱስ፣ 666 ፀረ ክርስቶሳዊ የአውሬው ቁጥር፣ 1000 የእግዚአብሔር ክብር ወዘተ እንደሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኚዎች ያስተምራሉ::[3]

<u>የአውሬው ቁጥር</u> የሚለውን ሐረግ ስንመረምር ከላይ በተጠቀሰው ምሳሌ መሠረት አውሬ በግሪክ ቋንቋ <u>ቴሪዮን</u> ሲሆን እያንዳንዱ ፊደል በዕብራይስጡ ሲተነተንና በቁጥር ተዛምዶ ሲደመር 666 ይሰጣል:: በተመሳሳይ መልኩ ወደፊት አውሬው ሲመጣና መደበኛ መጠሪያ ስሙ ሲታወቅ የእያንዳንዱ የስሙ ፊደል በኤ ቢ ሲ ... ቅማሬያዊ ስሌት ሲተነተን 666 ሊሰጥ እንደሚችል ማሰብ ይቻላል:: በሌላ መልኩ ደግሞ የሰው ቁጥር የተባለው ሰው የሚያመለክተው በቀጥታ አውሬውን ብቻ ላይሆን ይችላል የሚልም አመለካከት አለ:: በ1970ዎቹ መጨረሻ በሐምሌ 1979 በወጣው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ «ሕይወት አልባው ወታደርና ህይወት አልባው ነፍሰ ገዳይ» በሚል ርዕስ በወጣው ጽሑፍ ላይ ተመርኩዞ በሌላ ጊዜ «<u>ገበያ በኮምፒውተር</u>» በሚል ርዕስ በአድማስ ገጽ ላይ ስለ አውሬው ዝርዝር ነገር ተጽፏል:: ጸሐፊው በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚሰራ ኮምፒውተር እንደሚሰራና ይህንንም ኮምፒውተር አውሬው ተብሎ እንዲጠራ የገበያ ተንታኞች እንደተስማሙ አስፍሯል:: ይህ ወደፊት የሚመጣው አውሬው የሚባለው ኮምፒውተር ሰዎችን እንዴት እንደሚቆጣጠር ሲገልጽ «ይህ በዕቅድ የተያዘው ጥናት በምድር ላይ የሚኖሩትን <u>ሰብአዊ ፍጥረታት በሙሉ በቁጥር ለመሰየም ዕቅድ አለው</u>» ይላል:: ይህ የሰዎች ሁሉ መጠሪያ ስም በቁጥር እንደሚሆን ያመለክታል:: ስለሆነም «<u>የሰው ቁጥር</u>» የሚለው አውሬውንና ሌሎችንም ሊጠቁም እንደሚችል ማሰብ ይቻላል::

እንግዲህ የዛሬ 2000 ዓመታት አካባቢ እግዚአብሔር ወደፊት ሊሆን ያለውን ለሐዋርያው ዮሐንስ አስታውቋል:: የስሙ ቁጥር 666 ተብሎ የሚጠራው አውሬ የተባለው ሐሰተኛው ክርስቶስ ሰዎችን እንደሚያስገብር የሚያመለክት ነው:: የአውሬውን ምልክት፣ ቁጥርና ስም መቀበል የሚያመለክተው የሰዎቹን ሙሉ በሙሉ ታማኝ ሆኖ መገዛትን ነው::

## 2.2 <u>የአውሬው ስሞች</u>[4]

መጽሐፍ ቅዱሳችን ስለሐሰተኛው ክርስቶስ (ስለአውሬው) 15 ያህል ስሞችን ያመለክታል:: ስሞቹም ምን ዓይነት ባህሪና ተግባር እንዳለው የሚያመለክቱ ናቸው::
የአውሬው ዋነኛ ስሙ የክርስቶስ ተቃዋሚ የሚል ሲሆን በተጨማሪም በሌሎች ስሞች ተጠርቷል:: እነዚህም ስሞች፣



<u>ትንሹ ቀንድ</u>፡ ዳን.7:7-28 በቁጥር 8 እና 25፤ 11:36፤ ራዕይ 13:1-5፤ 17፤3 እንደተጠቀሰው ይህ ቀንድ እግዚአብሔርን የሚሰድብ ነው::

<u>የባቢሎን ንጉሥ</u> ኢሳ. 14:4 በዚህ ጥቅስ የሚታየው የእስራኤል የድል ዝማሬ ባለፉት ተቃዋሚ ነገስታቶቿ ላይ እንዳልተፈጸመ ሆኖም በሺሁ ዓመት መጀመሪያ ላይ በክርስቶስ አማካይነት አውሬውን ድል እንደሚያደርጉ ያሳያል::

<u>አስጨናቂ</u> ኢሳ. 14:4 ለሰው መብትና ነጻነት አሳቢ ቢመስልም ውስጡና ተግባሩ ግን ክፉ እንደሆነ ያሳያል::

<u>አስገባሪ</u> ኢሳ. 14:4 አውሬው ሰዎች በፍጹም ሌላን ማንነት እንዲያመልኩ፣ ሌሎች በራሳቸው ፈቃድ እንዲሔዱ አይፈልግም:: ለእርሱና ለአባቱ ለሰይጣን እንዲንበረከኩለት ብቻ ይፈልጋል::

<u>ፊተ ጨካኝ</u> ዳን. 8:23 ባለ 666ቱ አውሬ እርሱና አለቃው ሰይጣን በፍጻሜ ዘመን ወደ ጥፋት እንደሚሔዱ ያውቃል:: ሌሎችንም ከራሱ ጋር ለማጥፋት ፈቃዱን ብቻ ለማድረግ እርምጃ ይወስዳል::[5]

<u>የሚመጣው አለቃ</u> ዳን. 9:26

<u>እንደ ፈቃዱ</u> ዳን. 11:16፣36-38 ሰይጣን በሰጠውና በሞላው ኃይልና ፈቃድ እንጂ የማንንም አስተያየት እንደማይቀበል ያሳያል:: ምክንያቱም ራሱን እንደ አምላክ ስለሚቆጥር ነው የእኔ ኃሣብ ብቻ የሚል አቋም ያላቸው ክርስቲያን ነን ባዮች ሁሉ የያዙት መንፈስ የማን እንደሆነ በጥንቃቄ ሊመረምሩ እንደሚገባቸው ያሳስበናል::

<u>ክፉ</u> ኢሳ. 11:4 ጌታ ሲመጣ በራዕይ 19:15 እና ቁ. 21 እንደተጠቀሰው አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወደ እሳት ባህር እንዲጣሉና የቀሩት እንዲጠፉ የሚደረገው ከጌታ አፍ በሚወጣው የሥልጣንና የፍርድ ቃል ነው:: አውሬው የሁለንተናው ዋነኛ ዓላማ በሰው ላይ ክፉ ማድረግ ነው:: ለምሳሌ ሁሉን በተንኮሉ ማጥፋቱ::

<u>የአመጽ ሰው</u> 2ኛተሰ. 2:3 ይህ ማለት አውሬው ከጌታ እውነት ጋር የማይስማማ ክፉ የሆነውን ድርጊት እንደሚሰራ ነው:: ለምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈውን እውነት ለመበረዝና ለመቀየር የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች መጥቀስ ይበቃል::

<u>የጥፋት ልጅ</u> 2ኛተሰ. 2:3 የአውሬው ግብ ሰውን ማጥፋት በመጨረሻም ራሱ መጥፋት ነው::

<u>666</u> ራዕይ 13:1

<u>ንገሥ</u> ዳን. 8:23 ባለፉት ነገሥታትና በክርስቶስ ላይ ለመብለጥ ያለውን መሻት የሚያሳዩ ናቸው::

## 2.3 የአውሬው ባህሪያትና ዓላማዎች

ቀደም ብሎ በተጠቀሰው ርዕስ ስሞች የአውሬውን ባህሪ የሚገልጽ እውነት እንዳለ በማሰብ በተጨማሪ ሐሰተኛው ክርስቶስ:

1. ዓላማው ማሸነፍ ነው ራዕይ 6:2 በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የአውሬው ፕሮግራም በግዛቶች ሁሉ ላይ ድል አድራጊ መሆን ነው። በማንም መሪና ገዢ መበለጥን ፈጽሞ አይፈልግም። ምክንያቱም ራሱን እንደ አምላክ ስለሚቆጥር ነው። ልዕለ ተፈርሯዊነቱን ማረጋገጥ እንዳለበት ይሰማዋል።

2. ማስመሰል ራዕይ 6:2 በራዕይ መጽሐፍ በ6:2 እና 19:11 ላይ ሁለት ማንነቶች በነጭ ፈረስ ላይ ተቀምጠው ሲወጡ ይታያል። የምዕ.6ቱ ሐሰተኛውን ክርስቶስ ይወክላል። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን ከተነጠቀች በኋላ የመጀመሪያው ማህተም ሲፈታ ወደ ምድር ነዋሪዎች የሚመጣው ሐሰተኛው ክርስቶስ ስለሚሆን ነው። የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ሲሆን አውሬውን የሚቋቋመው ማንነት (ቤተ ክርስቲያን) ለጊዜው ስለማይኖር አውሬው በተፈቀደለት ኃይሉ ይመጣል፤ ድልም ያደርጋል። እግዚአብሔርም ወደ ተወሰነለት የምድር ስፋት እንዲወጣ ይፈቅድለታል። እውነተኛ ልጁን ጌታ ኢየሱስን የዓለም ሰዎች ስላልተቀበሉ አውሬውን በኃጢአተኞች ትውልድ ላይ ይለቅቀዋል። 2ኛተሰ. 2:9-12። ይህም የሚሆነው ማህተሙ ሲፈታ ነው። አውሬውም የሚመጣው ልክ በራዕይ 19:11 ላይ እንደተጠቀሰው እንደክርስቶስ ምሳሌ ጻድቅና እውነተኛ ተዋጊ ለመምሰል በነጭ ፈረስ ላይ ተቀምጦ ነው። ሆኖም ግን ፊተ ጨካኝ ነው። ዳን. 8:23 ክርስቶስ ከሞት እንደተነሳ እርሱም ያስመስላል ራዕይ 13:3፤ በንጉሥነት (ዳን. 8:23)፤ በአምላክነት (2ኛተሰ. 2:4) ፤ በእንቆቅልሽ ፈቺነት (ዳን. 8:23) ወዘተ ራሱን ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር ያመሳስላል።

3. እንቆቅልሽ ፈቺ ዳን.8:23 አውሬው በራዕይ 13:3-4 እንደተጠቀሰው ሰዎችን ከሚገዛበትና ከሚያንበረክክበት ዘዴዎቹ ውስጥ አንዱ የሰዎችን ልጆች ችግር ለጊዜው በመፍታት መፍትሔ ስለሚያስገኝ ነው። ሕዝብ ከአንድ መሪ አንድ ጠቃሚ ነገር ካላገኘ በስተቀር በቀላሉ አይሰግድም ወይም ታዛዥና ተገዢ አይሆንም። አውሬው በአጋንንት መሞላቱና እንደ ኮምፒዩተር ባሉ ዘመናዊ የችግር መፍትሔ አስገኚ መሣሪያዎች ስለሚጠቀም የሰዎችን ልብ ይሰርቃል። ብዙ ተከታዮችንም ያገኛል። በኢየሱስ ወደ እሳት ባህር እስከተጣለበት ጊዜ የዓለምን ቀውሶች ለጊዜው በመጠኑ ስለሚያረግብ በብዙዎች ላይ ይሰለጥናል። ለዓለም ቀውስ እንደ መፍትሔ ከሚያቀርባቸው ውስጥ ጥቂቶቹ ክርስቲያኖችን ከምድር ማስወገድ፣ ማንኛቸውም የአካል ጉድለት ያለበትን ሰው በሰይፍ በመግደል ወደ ሻምባላ ሔዶ በሌላ አካል እንዲወለድ መግደል፤ ፀልዮ ራስን መግደል እንደሚቻል ማደፋፈር፤ ሲኦል ማለት ገነት እንደሆነ ማሳመን ወዘተ ናቸው።



4. ገዢነት ራዕይ 6:2፤ 13:7 አውሬው ትልቁ ምኞቱ ሁሉን ከእግሩ በታች በማንበርከክ ገዢ መሆን ነው። ስለሆነም በ10 መንግስታት ላይ ይሰለጥናል። ራዕይ 17:13

5. ራስን ማግነን ዳን.11:37 በምድር ላይ የሚኖር ማንኛውም ሰብዓዊም ሆነ በነፍስ ትስብዕት ደረጃ ያለፈ ፍጡር ሊተካከለው እንደማይችል ራሱን ይቆጥራል።

6. ሕላዌ-ምጡቅነት 2ኛተሰ. 2:4 አውሬው እኔ እግዚአብሔር ነኝ ሲል በብዙ የህይወት ሽክርክሪት (የነፍስ-ትስብዕት) የኖረ ማንነት እንደሆነ ከሰው ሁሉ የመጠቀ አኗኗር እንዳለውና እርሱ ራሱ አምላክ መሆኑን ማመልከቱ ነው። ከእርሱ በላይ ሊሰገድለት የሚገባ ማንነት መኖሩን አይቀበልም። ፍጹም ከሃዲና ተቃዋሚ ነው። 2ኛተሰ. 2:3፤ 1ኛዮሐ. 4:1-3።

7. ነፍስ ገዳይ ራዕይ 6:9-11፤ 7:9-17፤ 20:4-6፤ 13:10 አውሬው መንፈሱን የሚቀበለው ከአባቱ ከዲያብሎስ ነው። አባቱም ነፍስ ገዳይ እንደነበር አውሬውም የብዙ ቅዱሳንን ደም ያፈስሳል። በመከራው ዘመን ጌታን የሚቀበሉትን፣ ቀድሞ ከደው የነበሩትን በኋላ ንስሀ የሚገቡትን የመከራው ዘመን ክርስቲያኖችን (ቤተ ክርስቲያን) ይገድላቸዋል። ነቢዩ ዳንኤልም በድንቅ ያጠፋል (8:24) ብሎታል። ጌታ ድንቅ መካርና አዳኝ ነው። አውሬው ደግሞ በድንቅ የሚያጠፋ ነው። ወደ ዘላለም መደነሻ ቦታ ትገባላችሁ ብሎ ሲኦል ሲያስገባ እንዴት አያስደንቅ! ሆኖም ምን ዋጋ አለው። ያን ጊዜ መፍትሔ ስለማይኖር!

8. ተሳዳቢ 2ኛተሰ. 2:4፤ ራዕይ 13:5-6 በዚህ ክፍል ስድብ ስንል ራስን መለኮት በሆነው በእግዚአብሔር ቦታ ማስቀመጥንና ጌታ ሥልጣን የሰጣቸውን ማንነቶች በሙሉ መናቅ ማለት ነው።
ለምሳሌ አውሬው ራሱን እኔ አምላክ ነኝ ሲል አስቀድሞ በምድር ይኖሩ የነበሩትን በኋላ መንፈሳቸው ወደ ሰማይ ጻድቃን መንፈሶች (ዕብ. 12:22-23) የተቀላቀለውን ሰዎች ከአጋንንትና ከኃጢአተኞች ሰዎች መንፈስ ጋር ሲደባልቅ፤ እንዲሁም የመላዕክትን ሥልጣንና ማንነት ሲያበላሽ ይህ ስድብ ነው። አውሬው የመንፈስ ዓይነቶችን ለይቶ አያይም። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን፣ የቅዱሳን መላዕክትንና የሰዎችን መንፈስ ከወደቁ መላዕክት፣ ከአጋንንትና ከኃጢአተኞች ሰዎች ጋር ሲያነጻጽር ለያይቶ ነው። አውሬው ግን ሁሉንም የሰው መንፈሶች አድርጐ ያቀርባቸዋል። ያረጉ ጌቶች፣ የጥንት ኃይላት፣ የውስጥ ሂያጆች፣ የጥበብ ጌቶች ወዘተ በማለት አውሬው የሚጠራቸው መንፈሳዊ የሚባሉ ኃይላትን በሙሉ ሳይለያይ በአንድነት ነው።[7]

9. ተጻብኦ ጦርነት አለበት[8] ራዕይ 6:2፤ 19:19-20፤ 16:13-16። በትዕቢት አውሬውን የሚተካከል ስለሌለ በሚያዘጋጃቸው የጦር መሣሪያዎች ተፋልሞ አሸናፊ ለመሆን እጅግ ከፍተኛ የጦርነት

ጥማት አለበት። ባለው የጦር መሣሪያ ዝግጅት የሚተካከለው ኃይል እንደሌለ ስለሚገምት በመነጠቅ ወደ ሰማይ ሔደው ከክርስቶስ ጋር ለሺህ ዓመት ለመንገስ ወደ ምድር የሚመጡትን፣ ክርስቶስን፣ ቅዱሳን መላዕክቱንና ሰዎችን እንኳን ለመዋጋት ደፋር ነው። ምክንያቱም ሁልጊዜ ድል ማድረግን ስለሚያስብ ነው። ሆኖም ለማሸነፍ እንደተጠማ ፍጻሜው በመሸነፍ ማፈር ይሆናል።

10. <u>መካነ ጣኦትን ማስፋፋት</u> ራዕይ 13:14፤ ቁ. 3-4 አውሬው በከፍተኛ ደረጃ ጣኦት አምልኮን ያስፋፋል የራሱ ምስል እንኳን በአጋንንታዊና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አሰራር እንዲናገር በማድረግ ሰዎች እንዲፈሩትና እንዲንበረከኩለት ያስደርጋል። ከመናፍስት ጋር ከፍተኛ ትስስር አለው። በጣም የረቀቁና ዘመናዊ የሆኑ የመናፍስት አሰራሮችን ያስፋፋል። (ክፍል አንድ ክህደት ይመልከቱ)

11. <u>ማስፈራራት</u> ራዕይ 13:4፣ 14-16 አውሬው የሚቃወመውን አይፈልግም። በቁጥሩ፣ በስሙና በምስሉ አማካይነት ተከታዮቹን ይገዛል። እውነትን እንደጌታ ኢየሱስ በመግለጽና ፈቃደኝነትን በማክበር አይገዛም። በዙሪያው ብዙ ኃይላት (መንፈሳዊና ቁሳዊ) ስላሉት ሰዎች ያለፈቃዳቸው እንኳን በፍርሃት ይገዙለታል።

12. <u>ሕግንና ዘመናትን መለወጥ</u> ዳን. 7:25 ጌታ ኢየሱስ ስለዘመናትና ሕግጋት አቆጣጠርና አመዛዘን የነበረው አቋም በጣም ጠንካራ ነበር። ደቀመዛሙርቱ እንኳን የተገለጠውን ከመመርመር ውጪ ሌላ እንዳያደርጉ አስጠንቅቋቸዋል። የሐዋ. 1:6-7፤ ሉቃስ 12:56፤ ማቴ. 24:36። በጌታ የተሰጡ ትዕዛዛትም እጅግ ክቡር እንደሆኑና ማንም በመቀነስም ሆነ በመመርመር ሊለውጣቸው እንደማይገባ መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጣል። ራዕይ 22:18-19፤ ኢሳ. 40:8። አውሬው ግን ዘመናትንና ሕግን ለመለወጥ ደፋር ነው። ለምሳሌ የዘመን አቆጣጠር ፍጻሜ እንደሌለው ዘላለማዊ እንደሆነ በመናገር ሰውም ወደ ገሃነም ሊገባ እንደማይችል ሁሉ ነገር እንዳለ እንደሚኖር ይናገራል። መጽሐፍ ቅዱስ የጥበብ ምንጭ እንዳይደለ ወዘተ ያስተምራል። (የዘመኑ የክህደት ዓይነቶች ይመልከቱ)። አውሬው በተጨማሪ የወንድን የቤተሰብ መሪነት፣ በዘፍ. 2:4 የተሰጠውን የጋብቻ መመሪያ ይቃወማል። ሰውን ለመስዋዕትነት በማቅረብ ደምን በማፍሰስ የዘፍ. 9:6ትን ሕግ ይለውጣል። የሰንበትን መኖር ባለመቀበል ሰዎች ለእግዚአብሔር ጊዜ እንዳይኖራቸው ያደርጋል።[9]

13. <u>ኃይልን መግለጽ</u> ዳን. 8:24፤ ራዕይ 13:3-4 አውሬው በኃይሉ እንደሚበረታ ሆኖም በራሱ ኃይል እንደማያከናውን ተገልጿል። አውሬው የሚኖረው ኃይል በጣም አስደናቂና ታላቅ መሆኑን በራዕይ 13:1-3 ከተጠቀሱት ሦስት አውሬዎች ኃይል ጋር ማነጻጸሩ ጠቃሚ ነው። እነዚህ በነብር፣ በአንበሳና በድብ የተመሰሉት አውሬዎች በዳን. 7:1-5 እንደተጠቀሰው የባቢሎንን፣ የሜዶንና ፋርስን እንዲሁም የግሪክን ያለፉ መንግስታት የሚያመለክት ነው። እነዚህ



መንግሥታት ባለፉት ዘመናት የሰሩትን የጭካኔ ሥራ ከዓለምም ሆነ ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ ንባባት መረዳት ይቻላል። አውሬው ደግሞ ከእነዚያ መንግሥታት በበለጠ ሁኔታ ኃይሉን መግለጽ ይፈልጋል። የአውሬው ዙፋን ይህንን ያህል ኃይልና ሥልጣን የሚያገኘው ከዘንዶው ከሰይጣን ይሆናል። ራዕይ 13:2 ዘንዶውም ኃይሉንና ዙፋኑን ትልቅም ሥልጣን ሰጠው፤ ለአውሬው ሥልጣን ሰጥቶታልና (ቁ. 4) ሲል ሰይጣን አውሬውን ልክ አብ ወልድን እንዳገነነው በዓለም ሊያከብረው እንዳቀደ ያሳያል። ይህ ለአውሬው ሲገለጥ ያለው ኃይል ልክ ወልድ ሲገልጸው ከሚፈልው መለኮታዊ ኃይል ጋር አመሳስሎ ወይም አስበልጦ ለመግለጽ የታሰመ ነው። ይህም ክርስቶስ ኢየሱስን ዋጋ ለማሳጣት የተሰላ ምኞት እንደሆነ ያሳያል። አውሬው ኃይሉን በተለያዩ መንገዶች መግለጽ ይፈልጋል። ኃይሉን ካልገለጸ መለኮታዊነቱ ተቀባይነት አይኖረውም። መመለክና ማስመለክ እንዲችል ኃይሉን እስራኤልን በማሳደድና በመዋጋት፣ አይሁዶችን በማሸነፍ፣ ሚስጢራትን (እንቆቅልሽን) በመፍታት፣ ተአምራት በማድረግ፣ ቅዱሳንን በመግደል፣ ብዙዎችን በማሳት፣ ነገስታትን ተዋግቶ በማሸነፍ፣ የሰዎችን ህይወት በመቆጣጠርና በማስገበር፣ ገንዘብን በመቆጣጠር (ዳን. 11:38-43)፣ እንደፈቃዱ በማድረግ ሁለቱን ነቢያት በመግደልና ጋለሞታይቱን ባቢሎን በማጥፋት ወዘተ ይገልጣል።ራዕይ13:1-18 ራዕይ 17:12-17፤ 11:6-18፤ ዳን. 7:1-8፤ 9:27፤ 11:36፤ 8:23-25።[10]

14. <u>የሴቶችን ፈቃድ አለመመልከት</u> ዳን. 11:37 የዚህ እውነት ሚስጢር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከመርገም በፊትም ሆነ በኋላ አንድ ዓይነት ነው። ዘፍ. 2:18-19፤ 3:16-18። የሴት አፈጣጠርና አመጣጥ ለወንድ የምትመች ረዳት መሆን በወንድ መወደድ ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል እንደተባለ በዚያ ቃል መሰረት መኖር ነው። አውሬውና ተከታዮቹ ግን በአሁኑ ጊዜ ሴቶች በአንድ ወንድ ጋብቻ መታሰር እንደሌለባቸው፣ ጋብቻቸውን ከመናፍስትና (ሳንትሪክ ሴክስ መ.ቃ.ይ.) ከብዙ ወንዶች ጋር ማድረግ እንዳለባቸው ይናገራሉ። እውነተኛ ህይወት ያላትና በክርስቶስ ያለች ሴት መኖር የምትፈልገው በውስጧ ባለው የተፈጥሮ ህይወት መመሪያ ነው። ያም አንዱን እግዚአብሔርን ለማምለክ ነጻነቷ ተጠብቆ መመላለስን ነው። አውሬው ግን ከሴት ፈቃድ ውጪ በራሱ ፈቃድ እንድትኖር ባመጣውና በቀየረው የህግ ለውጥ እንድታመልከውና <u>አወስቦ</u> እንድትፈጽም ያደርጋል። ሴቶች የዘመኑ-ኖህንና ሎጥን ግብረሰዶማዊ አወስቦ እንዲፈጽሙ ያስገድዳል። (<u>ዘ ኒው ኤጅ ላይስ ቱ ኤ ውመን</u> የተባለውን በዋንዳ ማርስ የተጻፈውን መጽሐፍ ያንብቡ።)

በአሁኑ ጊዜ ግማሽ ሚሊየን የሚደርሱ የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ሴት አባላት በራሳቸው ለራሳቸው አማልክት እንደሆኑ ማንም በእነርሱ ላይ ሊያዝዝ እንደማይችል፤ እናታቸው ሔዋን አምላክ ለመሆን ከወንዱ ቀድማ የወሰደችው እርምጃ ትክክል እንደሆነና የዘመኑ <u>ማየዊ ትውልድም</u> በሔዋን ፈለግ ሊከተላቸው እንደሚገባ በማወጅ ላይ ይገኛሉ። የያዝነው 2000 ዓመት አልቆ አዲሱ ዘመን

ሲጀመር አምላክ በሴት ጾታ እንጂ በወንድ ጾታ መጠራት እንደሌለበት ያስተምራሉ:: ለማስተማርም ልዩ ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛሉ:: ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፍ ውስጥ እባብ ለሴት ልዩ የመገለጥ ምንጭና ምሪት ማግኛ እንደሆነ በማሰብ ሴቶች በአንገታቸው ላይ በመጠምጠም፣ አቅፎ አብሮ በመተኛትና በመንዝ ዕባብን ወዳጅ ማድረግ እንዳለባቸው በአውሬው መንፈስ እየተስተማረ መሆኑ ተገልጿል:: በተጨማሪም ዕባብን ከህጻናት ጋር በማጫወት የሰው ልጅ ወዳጅ እንደሆነ ማብሰር ተጀምሯል:: ይህ በሐሰተኛው ክርስቶስ የመጣ የዘፍጥረት ሦስቱ የዘንዶው (የቀደመው ዕባብ) መንፈስ ነው::

## 2.4 የአውሬው የግዛት ክልል

የአውሬውን የግዛት ክልል ለይቶ ለማወቅ የግድ ወደ ኋላ መለስ ብሎ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ታሪክ መቃኘት ያሻል:: ዳን. 2:7 እና 8 ስንመለከት ከክ-ልበ-ስለነበሩ ስለ ባቢሎን፣ ሜዶንና ፋርስ፣ ግሪክና ሮም የወቅቱ ኃያላን መንግስታት አነሳስና አወዳደቅ የወደፊትም ሂደት መረዳት እንችላለን:: በዳን. 2:31-45 በቁሳቁሳዊ ምሳሌዎች የተጠቀሱት አምስት መንግሥታት ወርቁ የባቢሎንን፣ ብሩ የሜዶንና ፋርስን፣ ነሐሱ የግሪክን ብረቱ የቀድሞውን ሮም፣ ብረትና ሸክላው የፍጻሜውን ሮም የሚወክሉ መንግሥታት ናቸው:: የቀድሞው ሮም ስንል ክርስቶስ ኢየሱስ በምድር በነበረበት ጊዜ ዓለምን ይገዛ የነበረውን የሮም ግዛት የሚያመለክት ነው:: ይህ መንግሥት ከላይ ከተጠቀሱት መንግሥታት የሚያመለክት ነው:: ይህ መንግሥት ከላይ ከተጠቀሱት መንግሥታት ረጅም ጊዜ የቆየው ነበር:: የሮም መንግሥት ረጅም ጊዜ ቢቆይም ቀስ በቀስ እየደከመ ሔዷል:: እስከ 15ኛው ክፍለ ዘመን ቆይቶ ምዕራባዊና ምሥራቃዊ ተብሎ ለሁለት ከተከፈለ በኋላ የምዕራቡ ክፍል እ.ኤ.አ. በ476 ሲያከትም የምሥራቁ ክፍል ደግሞ በ1453 ቆይቶ ወድቋል::11 እንግዲህ በክርስቶስ ዘመን ይገዛ የነበረው የሮም መንግሥት (የብረት) ከ1453 ወዲህ ቢያከትምም ክርስቶስ ኢየሱስ ከሰማይ መጥቶ የሚያፈርሰው መንግሥት በብረትና በሸክላ የተመሰለው የተከለሰው (በዘመን ፍጻሜ የሚከሰተው) የሮም መንግሥት ነው:: በዚህ ክፍል ብረት ብርታት ያለውን የንጉሥን (ኃይልና ሥልጣን ያለውን መሪ) ሲወክል ሸክላ ደግሞ ተገዢ የሆነውን ደካማ ህዝብ ይወክላል:: ዳን. 2:41-43 ሁለቱም እርስ በእርስ እንደማይስማሙ መረዳት አያዳግትም:: በናቡከደነጾር የምስል ራዕይ 5ኛ የሆነው የተከለሰው የሮም መንግሥት የግድ ወደፊት ሊመጣ ያስፈልገዋል:: ምክንያቱም በድንጋይ የተመሰለው ከሰማይ የሚመጣው የክርስቶስ መንግሥት ይህንን የተከለሰውን (ሪቫይዝድ) የሮም መንግሥት ማፍረስ ስለሚኖርበት ነው::

የ10 ቁጥር ተመሳሳይነት

በዳን. 2:33 ላይ እኩሉ ሸክላ እኩሉ ብረት የተባለው የምስሉ ክፍል ያተኮረው እግሮች ላይ ነው:: ሁለት እግሮች አሥር ጣቶች ይኖሯቸዋል:: በዳን. 7 ውስጥ የተነሳው አውሬ 10 ቀንዶች እንዳሉት ሁሉ በራዕይ 13 እና 17 ላይ ባለ 10 ቀንድ ሆኖ እንደሚነሳ ተጠቅሷል:: 10ሩም ቀንዶች ሆኑ



10ሩ ጣቶች የሚያመለክቱት መንግሥታትንና ገዢዎቻቸውን ነው:: በዳን. 2 ውስጥ የተጠቀሱት 10 የብረትና የሸክላ መንግሥታት ፍጻሜ ከሰማይ በሚመጣ የክርስቶስ መለኮታዊ መገለጥ እንደሆነ ሁሉ በራዕይ 13 የተጠቀሱትም 10 ቀንዶች ፍጻሜ ከሰማይ በሚመጣው በክርስቶስ ኢየሱስ ነው:: ዳን. 2:44-45፤ ራዕይ 19:11-21:: በዳንኤልና በራዕይ ዮሐንስ ቀንዶች መካከል ተመሳሳይነት ካለ ወደ ዳን. 2:35 እና 44 በመመለስ ማጤን ይኖርብናል:: የብረቱና የሸክላው መንግሥት አሁን ይኖር ይሆን? ብለን ስንጠይቅ ይህ መንግሥት አሁን እንደሌለና ትንቢቱም እንዳልተፈጸመ ከዓለምና ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንረዳለን:: የዳንኤል ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ቀድሞ የነበረው የብረት (የሮም) መንግሥት ተነስቶ በመቋቋም በክርስቶስ መወጋትና መፍረስ ይኖርበታል:: እንግዲህ በ1453 ወደ ፍጻሜ የመጣው የሮም መንግሥት ይዘት አሁን ምን ይመስል ይሆን?

## የራዕይ 13:1-3 ትንታኔ

በዚህ ክፍል ውስጥ ከባህር የወጣው አውሬ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶች እንዳሉት ተጠቅሷል:: ሰባቱ ራሶች የሚያመለክቱት መንግሥታትን ነው:: ስድስቱ አስቀድሞ የነበሩትን የግብጽን፣ አሶርን፣ ባቢሎንን፣ ሜዶንና ፋርስን፣ ግሪክንና የሮምን ሲያመለክት፣ ሰባተኛው ግን የታደሰውን (የተከለሰውን) የሮም መንግሥት የሚያመለክት ነው:: ሰባት ራሶች ያሉት አውሬ የሰውነቱ ክፍሎች ነብርን፣ አንበሳንና ድብን ይመስላሉ ማለት ከባቢሎን፣ ከሜዶንና ፋርስ ከግሪክ (ዳን. 7) የአገዛዝ ኃይል፣ ዘይቤና የግዛት ማስፋፋት አቋም ጋር ተመሳሳይነት ኖሮት ከሁሉ የበለጠ አሠራር እንዳለው ያመለክታል:: ይህም ማለት አውሬው ባለፉት ዘመናት የዓለም ኃያላን መንግሥታት እንደተባሉት አገሮች ለመኖር ናፍቆት ይኖረዋል ማለት ነው:: ከራሶቹም ለሞት እንደታረደ ሆኖ አንዱን አየሁ ለሞቱ የሆነውም ቁስል ተፈወሰ (ቁ. 3) ሲል የሚያመለክተው ከሰባቱ ያለፉ መንግሥታት አንዱ ለማለት እንጂ የአውሬውን ሞቶ መነሳት አያሳይም:: ይህ ለሞት የተቃረበው ራስ መፈወሱ የሚጠቁመንም ከሚመጣውና ካልተፈጸመው የብረትና ሸክላ መንግሥት ትንቢት አኳያ በ15ኛው ክፍለ ዘመን ወድቆ የነበረው የብረት መንግሥት ወደፊት መነሳቱን ነው:: ይህም የተከለሰው (የታደሰው) የሮም መንግሥት ይሆናል::[12] አንዳንዶች ደግሞ ለሞቱ የሆነው ቁስል የሚፈወሰው የግሪክ መንግሥት ነው የሚሉም አሉ::[13] ሌሎችም የአውሬውን ሞቶ መነሳት ነው ይላሉ:: ሆኖም ብረት የሮምን መንግሥት ስለሚያመለክት ይህ መንግሥት ተነስቶ በክርስቶስ ሊጠፋ የግድ ነው:: ዳን. 2:35፣ 44

የግሪክ መንግሥት ከወደቀ በኋላ የገዛው የሮም መንግሥት ነበር:: ይህ መንግሥት ደግሞ የያዛቸው አገሮች አስቀድሞ በግሪክ ቁጥጥር ሥር የነበሩ ከሆነና ይህም በታሪክ ከተረጋገጠ ሁለቱም አነጋገር እውነት ሊሆን እንደሚችል ማሰብ ይቻላል:: አስታራቂ ሐሣብም ሊሆን ይችላል:: ሆኖም ግን ሊረጋገጥ የሚገባው አንድ እውነት አለ:: ይኸውም ክርስቶስ ኢየሱስ ከሰማይ ሲገለጥ የሚያጠፋው መንግሥት የብረትና የሸክላ መንግሥት መሆኑ ነው:: ይህ መንግሥት ደግሞ ባህሪው ቀድሞ የነበሩትን ኃያላን

መንግሥታት የሚመስል ባህሪ ሲኖረው የእርሱ መሠረት መመታት (ዳን. 2:35-44) የዓለም መንግሥታትም መውደቅ ይሆናል:: ይህም በራዕይ 11:15 የዓለም መንግሥታት ለጌታችንና ለአምላካችን እንደምትሰጥ በግልጽ ተቀምጧል:: ቀድሞ በግሪክ ቁጥጥር ሥር የነበሩ በኋላ በሮም ግዛት ሥር ስለነበሩ የቀድሞና የአሁኑ ዘመን ወደፊትም ሲቀናጁ ስላሉት የአውሬው ከተሞች (ግዛቶች) የተለያዩ ሐሳቦች ተሰንዝረዋል:: ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው::

## ሰባቱ ራሶች

የአውሬው ስለሆኑት ሰባቱ ራሶች (ራዕይ 13:1) ሦስት ዓይነት ትርጉሞች ይሰነዘራሉ:: ከእነዚህ ውስጥ የመጀመሪያው በሮማውያን አገዛዝ ዘመናት ውስጥ የተከሰቱትን የታሪክ ደረጃዎች ማለትም እንደ ንጉሣዊ፣ አምባገነናዊ ወታደራዊ ወዘተ ያመለክታል የሚል ነው:: ሁለተኛው ደግሞ ሰባት ራስ በተሳካ ሁኔታ የገዙትን የሮማውያን አጼዎች ማለት እንደ ጁሊየስ ቄሳር፣ ጢባሪዮስ፣ ካሊጉላ፣ ክላውዴዎስ፣ ኔሮ፣ ዶሚታንና ፀረ-ክርስቶስን ያሳያል የሚል ነው:: በመጨረሻም ሰባት የሚወክለው አስቀድሞ የተጠቀሱትን እስራኤልንና የእግዚአብሔርን ሕዝብ በዘመናት ውስጥ ያሰቃዩትን እንደ ግብጽ፣ አሶር፣ ባቢሎን፣ ሜዶንና ፋርስ፣ ግሪክና ሮምን ወዘተ የመሳሰሉትን አገሮች ያመለክታል የሚል ነው::[14] ሚዛን የሚደፋው ግን የመጨረሻው ሐሳብ ነው::

## የሮም ታሪካዊ ሂደት

ወደፊት የሮም ኃይል ትንሳኤ ያገኛል ሲባል ሁለት ዓይነት ሃሣቦች አሉ:: የመጀመሪያው የሮም አነሳስ ቀድሞ ከገዛቻቸው መልክአ ምድራዊ ክልሎች አይዘልም የሚል ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የግዛት ክልል ብቻ ሳይሆን ፖለቲካዊውን ባህላዊውንና ህብረተሰባዊውን አገዛዝ ይጨምራል የሚል ነው::[15] ሁለተኛውን አመለካከት የሚያጠነክሩት ክፍሎች የሚያቀርቡት መረጃ ሮም በቀደሙት ዘመናት የተለያዩ አገሮችን በገዛችበት ወቅት ህዝቡ እዚያው ስለቀረ፣ በአሁኑ ጊዜም በተለያየ መልኩ ሃይማኖታዊውና ባህላዊው አገዛዝ በተለያዩ አገሮች ዘንድ ስለሚገኝ የወደፊቱ የሮም አነሳስ (ተሃድሶ) መልክ ምድራዊ ብቻ አይደለም የሚል ነው:: በዳን. 2 ውስጥ የተጠቀሰውን ዳግም የሚነሳው የሮም አገዛዝ ተግባራዊ ለማድረግ ከሮም እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ታሪክ የሚመሰክረው ጉዳይ አለ:: ይኸውም የምሥራቃዊና ምዕራባዊ ተብሎ የተከፈለውን የቀድሞ የሮም ግዛት ወደ አንድነት ለማምጣት በታሪክ ውስጥ ብዙ ሙከራ መደረጉ ነው:: ከእነዚህም ውስጥ የመጀመሪያው በ800 ዓ.ም. የተነሳው ቻርል ማኜ የወሰደው እርምጃ ነበር:: ቻርል ማኜ በአሁኑ ወቅት ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ጣሊያን፣ ሆላንድና ቤልጂየም ተብለው የሚጠሩትን አገሮች በሮም ግዛት ሥር አድርጓቸዋል::[16] በሁለተኛ ደረጃ ፈረንሳዊው ናፖሊዮን በመጨረሻም ሂትለር የቀድሞዋን ሮም ለመመስረት ሙከራ አድርገው እንደ ራዕይ 13:1 አሥር መንግሥታትን (ሰባት ራሶችን) መመስረት አልቻሉም:: ሆኖም እስካሁን ድረስ ሮምን ወደ ቀድሞ ስፍራዋ ለመመለስ ጥረቱ ቀጥሏል::



## አሥር ቀንዶች

የሰባቱን ራሶች ማንነት ለይቶ ለማውጣት እንደሚያስቸግር ሁሉ የ10 ቀንዶችም አተረጓጐም እንዲሁ አስቸጋሪ ገጽታ አለው:: ለመሆኑ እነዚህ በአውሬው ስር የሚገዙ መንግሥታት እነማን ይሆኑ? ታሪካዊው ዳታስ (መረጃ) ምን ያመለክተናል? የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ስለ አሥሩ ቀንዶች የየራሳቸውን ጥናት ለማቅረብ ሞክረዋል:: ከእነዚህም ውስጥ ዋናዎቹ የሚከተሉት ይሆናሉ::

### ሀ. ሮበርት ፊይድ

ፊይድ አሥሩን ቀንዶች እንደሚከተለው ይዘግባል::

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ላቲቪያ | 5. | ቺኮዝሎቫኪያ | 9. | ቡልጋሪያ |
| 2. | ኢስቶኒያ | 6. | ሃንጋሪ | 10. | አፍጋኒስታን |
| 3. | ሊቱኒያ | 7. | ሩማኒያ | | |
| 4. | ፖላንድ | 8. | ምሥራቅ ጀርመን | | |

### ለ. ቤሪ ስሚዝ

በ1970ዎቹ ከተነሱት እውቅ የፍጻሜ ዘመን መምህራን ውስጥ አንዱ ናቸው:: ስሚዝ «ዎርኒንግ» በተሰኘው መጽሐፋቸው እ.ኤ.አ. በ1970 ዓ.ም. የታላቋ ብሪታንያ ከፍተኛ ልዑክ ከነበሩት ጓደኛቸው ከሚስተር ዴሪክ ጆን የአውሮጳ ማህበረሰብን አባላት ቁጥር ጠይቀዋቸው ያገኙትን መልስ ዘግበዋል::

| | | |
|---|---|---|
| በ1948 እ.ኤ.አ. | 1. | ቤልጂየም |
| | 2. | ሉክሰምበርግ |
| | 3. | ሆላንድ ስምምነት አደረጉ:: |
| በ1957 ዓ.ም. | 4. | ጣሊያን |
| | 5. | ፈረንሳይ |
| | 6. | ምዕራብ ጀርመን 6ቱ ሲጨመሩ በዚሁ ዓ.ም. ሚያዝያ 25 «የሮም ስምምነት» (ትሪቲ ኦፍ ሮም) በሚል ቃል ኪዳን ተፈራረሙ:: |
| በ1972 ዓ.ም. | 7. | ታላቋ ብሪታኒያ |
| | 8. | ኖርዌይ |
| | 9. | አይሪሽ ሪፐብሊክ |
| | 10. | ዴንማርክ በጥር ወር ስምምነተ አደረጉ:: |

በተለያዩ ጊዜያት አንዳንዶች ሲወጡ ሌሎች ሲገቡ ቁጥራቸው ከአሥር በላይ አንዳንዴም በታች ሲሆን ተስተውሏል:: ይህ ቢሆንም በሰንደቅ አላማቸው ቁጥር አሥር እንደሆነ ስሚዝ ይናገራሉ::[17] ስሚዝ

የአውሮጳን ማህበረሰብ በቀጥታ አሥር ቀንዶች እንደሆኑ አሁን ቁጥራቸው ከአሥር ቢበልጥም ወደ አሥር እንደሚወርድ አበክረው ያስተምራሉ:: በተጨማሪም የአውሮፓ ማህበረሰብ ሌላ ስማቸው «የሮም ቃል ኪዳን» እንደሆነም ይናገራሉ::[18]

ሐ. <u>አርኖ ፍሮይዝ</u>

ሚስተር ፍሮይዝ የሚድናይትኮልን መጽሔት ከሚያዘጋጁ የፍጻሜ ዘመን ፀሐፊዎች አንዱ ናቸው:: እኚህ ሰው በአሁኑ ወቅት አሥራ ሁለት ስለደረሱት የአውሮፓ ማህበረሰብ አባላት ያላቸው አመለካከት ትንሽ ከቀደሙት ሁለቱ ለየት ያለ ነው:: ፍሮይዝ የመጀመሪያዎቹ ስድስቱ አባል አገሮች ቤልጂየም፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ጣሊያን፣ ሉክሰምበርግ፣ ኔዘርላንድስ እንደነበሩ በመቀጠልም ብሪታኒያ፣ ዴንማርክና ኤርላንድ እንደገቡና ቀጥሎ በአሥረኛ ደረጃ በ1981 ዓ.ም. ግሪክ እንደተጨመረች ያመለክታሉ:: ከዚያም በ1986 ፖርቱጋልና ስፔይን እንዲሁም በ1995 በጥር ወር ሦስት አገሮች ማለትም ፊንላንድ፣ ስዊድንና አውስትሪያ ተጨምረው 15 አገሮች እንደሆኑ የህዝባቸውም ብዛት ከ1949 እስከ 1995 ዓ.ም. ባሉት ዓመታት ከ220,000,000ወደ 362,000,000ማደጉን ገልጸዋል:: ፍሮይዝ ወደ ዳን. 7:24 እና ራዕይ 17:12 በመመለስና ትንታኔ በመስጠት ተለዋዋጭ ስለሆነው የአውሮፓ የጋራ ገበያ ማህበር አባላት ቁጥር የሚከተለውን ትንታኔ ያቀርባሉ:: ትንታኔውም እነዚህ አሥር ቀንዶች አገሮች ሳይሆኑ በአውሮፓ አማካኝነት ዓለም አቀፋዊ በሆነ መልኩ ሊደራጁ የሚችሉ አሥር የተለያየ አወቃቀርና ኃይል ያላቸው <u>ቡድናዊ አገሮች</u> እንደሆኑ የሚያመለክት ነው:: እነዚህም አሥር ቀንዶች (ብሎክስ) የሚቀጥለው ዓይነት መልክ ሊኖራቸው እንደሚችል ጽፈዋል::

<u>አሥሩ ኃያላን የኤኮኖሚ አወቃቀሮች</u>[19]

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1. | አውሮጳ | 5. ደቡብ አሜሪካ | 9. | አውስትራሊያ |
| 2. | ሩቅ ምሥራቅ | 6. ደቡብ እስያ | 10. | ኒውዚላንድ |
| 3. | መካከለኛው ምሥራቅ | 7. መካከለኛው እስያ | 11. | መካከለኛው አፍሪካ |
| 4. | ሰሜን አሜሪካ | 8. ደቡብ አፍሪካ | | |

ከላይ የተጠቀሱትን 11 ቡድኖች ስናወዳድር የየራሳቸው ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ ባህላዊና ኃይማኖታዊ ልዩነቶችና ተመሳሳይነቶች አሏቸው:: በአመዛኙ ግን ስንመለከት 50% የአፍሪካ ህዝብ የፈረንሳይኛ ቋንቋ መናገሩና ዝንባሌው ወደ አውሮፓ መሆኑ እንዲሁም የእስያ ክፍል የሆኑት ጃፓን፣ ኮሪያ፣ ሆንግ ኮንግ፣ ህንድ፣ ታይዋንና ሌሎችም ታዳጊ የእስያ አገሮች የኑሮ መርሃቸው በምዕራብ አውሮጳ የኑሮ አወቃቀር ላይ የተመሠረተ መሆኑ የአውሮጳን ሉዓላዊነት የሚያገንንና ወደ እርሷም ለመሳብ የሚፈትን ነገር መኖሩን መገንዘብ ይቻላል:: በተጨማሪም አውሬው የተሰኘው ስም አቀፋዊው ኮምፒውተር በብሩሴልስ መተከሉ፣ የሮማውያን ኃይማኖት፣ ባህልና ህዝብ በተለያዩ የዓለም ህብረተሰብ ውስጥ



መገኘቱ ወደ ፊት በአሥር አገሮችም ደረጃ ይሁን በአሥር ኤኮኖሚያዊ ቡድን ኃይላት ደረጃ ለሚቋቋመው ኅብረት አንድ እውቅ መሪ መፈለጉና መገኘቱ የማይቀር ነው::[20]

ታዲያ የአውሬው ግዛት ክልል ዓለም አቀፋዊ ነው ወይስ ውሱን ይሆን?

ስለአውሬውም የግዛት ክልል እንዲሁ የተለያዩ ሃሣቦች ተሰንዝረዋል:: ይኸውም ሁሉን ይገዛል የሚለውና አሥሩን አገሮች ብቻ ነው የሚገዛው የሚል ነው:: አውሬው የሚገዛው ዓለምን በሙሉ ሳይሆን የተወሰኑ አገሮችን ብቻ ነው የሚሉት የሚያቀርቡት ማስረጃ፣

1. አውሬው ያሉት አሥር ቀንዶች ብቻ ሆኖ መጠቀሱ:: ራዕይ 12:6-13

2. እስራኤል የማትገዛለት መሆኑ ዳን. 9:27፤ ራዕይ 12:6-13

3. እስራኤላውያን (ሴቲቱ) ሽሽታ የምትቀመጥባቸው እንደ ኤዶምና ሞአብ (ጆርዳንና አረቢያ) የማይገዙለት መሆኑ:: ዳን. 11:40-45

4. ከአሥሩ ቀንዶች (ግዛቶች) በስተ ሰሜንና ምሥራቅ ያሉ አገሮች አውሬውን ሊወጉት መምጣታቸው:: ዳን. 11:44-45

5. <u>ማንስ ሊዋጋው ይችላል</u> የሚለው የራዕይ 13:4 ንግግር ሌላ ያልተገዛለት መኖሩን ማሳየቱ

6. ለሺህ ዓመት መንግሥት ንግስት የሚተርፉ ሰዎች መኖራቸው ወዘተ ናቸው:: እነዚህ የአውሬውን ቁጥርም ሆነ ምስልና ምልክት ባለመቀበላቸው የተረፉ ናቸው:: ዘካ. 14:16-21 ይህ ባይሆን መቅሰፍት ወርዶባቸው በመከራው ዘመን በጠፉ ነበር::

ስለሆነም በራዕይ 13:3-4 ላይ ምድርም ሁሉ አውሬውን እየተከተለ ተደነቀ ሲል የዓለም ህዝብ ሁሉ ተገዛለት ማለት ሳይሆን በዳን. 7:23-24፣ 2:38፤ ቁ. 39፤ <u>በምድር ሁሉ ላይ የሚገዛ</u> እንደተባለ ዓይነት አነጋገር ነው:: ይህም ማለት በደረሱባቸው አካባቢዎች ማለት ነው:: ናቡከደነጾርም ሆነ ሌሎች የቀድሞ ኃያላን መንግሥታት ዓለምን ፈጽሞ አልገዙም:: ሆኖም ባስገበሯቸው ሰዎች ዘንድ ግን ገዢ ነበሩ::

<u>ፊኒስ ጄኒንግስ ዴክ</u> በመባል የታወቀው የእግዚአብሔር ሰው ደግሞ ሐሰተኛው ክርስቶስ በዳን. 8:8-9፤ 21-23 ከተጠቀሱት አራት ግዛቶች እንደሚነሳና እነዚህም አውሬው የሚገዛቸው አገሮች ዛሬ ግሪክ፣ ግብጽ፣ ቱርክና ሶርያ እንደሆኑ ይገልጻል:: ዴክ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ዳን. 8 በደንብ ካልመረመረ አውሬው ከኢንግላንድ፣ ስፔይን፣ ቤልጂየም፣ ጣሊያን፣ ፖርቹጋል፣ ፈረንሳይ፣ ስዊትዘርላንድ፣ ሆላንድ፣ ሃንጋሪ፣ ዩጐዝላቪያ፣ አልባኒያና አውስትሪያ እንደሚመጣ ሊቀበል ይችላል:: በማለት አውሬው ቀደም ብለው ከተዘረዘሩት 12 አገሮች እንደማይነሳና እነዚህም ግዛቶቹ እንዳይደሉ ይገልጻል::

የአውሬውን የግዛት ክልል በተመለከተ አንድ ሊተኮርበት የሚገባ ነገር አለ:: ይኸውም ግዛቱን በትክክል ነጥሎ ማውጣት ያለመቻሉ ጉዳይ ነው:: ይህም ሊሆን የቻለው በመጀመሪያ የ10 ቁጥር ተግባራዊነት በታሪክ ሲመረመር ሚስጢራዊነቱ እያየለ መምጣቱ፤ በሁለተኛ ደረጃ አውሬው ሲመጣ የራሱን መልክ ብቻ ይዞ አለመምጣቱ ማለትም የባቢሎንን፣ የሜዶንና ፋርስን፣ እንዲሁም የግሪክን መልክ መያዙና ግዛቱ የተለያየ ሊሆን መቻሉ፤ በሦስተኛ ደረጃ ዛሬ ሮም የምንላትን አገር መልክአ ምድራዊ በሆነ መልኩ ብቻ መተርጐም እንደማይቻልና የሮም ዝርያዎች በባህላዊና ኃይማኖታዊ መልኩ በየቦታውና አገሩ መኖራቸው፣ በመጨረሻም የአውሬው ግዛት ዓለም አቀፋዊ ነው የሚልም አመለካከት በመኖሩ ነው:: ከላይ የተጠቀሱትን ሃሣቦች ልብ በማለት የዘመኑ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት መርማሪዎች ልንወስደው የሚገባን እርምጃ የ10 ቁጥርን ትንቢታዊና ታሪካዊ አፈጻጸም ወደ ምሳሌያዊ ወይም ቃል በቃል ፍቺ ማድላቱን በጥንቃቄ መመርመር ነው::

ተጨማሪ ዘገባ

ያለፈውና የወደፊቱ የአውሮፓ ማህበረሰብ አወቃቀር ሂደት

1. ስድስቱ የመጀመሪያ አባላት
ቤልጂየም፣ ጀርመን፣ ፍራንክሬይክ፣ ጣሊያን፣ ሉክሰምበርግና ኔዘርላንድስ

2. አራቱ ተጨማሪ አባላት
ግሪክ፣ ኤርላንድ፣ ስፔይንና ፖርቹጋል

3. በመጨረሻ ሙሉ አባልነት ያገኙ
ዴንማርክና ታላቋ ብሪታኒያ

5. በ1995 የገባች ኦስትሪያ

5. እንደሚቀበሏቸው የሚጠብቁ
ኖርዌይ፣ ፊንላንድና ስዊድን

6. ተቀባይነት ማግኘታቸው ያልታወቀ
ሃንጋሪና ፖላንድ

7. በኅብረቱ ለመያዝ የመጀመሪያ እርምጃ የወሰዱ
ቡልጋሪያ፣ ሩማኒያ፣ የስሎቫክ ሪፑብሊክ፣ ስሎቬኒያ፣ የዜክ ሪፑብሊክ

8. ለመተባበር የሚያስቡ
ማልታ፣ ቆጵሮስና ስዊትዘርላንድ




9. ከፍተኛ ግንኙነት ያላቸው አገሮች
አልባኒያ፣ ኢስቶኒያ፣ ላቲቪያና ሊቱኒያ

እንግዲህ ከላይ የተዘረዘሩትን አገሮች ሂደት ስንመለከት 30 እንደደረሱ ማየት ይቻላል:: የወደፊት አወቃቀራቸው ከ10 ቁጥር ጋር በተያያዘ በምን መልኩ ይዋቀሩ ይሆን? (ሲ.ይ.)

የ10 ቀንዶች ስያሜ ገጽታ

አዲሱ የአውሮጳ ማህበረሰብ ገንዘብ

አውሬው በአውሮጳ ግዛቶች ተቆጣጠሪ ይሆን?





"THE NEW MONEY," the "ECU," European Currency Unit.






## 2.5 የአውሬው ተከታዮች

መጽሐፍ ቅዱሳችንን ስናጠና የአውሬው ተከታዮች ምን ዓይነት ሰዎች እንደሆኑና ውጤታቸውም ምን ሊሆን እንደሚችል በግልጽ ተቀምጦ እናያለን:: በመጀመሪያ ደረጃ የአውሬው ተከታዮች ተገዢነታቸው ለአውሬው ይሆናል:: ልክ ቅዱሳን ጌታን ክርስቶስ ኢየሱስን እንደሚያመልኩት እነርሱም ለአውሬው ሰጋጆች ናቸው:: ራዕይ 13:3-4:: ፈቃዳቸውን ሙሉ በሙሉ ይሰጡታል:: ዳን. 7:25 ለአውሬው ካላቸው መገዛትና ታማኝነት የተነሳ ከአውሬው ጋር በመሆን ቅዱሳንን ይወጋሉ:: በምድር የሚኖሩ እውነተኛውን የክርስትና እምነት በዳግም ልደት ለውጥ ያገኙ ሁሉ የአውሬውን ተከታዮች ስለማይተባበሯቸው ይዋጉአቸዋል:: ከአውሬው ጋር በመሆን ቅዱሳንን ይወጋሉ:: ጌታንም ይሰድባሉ:: ዳን. 7:25፤ 8:24:: በሁለተኛ ደረጃ ተከታዮቹ የሚሰሩት ሥራ ሁሉ በአብዛኛው በአጋንንት ተሞልተው ስለሚሆን ሰብአዊ ርህራሄ አይታይባቸውም:: ዳን. 8:24 በራሱ ኃይል አይደለም ከሚለው ዐረፍተ ነገር አውሬው ኃይልን ከአባቱ ከዲያብሎስ ተቀብሎ ለተከታዮቹ እንደሚሰጣቸው መገንዘብ ይቻላል:: በአሁኑ ጊዜ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አባላት ከ15 ያላነሱ በአጋንንት ለመሞላት የሚጠቀሙባቸው ልምምዶች አሏቸው:: ማንኛውንም የአውሬውን ፈቃድ ለማከናወን የሚጠቀሙት በአብዛኛው በአጋንንት መንፈስ ነው:: ልክ ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደምታከናውን ሁሉ እነርሱም በአጋንንት ያደርጋሉ:: በሦስተኛ ደረጃ የደም መስዋዕትን ያቀርባሉ:: ይህም በራዕይ 17:4-6 ተጠቅሷል:: እግዚአብሔር የሰውን ደም ማፍሰስ በጥብቅ ይከለክላል:: ጋለሞታይቱ ቤተ ክርስቲያን (የአውሬው) ግን ይህንን በደንብ ትጠቀማለች:: የአውሬው ተከታዮች በሙሉ በግልሙትና ኃይማኖት ይንዛሉ:: እነዚህ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን ፈጽሞ ስለማይወዱ በመግደልና ደማቸውን በማፍሰስ ሐሴት ያደርጋሉ:: ራዕይ 6:2፤ 9-10፤ 18:24፤ 16:6:: የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አባላት የቅዱሳንን ደም የሚያፈሱት ቅዱሳን ምድሪቱን ስላረከሱ ምድሪቱ በደማቸው መፍሰስ እንድትጠራ በማመን ነው:: እግዚአብሔር የዓለምን ኃጢአት በልጁ ደም እንደሚያነጻ እነርሱ ደግሞ የክርስቲያኖችን ደም በማፍሰስ ምድሪቱን እናነጻለን ይላሉ::

በአራተኛ ደረጃ የአውሬው ተከታዮች ህይወታቸው በክርስቶስ የተመዘገበ አይደለም:: ራዕይ 13:8:: የራሳቸውን አምላክነት የተቀበሉ የእግዚአብሔርን አምላክነት የማይቀበሉ ናቸው:: በአምስተኛ ደረጃ የተታለሉ ናቸው:: አውሬው ራሱ ከሰይጣን በተሰጠው መንፈስ አማካኝነት የተታለለ ነው:: ተከታዮቹንም የሚመራቸው በተመሣሣይ የማታለል መንፈስ ነው:: ዳን. 8:25:: በስድስተኛ ደረጃ ቅዱሱን ቃል ኪዳን የተዉ ናቸው:: ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ዛሬ በብዙ ሰዎች ዘንድ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት እንደተራ ንባብ መቁጠርና ዋጋ ማሳጣት እያየለ መጥቷል:: ይህንን የሚያደርግ ሁሉ የጌታን ቃል ይተዋል ውጤቱም እግዚአብሔርን መበደል ነው:: ይህ ከሆነ ደግሞ በእግዚአብሔር የቁጣ ፍርድ ለአውሬው አልፎ መስጠት ይመጣል:: 2ኛ ተሰ. 2:11-12:: ምክንያቱም «ለዚህም

ምክንያት በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በአመጽ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስህተትን አሠራር ይልክባቸዋል የሚል ቃል ስለተጻፈ ነው:: ይህ ፍርድ በቅድመ ሺህ ዓመትና ከገሃነመ እሳት ፍርድ በፊት የሚደረግ ፍርድ ነው:: እግዚአብሔር የምህረት እጁን ሲያስወግድ ይህንን ያህል ጭካኔ የተሞላው መሆኑን ልብ ማለት ያሻል:: በአሁኑ ጊዜ በካቶሊክ፣ ኦርቶዶክስ፣ፕሮቴስታንትና በመንፈስ ቅ. (በካሪዝማቲክ) እንቅስቃሴ ፈርጅ ራሳችንን የመደብን ብዙ የእምነትና የኃይማኖት ልማድ አዘውታሪ ሰዎች አለን:: ሆኖም ስማችንና ተግባራችን የምሥራቅንና የምዕራብን ያህል ተራርቆ ለፍርድ ልንሰጥ ጥቂት ቀርቶን እንዳይሆን አሁኑኑ ራሳችንን ልንመረምር ይገባል:: <u>ሳይቃጠል ቸብ ቸብ በቅጠል</u> እንደተባለ ዛሬ ትንሽ ብለን የናቅናት ቃል ኪዳኑን (የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት) የመበደል ኃጢአት ነገ አድጋ ሲወጣ በማይቻል የህይወት አረንቋ (ማጥ) ውስጥ እንዳይጥለን አሁኑኑ ህይወታችንን ልናስተካክል ይገባል:: ለእውነተኛ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር የተፈቀደው አምላኩን በማወቅ መበርታት እንጂ ዳተኛ ወይም የኋሊት ተንሸራታች መሆን አይደለም:: ዳን. 11:32:: የልዑል ቅዱሳን ምንም እንኳን በአውሬው ተከታዮች ሰይፍ ቢወድቁ ቃል ኪዳኑን አይበድሉም፤ ጥበበኞች ናቸውና፤ ቃል ኪዳንን እየበደሉ ጥበበኛ መሆን የለም:: በቀደመው የእስራኤል ህዝብ ታሪክ የደረሰው ነገር በእኛም ላይ እንዳይደርስ እንጠንቀቅ::

## 2.6 <u>አውሬው የሚገዛበት ጊዜ</u>

አውሬው የሚገዛበትን የዓመታት ርዝመት ለማወቅ በዳን. 9:24-27 የተጠቀሰውን የ70ውን ሱባኤ ሚስጢር ማጥናት ነው:: በዚህ ክፍል አውሬው ከእስራኤል (ሌሎችም) ጋር ለአንድ ሱባኤ (ቁ. 27) ቃል ኪዳን እንደሚያደርግ ተገልጿል:: ሱባኤ የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ቃል ሻቡአ ሲሆን ትርጉሙም ሰባት ወይም ሳምንት ማለት ነው:: ይህ ደግሞ ወርን ወይም ሳምንታትን ሳይሆን በቀጥታ የሚያመለክተው ዓመትን (365 ቀናትን) ነው:: ይህንን ከታሪክ ማረጋገጥ ተችሏል:: ከቁ. 24-27 ከተጠቀሱት 70 ሱባኤዎች ወይም ሰባ-ሰባቶች (70×70) ውስጥ በሦስት የመከፈሉ ሁኔታ እንደሚከተለው ይሆናል::

1. የመጀመሪያዎቹ ሰባት ሱባኤዎች (7×7)=49 ዓመታት ኢየሩሳሌም በናቡከደነጾር መንግሥት ፈርሳ ለ70 ዓመታት ወድቃ በተገነባች ጊዜ የሆነውን

2. ሁለተኛው የሱባኤ ክፍል 62 ሱባኤ (62×7)=434 ዓመታት ደግሞ ከኢየሩሳሌም መገንባት ፍጻሜ እስከ ጌታ ኢየሱስ መሰቀል የሆነውን ያሳያል:: በጠቅላላ 62+7=69 ሱባኤዎች ወይም 483 ዓመታት እ.ኤ.አ. በ34 ዓ.ም. አካባቢ ተፈጽመዋል::

3. አንዱ ሱባኤ 1×7=ሰባት ዓመታት ከ34 ዓ.ም. ጌታ ከተሰቀለበት ጊዜ አንስቶ አሁን እስካለንበት ጊዜ አልተፈጸመም:: ሰባቱ ዓመት (አንዱ ሱባኤ) ገና ወደፊት የሚፈጸም ነው:: ዳን. 9:27::



በዳን. 9:27 ላይ የሚመጣው አለቃ የተከለሰው የሮም ጊዜ (አውሬው) ለአንድ ሱባኤ (ሰባት ዓመታት) ቃል ኪዳን እንደሚያደርግ ተተንብዮአል:: ይህ ትንቢት በታሪክ ውስጥ ተፈጻሚነትን አላገኘም:: ለሰባት ዓመት ቃል ኪዳን ከገባ በኋላ (ከእስራኤልና ከሌሎች ጋር) በሱባኤው እኩሌታ መስዋዕቱን ያስቀራል ይላል:: ይህም ተፈጻሚነትን አላገኘም:: በራዕይ 12::6 እና 14 ላይ የተተነበየው የአውሬውና የሴቲቱ ትንቢት-እውነት ገና ወደፊት የሚፈጸም ነው:: እስካሁን እስራኤል በብሔር ደረጃ ክርስቶስ ኢየሱስን አልተቀበለችም:: ገና መሢሃችን ይመጣል በማለት በመጠባበቅ ላይ ናቸው:: ከዚህም የተነሳ ወደፊት አውሬው ሲመጣ መሢሃቸው መስሏቸው ይቀበሉታል:: ከእርሱም ጋር ለሰባት ዓመት ቃል ኪዳን ያደርጋሉ:: ለመጀመሪያ 3½ ዓመታት በጥሩ ሁኔታ ከቆዩ በኋላ አውሬው በሱባኤው እኩሌታ መስዋዕቱን በማስቀረት ርኩሰት በሚያደርግበት ጊዜ እስራኤል በ144000 አይሁዶች (ወንዱ ልጅ) አማካኝነት አውሬውን ይቃወሙታል:: ከዚህም የተነሳ አውሬው እስራኤልን ሲዋጋና ሊያጠፋት ይነሳል:: እርሷም ለ1260 ቀናት (3½ ዓመታት) ወደ ኤዶምና ሞአብ ምድር ትሸሻለች:: ራዕይ 12:6፤ 14፤ እዚህ ላይ አውሬው ከእስራኤል ጋር የሚኖረው ግንኙነት ይቋረጣል:: ከሱባኤው (ከሰባቱ ዓመታት) እኩሌታ በኋላ በተጠናከረ መንገድ ለ42 ወራት (3½ ዓመታት) ይገዛል:: ራዕይ 13:5 ይህ 42 ወር እስራኤል ወደ ምድረ በዳ ከሸሸችበት 3½ ዓመታት ወይም 1260 ቀናት (ዘመን፣ ዘመናት፣ የዘመንም እኩሌታ ጋር) ተመሣሣይ ነው:: ስለሆነም አውሬው ከእስራኤልና ከሌሎች የዓለም ሰዎች ጋር በተያያዘ አንድ ሱባኤ (ሰባት ዓመት) ሲኖር ከ10ሩ ቀንዶች ጋር ሆኖ በግልጽ በመሥራት ግን ለ3½ ዓመታት ይገዛል:: የመጀመሪያዎቹ 3½ ዓመታት የዝግጅት ጊዜ እንደሆነም ይታሰባል::[21]

ስለ 7ቱ ዓመታት ጊዜ (70ኛው ሱባኤ) የተለያዩ አመለካከቶች አሉ:: አንዳንዶቹ ሰዎች 70ኛው ሱባኤ ተፈጽሟል ይላሉ:: የቀሩት ደግሞ እንዳልተፈጸመ ይናገራሉ:: ትክክለኛው ግን አለመፈጸሙ ነው:: ምክንያቱም 70ው ሱባኤ ራሱ የተተነበየው የእስራኤልን ከተማና ህዝቡን በተመለከተ ነው:: ዳን. 9:24-25:: ሰባኛው ሱባኤ ተፈጻሚነት ቢኖረው ኖሮ በዳን. 9:24 የተጠቀሱት ስድስቱ በረከቶች ዛሬ በእስራኤላውያን ህይወት ሲፈጸም ይታይ ነበር:: እስራኤላውያን እንደ ብሔር (ምርጥ ከተማ) አመጻቸው፣ ኃጢአታቸው፣ በደላቸው እስከአሁን አለ:: ወደ ዘላለም ጽድቅ አልገቡም:: ስለ እነርሱ የተነገሩ የብሉይና አዲስ ኪዳን ትንቢቶች ገና ተፈጻሚነትን አላገኙም:: የቤተ መቅደሱ መታደስ ገና ይጠበቃል:: በማቴ. 21:43 እንደተጠቀሰው መንግሥት ከእነርሱ ተወስዷል:: ሆኖም ክርስቶስ ሲመጣ ከሰባኛው ሱባኤ በኋላ ሰው ለበኩር ልጁ እንደሚያለቅስ በንስሀ ጌታን ይቀበሉታል:: በሺሁ ዓመት መንግሥት መጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን በዘላለም ቅድስና እንደምትታተም እስራኤላውያንም እንዲሁ ይታተማሉ:: ዘካ. 12:10-14:: ስለሆነም ስለ እስራኤል ከተነገረው 70 ሱባኤ ውስጥ የተፈጸመው 69 እንጂ ሁሉም አይደለም::

## 2.7 አውሬውና ጋለሞታይቱ

ከራዕይ 16:19 ጀምሮ እስከ 18ኛው ምዕራፍ ስለ ታላቂቱ ባቢሎን እናነብባለን:: በእነዚህ ምዕራፎች የተጠቀሰችው ባቢሎን ምንን ያመለክታል? ለምንስ ታላቂቱ ጋለሞታ ተባለች? ፍቺውስ ምንድነው? የተጠቀሰችው ባቢሎን ሁለት ዓይነት ትርጉም አላት:: ይኸውም ቃል በቃል የሆነና (ሊትራል) ሚስጢራዊ (ፊገራቲቭ) ትርጉም ነው:: ሁለቱም ልዩነቶችና ተመሳሳይነቶች አላቸው:: ባቢሎን የሚለው መጠሪያ ቃል በቃል ስንተረጉመው በዘፍ. 11 ላይ ጌታ ከሰማይ ወርዶ ያፈራረሳትን ምድራዊ ከተማ የሚያመለክት ሲሆን ሚስጢራዊ በሆነ መልኩ ደግሞ ሲተረጐም የሚያሳየው <u>ክህደት የሞላበትን ኃይማኖታዊ ሥርዓት ነው</u>:: ሆኖም ይኸው ሥርዓት በውጪአዊ መልኩ (ሊትራል) ባቢሎን በተባለችው ከተማ ውስጥና ሌላም ቦታ ሊገለጥ ይችላል:: የራዕይ 17ቱ ሚስጢራዊነቱን ሲያመለክት የ16ቱና የ18:19-21 ያለው ደግሞ በከፊል ምድራዊቷን ከተማ ያሳያል::

### <u>በሁለቱ መካከል ያለ ተመሣሣይነት</u>

1. ሁለቱም ከነገሥታትና አገሮች ጋር ይሴስናሉ:: (ራዕይ 17:2፤ 18:3-14)
2. ሁለቱም የቅዱሳንን ደም ያፈስሳሉ:: ራዕይ 17:6፤ 18:24
3. የኃጢአት የወርቅ ጽዋ ይይዛሉ:: ራዕይ 17:4፤ 18:6
4. ራቁታቸውን ይጣላሉ (መጣል):: ራዕይ 17:16፤ 18:19
5. ታላቅ ተብለዋል:: ራዕይ 17:5፤ 16:19፤ 18:2
6. ያጌጡና የተዋቡ ናቸው:: ራዕይ 17:4፤ 18:16[22]

ይህች ጋለሞታ የቆመችው ለአውሬው መሣሪያነት ነው:: አውሬው ትዕቢቱን ከሚገልጽባት ከተማ ዋነኛዋ ናት:: ክርስቶስ ኢየሱስ ኢየሩሳሌምን ምድራዊ ከተማው አድርጐ እንደመረጣት ሁሉ ይህም አውሬ ባሊሎንን ለራሱ ዋና ከተማ አድርጐ ይመርጣል:: ይህች ከተማ በብዙ ነገርዋ ማለትም በሃብቷ፣ በፖለቲካዊ አቋሟ በዓለም ገንና ልትታይ ትችላለች:: ራዕይ 18:6-8:: ያላት ነገር ሁሉ ለራስዋ በቂ እንደሆነ ታስባለች:: ይህች ባቢሎን የምትባለዋ የዘፍ. 11 ባቢሎን በአሁኑ ጊዜ የምትገኘው በኢራቅ ከተማ ውስጥ ሲሆን 8 ኪሎ ሜትር ወደ ውስጥ ገባ ብላ ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህች ከተማ ዳግም እንዳትሰራ መርገም አለ:: በሚሰራትም ሰው ላይ መቅሰፍት እንደሚደርስ ተተንብዮአል:: የምትሰራም ቢሆን ወደፊት መጥፋቷ አይቀርም:: ኤር. 50:39-40:: ባለፉት 5 ዓመታት ሳዳም ሁሴን የአባቴን ከተማ እሰራለሁ ብሎ ስሙ የተጻፈባቸውን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሸክላዎች አዘጋጅቶ ለመሥራት መሃንዲሶች ሲፈለጉ የኀብረብሔሩ ጦር በመምጣቱ መሰናክል ተፈጥሯል:: በሚስጢራዊ መልኩ ባቢሎን በዓለም የሚከሰተውን ኃይማኖታዊ ርኩሰት ያሳያል:: ይህንን ከራዕይ 17:2-6 መረዳት ይቻላል:: ኢሳ. 23:17፤ 57:3-7፤ ኤር. 3:2-9፤ ሕዝ. 16:1-63፤ 20:30-32፤ 23:7-49፤ ሆሴዕ 4:12-19:: ይህች ከተማ በመንፈሳዊ ይዘቷ ብዙ ነገሥታትንና ከተሞችን የሚያስገለሙት መንፈስ አለባት:: ፀረ-ክርስቶሳዊ አቋም ይዛ በመንፈሳዊ ውበቷ የሚተካከላት



እንደሌለ ትናገራለች:: ይህ ነው የማይባል ትዕቢት አለባት:: ራዕይ 18:3-8:: በራዕይ 17:5 ላይ የ<u>ጋለሞታዎችና የምድር ርኩሰት እናት</u> የሚለው ስም በዓለም ለሚከሰተው የክህደት ኃይማኖት ምንጩ ባቢሎን መሆኗን ያመለክታል:: ይህች ከተማ ብዙ ጋለሞታዎች አሏት:: ጋለሞታ ማለት በሁለት መልክ የምትኖር ማለት ነው:: ባል እንዳላት ትናገራለች ሆኖም በስውር ታመነዝራለች፤ ማለትም እግዚአብሔርን እንደምታመልክ ትናገራለች ሆኖም ግን ኑሮዋ (የህዝቡ ኑሮ) ፍጹም ክህደት የተሞላበትና ፀረ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው::

በፖለቲካዊ መልኩ በመጀመሪያው 3½ ዓመታት ሐሰተኛው ክርስቶስ (አውሬው) ይህችን ከተማ መኖሪያ ሥፍራው እንደሚያደርጋትና የከተማይቱም ንጉሥ እንደሚሆን ይታሰባል:: ኢሳ. 14:4 ሰባቱ የአውሬው ትምህርቶች በሚለው የክፍል አንድ ንዑስ ርዕስ ውስጥ አውሬው የባቢሎን የግሪክና የግብጽ ጥበብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ ቦታ ሊሰጠው እንደሚገባ ያስተምራል:: ዋነኛው ትኩረቱ ግን ባቢሎን ላይ ነው:: (ዘፍ. 11 ትዝ ይሏል):: በራዕይ 17:1 ይህች ጋለሞታ በብዙ ውኃዎች (ህዝቦች) ላይ እንደምትቀመጥ ሲነገር ሚስጢሩ በአህዛብ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት እንደሚኖራት የሚያሳይ ነው:: በተጨማሪም ይህች ሴት በአውሬው ላይ ተቀምጣ ይታያል:: ቁ. 3 ይህም የሚያመለክተን ሴቲቱ ርኩሰትዋን የአውሬው ግዛት ባለበት ሥፍራ ሁሉ ማሰራጨት እንደምትችል ነው:: አውሬው ፖለቲካዊውን ክፍል ሲያንቀሳቅስ በፖለቲካው ሥልጣንና ጉልበት ደግሞ ተደግፋ ይህች ሴት ግልሙትና የሞላበትን ኃይማኖት ለዓለም ህዝብ እንደምታስተላልፍ መረዳት ይቻላል:: እስከ ተወሰነው ጊዜ በአውሬውና በጋለሞታይቱ መካከል ከፍተኛ መደጋገፍ ይኖራል:: በፍጻሜው ላይ ሁለቱም የዘሩትን ያጭዳሉ:: ራዕይ 17:16-17::

የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ስናጠና ተንኮለኞች የፖለቲካ መሪዎች በራስ ወዳድነት ላይ አትኩራ የእግዚአብሔርን ነገር ቸል ባለች ቤተ ክርስቲያን እንደተጠቀሙባት ከ15ኛውና 16ኛው ክፍለ ዘመን ታሪክ መረዳት ይቻላል:: በተመሣሣይ መልኩ ዛሬም ሆነ ነገ የጌታን ቃል ኪዳኑን የምትበድል ቤተ ክርስቲያን ካለች ለአውሬው ፈቃድ መንበርከኳ ፍጹም አይቀሬ ነው:: ስለሆነም ጥንቃቄ ይጠብቅሃል ማስተዋል ይጋርድሃል እንደተባለ መሆንና መኖር የመንፈሳዊ ጠቢብ አቋም ነው::

## 2.8 <u>እስራኤልና አውሬው</u>

በአውሬውና በእስራኤል መካከል ስለሚኖረው ግንኙነት የተወሰኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች ተጠቅሰዋል:: ከእነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹ በዳንኤልና በዮሐንስ የተገለጹት ናቸው:: ዳንኤል ስለእስራኤላውያን የስቃይ ዘመን ማብቂያ በጥብቅ ሲጸልይ ጌታ የሕዝቡ መከራና ስቃይ ከ70 ሱባኤ ወይም ከ490 ዓመታት በኋላ እንደሚያበቃ በመልዓኩ በኩል ተነግሮት ነበር:: ዳን. 9:24-27:: ከሰባ ሱባኤ ውስጥ አንድ ሱባኤ ቀርቷል:: በዚህ በቀረው ሱባኤ (ሰባት ዓመት) እስራኤል ከሮም ልዑል ጋር (ከሌሎችም) ስምምነት እንደምታደርግ ተተንብዮአል ዳን. 9:27:: በዚህ ክፍል አውሬው

(ሐሰተኛው ክርስቶስ) ከእስራኤል ጋር የሚያደርገው ውል ምን እንደሆነም በግልጽ ባይታወቅም የጦር መሣሪያ አቅርቦትና የፀጥታ ጉዳይ እንደሚሆን ይታሰባል:: ስውር የሆነው ጉዳይ ግን በእስራኤል ከርሰ ምድር ውስጥ ያለውን ሃብት በቁጥጥር ሥር ለማድረግ እንደሆነ ይታመናል:: በአሁኑ ጊዜ በእስራኤልና በአረቦች ፍልስጥኤማውያን መካከል ከፍተኛ ቅራኔና ፍጥጫ አለ:: ባለ 666ቱ አውሬ ሲመጣ ይህንንም ፍጥጫ ሊያረግብ እንደሚችል ይታመናል::

አውሬው በዳን. 8:23 እንቆቅልሽ ፈቺ እንደተባለ ሁሉ በእስራኤልና በአረቦች መካከል ያለውን እንቆቅልሽ ሙሉ በሙሉ ባይፈታም ለ3½ ዓመታት በማስመሰል ሊያረግብ ይችል ይሆናል:: ዳን. 9:27:: በአጋንንት መንፈስ ስለሚናገር የሰዎችን ልብ የመስረቅ አቋሙ ከፍተኛ ነው:: እስራኤላውያን እንደመሲሃቸው ሊቀበሉት እስኪችሉ አመጣጡ እንደ ጌታ ኢየሱስ ሊሆን ይችላል:: ሆኖም ከእስራኤላውያን ጋር ለ7 ዓመት የሰላም ቃል ኪዳን ተግባብተው በአጋማሹ ላይ የገባውን ቃል ኪዳን ያፈርሳል::[23] በዚህ ጊዜ ከእስራኤል ጋር ይጣላል:: በተለይ 144000 አይሁዶች በከፍተኛ ተቃውሞ ስለሚቋቋሙት ሊገድላቸው ሙከራ ሲያደርግ ወደ ሰማይ ይነጠቃሉ:: ራዕይ 12:5:: 144000ዎቹን ማጥቃት ሳይሆንለት ሲቀር የእስራኤልን ሕዝብ ባጠቃላይ ሊዋጋ ሙከራ ያደርጋል:: የተወሰኑትም እስራኤላውያን በእግዚአብሔር እርዳታ በብሉይ ኪዳን ነቢያት እንደተተነበየው ለ1260 ቀናት (3½ ዓመታት) ወደ ተዘጋጀላቸው መኖሪያ ስፍራ ይሸሻሉ:: ራዕይ 12:6፤ 13-14:: ይህ የመሰደዳቸው ጉዳይ በነቢዩ ኢሳያስ 16:1-5፤ 26:10-21፤ በሕዝ. 20:33-44፤ በዳን. 11:36-45:: በሆሴዕ 2:14-23 እና በማቴ. 24:15-22 ተተንብዮአል:: እስራኤላውያን ሊሸሹበት ያለው ሥፍራ በቀደሙት ነቢያት እንደተተነበየው ወደ ኤዶም፣ ሞአብና አሞን ምድር ነው:: በመልክዓ ምድር አቀማመጥ እነዚህ ስፍራዎች በአሁኑ ጊዜ በአረቢያና በዮርዳኖስ ውስጥ እንደሚገኙ ይነገራል:: አውሬው 144000ዎቹን ለማጥፋት ይፈልጋል፤ አይሳካለትም:: በተጨማሪም ሴቷን (እስራኤልን) በሙሉ ለማጥፋት ይጣጣራል:: ራዕይ 12:13 ይህም አይሳካለትም:: ሴቲቱ ትሸሽና ታመልጣለች፤ በመቀጠል ከሸሹት እስራኤላውያን የቀሩትን ዘርዋን ሊያጠፉ ማሳደድ ይጀምራል:: ራዕይ 12:15-16 በከፍተኛ የፖለቲካ ዜና ወይም ወታደሮችን በማሰማራት ያልሸሹትን እስራኤላውያንን ይከታተላል:: አሁንም ምድሪቱ አፍዋን ከፍታ ከአውሬው አፍ የወጣውን ውሃ ትውጣለች:: እስራኤላውያንም ያመልጣሉ:: በዚህ ክፍል ውኃ የተባለው የሕዝብና የወታደሮች ምሳሌ ወይም የፖለቲካ ወሬ አዋጅ ሊሆን ይችላል:: ሊተኮርበት የሚገባው እውነት በዚህ ውሃ እስራኤል ልትጠፋ አለመቻሏ ነው:: ምክንያቱም በእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን የሚጠበቅ ሕዝብ ስለሆነ ነው::

ለመሆኑ አውሬው ከእስራኤልና ከሌሎች ጋር የአንድ ሱባኤ ጽኑ ቃል ኪዳን የሚያደርገው ለምንድነው? ቀደም ብለን እንደተመለከትነው አውሬው 10ሩን ቀንዶች (መንግሥታት) ማስተባበሩ በእስራኤል ላይ አንድ ተጽዕኖ ለመፍጠርና እስራኤልን ለመቆጣጠር ዓላማ እንዳለ ይታሰባል:: ይህስ ለምንድነው? በነቢዩ ኢሳያስ የተነገረ የትንቢት ቃል አለ:: 29:1-8::



በዚህ ክፍል የተወሰኑ የዓለም መንግሥታት እስራኤልን እጅግ እንደሚፈልጓት በግልጽ ያሳየናል:: ጠላቶቿም እንደ አሸዋ እንደሚበዙ ተተንብዮአል:: ቁ.5:: እነዚህ ነገሥታት ያላቸው ትልቅ መሻት የእስራኤልን ሕዝብ አጥፍቶ ምሽጓን (በከርሰ ምድሯ ውስጥ ያለውን ሃብት) ለመበዝበዝ ነው:: ቁ. 7 ሆኖም ግን የእስራኤልን ሃብት ፍጹም መበዝበዝ እንደማይችሉና እንደተመኙ እንደሚቀር ቃሉ ይናገራል:: ቁ. 7-8 እግዚአብሔር በነቢዩ ኢሳያስ በኩል «ነገር ግን የጠላቶችሽ ብዛት እንደደቀቀ ትቢያ የጨካኞችም ብዛት እንደሚያልፍ ገለባ ይሆናል::... በአርኤልም ላይ የሚዋጉ እርስዋንና ምሽጓንም የሚወጉ የሚያስጨንቋትም የአህዛብ ሁሉ ብዛት እንደ ሕልምና እንደ ሌሊት ራዕይ ይሆናል:: ተርቦም እንደሚያልም ሰው ይሆናል:: እነሆ በህልሙ ይበላል ይጠጣልም ነገር ግን ይነቃል ሰውነቱም ባዶ ነው:: ... እነሆ ይዝላል:: ሰውነቱም አምሮት አለው:: እንዲሁ የጽዮንን ተራራ የሚወጉ የአህዛብ ሁሉ ብዛት ይሆናል:: ብሎ ተናግሯል:: ይህ የሚያመለክተን እግዚአብሔር የእስራኤል ጠባቂና ተከላካይ መሆኑን ነው:: በእስራኤል ላይ የሚሆነው ሁሉ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ነው:: እግዚአብሔር ሳይፈቅድ ምንም ነገር አይደርስባትም ማለት ነው:: ይህም ብቻ አይደለም በጌታ ቃልና በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደትን ያገኙ እውነተኛ ክርስቲያኖችም እንዲሁ በእግዚአብሔር የተጠበቁ ናቸው:: ወለም ዘለም የሚል አማኝ ነኝ ባይ ብቻ ነው ለልዩ ልዩ ፈተናና ውርደት የሚጋለጠው:: አሁንም ቢሆን ለምን አህዛብ እስራኤልን ይፈልጓታል? በሕዝ. 38 እና 39 እንደተጠቀሰው ለምን ራሺያና አበሮቿስ እስራኤልን ሊዋጉ ይሻሉ? አረቦችስ? ለዚህ ሁሉ ጥያቄ መልስ ሊሆነን የሚችለው በኢሳ. 29:7 የተጠቀሰው የእስራኤል ምሽግ ጉዳይ ነው::

በተለያዩ ጊዜያት የራሺያ ሳይንቲስቶች ወደ እስራኤል መጥተው በከርሰ ምድሯ ውስጥ ያለውን ሃብት አጥንተዋል:: በከተማይቱ ውስጥ በተለይ በሙት ባህር ያለው የተለያዩ ማዕድናት ክምችት በገንዘብ ሲተመን እጅግ የሚያስደንቅ ነው በኢሳ. 35 እንደተጠቀሰው የእስራኤል ምድረበዳ ወደፊት አብቦ ከፍተኛ ገቢ እንደሚኖረው፤ እንደ ፖታሽ፣ ጨውና ወዘተ ምርቶች ተገኝተው ለልዩ ልዩ ኬሚካሎችና መድኃኒቶች እንደሚውሉ ተጠንቷል:: ሳሌም ኪርባን የተባለው የነገረ ፍጻሜ ተመራማሪ በእስራኤል ከርሰ ምድር ውስጥ ያለውን ሃብት እንደሚከተለው ዘግቦታል:: «በእስራኤል ምድር ውስጥ (በሙት ባህር ብቻ) በአንድ ትሪሊየን ሁለት መቶ ሰባ ቢሊዮን (1,270,000,000,000) ዶላር የሚተመን ኬሚካል መኖሩንና ይህም ባለፉት 24 ዓመታት አሜሪካ፣ ታላቋ ብሪታኒያ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመንና ጣሊያን የነበራቸውን ሃብት የሚስተካከል እንደሆነ ሳይንቲስቶቹ ማመልከታቸውን የሚያሳውቅ ነው»::[24] ወደፊት ሥልጣናቸውን ለአውሬው የሚሰጡት 10ሩ ነገሥታት ዋና ዓላማቸው ይህንን በእስራኤል ውስጥ ያለውን ሃብት ለመበዝበዝ እንደሆነም ይታሰባል:: ይህ ካልሆነ በኢሳ. 29 እንደተጠቀሰው የሚጐመዡበትና ምሽጓን የሚፈልጉበት ምንም ምክንያት አይኖርም:: መንፈሳዊ ነገሯንና ሐብቷን አይፈልጉትምና::

እንግዲህ ስለ እስራኤል አንድ ልናተኩርበት የሚገባ እውነት አለ:: ይኸውም በከርሰ ምድርዋ ውስጥ ያለውን የተፈጥሮ ሃብት ለመበዝበዝ

የተወሰኑ የዓለም መንግሥታት ከፍተኛ ጥረት እንደሚያደርጉ ለዚህም አውሬው መንገድ ጠራጊ እንደሚሆን (ዳን. 9:27) ነው:: አሁንም እንኳን እስራኤል ከአውሮፓ ማሕበረሰብ ጋር የንግድ ስምምነት ጀምራለች:: ይህም ቢሆን ቅሉ እግዚአብሔር 144000 አይሁዶችን፣ ሁለቱን ነቢያት በማስነሳት የአውሬውን ስውር እቅድ እንደሚያደናቅፍበት ተተንብዮአል፤ ፈጽሞ አይሳካላቸውም ማለት ነው:: ይህንን ያህል ጥረት ቢደረግም የእነዚህ መንግሥታት መጨረሻ ከሰማይ በሚገለጠው በአይሁዶችና በቅዱሳን መሢህ በክርስቶስ ኢየሱስ ድል መሆን ነው:: ራዕይ 19:11-21:: እዚህ ላይ ነው ከእግዚአብሔር ጋር የሚዋጉ ይደቅቃሉ የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እውነት የሚሆነው::

በውጪአዊ ዕይታ የእስራኤልና የሌሎች መንግሥታት ኃይል ሲነጻጸር የእስራኤል ከቁጥር አይገቤ ነው:: ሆኖም ባቢሎን የአውሬው ከተማ እንደሆነች (ዘፍ. 11) እስራኤልም የመሢሁ ከተማ ናት:: በከተማይቱ የሚገኘው ሃብት ለሺህ ዓመት መንግሥት የተዘጋጀ በረከት ነው:: ኢሳ. 2:2-4፤ ሚክ. 4:1-4:: ስለሆነም በከተማይቱ ላይ መለኮታዊ የእግዚአብሔር ተቆጣጣሪነትና ገዢነት መኖሩን ሁሉም ልብ ሊለው የሚገባ እውነት ነው::

## 2.9 <u>አውሬውና ቤተ ክርስቲያን</u>

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አውሬው ከቤተ ክርስቲያን ጋር ሊኖረው ስለሚገባ አሉታዊ ግንኙነት በመጠኑ ተጠቅሷል:: የሁለቱን ግንኙነት በዝርዝር ካመመልከታችን በፊት ከቃሉ ትርጉም አኳያ «ቤተ ክርስቲያን» የሚለውን መፍታት ያሻል:: በግሪኩ ቃል ቤተ ክርስቲያን የሚለው ተጠርተው የወጡ ወይም ወንጌልን አምነው የተቀበሉና ለአውሬው ስውርም ሆነ ግልጽ ጥያቄ የማይንበረከኩ ተገዢነታቸው ለክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ የሆኑ ሰዎች ሁሉ የሚታወቁበት መጠሪያ ነው:: ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን <u>በቅድመ መከራ ሰባቱ ዓመት መከራና ድህረመከራ ሂደት</u> ውስጥ ልትኖር የምትችለበትንም ሁኔታ እንድናስብ ያስገድደናል:: ምክንያቱም በሦስቱም ጊዜአት ለእግዚአብሔር ተለይተው የሚቆሙ ቅዱሳን በመኖራቸው ነው::

### <u>ቅድመ መከራ ቤተ ክርስቲያን</u>

ከ70ኛው ሱባኤ (ከሰባቱ ዓመት መከራ) በፊት በቅድመ መከራ ቤተ ክርስቲያን በምድር ገጽ መኖሯ ለሁሉም ግልጽ ነው:: ከ68 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የአውሬው አሠራር እየረቀቀ መጥቷል:: ሆኖም በስውር እንጂ በግልጽ አልነበረም:: 2ኛ ተሰ. 2:6-7:: በዚህ ጥቅስ ውስጥ የአመጽ ሚስጢር ይሰራ እንደነበር አሠራሩም በስውር እንደሆነና እንዲህም እንዲሰራ ያደረገው <u>ከልካይ</u> መኖሩም ተገልጿል:: ይህ <u>ከልካይ</u> ማለትም አውሬው በግልጽ እንዳይሰራ ያደረገው ማነው? በየዘመኑ የተነሱ ሥነ-መለኮታውያን የተለያዩ ሐሣቦችን ሰንዝረዋል:: ከልካዩ ሰይጣን ነው፤ መንፈስ ቅዱስ ነው፤ የዓለም መንግሥታት ናቸው፤ ሁኔታዎች ናቸው፤ ቤተ ክርስቲያን ናት ወዘተ ያሉ ይገኛሉ:: ሆኖም የከልካዩ ማንነት የሚያመዝነው ወደ <u>ቤተ ክርስቲያን</u> ነው:: ምክንያቱም፣



### 1ኛ. <u>የጌታ ኢየሱስ የፍልሚያ ትንቢት ቃል መኖሩ</u>

በማቴ. 16:18 ላይ ...በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሰራለሁ:: የገሃነም ደጆችም አይችሏትም በማለት ጌታ ሲናገር ቤተ ክርስቲያን የክፉን ኃይላት የመቋቋም ሥልጣን እንደተሰጣት የሚያሳይ ነው:: ከሰይጣን ጀምሮ እስከ ዝቅተኛው የሰይጣን መሣሪያዎች ያሉትን በሙሉ ከመንፈስ ቅዱስ በተሰጣት ኃይል የምትፋለመው ቤተ ክርስቲያን ናት::

### 2ኛ. <u>የጳውሎስ ትንቢት</u>

ሐዋርያው ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን መጋደል ከደምና ከሥጋ ጋር ሳይሆን ከክፉት መንፈሳውያን ሠራዊትና ከዚህ ከጨለማ ዓለም ገዢዎች ጋር መሆኑን ሲገልጽ በአውሬው ውስጥ በሚስጢርም ሆነ በግልጽ የሚሠራውን ሥራ የመቋቋም ሥልጣን እንዳላት ያመለክታል:: ኤፌ. 6:12:: ቤተ ክርስቲያን የገሃነም ደጆችን ሥራ የምታፈርሰው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወንጌልን ለሰዎች በመስበክ፣ በጾምና በፀሎት፣ በልዩ ልዩ የፀጋ ስጦታዎች፣ በትንቢት የወደፊቱን በመግለጽ፣ በማጽናናት፣ ተአምራትን ድንቆችንና ምልክቶችን በመሥራት፣ የኃጢአትን ኃይል በክርስቶስ ደምና በመንፈስ ቅዱስ በማንጻት፤ ወዘተ ነው:: በእግዚአብሔር እውቀትና ሃሣብ ላይ የሚነሳውን የክፉ ሃሣብ በጌታ ስምና በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የምታፈርሰው ቤተ ክርስቲያን ናት:: 2ኛቆሮ. 10:3-5፤ እባብና ጊንጡን ትረግጣለች:: ሉቃስ 10:19:: የክፉን ኃይል ታስራለች:: ቀደም ብሎ እንደተመለከትነው ከተሰጡት ማስረጃዎች አኳያ በ2ኛ ተሰ. 2:6-7 የተጠቀሰው የሚያመለክተው መንፈስ ቅዱስን ሳይሆን ቤተ ክርስቲያንን ነው:: ይህ ማለት ደግሞ ቤተ ክርስቲያን በምትሰራቸው ሥራዎች መንፈስ ቅዱስ ምንም ድርሻ የለውም ማለት አይደለም::

ከልካዩ ለምን መንፈስ ቅዱስ አይሆንም? መንፈስ ቅዱስ ሊሆን የማይችልበት ምክንያት ይህ ከልካይ ይወገዳል ተብሎ ስለተነገረለት ነው:: ከልካዩ ከመንገድ ተወገደ ማለት አውሬው እንዲመጣ መንገድ ለቀቀለት ማለት ነው:: <u>ከመንገድ እስኪወገድ</u> የሚለው ሐረግ የተጻፈበት የግሪኩ ስርወ ግንድ ወደ ጐን ወይም ወደ ታች ዞር ማለትን ሳይሆን ወደ ላይ መወሰድን ነው:: በእንግሊዝኛ <u>ቴክን አፕ</u> በጣሊያንኛ <u>ራፔመር</u> የሚለው ቃል የሚያሳየው ወደ ላይ መወሰድን ወይም መሄድን ነው:: በሰባቱ ዓመት መከራ ጅማሬ ወይም አጋማሽ ላይ ቤተ ክርስቲያን ስትነጠቅ በምድር ላይ እንደ ቅድመ መነጠቅ በልዩ ልዩ መንፈሳዊ ቤተ ክርስቲያናዊ ውጊያ የአውሬውን ሥራ የሚያፈርስ አይኖርም:: ከዚህም የተነሳ አውሬውን ሙሉ በሙሉ የሚቋቋመው ስለማይኖር በኃይል ይወጣል፤ ይዋጋልም:: ራዕ. 6:2:: ይህ የሚያመለክተን አስቀድመን የተዋጋችው ቤተ ክርስቲያን መነጠቋን መንፈስ ቅዱስ ግን መኖሩን ነው:: መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን ይኖራል:: ለዚህም ማስረጃ የሚሆነን፤

- ሰዎች በመከራው ዘመን መዳናቸው ራዕይ 7:9-17::
- ሰዎች በክርስቶስ ደም መታጠባቸውና መንጻታቸው ራዕይ 7:1::

- አማኞች ከአውሬው የሚደርስባቸውን ተቃውሞ መጋፈጥ ችለው ራሳቸውን እስከ መሰዋት ማድረሳቸው ራዕይ 13:10::
- የክርስቶስ ምሥክር (መንፈስ ቅዱስ) ያላቸው ሰዎች በመከራው ዘመን (በ1260 ቀናት) ውስጥ መኖራቸው ራዕይ 12:17::
- በበዓለ ሃምሣ የወረደው መንፈስ ቅዱስ በስጋ ለባሽ ሁሉ እስኪደርስ በሰባቱ ዓመት መከራና እስከ ሺህ ዓመት መንግሥት መቀጠሉ ሐዋ. 2:16-18:: በሺህ ዓመት መንግሥት እጅግ ብዙ ሰዎች ወደ ጌታ ይመጣሉ:: ፍጹምም አምልኮ ለፈጣሪያቸው ያቀርባሉ:: ኢሳ. 2:2-4:: ይህ ከሆነ በበዓለ ሃምሣ አገልግሎት የጀመረው መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን የሚያቋርጥበት ምንም ምክንያት አይኖርም:: ምንም እንኳን የመከራ ዘመን ቢሆንም የምህረቱ በር ፈጽሞ አይዘጋም:: በመከራው ዘመን ብዙ ሰዎች ይድናሉ::
- በመከራው ዘመን መጽሐፍ ቅዱስ ይሰበካል:: ሰዎች የሚድኑ ከሆነ ለዚህ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ያለ መንፈስ ቅዱስ ትርጉም የለሽ ስለሚሆን መንፈስ ቅዱስ በምድር ላይ ይኖራል:: ስለሆነም የሚነጠቀው መንፈስ ቅዱስ ሳይሆን ቤተ ክርስቲያን ትሆናለች::

ስለሆነም በአውሬውና በቤተ ክርስቲያን መካከል የሚኖረው ግንኙነት የወደረኝነትና የጥላቻ ግንኙነት ነው:: ቤተ ክ. የአውሬውን ሥራ በመለኮታዊ አሠራር ታፈርሳለች:: በመካከላቸው የፍቅር ግንኙነት ፈጽሞ አይኖርም ራዕይ 13:10:: ይህች ከአውሬው ጋር በ70ኛው ሱባኤ የምትጋፈጠው ቤተ ክ. <u>የመከራው ዘመን ቅዱስን</u> ትባላለች::ራዕይ7፣13-14::

## 2.10 <u>አውሬው በሰይጣን ሥላሴ</u>

ሰይጣን የእግዚአብሔርን ህዝብ ከሚዋጋባቸው መንገዶች ወይም ዘዴዎች አንዱ ተመሳስሎ መምጣት ነው:: የሰይጣን ሠራተኞች የጌታን ሠራተኞች መስለው ይመጣሉ:: 2ኛ ቆሮ. 11:16-17:: ሐሰተኞች ክርስቶሶችና መሢሆች በጌታ ስም ይመጣሉ:: ይህ አሠራራቸው የመነጨው ከዲያብሎስ ነው::ዲያብሎስ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጣለበት ምክንያት ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር በማመሳሰሉ ነው:: ዛሬም ደግሞ የዓለምን ህዝብ ለማሳት ራሱን በሥላሴ መልክ ለመግለጽ ሙከራ ያደርጋል:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰይጣን ሥላሴ በተለይ በኢሳያስና በራዕይ ውስጥ ግልጽ ሆኖ ተቀምጧል:: ኢሳያስ <u>ፈጣኑ እባብ ሌዋታን፣ ጠማማው እባብ ሌዋታንና ዘንዶ</u> ሲላቸው ኢሳ. 27:1፤ ዮሐንስ ደግሞ <u>ዘንዶው፣ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ</u> ብሏቸዋል:: ራዕይ 16:13:: ሰይጣን ይህንን ዘዴ ያመጣው ለዓላማው ነው:: ይኸውም ሰዎች እንዲከተሉት ስለፈለገ ነው:: ራሱን በእውነተኛ የእግዚአብሔር ስላሴ ያስመስላል:: ሰይጣን (ዘንዶው) የአብን ቦታ፣ አውሬው የሬታ ኢየሱስን ቦታ፣ ሐሰተኛው ነቢይ የመንፈስ ቅዱስን ቦታ ለመውሰድ የጠነሰሱት ዘዴ ነው:: ይህ ስውር የሰይጣን የውጊያ ዘዴ ነው::

ይህ ግንኙነታቸው በእግዚአብሔር ሥላሴ መካከል እንዳለው ተመሣሣይ ነው:: ለምሳሌ እኛ በምድር የምንኖር ቅዱሳን መንፈስ ቅዱስን እንገልጻለን:: 1ኛ ቆሮ. 12:7 መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ወልድን በመግለጽ



ይመሰክራል:: ዮሐ. 16:14 ወልድ ደግሞ አብን ይተርካል (ይገልጻል):: ዮሐ. 1:18 ልክ በቅዱሳኑና በእግዚአብሔር መካከል የዚህ ዓይነት ኅብረት እንዳለ ሁሉ በአዲስ ዘመን እንቅስቃሴና በሰይጣንም መካከል ተመሳሳይ የሆነ ኅብረት አለ:: የአዲስ ዘመን እንቅስቃሴ አባላት ሐሰተኛውን ነቢይ ያከብራሉ ወይም ይገልጻሉ:: ራዕይ 13:12:: ሐሰተኛው ነቢይ ደግሞ አውሬውን ያከብራል ራዕይ 13:12:: አውሬው ደግሞ ዲያብሎስን ያከብራል:: አውሬው ስራውን ሁሉ የሚሰራው ልክ አብ ለወልድ ሥልጣን እንደሰጠው ከዘንዶው ሥልጣኑን ተቀብሎ ነው:: ራዕይ 13:3-4:: አውሬው ራሱን እንደ ክርስቶስ የሚያስመስለው አዳኝ፣ እንቆቅልሽ ፈቺ፣ ተዋጊ፣ ሰላም አምጪ፣ የዓለም ንጉሥ፣ መሢህ፣ ወዘተ እንደሆነ በመስፈፍ ነው:: ዳን. 8:23፤ 16:13-16:: ስለሆነም ምናልባት በመከራው ዘመን ብንኖር ሰይጣን ራሱን በስላሴ መስሎ ሲመጣ የእውነተኛው ስላሴ መስሎን እንዳንታለል ከአሁኑው በቃሉና በመንፈስ ቅ. ብርሃን ትክክለኛ አብርሆት ለማግኘትና ለመዘጋጀት መጣር ይኖርብናል:: ህይወት እንደዋዛ አይታይምና::

## 2.11 የአውሬው ፍጻሜ

ስለ ፍካሬ 666 በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀሱት ውስጥ በጣም የሚገርመውና የሚያሳዝነው የአውሬው የህይወት ፍጻሜ ነው:: የአውሬውን አጀማመርና ሂደት ከትንቢት አኳያ ተመልክተናል:: ስለፍጻሜውም እንዲሁ ተተንብዮአል:: ራዕይ 20:19-20 አውሬው 10ሩን ነገሥታት በከፍተኛ ደረጃ ያንቀጠቀጠ፣ ማንስ ሊዋጋው ይችላል ተብሎ የተነገረለትና ሰዎችም እየተከተሉ ያደነቁት ገገር ነው:: ራዕይ 13:1-4 የአውሬው ኃይል በዳን. 7፤ 8 እና 11 ውስጥ ታሪካቸው የተጠቀሰውን የግብጽን፣ የሜዶንና ፋርስን፣ የሮምን፣ የግሪክንና ወዘተ መንግሥታት ዓይነትና የበለጠም ኃይል የነበረው ንጉሥ ነበር:: ይህ አውሬ ከጋለሞታይቱ ጋር በመተባበር በክርስቶስ ያመኑትን ቅዱሳን ደም የማያፈስስና ክርስቶስን የሚቃወም የዓለም ገዢኛ መሪ ነው:: ራዕይ 13፣10፤ 17፣3-6፤ 18፣24:: አውሬው በዓለም እጅግ ይገንናል:: ሰዎችም አምላክ ነው ብለው ይሰግዱለታል:: ይህንን ሁሉ ካደረገ በኋላ ከመጨረሻው ሱባኤ በፊት ክርስቶስ ቅዱሳኑን ለመውሰድ (መነጠቅ) መጥቶ፤ ይዟቸውም በአየር ወደ ሰማይ ተመልሶ፤ ከዚያም ከሱባኤው በኋላ ለሺህ ዓመት ለመንገስ ከሰማይ ከመላዕክቱና ከ<u>ሚስቱ</u> (ከቤተ ክርስቲያን፣ ከብሉይ ኪዳን አማኞች፣ ከ144000 አይሁዶችና ከመከራው ዘመን ቅዱሳን ጋር) ሲመለስ ራዕይ 19:14 አውሬው ጌታንና ቅዱሳንን ሊዋጋ ከሰራዊቱ ጋር በአርማጌዶን ይሰበሰባል:: ክርስቶስ ኢየሱስም በአምባላይ (ነጭ) ፈረስ ተቀምጦ ከሰማይ በመምጣት አውሬውንና ተከታዮቹን ይዋጋል:: ሁሉም ይሞታሉ:: ደማቸውም እስከ 1600 ምዕራፍ (320 ኪ. ሜትር ያህል) ይፈስሳል ራዕይ 14:20:: አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይም ተይዘው ወደ እሳት ባህር በህይወት ሳሉ ይጣላሉ:: መንግሥትም ለልዑል ቅዱሳን ይሰጣል የተባለው ትንቢት ይፈጸማል:: ዳን. 7:27:: ራዕይ 19:14-21:: ያ ሁሉ ልዕልናና-ክብር በአንድ ጊዜ ሲፈርስ እጅግ ድንቅ ነው:: የኢየሱስ ጌትነት ማለት ይህ ነው:: አሜን!

በዘመኑ የ666 ማግኔታዊ ስበት የተወሰዱና በጌታ ኢየሱስና በቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ ስደትና መከራ የሚያመጡም ሁሉ ዕድል ፈንታቸው እንዲሁ እንደሚሆን ሊዘነጉት አይገባም:: የሰው ልጅ ሊያስበው የሚገባው ዐቢይ ነገር ስለ ህይወቱ ፍጻሜ ጉዳይ ነው:: ሰውን አትመኑ አብዷል ዘመኑ እንደተባለ ሰውን ከማመን ይልቅ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ማመኑ ጠቢብነት ነው:: በተለይ ህይወትን በተመለከተ አስተማማኝ ምሪት ሊሰጠን የሚችል መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው:: ትንቢቶችን መርምሮ በመረዳት ወደ ቁም ነገር መድረሱ የእያንዳንዱ ሰው ኃላፊነት ነው:: በአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ድንበር ውስጥ የገባንና የአውሬውን መንገድ የያዝን የዳግም ልደትን መንገድ ያልያዝን ሆኖም እንደ ኒቆዲሞስ ሃይማኖታዊ ሥርዓትን የምንከተል ይህንን እውነት ልብ ልንለው ይገባል:: የአውሬውን መንገድ ተከትለን በኋላ ጽድቁ ቀርቶ በውል በኮነነኝ ጸጸት ውስጥ እንዳንወድቅ ዛሬውኑ መንገዳችንን ስልለን ልንቀና ይገባል::

ጌታን እንደግል አዳኛችን ተቀብለን የእግዚአብሔርን ልጅነት ሥልጣን አግኝተናል የምንለውም ብንሆን ዝንባሌያችንን በጥንቃቄ ልንመረምር ይገባናል:: የተቀደሰውን ኃይማኖት በመበረዝ ልምምድ ውስጥ እንግባ:: ግርግርታ የሌባ ደስታ እንደተባለ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልሆነ ሆኖም በሚመስል ጉዞ ብንመላለስ እየተበረዝን መሆኑን እንዘንጋ:: የቃሉ ትርጉም ትንሽ ሲጣመም አይተን የሚቆጠቁጠን ካልሆነ ድንዛዜ እንደወደቀብን ልብ ልንል ለአስቸኳይም ንስሃ ልንዘጋጅ ያሻል:: አውሬው ጣፋጭ ጣፋጭ ነገርን እንጂ መራራን ይዞ አይመጣም:: ሰይጣን ለወዳጁ ድርብ ነው እንደተባለ ሰዎችን ለመሳብ ጊዜአዊውን እንቆቅልሽ መፍቻ መሣሪያ በብዛትና በጥራት መጠቀሙ አይቀርም:: ዳን. 8:23:: ለዚህም ነው በአውሬው ዘመን ሰዎች ሰላምና ደህንነት ነው የሚሉት 1ኛ ተሰ. 5:3 የሐሰተኛው ክርስቶስ ነቢይና የአርማጌዶን ጦር ሜዳ ተሳታፊዎች ዕድላቸው ለገሃነም፣ ለሰማይ ወፎችና ለዱር አራዊት እንደሆነ፣ በአውሬው ተከታዮችና ቁጥሩን በተቀበሉት ሁሉ ላይ ክፉኛ የሚነዘንዝ ቁስል እንደሚሆንባቸው፣ ራዕይ 16 በትንቢቱም እንዳየነው በእኛ ላይና በሰው ልጆች ሁሉ ላይ እንዳይደርስ ወንጌልን በመስበክ ሰዎችን ወደ እውነት ልንመልስ ያሻል::

በፍካሬ 666 የቁጥሩን ትንቢታዊ መልክ ተመልክተናል:: በክፍል 3 ደግሞ በዕይታ 666 በአሁኑ ወቅት ከ666 ጋር በተያያዘ ያለውን እንቅስቃሴ እንመለከታለን::



# ክፍል ሦስት

## ዕይታ 666

አስቀድሞ ትንቢታዊ መልኩን ለማሳየት የተሞከረው 666 በአሁኑ ጊዜ በምን ዓይነት ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ታሪካዊ ሂደቱን ደግሞ እንመለከታለን:: ታሪካዊ ሂደት ሲባል 666 ቁጥር በምድራችን በምን ዓይነት መልክ እየተገለጠ መሆኑንና ሰዎችም ያላቸው ምላሽ እንዴት እንደሆነ ማሳየት ነው::

### 3.1 የዓለም ህዝብ መሪዎች ጩኸት

መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ትንቢት ሰዎች ቢያስተውሉትም ባያስተውሉትም መፈጸሙ ፈጽሞ አይቀርም:: ስለ ሐሰተኛው ክርስቶስና ስለ ተከታዮቹ የተነገረው የትንቢት ቃል እውን ይሆን ዘንድ የቃሉ ባለቤት በሥልጣኑ መሠረት እንዲፈጸም ያደርጋል:: ከዚህ ሃሣብ በመነሳት በአሁኑ ጊዜ የዓለም ህዝብ መሪዎች ያሉበትን ጭንቀትና የውስጥ ጥማት መመርመር አያዳግትም:: በዓለማችን ላይ የተከሰተውና ሊከሰት ያለው የፖለቲካ፣ የማኅበረሰብ ግንኙነት የኤኮኖሚና የተፈጥሮ ችግሮች የቀደሙትንም ሆነ አሁን ያሉተን የፖለቲካ መሪዎች ጭንቅላት አዙሯል:: ችግሮችን ለማርገብ ወይም ለመፍታት በየጊዜው የተባበሩት መንግሥታት መሪዎች የክብ ጠረጴዛ ስብሰባ ያደርጋሉ:: የሚያቀርቧቸው መፍትሔዎች አንደኛውን ክፍል ሲያስደስት ሌላውን ያሳዝናል:: አንዱን ሲጠቅም ሌላውን ይጎዳል:: የዩሮፓች ሚስጢር ሙሉ በሙሉ ያለመታወቁ፤ አምባገነናዊ አመራርን የሚያከሩ፣ ዘረኝነትን የሚያጧጡፉ፣ ስውር አመራርንና ራስ ወዳድነትን የሚያካሂዱ ወዘተ መሪዎች በስብሰባ መካከል መገኘታቸው የፖለቲካ መሪዎችን ሲያበሳጭና ሲያሳዝን ቆይቷል:: መፍትሔ ለማስገኘት ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን ሰውተው በመሰባሰብ የሚያቀርቧቸው ሐሣቦች ሲወድቁ መሰላቸት ሲፈታተናቸው ይታያል:: ባለፉት ዘመናት ልዩ ዓይነት የአመራር ችሎታ ያለው ሰው ብዙ ጊዜ ፈልገዋል:: ለምሳሌ እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ ወይም እንደ ሰለሞን ያለ መለኮታዊነት የታከለበት ማንነት በጥብቅ ተፈልጓል:: እንደ ናፖሊዮን፣ ሂትለርና ሙሶሊኒ ... ያሉ ግለሰቦችም ተነስተው ብዙ በማለት የተለያዩ እርምጃዎችን ወስደዋል:: ሆኖም ለዓለም ቀውስ ዘላቂ መፍትሔ አልተገኘም:: የመንግሥታቱ ድርጅት ትላንትና ይናፍቁት የነበረውን ሰው ዛሬም ይናፍቁታል፤ አሰፍስፈውም ይፈልጉታል:: ለጊዜውም ቢሆን ማግኘታቸው አይቀሬ ነው::

ዓለምን አሁን ካለችበት የኤኮኖሚና የፖለቲካ ቀውስ ሊያወጣት የሚችለው ሰው ከዚህ ቀደም ከተነሱት መሪዎች የተለየ እንደሚሆን ታላቅ ተስፋ ተደርጓል:: ይህንን ሃሣብ ለማጠናከር እ.ኤ.አ. በ1957 ዓ.ም. የሰሜን አትላንቲክ የቃል ኪዳን አገሮች ዋና ፀሐፊ የነበሩት ሄንሪ ስፓክ በፓሪስ በነበራቸው ስብሰባ ላይ የተናገሩትን ማስታወሱ ጠቃሚ ነው:: ስፓክ «ሌላ ኮሚቴ አንፈልግም፤ አስቀድሞ ብዙ ኮሚቴዎችን አይተናል፤ የምንፈልገው

የህዝብን ሁሉ ክብር የመጠበቅ በቂ ችሎታ ያሰውንና እየሰጠምንበት ካሰው የኤኮኖሚ አዘቅት የሚያወጣንን አንድ ሰው ነው::[1] ሰይጣንም ይሁን እግዚአብሔር የዚህን ዓይነቱን ሰው ላኩልን፤ እንቀበለዋለን::» በማለት ተናግረው ነበር:: ይህ አነጋገር መሪ ከተባሉ ሰው ሲወጣ በመካከላቸው ችግር አስወጋጅ ሰው ምን ያህል እንደጠፋና ሰይጣንም እንኳን ቢመጣ ሊቀበሉት እንደሚችሉ ያላቸውንም ጉጉት ያሳያል:: እንግዲህ ሰዎች የእውቀትና የጥበብ ምንጭና ጌታ የሆነውን ክርስቶስ ኢየሱስን አምነው ካልተቀበሉ አውሬውን መቀበላቸው የማይቀር ነው:: 2ኛ ተሰ. 2:11:12፤ ቆላ. 2:2-3:: ከላይ ስፓክ የገለጹት ንግግር በሰዎች ውስጥ አውሬውን ለመቀበል ምን ያህል መነሳሳት እንዳለ በግልጽ የሚያመለክት ነው:: ስለሆነም አውሬው በደጅ መሆኑን መረዳት ይቻላል::

### 3.2 666 የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ መብራት

የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ የ666ን መስፋፋት ከሚያፋፍሙ ክፍሎች ውስጥ የመጀመሪያውን ሥፍራ ይይዛሉ:: በአሁኑ ጊዜ እንቅስቃሴው ወደ 1,000,000,000 (አንድ ቢሊየን) የሚጠጉ አባላት ያሉት ሲሆን በ2000 ዓመት ማብቂያ ላይ አውሬውን ማግነን ዐቢይ አላማቸው እንደሚሆን ተናግረዋል:: የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ከ666 ጋር ከፍተኛና ጥብቅ ግንኙነት አላቸው:: አባላቱ 6ትን፣ 66ትን ወይም 666ትን የሚጠሩበት ስም አላቸው:: ይኸውም 666 ቁጥር፤[2]

1. «የመሚሃችን ቁጥር» ይሉታል:: አውሬው በጣም ታላቅና ኃይለኛ አቋም ያለው በመሆኑ አቀራረቡ በሙሉ አስፈሪ ነው:: ራሱን እንደአምላክ ማየትና መቆጣር የሚችልበት ኃይል አለው ስለሆነም የእርሱን ኃይል ለማግኘት አዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ናፍቆት አላቸው:: የታላቁ መምህር ቁጥርም ተብሎ ይጠራል::

2. የመለኮታዊ ብርሃን ቁጥር: አንድ ሰው ቁጥሩን ከተቀበለ መለኮታዊነቱን ማየት ይችላል:: ካልተቀበለ ግን እንደታወረ ይቀራል ስለሚሉ አምላክ መሆናቸውን ለማየት ቁጥሩን እንዲቀበሉ ይነሳሳሉ ሰዎችንም ያነሳሳሉ::

3. የጨለማ ኃይላት ቁጥር: በክርስትና ብርሃን ተወዳጅ እንደሆነ ሁሉ በአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ደግሞ ጨለማ ተወዳጅ ሁኔታ ነው:: አባላቱ በጨለማ መሆንን በጣም ይናፍቁታል:: ጨለማ የኃይል ማግኛ ቦታቸው እንደሆነ ይቆጥራሉ:: ስለሆነም 666 ተወዳጅ የኃይል ምንጭ ቁጥራቸው ነው::

4. አጥፊ ቁጥር: የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ እንደሚናገሩት በ2000 መጨረሻ ማንኛውም የምድር ነዋሪ ሁሉ 666ን እንዲቀበል ባይቀበል ግን እንዲገደል የማድረግ እቅድ አላቸው:: ይህ ደግሞ በራዕይ 13 ተነግሯል:: በቀኝ እጃቸው (በግምባራቸው) እንዲቀበሉ ያደርጋል ተብሏል::ይህንን ተግባራዊ የሚያደርጉት የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ



አባላት ይሆናሉ:: ቁጥሩ ያለበት ሰው ሲድን የሌለው ግን ይጠፋል:: ስለሆነም የቁጥሩ በሰው ላይ መኖሩ ለመለየትና የሌለበትን ለማጥፋት ይሆናል ማለት ነው::

የኮምፒውተር ፍጹም ቁጥር: የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ራሳቸውን የሚያስተካክሉት ልዩና መለኮታዊ ጭንቅላት ካለውና መመሪያው በኮምፒውተራዊ አስተሳሰብ ከሆነው መሢሃቸው ጋር ነው:: 6 ቁጥርን እንደ ኮምፒውተር ፍጹም ቁጥር ይመለከቷታል:: የእነርሱም ጭንቅላት እንደ ኮምፒውተር ማሰላት የሚችል መሆኑን ለማመልከት የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው::

የሦስተኛው ዓይን ከፋች ቁጥር: አዲሱ ዘመነ እንቅስቃሴ ሰው ከተፈጥሮ ዓይን ሌላ ከኋላ በኩል ከአንገት በላይ በጭንቅላት ሥር፣ በቀኝ እጅ መዳፍ ውስጥና በግንባር መካከል ሰው ሦስተኛ ዓይን አለው ይላሉ:: ሰው ሁሉ ይህ ዓይኑ ቢከፈትለት አምላክ መሆኑን ወይም ለአምላክነት የሚያበቃው እምቅ ኃይል በውስጡ መኖሩን ማወቅ ይችላል በማለት ያስተምራሉ:: ከዚህም ጋር በማያያዝ ይህ ዓይን የሚከፈትበትንም ዘዴ ይዘው ቀርበዋል:: ይኸውም ሰዎች ሁሉ የሦስተኛው ዓይኑ ከፋች የሆነችውን የኮምፒውተር ፍጹም ቁጥር 666ትን መቀበል እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው:: ይህ የሚጠቁመው ቁጥሩ የሌለው ሁሉ አምላክነቱን ማወቅ እንደማይችልና ደንቆሮ ሆኖ እንደሚቀር ነው:: ስለሆነም ይህ ሃሣብ የዚህ ዓይነቱ ሰው ለዚህ ዓለም ኑሮ (ነዋሪነት) የማይስማማ (Unfit) ስለሚሆን እርሱን በመግደል ማስወገድ ይሻላል ወደሚለው ድምዳሜ የመጣቸዋል:: ስለ|ዮነም ፊፊፊ



7. <u>በክርስቲያኖች ላይ ጦርነት የሚያውጅ ቁጥር</u> ይሆናል ማለት ነው:: ቁጥሩ አገልግሎት አለው:: ይኸውም እውነተኛ አማኝ የሆነውንና ያልሆነውን ይለያል:: ቁጥሩ የሌለባቸው ሁሉ ቅዱሳን ስለሚሆኑና ለአውሬው ስለማይሰግዱ ምድሪቱን እንደሚያረክሱ ክፍሎች ይቆጠራሉ:: ስለሆነም የቁጥሩ በእነርሱ ላይ አለመገኘቱ በአውሬው የሚተረጐመው «የእኔ ስላይደሉ ይገደሉ« በሚል ሃሣብ ይሆናል:: ከላይ በተዘረዘሩት ዓይነት አሠራሮች በ2000 ማብቂያ አዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ የ666ትን አሰራር ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛሉ:: የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ይህንን ዓላማ ማድረጋቸው የራሳቸውን ትንቢት ያመለክታል:: ይህ ትንቢታቸው ደግሞ ከ666 መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢት ጋር ይሄዳል:: ይህም የአውሬው መገለጫ ጊዜ እጅግ መቅረቡን ጌታም በተከታታይ ሊመጣ መሆኑን ያሳየናል::

## 3.3 <u>666 በኮምፒውተር (COMPUTER) ውስጥ</u>

ባለንበት ዘመን የኮምፒውተር ጉዳይ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ መልኩ አሳሳቢና ብዙ አነጋጋሪ ጉዳይ ሆኗል:: ብዙ ታላላቅ የዓለም ሳይንቲስቶች በኮምፒውተር መገኘት ቢደሰቱም ያንኑ ያህል ስጋት ላይ ሳይጥላቸው አልቀረም:: በተለይም ለመልካም የታሰበው ሳይንሳዊ ግኝት በአንዳንድ ሁኔታና አተረጓጐም ለአጥፊዎች መጠቀሚያ ሲውል ተመራማሪዎችን በእጅጉ አስቆጥቷቸዋል:: ይህንን ሁኔታ እስቲ ቀጥሎ ከሚቀርቡት ማስረጃዎች እንገምግም::

### ሀ. <u>የኮምፒውተር ምንነትና አፈጣጠር</u>

ኮምፒውተር ማለት በተወሰነ የእዝ ሰንሰለት ወይም ፕሮግራም አማካኝነት መረጃዎችን ማሰላሰል የተሰጡትን መረጃዎች መሠረት በማድረግ የተሰጡትን ፕሮግራሞች መፍታት፣ ውጤታቸውን ማሳወቅ እንዲሁም መረጃዎችንና ትዕዛዞችን በማህደረ-ትውስታ ማኖር የሚችል ኪን (ልዩ መሣሪያ) ማለት ነው::[3] በዚህ ትርጉም መሠረት ኮምፒውተሮች የአንድን መሥሪያ ቤት ደመወዝ በማዘጋጀት በአይሮፕላን ለሚደረግ የበረራ ጉዞ ቦታ በመያዝ፤ በሆስፒታሎች ውስጥ ያሉ ሰዎችን የደም ዓይነት በመለየት፤ የስልክ መስመሮችን መጨናነቅ በመቆጣጠርና በሆስፒታል በሽተኞችን ለመመዝገብና የበሽታውን ዓይነት ለማወቅ ይጠቅማሉ:: ሂሣባዊ ስሌቶችን ብቻ በመስራት አይወሰኑም:: በራሳቸው አያስቡም:: በመረጃ ተደግፈው የሚሰሩ ናቸው:: ለሰው ልጅ ብዙ ዓመታት ሊወስዱ የሚችሉ የሂሣብ ስሌቶችን በማይገመት ፍጥነትና ጥራት በአስተማማኝ ሁኔታ ይሰራሉ::

### ለ. <u>የኮምፒውተር አመጣጥ ታሪክ</u>

የመጀመሪያው የስሌት መሣሪያ <u>አባከስ</u> በመባል የሚታወቅ ሲሆን በጥንታዊ የባቢሎን ዘመን ሥራ ላይ ውሎ ነበር:: መሣሪያው ኋላ ቀር



...ንም ለአሁኖቹ ኮምፒውተሮች መገኘት መሠረት መሆኑ ይነገራል::[4] ... ደረጃ <u>ፓስካሊይን</u> በመባል የሚታወቀው የፓስካል የስሌት መሣሪያ ...623 ተሰርቷል:: የሚያሰላውም መደመርንና መቀነስን ብቻ ነበር:: ...ስተኛ ደረጃ <u>ሌብኒዝ</u> (1646-1716) የኖረው 4ቱን የሂሣብ መደቦች ...ሰራ የመጀመሪያውን የተሳካ ሂሣባዊ መሣሪያ ሰርቷል:: ሌሎች ብዙ ...በራዎች የተደረጉ ሲሆን የመጀመሪያው የኤሌክትሪክ ዲጂታል ...ፒውተር የተሰራው በጀርመን ውስጥ እ.ኤ.አ. በ1941 ዓ.ም. ነበር:: ...ቀጠል በጣም ፈጣኑ <u>ኤኒያክ</u> ተሰርቷል:: ኤኔያክ 5000 የሂሣብ ...ቶችን በአንድ ሴኮንድ ውስጥ የመሥራት ችሎታ ነበረው:: ኤኒያክ ...ደዘመኑ ኮምፒውተሮች በጠረጴዛ ላይ የሚቀመጥ ሳይሆን 15000 ስኩዌር ...ትር ስፋት ቦታ ይፈልግ ነበር:: ክብደቱ 30 ቶን ነበር:: ኤኒያክ ...ሥራት ሲጀምር 200000 ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ይጠቀም ነበር:: ይህ ...ለት በአሁኑ ጊዜ በየቤቱ ለግል የሚያገለግሉ 600 ዘመናዊ ኮምፒዩተሮች ...ገለገሉበት ኃይል ማለት ነው::[5]

### ሐ. <u>የኮምፒውተር ዓይነቶች</u>[6]

የኮምፒውተር ዓይነቶች የተለያዩ ናቸው:: አናሎግ፣ ብሪፍ ኬዝ፣ ...ስክቶፕ፣ ዲጂታል፣ ሆም ኮምፒውተር፣ ማይክሮ፣ ሚኒ፣ ፐርሰናል፣ ...ሞልቢዝነስ ኮምፒውተር ወዘተ በመባል የሚታወቁ አሉ:: ከላይ ...ተዘረዘሩት ሌላ ሦስት የተለያዩ መጠን ያላቸው ኮምፒውተሮች ይገኛሉ:: ...ነዚህም ኮምፒውተሮች፤

#### 1. <u>የተለመደ (ኖርማል) ኮምፒውተር</u>

ይህ ኮምፒውተር በተለይ በትናንሽ ቢሮዎችና ቤቶች ውስጥ ...ልግሎት የሚሰጥ ነው:: አንድ ድርጅት በውስጡ ያሉትን ልዩ ልዩ ...ምርት ዓይነቶችን፣ የሠራተኞችንም ሁኔታ በመመዝገብ ስሌቶችንና ...ዕዛዛትን ለማከናወን የሚረዳ መሣሪያ ነው::

#### 2. <u>ከፍተኛው (ሱፐር) ኮምፒውተር</u>

የዛሬ 40 ዓመታት አካባቢ የተሰሩት የኮምፒውተር ዓይነቶች ...ሰኮንድ ወደ 5000 ትዕዛዛትን መሥራት የሚችሉ ነበሩ:: ይህ ሱፐር ...ምፒውተር ግን ብዛታቸው ከ200 በሚበልጡ አገሮች ጋር በተያያዘ ሁኔታ መረጃዎችን ማቅረብ የሚችል ነው:: በአሁኑ ጊዜ ከሚሰራባቸው ኖርማል ...ምፒውተሮች ከ15-25 እጥፍ የሚበልጡ ናቸው:: ሱፐር ኮምፒውተሮች ...ሰኮንድ ከ70 እስከ 100 ሚሊዮን ትዕዛዛትን መሥራት ይችላሉ:: እነዚህ ...ምፒዩተሮች ከኖርማል ኮምፒውተሮች የተላኩላቸውን መረጃዎች መያዝ ...ሚችሉ ናቸው::[7]

## 3. ልዕለ-ኮምፒዩተር (ማስተር ኮምፒውተር)

ይህ ኮምፒዩተር ከማናቸውም ይልቅ በብዙ እጥፍ የበለጠ ሲሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ሊሰራበት የታሰበው ነው:: ይህ ኮምፒዩተር በሰከንድ ውስጥ እስከ 250000000 ትዕዛዛትን ማስላትና ማከናወን የሚችል ነው:: በ1980ዎቹ መጀመሪያ ላይ ይህ ማስተር ኮምፒዩተር እንደሚሠራ ተተንብዮ ነበር:: ብዙ ሙከራዎች ተደርገው ኮምፒዩተሩ በአሁኑ ጊዜ በቤልጀም (ብሩሴልስ) ተሰርቷል:: ቤልጀም (ብሩሴልስ) ከአውሮፓ የጋራ ገበያ አባላት ከሆኑት አገሮች ውስጥ የመጀመሪያዋ አገር ናት:: ይህች አገር ለዓለም አቀፉ የኮምፒዩተር ሥራና ገንዘብ አልባ የሆነውን ህብረተሰብ ለመፍጠርና ለመቆጣጠር በማዕከልነት የምታገለግል አገር ሆናለች:: ይህ የኮምፒዩተር የቁጥጥር ማዕከል ባለ 3 ፎቅ ሕንጻ ያለው ሲሆን የአውሮፓ የኤኮኖሚ ማኅበረሰብ ዋና ቢሮም የሚገኘው እዚሁ ነው:: የታወቁት የኮምፒዩተር አናሊስት ዶ/ር ሃንሪክኤልድማን በአሁኑ ጊዜ ሰውን ሁሉ በባለ 18 ዲጂት ቁጥር ለመሰየም ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ እንደሆነ ተናግረዋል:: በተጨማሪም «ሳን ጆስ ሜርኩሪ» ተብሎ በሚጠራ ጽሑፋዊ መገናኛ እ.ኤ.አ. በነሐሴ 1975 «ይህስ» በሚል ርዕስ በወጣው ጽሑፍ ውስጥ አውሬው ማለት ታላቅ ኮምፒዩተር እንደሆነ፣ እያንዳንዱን ሰው በቁጥር ለመሰየም የታቀደና ቁጥሩም ለሰዎች ሲታደል ለመግዛትና ለመሸጥ ብቻ የሚያስችል እንደሆነ ታትቷል:: ዘጋቢዎቹ እንደገለጹት ይህ መለያ ኮድ (ቁጥር) በጨረር ኃይል እንደሚነበብ ሆኖ በግምባር ወይም በእጅ መዳፍ ጀርባ ላይ እንደሚደረግም ጽፈዋል:: በተጨማሪም ይህ ዲጂታል ምልክት የሌለው ማንም ቢሆን ሊገዛ ወይም ሊሸጥ እንደማይችል ገልጸዋል::

### የቃለ መጠይቅ ምልልስ

ዶ/ር ኤሚል ጋቨርለክ «አውሬው ተብሎ ስለሚጠራው በብሩሴልስ ውስጥ ስለተሠራው ግዙፉ ኮምፒዩተር ሊነግሩን ይችላሉ?


ዶ/ር ፓትሪክ ፊሸር «አዎን ይህ ኮምፒዩተር ለ4 ዓመታት ያህል እዚህ ነበር:: በካርድ ሲስተም የዓለም የንግድ ብሔሮችን ዘግቦ ይይዛል:: በወሊድ ሰርቲፊኬት፣ በመንጃ ፈቃድ ይሁን በሌላ ሁኔታ እኔና አንተም በዚያ ተመዝግበናል:: ከአገር ውስጥ ገቢ ጋር በተያያዘ ያደረግሃቸው እንቅስቃሴዎች በሙሉ ተይዘዋል:: ከ4 ዓመታት በፊት ይህ ኮምፒዩተር የ2,000,000,000 (ሁለት ቢሊየን) ሰዎችን መረጃ ሊይዝ እንደሚችል ታስቦ ነበር:: ይህም መረጃ ከአገር ወደ አገር ከሚንጓዙ፣ የዱቤ ካርዶችን ከሚጠቀሙ፣ ወዘተ ጋር የተያያዘ ነው::»

ዶ/ር ጋቨርለክ «በድጋሜ አጥብቄ መጠየቅ እፈልጋለሁ እያንዳንዱ የዓለም ኢንዱስትሪ ቀጠናዎች አባል አገር የሆነ ሁሉ ገና ዱሮ በኮምፒዩተሩ ውስጥ ናቸው ማለትህ ነው?»



ዶ/ር ፊሸር «በእርግጥ አዎን» የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች የአድራሻ ለውጦች፣ የሚያገኘው ገቢና የሥራ ዓይነት፣ በየዓመቱ ለአገር ውስጥ ገቢ የሚከፈለው ሁሉ በዚያ አለ::»

ጋቨርለክ «ይህንን ሰዎች ሁሉ የተገነዘቡ አይመስለኝም» ይህ ቃለ መጠይቅ የጌታ አገልጋይና ሳይንቲስት በሆኑት በዶ/ር ጋቨርለክና የካናዳ ኮምፒዩተር ሳይንቲስት በሆኑት ዶ/ር ፊሸር መካከል የተደረገ ቃለ ምልልስ ነው::[8]



The European Economic Community's 3-story computer complex in Luxembourg ... the largest in the ... is called "The Beast." Photo courtesy of Southwest Radio Church, Oklahoma City.



በሐምሌ ወር 1979 ዓ.ም. ህይወት አልባው ወታደርና ህይወት አልባው ነፍሰ ገዳይ በሚል ርዕስ ላይ በመንተራስ በአድማስ ገጽ ላይ «ገበያ በኮምፒዩተር» በሚል ርዕስ ብርሃኑ ምትኩ አውሬው ተብሎ ስለተሰየመው ኮምፒዩተር አሠራር መጠነኛ ጽሑፍ አውጥቷል። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የዓለም የኮምፒዩተር አናሊስቶች በምድር ላይ የሚኖሩትን ሰብዓዊ ፍጥረቶች በሙሉ በቁጥር ለመሰየም ማለትም የሰውን ሁሉ ስም በቁጥር ለመተካት እቅድ እንዳላቸውና ይህንንም በዚሁ «አውሬው» ተብሎ በሚጠራው ኮምፒዩተር እንደሚሰሩት ተናግረዋል። ይህም ዘዴ የተቀየሰው በዱቤ መሸጥና መለወጥ የሚያመጣውን ችግር ለማስወገድ፤ ሁሉን በቁጥር መሰየም አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት ነው። የማንኛውም አባል አገር ግን ቁጥሩ ከሌላው መግዛትና መሸጥ መለወጥም እንዳይችል እቀባ እንደሚደረግበትም ተገልጿል።

ትኩረት ከኮምፒዩተር ጋር በተያያዘ የዛሬ 2000 ዓመት ገደማ በራዕይ 13:16-18 የተነገረውን ትንቢት-መጽሐፍ ቅዱስ ልብ እንድንል በሁኔታዎች ያስገድደናል። ይህ በሰው ፈቃድ ያልመጣው የትንቢት ቃል ዛሬ መፈጸሙ ጌታ እግዚአብሔር ምን ያህል የፍጥረታት ሁሉ ተቆጣጣሪና ትንቢያዊውን ቃል አስፈጻሚ መሆኑን ያሳየናል። ጌታ እግዚአብሔር አውሬ ይመጣል አለ ዘመኑን ስንመረምር በደጅ መሆኑን አየን፤ በ666 ቁጥር እንደሚሰራና ከመግዛትና መሸጥ ጋር እንኳን በተያያዘ ሲፈጠር ስላለው ቀውስ ተተነበየ፤ ይህም ዛሬ ሲፈጸም አየን። እንግዲህ ይህ ፍካሬ-666 በ666-ዕይታ እየተረጋገጠ ከሆነ ስለ ጌታ ምጽአትና ስለ ዓለም ፍጻሜ የተነገረውም ትንቢት እውነት መሆኑን ልንቀበልና እንደ እውነተኛ አማኝ በቅድስና ልንኖር ይጠበቅብናል። ቲቶ 2:11-13። በተጨማሪም ህይወታቸውን እንደ እግዚአብሔር ቃልና ፈቃድ የማይመሩ ሰዎች ሁሉ ቆም በማለት ሊያስተውሉና ለዘለዓለማዊው ጌታ ራሳቸውን ሊሰጡ ይገባቸዋል።

## ኮምፒዩተር እንደ እግዚአብሔር

ባህሪየ-እግዚአብሔርን (ጋድስ አትሪቢዩትስ) ስናጠና እጅግ እንደነቃለን። ምክንያቱም ፈጣሪ ሁሉን ቻይ፣ ሁሉን አዋቂ፣ በሁሉ ሥፍራ የሚገኝና ዘላለማዊ ወዘተ በመሆኑ ነው። እግዚአብሔር ልወቅ ብሎ ቤተ ሙከራ ወይም ት/ቤት አይገባም። አማካሪም አይፈልግም። በምንም ነገር አይወሰንም። ኢሳ. 40:12-18። የመጀመሪያውን የሰይጣን ሐሣብ ስንመለከት ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር ማስተካከልና መመሰል ነበር። ኢሣ. 14:13-14። ይህ መሻቱ እስከዛሬ ድረስ አለ። በዚህ ዓላማውም የዓለምን ህዝብ በተለያዩ ረቂቅ ዘዴዎች በማንበርከክና በማስገዛት ላይ ይገኛል። ዮሐ. 12:31። እንደ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይና ሁሉን አዋቂ መሆኑን በማስመሰል ለማሳየት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሁሉ እንዲሰግዱለት ሊያደርግ በመጣጣር ላይ ይገኛል። ይህንንም ዓላማውን ከግብ ለማድረስ በከፍተኛ ደረጃ ከሚጠቀምባቸው መሣሪያዎች ውስጥ አንዱ ዘመናዊው ኮምፒዩተር ነው። ስለሆነ የዚህ የኮምፒዩተር ይዘትና አሠራር ለሰይጣን መሣሪያነት ያገለግል ይሆን?[9]



## የኮምፒዩተር አሠራር

ቀደም ብሎ ከተጠቀሱት ሦስቱ የኮምፒዩተር ዓይነቶች ውስጥ ልዕለ-ኮምፒዩተር ተብሎ የሚጠራው መሣሪያ የማሰላትና ትዕዛዛትን የመፈጸም ችሎታውን ለመረዳት ለሰው አእምሮ እጅግ የሚከብድ ይመስላል። ይህ ኮምፒዩተር በሰኮንድ ውስጥ ለ250,000,000 (ሁለት መቶ ሃምሣ ሚሊየን) ትዕዛዛት ምላሽ መስጠት እንደሚችል ተነግሯል። ሁኔታውን እስቲ በመጠኑም ቢሆን በገላጭ ምሳሌ ለማየት እንሞክር።

አንድ ፋብሪካ መስራት ከጀመረ 100 ዓመት ሆኖታል እንበል። የፋብሪካው ባለቤት በየቀኑ የሚያመርታቸውን የመጻሕፍት ዓይነቶች፣ ብዛታቸውን፣ የተሸጠውን ትርፉንና ኪሣራውን ጨምሮ፤ የሞቱትንና በህይወት ያሉትን ሠራተኞች ጨምሮ፤ በየትኛው ዓመት ከፍተኛ ትርፍ እንዳገኘ ወዘተ ሁሉ በልዕለ-ኮምፒዩተሩ እያስመዘገበ ይይዛል። ፋብሪካው ሥራ የጀመረው በ1999 ዓ.ም. ቢሆንና በ2099 ዓመት ላይ በ100 ዓመት ጊዜ ውስጥ 1ኛ. ስንት ሠራተኞች (በጾታ ተለይተው) እንደተሳተፉ 2ኛ. የከሰረባቸውንና ያተረፈባቸውን ዓመታት ጭምር 3ኛ. ከየትኞቹ አገሮች ጥሬ ዕቃ እንዳስመጣ 4ኛ. በዱቤ መጻህፍት ወስደው ያልከፈሉትን 5ኛ. ኮከብ የነበሩትን አምራቾች ስም ዝርዝርና ወዘተ ለመሳሰሉት 250,000,000 ጥያቄዎች (ትዕዛዛት) መልስ እንዲሰጥ ልዕለ-ኮምፒዩተሩን ቢጠይቀው ይህንን መልስ ለመስጠት የሚወስድበት ጊዜ አንድ ሴኮንድ ነው። ይህ መሣሪያ ምን ያህል አስደናቂ መሆኑን ለመገንዘብ ያለውን ጉልበት ከሰው ጭንቅላት ጋር ማነጻጸር ነው። ከላይ በተራ ቁጥር 1 ላይ ብቻ ያለውን ትዕዛዝ ብቻ እንመልከት። በእነዚህ 100 ዓመታት፣ መጻህፍት ማምረቻ ድርጅቱ ውስጥ የተሳተፉት የወንዶችና ሴቶች ቁጥር ምን ያህል ነበር? የሚለውን ጥያቄ ለመ/ቤቱ ፀሐፊ ቢሰጥ ፀሐፊዋ ኮምፒዩተር ሳትጠቀም በአካሏ የ100 ዓመታትን ስም ዝርዝር አውጥታና በጾታ ለይታ በድጋሚ ደግሞ ቆጥራ ትክክለኛውን መልስ ከፋይሉ ፈልጋ ለማውጣት የሚወስድባትን ጊዜና ጉልበት ማስላት የሚያዳግት አይመስለኝም። ያውም ደግሞ ስህተት ሊገኝ ይችላል። ይህ ልዕለ-ኮምፒዩተር ግን በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ጥያቄዎችን ከራሱ ነፍስ መሰል አእምሮ (ቺፕ) ውስጥ ለማግኘት የወሰደበት አንድ ሴኮንድ ብቻ ነው። በዚህ ላይ አንድ ልብ ልንለው የሚገባ ነገር አለ። ይኸውም የኮምፒዩተሩን ቋንቋ ነው።

## የኮምፒዩተር ቋንቋ

የኮምፒዩተር ቋንቋ የሚሰራው በሁለት ቁጥሮች መለዋወጥ ነው። ቁጥሮቹም 0 እና 1 ናቸው።[10] ኮምፒዩተሩ በሆነው ዓይነት አገር ቋንቋ ጥያቄ ወይም ትዕዛዝ ቢቀርብለት ምላሽ የሚሰጠው ቋንቋውን በዜሮና በአንድ አናብቦ ነው። ለምሣሌ ለኮምፒዩተሩ የቀረበው ጥያቄ በፋብሪካዬ ስንት መጻህፍት አሉኝ ቢሆን ይህንን ጥያቄ ለማንበብ በ=0011 ፋ=0101 ብ=00111 ሪ=11011 ካ=10101 ዬ=11111 ወዘተ በማለት መለወጥ ይኖርበታል። በመቀጠል ትክክለኛውን መልስ ይሰጣል። (ከላይ የተሰጠው ምሳሌ አሠራሩን ለመግለጽ እንጂ ፊደሎቹ ቁጥሮቹን ይወክላሉ ማለት

እንዳይደለ ይታወቅ):: እንግዲህ በዚህ ዓይነት ሁኔታ የኮምፒዩተሩ አሠራርና ጭንቅላት ሲሰላ ከሰው አእምሮ በላይ አይሆንም? እንኳን የመልሱን መገኘት ይቅርና ፊደሎቹን ለዋውጦ በራሱ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ደረጃ እስኪደርስ የሚያልፍበትን ፍጥነትና ችሎታ ስንገነዘበው እጅግ የሚያስገርም ነው:: ኮምፒዩተሩና ሰው ያላቸው የአስተሳሰብና የችሎታ ልዩነት በጣም ከፍተኛና የተራራቀ ነው:: ይህንን መሣሪያ የሰራው ሰው ነው:: ሆኖም ይህ ሰው ያለፈበትን ሁኔታ መለስ ብሎ ማጤን ሲያቅተው ኮምፒዩተሩ ግን ያ ችሎታ አለው:: ከዚህም የተነሳ ሰዎች ኮምፒዩተርንና አብሮት ያለውን ማንነት እንደ አምላክ እንዲያዩት ግዴታ ይሆንባቸዋል:: ሰዎች ይህንን ኮምፒዩተር የሰራው በቀጥታ አምላክ እንደሆነ ያስባሉ:: ችሎታው እጅግ አስደናቂ በመሆኑ ስለሚፈሩ የ666ቱን ጌታ እንደ አምላክ ቆጥረው ሊሰግዱለት ይችላሉ::


## የኮምፒዩተር ጥቅም

የሰው ልጆች ኮምፒዩተርንና አብሮት ያለውን እንደ እግዚአብሔር እንዲያዩ ከሚያደርጋቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ ከኮምፒዩተሩ የሚገኘው ጊዜያዊ ጥቅምና ፋይዳ (ቫልዩ) ነው:: ዓለማችን በከፍተኛ የኤኬኖሚ፣ የፖለቲካና የኅብረተሰብ ቀውስ ውጥረት ውስጥ በምትገኝበት በአሁኑ ወቅት ፍቱን መፍትሔ ሰጪ አካል በታላቅ ናፍቆት በመጠበቅ ላይ ነው:: ለዚህ የዓለም ህዝብ ናፍቆት አምንታዊና አጥጋቢ ምላሽ ሊሰጥ እንደሚችል የሚታሰበው የልዕለ-ኮምፒዩተር አሠራር ነው:: በዚህ መሣሪያ አስደናቂ ስራዎችን ለመሥራት ብዙ ሳይንቲስቶች አዳዲስ ግኝቶችን በማቅረብ ላይ ይገኛሉ:: ከእነዚህም ግኝቶች ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው::[11]

ዘጋቢ ኮምፒዩተር ይህ መሣሪያ ማናቸውንም ዓይነት ድርጊቶች ካየ በኋላ ሁኔታዎቹ በሙሉ ዘግቦ የሚይዝ ነው:: መገናኛ: ይህ ኮምፒዩተር በአሁኑ ወቅት የሰው ልጅ በስልክ፣ በፋክስ፣ በሰው መላላክና በጽሑፍ የሚደረገውን የሰው አቅም የሚጠይቅ አድካሚ ሥራ በማስወገድ ራሱ ከሌላ መሣሪያ ጋር በመነጋገር ለችግሮች መፍትሔ የሚያስገኝ ነው:: 10,000,000,000 (አሥር ቢሊዮን) ስሌቶችን የሚሰራ ኮምፒዩተር በ2000 ዓመታት ማብቂያ እንደሚሰራ ይታሰባል:: አልትራ ኤል ኤስ አይ ይህ የማስታወስ ችሎታ የሌላቸውንም ሆነ ሌሎችን ሰዎች ባለማስታወስ የሚፈጠረውን ቀውስ ለማስወገድ የማስታወስ ችሎታ ያለው ነው:: በ1998 እንደሚሰራ ታስቦ ነበር:: በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ አገሮች በመከለት ላይ ያሉትን የአውሮፕላን ጠለፋና አደጋዎቹን ለመቆጣጠር ጠላፊዎቹን የሚያጋልጡ ኮምፒዩተሮች ለመሥራት ሳይንቲስቶች በሙከራ ላይ ይገኛሉ:: ቋንቋ ተርጓሚው ኮ: ቋንቋ የማያውቁ አገር ጎብኚዎች ከአገር ወደሌላ አገር ሲዘዋወሩ እንደ ሬዲዮ በኪሣቸው ይዘውት የሚሔዱትና የማናቸውንም አገር ቋንቋ በጎብኚዎቹ ቋንቋ የሚተረጉም ማይክሮ ኮ በመባል የሚታወቅ መሣሪያ ነው::[12] መምህሩ ኮ በአሁኑ ጊዜ ባህላዊ የሆነውን የማስተማሪያ ዘዴ ስናይ፣ ደብተር መግዛቱ፣ ተሸክሞ ረጅም ዓመታት ት/ቤት መመላለሱ፣ በኋላም ከፈተና መውደቁ በቤተሰብ ተባርሮ ለወንበዴነትና ሌብነት ብሎም ለድህነት መጋለጡ ሰውን እያስቀቀው ነው::



ለሆነም ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮችና ስጋቶች ለማስወገድ ዘመናዊ የሆነ ምፒዩተራዊ የመማሪያ ዘዴ ተዘጋጅቷል:: እ.ኤ.አ. በ1993 ዓ.ም. በወጣው ፖፑላር ሳይንስ መጽሔት ገጽ 58-59 ላይ የሰው አእምሮ እንዴት ዝቅተኛው የግንዛቤ ችሎታ ወደ ልዕለ ተፈጥሮአዊ የማወቅ ችሎታ ለወጥ እንደሚችል ተዘግቧል:: በተጨማሪም በጥቅምት 1994 ዓ.ም. ዚሁ መጽሔት ላይ የወጣው መጣጥፍ በኮ. ዲስክ ስለመማር ቅደም ከተል አስቀምጦ ይነበባል:: ይኸውም አንድ ሰው የፈለገውን ዓይነት ኮርስ (ትምህርት) ለመማር ቢፈልግ ትምህርቶቹ የተቀረጹበትን መማሪያ ዲስክ (ለርኒንግ ዲስክ ማሽን) ይመርጣል:: ቀጥሎ ዲስኩን በኮ. ውስጥ ያስገባል:: ትምህርቱ የሚተላለፈው በውጪአዊ ጆሮ ወይም ዓይን ሳይሆን ዲስኩን የያዘውን ማሽን አንስቶ ጭንቅላት ላይ በማጥለቅ ነው:: በመጨረሻም የፈለገው ትምህርት በአንጎሉ ውስጥ ይቀረጻል:: እውቀቱ በግለሰቡ ውስጥ ይቀመጣል ማለት ነው:: አሁን በዓለም በሚሰጠው የትምህርት ሥርዓት መሠረት አንድ ተማሪ ከ90-100% ውጤት ቢያመጣ በጣም ብሩህ አእምሮ እንዳለው ይታወቃል:: በኮ. ዲስክ በሚሰጠው ትምህርት ግን የአንድ ሰው ጭንቅላት ችሎታ ከ300% እስከ 500% እንደሚደርስ ይነገራል::[13] (ስ.ይ.)




ከዚህም የተነሳ በዚህ <u>ኮ. ዲስክ</u> ለመማር የሰው ልጅ ከፍተኛ ጉጉት አለው:: የሰው ልጅ ሁሉ በዚህ ዓይነት አመራር ውስጥ ሲገባ ለማወቅ የሚቸገር አይመስልም:: እውቀቱም ከፍተኛ ስለሚሆን ራሱን መለኮት አድርጐ ለመቁጠር ምንም ቅር አይለውም:: ሰይጣንና አውሬው ወደዚህ ደረጃ ሰዎች ሲደርሱ የቻሉት በሁለቱ አማካኝነት እንደሆነ ስለሚያስተምሩ ከኮምፒዩተር አሠራር የበለጠ እውቀትና ጥበብ ማግኛ ዘዴ ያለ መስሎ ስለማይታያቸው ሰዎች በቀላሉ አውሬውን ይቀበላሉ:: እርሱን ከተቀበሉ ደግሞ ሰይጣንን መቀበላቸው አይቀርም::

ኮምፒዩተር የሰውን አእምሮ ሲቆጣጠር

የዓለም ሰዎች ከኮ. የሚያገኙትና ተስፋ የሚያደርጉት ጥቅም ውሉን እንደሚሆን እምብዛም አይመለከቱም:: ካለፈው ልምድና የኮምፒዩተር ጥቅም በመነሳት የወደፊቱን በተወሰነ ደረጃ መተንበይና መገመት ይችሉ ይሆናል:: የኮምፒዩተርን አመጣጥ ወደኋላ መለስ ብለን ብናስብ አፈጣጠሩ ከሰው አእምሮ ጋር ተመሣሣይ ሆኖ ነው:: ዛሬ ሰው ሊሰራቸው ያልቻለውን ትላልቅ የጉልበት ሥራዎች በትንሽ የኤሌክትሪክ አሠራር ሲከውናቸው ይስተዋላል:: ወደፊት ደግሞ በኮምፒዩተር ኃይል በፍጥነትና በጥራት ከሰው በበለጠ ሁኔታ ጉዳዮችን ለማከናወን ይታሰባል:: ውጤቱም ነፍስ ማለት ኮምፒዩተር እንደሆነ ኮምፒዩተር ደግሞ ነፍስ ማለት እንደሆነ ማስረገጥ ነው:: የሰው ልጅ እስካሁን አልተሳካለትም እንጂ አስቀድሞ የተፈጠረውን ዓይነት ሰው ዛሬ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለመፍጠር በከፍተኛ ጥረት ላይ ይገኛል:: ሳይንቲስቶች እግዚአብሔር የፈጠረውን ዓይነት የሰው ሥጋ መንፈስና ነፍስ አዘጋጅቶ ሰውን ለመፍጠር ሙከራቸው እየቀጠለ ነው:: በዘመኑ የተለሩት ሮቦቶች (ተንቀሳቃሽ ሰው ሰራሽ ሰዎች) ለሳይንቲስቱ ከፍተኛ መበረታቻና ለወደፊቱ ክዋኔ ተስፋ አነሳሽ ሆነዋል:: በሮቦቶች የተጀመረው ሰው ሰራሽ እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ ሰው ወደሚሆንበት ደረጃ እንዲደርስ ይጠበቃል::

<u>ማይክሮ ቺፕ</u> ይህ መሣሪያ በጣም አነስተኛ የሆነና ከስንዴ ቅንጣት ጋር ተመሣሣይ መጠን ያለው ከዋናው ኮምፒዩተር ጋር በመገናኘት ሂሣባዊ ስሌቶችን፣ ልዩ ልዩ ግዛቤዎችንና ትዕዛዛትን ማከናወን የሚችል ረቂቅ መሣሪያ ነው:: መሣሪያው በጣም አነስተኛ ከመሆኑ የተነሳ በደም ሥሮች ውስጥ እንኳን ተቀምጦ የሰውን ህይወት ሊቆጣጠር የሚችል ነው:: ይህ መሣሪያ ሰው ውስጥ ሲቀመጥ በግለሰቡ የማሰብ ችሎታና ስሜት ላይ ተጽዕኖ በማድረስ ሊመራው እንደሚችል ተረጋግጧል::14 በተጨማሪም ይህንን መሣሪያ (ማይክሮቺፕ) በሰው አንጐል ውስጥ በማስቀመጥና ከሬዲዮ ሞገድ ጋር ግንኙነት እንዲኖረውም በማድረግ ልዩ ልዩ የአእምሮ ችግር ያለባቸውን ሰዎች መቆጣጠር እንደሚቻል ታውቋል:: ይህን አሠራር በወታደሮች እንኳን በመጠቀም ተዋጊዎቹ ለሳምንታት እንኳን ሳይደክሙ ሊዋጉ የሚችሉበትም ሁኔታ ተመቻችቷል::15 የማይክሮ ቺፑ አሠራር አስተማማኝ እንደሚሆን በእንስሳ ተሞክሮ አጥጋቢ ውጤትን አስገኝቷል:: (ሰ. ይ)






አውሬው በዚህ ዓይነት ዘዴ የሚዋጉ ወታደሮችን የሚያስማራ ከሆነ በራዕይ 13:4 ላይ እርሱንስ <u>ሊዋጋ ማን ይችላል እያሉ ሰገዱለት</u> በማለት የተነገረው ትንቢት መፈጸሙ የማያጠራጥር እውነት ይሆናል ማለት ነው:: ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ አውሬው የማይክሮቺፕን መሣሪያ ተጠቅሞ በሰው ልጆች ላይ ይህንን ያህል ተጽዕኖ የሚያደርስ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪም ክፉ መናፍስትን መጠቀሙ የማይቀር ነው:: ምክንያቱም በመጀመሪያ ለአውሬው ሥልጣን የሚሰጠው ሰይጣን በመሆኑና ሰይጣንም ደግሞ ያለ አጋንንት ተላላኪነት ሥራውን መስራት ስለማይችል ነው:: ራዕ.16:13፤ 13:3-4:: አውሬውን የቀደሙት መንግሥታት እንደማይተካከሉትና እንደሚያሸንፋቸው ይህም በገዛ ኃይሉ እንዳይደለ ተገልጿል:: ዳን. 8:24:: ይህንን የሚሰራው የወታደሮችን አእምሮ በሚቆጣጠር ኮምፒዩተራዊ ኃይል ይሆን?

<u>ዴመን ሲድ</u> በመባል የታወቀው ፊልም (ሙቪ) በማህፀን ውስጥ እንዴት የስፐርም ሴል እንደሚቀመጥና ወደ ሽልነት ተለውጦ በመጨረሻም ሰው እንደሚወለድ፤ የተወለደውም ህጻን ከዓይኑ ኮምፒዩተራዊ ጨረር አዘል ብርሃን እንደሚያወጣ ያሳያል:: ይህ ልክ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደተፀነሰ የሚመጣውም አውሬ ክርስቶሳዊ ባህሪ እንደሚኖረው ለማመልከት ነው:: አውሬው ዘመናዊውን የኮምፒዩተር መሣሪያ ብቻ እንኳን ይዞ ቢነሳና በሰዎች ግንባር፣ ድምጽና እጅ ውስጥ በማይክሮቺፕ አማካኝነት ቁጥጥር ቢያደርግ ማንም አያመልጠውም:: በዚህ ላይ ከኮምፒዩተር ችሎታ ብዙ እጥፍ የበለጠ ከእግዚአብሔር ደግሞ ብዙ እጥፍ ያነሰ ችሎታ ያላቸው አጋንንት በማሳት ሥራ ከተጨመሩበት ለምስኪኑ

የሰው ልጅ ምንኛ የከፋ ሊሆን እንደሚችል መረዳት ያሻል:: መንፈስ ቅዱስ በማርያም ማህፀን እንዳደረና ተዓምር እንደሰራ አጋንንት ሰውን የመፍጠር ሥራ ይሠራሉ ባይባልም ክርስቶስ በሌላቸው ሴቶች ውስጥ ገብተው በማህፀናቸው ባሉ ህጻናት ውስጥ በመግባት ሊወለዱ እንደሚችሉ ከታሪክ ማረጋገጥ ይቻላል:: ምክንያቱም ህጻናት በሆድ ውስጥ ሆነው ንግግር ሲያደርጉ የ4 እና 5 ዓመት ዕድሜ ኖሯቸው ለሰው መረዳት እጅግ በሚያዳግት መልኩ እስኪሰገድላቸው ተዓምራት መስራታቸው ገሃድ ስለወጣ ነው::[16] በሴቶቹ ውስጥ የተናገረው በማህፀን አካባቢ በህጻናቱ ህልውና ያደገው ክፉ መንፈስ እንጂ ህጻናቱ አይደሉም:: ለምሳሌ ያህል በኔፖል (እስያ) ከተማ በድንግላዊ አምላክ አምሳያ ዳግም ተወልዳለች (ሪኢንካርኔሽን) ተብሎ ንጉሡ ሳይቀሩ 20 ሚሊዮን ህዝብ የ4 ዓመቷን ልጅ እንደሚያመልኩ ታሪክ ዘግቧል:: ለልጅቱ ይህ ክብር ሊሰጣት የቻለው ልዩ ልዩ ፈተናዎችን አልፋ ከሰው የተፈጥሮ ችሎታ በላይ የሆነ መረጃ ስለተገኘባት ነው::[17] ይህ እንግዲህ ከተፈጥሮ እድገት ውጪ ነው:: ይህ ደግሞ ወይ ከእግዚአብሔር ካልሆነም ከሰይጣን ነው:: የልጅቷ ታሪክ ግን ከእግዚአብሔር ሊሆን አይችልም:: በውስጧ ያደረው ክፉ መንፈስ እንጂ እርሷ ደጋግማ በመወለዷ የሆነ ታሪክ አይደለም:: ይህ ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ነው:: በተመሣሣይ መልኩ የአጋንንት መንፈስ በአውሬው ሕልውናና በዘመናዊ የቴክኖሎጂ ውጤቶችም ሊሰራ እንደሚችል ልንገነዘብ ያሻል:: ሆኖም በመመርመር እንጂ ሁሉን ከአጋንንት ነው እንዳንል ጥንቃቄ ያሻል:: አጋንንት ምንም ይሁን ምን ራሳቸውን መግለጥ አይፈልጉም:: መገለጥንም አይሹም እንደአለቃቸው ሰይጣን ሌቦች ስለሆኑ ሰዎችን ማረድ ይፈልጋሉ ክፉ ማንነታቸው ከተገለጠ ብዙዎች ሊቃወሟቸው ስለሚችሉ ይሰወራሉ:: ስለሆነም በተቻለ መጠን ጠቃሚ መስለው ሰው በሚታለልላቸው መንገድ ሁሉ መቅረብ ይኖርባቸዋል:: ከዚህም በመነሳት እንዳንታለል ልንጠነቀቅ ይገባናል:: 2ኛ ቆሮ. 2:11::

ኮምፒዩተር ለሰው ልጆች ሊያስገኝ የተነሳው ከላይ የተዘረዘሩትን ፋይዳዎች ብቻ አይደለም:: ሌሎችም አሉ:: የፒ ኤች ዲ፣ ኤም ኤ እና የተለያዩ የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ ያላቸው ሰዎች በዘመናዊ ኮምፒዩተር ተፈናቅለው ሲቀሩ በአልሞት ባይ ተጋዳይ አቋም ለዝርፊያና ለወንጀለኛነት ፈተና ተጋልጠው በህብረተሰቡ ላይ ከፍተኛ አደጋ በማድረስ ላይ ይገኛሉ:: ሆኖም በኮምፒዩተር ኃይል በቁጥጥር ስር ሊውሉ ነው:: በተጨማሪም አስቀድሞ ልዩ ሙያ የነበራቸው በኋላ ግን የቀወሱና ለቤተሰብ ጉዳትና ችግር መንስኤ የሆኑትን ሁሉ የሚቆጣጠር ከአባካኝነት ወደ አምራችነት ሊለውጣቸው ኮምፒዩተር በዝግጅት ላይ ይገኛል:: የአእምሮ በሽተኞችም (አልዜመርስ) በኮምፒዩተር አሠራር 100% አምራች ሊሆኑ እንደሚችሉ ይታመናል::[17] እንግዲህ የተጣለውንና ዋጋ ያጣ የመሰለውን እንዲሁም ጉጂ የሆነውን አመጸኛ ሰው በኮምፒዩተር ማይክሮፒፕ አማካይነት ጠቃሚ ማድረግ የሚቻል ከሆነ ኮምፒዩተር ምን ያህል አክብሮት እንደሚሰጠው መረዳት አያዳግትም:: ኮምርፒዩተር በአንድ በኩል ፋይዳ ያለው ሲሆን በሌላ በኩል ጭንቅ ሳያመጣ የማይቀር እንደሆነም ይነገራል:: ኮምፒዩተር የሰውን የውስጥ ሃሣብ እንኳን ሳይቀር ሊያውቅ እንደሚችልም ይነገርለታል:: የሰውን ልብ ሰርስሮ ገብቶ ምን እንደሚያስብ




በተጨማሪም ሃሣቡን በቴፕ ቀድቶ ማለማት የሚችል ኮምፒዩተር ሄይንዝ ብሩማን የተባለ ሳይንቲስት እንደሰራ ታሪክ ይመሰክራል::18 በዚሁ ዋቢ መጽሔት ውስጥ ይህ የአእምሮን ጓዳ የሚዳስሰው ኮምፒዩተር ቀጣሪዎች የተቀጣሪዎችን ሃሣብ፣ የጦር አለቆች የወታደሮቻቸውን ሃሣብ ወኔያቸውን ሊያነብቡበት እንደሚችሉ፣ የሥነ አእምሮ ሃኪሞች የበሽተኞቻቸውን ችግር መንስኤ ሊያውቁ፣ ወዳጃሞች መሸዋወድ እንደማይችሉና አስመስሎ ማምለጥ ፈጽሞ እንዳይቻል ኃይል ሊሰጥ እንደሚችል ተጽፏል:: የሰውን አእምሮ ሙሉ በሙሉ የማወቅ ሥልጣን የሚገኘው በእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ ነው:: ታዲያ ኮምፒዩተር ይህንን መሥራት በእርግጥ ቻለ ወይስ ከበስተ ኋላው ሌላ ነገር (ገላጭ) ይኖር ይሆን? ሰውን ሁሉ በቁጥጥሩ ሥር የሚያደርግ ስለሆነ፣ ማንም ሊያመልጠው ባለመቻሉ፣ ሁሉን በ666 አሠራር ማንበርከክ እንደሚችል መታመኑ አምላክ የሚል ስም አለጥቶታል:: የሜጋ ፎርስ መጽሐፍ ደራሲ ቴክስማርስ ዴቪድ ፎስተር የተባሉት ሳይንቲስት ኮምፒዩተሩን አምላክ እንደሆነና የመጽሐፍ ቅዱስ አምላክ እንደሌለ እንዲሁም የሰውን አእምሮ አቅጣጫ ማስያዝ እስከቻለ ድረስ አምላክ ተብሎ ሊጠራ ሥልጣን እንዳለው አድርጕ እንዳስቀመጡት ገልጿል:: ስለሆነም እንደ ሳይንቲስቱ ዕይታ ነፍስ ማለት ኮምፒዩተር ነው ኮምፒዩተር ደግሞ ሰው ነው:: አምላክም ነው ማለት ይሆናል:: በሌላ ትርጉሙ ሰው አምላክ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ያመጣናል::19 እንግዲህ ጠጢብ የሆነ አንባቢ ማስተዋል ያለበት እዚህ ላይ ነው:: የሰው ልጅ ራሱን እግዚአብሔር ጋር ለማስተካከል እንዲነሳሳ የሚያደርገው ሃሣብ ሁሉ የመጣው ከዲያብሎስ ነው:: ሰይጣን ለመጀመሪያ ጊዜ የወደቀው ራሱን ከፈጣሪ ጋር ለማስተካከል ስለሞከረ ነው:: ኢሣ. 14:12-14:: ይህ ሃሣቡ 100( እስከተሸነፈበትና በዲን ወደሚቃጠል የእሣት ባህር እስከሚጣልበት ጊዜ ድረስ ይቀጥላል:: በዘፍ. 3:1-24 ሰውን ወደ አምላክነት ደረጃ ለማድረስ የወሰደውን እርምጃ ዛሬም አልተወውም:: የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አባላትን በማነሳሳት ላይ የሚገኘውም በዚሁ ሃሣብ ነው:: እነዚህ ሰዎች ሰው ራሱ አምላክ መሆኑንና ለአምላክነት የሚያበቃውን በውስጡ ያለውን እምቅ ኃይል ስላልተጠቀመበት አምላክነቱን ሊረዳው አለመቻሉን ያስተምራሉ:: ይህምጩታቸው በከፍተኛ ፍጥነት ወደ ዓለም ኅብረተሰብ በመሠራጨት ላይ ይገኛል? ስለሆነም ሰይጣን ለመጨረሻ ጊዜ መውደቂያውና ተከታዮቹንም ሁሉ ይዞ ሊያጠፋና ሊጠፋ ዘመኑ መቃረቡን እንድናስተውል ሁኔታው ያስገድደናል::

## ኮምፒዩተራዊ ኢንተርኔት (የኢንፎርሜሽን ውቅያኖስ)

በአንድ ከተማ ውስጥ 30 አነስተኛ ገበያዎች ቢኖሩና እነዚህ ገበያተኞች በጋራ ንግዳቸውን ለማካሄድ ቢስማሙ የግድ እርስ በርስ መገናኘት ይኖርባቸዋል:: ግንኙነታቸውም በሰው ተላላኪነት፣ በስልክና በኮምፒዩተር ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይችላል:: ሥራቸውም በጥራትና በፍጥነት እንዲከናወንላቸው የተሻለውን ዘዴ መምረጣቸው የታወቀ ነው:: በዚህ ዓይነት መልኩ በከተማ፣ በአገር፣ በክፍለ ሃገርና ክፍለ ዓለም ደረጃ የሚካሄደውን የኅብረተሰብ ትምህርታዊ፣ ኤኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ወዘተ ግንኙነት በፍጥነትና በጥራት ለማካሄድ አሁንም የተሻለ ዘዴ ይፈለጋል::

እስከ ዛሬ ሰዎች የተጠቀሙበት የስልክ መገናኛ ዘዴ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ቢያደርግም የሚፈለገውን ያህል አጥጋቢ አልነበረም:: ስለሆነም የኢንተርኔት አገልግሎት መምጣት እጅግ አስፈላጊ ሆኗል:: ለመሆኑ ኢንተርኔት ምንድነው? ምንስ ይጠቅማል?

ኢንተርኔት ኮምፒዩተሮች በስልክ መስመር አማካይነት እርስ በርስ ተገናኝተው የፈጠሩት የኢንፎርሜሽን መረብ ወይም ኔትወርክ ከመሆኑም በላይ እንደ ትልቅ ዓሣ ማጥመጃ መረብ በዓለም ላይ ተንሰራፍቶ የተዘረጋ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ነው::[20] የኢንተርኔት ተጠቃሚ ከአካባቢ የመረጃ ምንጭነት ባሻገር በየትኛውም የዓለም ክፍል ከሚገኙ አብያተ መጻህፍት፣ የትምህርት ተቋማት ሙዚየሞች ወዘተ መረጃ መቀሰም ይችላል:: አንድን የኮምፒዩተር ቁልፍ በመጫን አንድ ተማሪ ማወቅ ስለሚፈልገው እውቀት ከታወቁ የዓለም ዩኒቨርስቲዎች፣ ፕሮፌሰሮችና ዶክተሮች፣ መጻህፍትና ምሁራን ጋር በሴኮንድ ውስጥ መገናኘት ይችላል:: በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ከ40 ሚሊዮን በላይ ሰዎች የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ናቸው:: ጠቅለል ባለ መልኩ ኮምፒዩተራዊ ኢንተርኔት ማለት ለመማርና ለማስተማር ትዕግስቱና ችሎታው፣ ሂሣቡን ለመክፈል ደግሞ ሃብቱ ያላቸው ሰዎች ማንኛውንም ዓይነት መረጃ የሚቀዱበት የኢንፎርሜሽን ውቅያኖስ ነው:: ዶ/ር ዌቨር ወደፊት የሚመጣው አውሬ ኢንተርኔትን በደንብ እንደሚጠቀምበትና ምናልባትም የአውሬው ምስል ሊሆን እንደሚችል ይናገራሉ:: በተጨማሪም የኢንተርኔት ነፍስ (ውስጣዊ ክፍል) ያለ ጥርጥር ሰዎች ሁሉ ባለ 666ቱን ሐሰተኛ ክርስቶስ እንዲያመልኩ የሚመራ የአውሬው ምስል ሊሆን እንደሚችልም ይናገራሉ::[21] (ሲ.ይ.)




ህጻናት ገና ሲወለዱ በቀኝ ቁጥር ስለሚደረግባቸው በማንም እንደማይሰረቁ ይረጋገጣል



## የ"COMPUTER" ስሌት

ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው በብሩሴልስ የተሰራውን ማስተር ኮምፒዩተር የገበያ አናሊስቶቹ (እንደ ዶ/ር ሃንሪክ ኤልድማን) ዘ ቢስት ወይም አውሬው ብለው እንደ ሰየሙት ተገንዝበናል:: ከአንዳንድ በራሪ ረቂቅ ንባባት (ማኑስክሪፕት) እንደሚስተዋለው ከሆነ ይህንን ኮምፒዩተር ዓአውሬውን ብሎ ለመጥራትም ሆነ ላለመጥራት የንግድ ጠበብቱን ብዙ እንዳከራከረ ይነበባል:: ዘ ቢስት (አውሬው) ተብሎ እንዳይጠራና የመጽሐፍ ቅዱሱ ትንቢት እንዳይፈጸምም ለመከላከል ሙከራ እንደተደረገ ተሰምቷል:: ለመሆኑ ይህን ዓአውሬን የሚለውን ቃልና ዓCOMPUTERንን ውስጥ ለውስጥ ሊያገናኛቸው የሚችል ፍቺ ይኖር ይሆን?

ከራዕይ 13:1 ጀምሮ ስናነብብ ዓአውሬን የተሰኘውን ቃል በአንድ ምዕራፍ ውስጥ ብቻ 16 ጊዜ ተደጋግሞ ተጽፏል:: ይህ አውሬ የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ ቴሪዮን ተብሎ ይጠራል:: በዕብራይስጥ አልፋቤት (የፊደሎች ቅደም ተከተላዊ አቀማመጥ) ቴሪዮን ቀጥሎ በሚዘረዘረው የኮምፒዩተር ስሌት መሠረት ሲሰላ 666 ይመጣል:: ስለዚህ አውሬ (ቴሪዮን) ማለት 666 ማለት ይሆናል::

የኮምፒዩተርንም ስሌት በተመለከተ ቀጥሎ በተዘረዘረው መሠረት ቁጥሮቹን ስንደምራቸው 666ትን ይሰጠናል::

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| A-6 | G-42 | M-78 | S-114 | |
| B-12 | H-48 | N-84 | T-120 | |
| C-18 | I-54 | O-90 | U-126 | Y-150 |
| D-24 | J-60 | P-96 | V-132 | Z-156 |
| E-30 | K-66 | Q-102 | W-138 | |
| F-36 | l-72 | R-108 | X-144 | |

C-18 O=90 M=78 P=96 U=126 T=120 E=30 R=108=666


የዛሬ 2000 ዓመት አካባቢ ሐዋርያው ዮሐንስ የስሙ ቁጥር 666 የሚባል አውሬ እንደሚመጣ ተገልጦለት ተንብዮአል:: ያ ትንቢት ሳይወድቅ ዛሬ የእንግሊዝኛ ፊደሎች ተፈጥረውና በ"COMPUTER" መልክ ተቀምጠው ከላይ በተዘረዘረው መሠረት ተደምረው 666 ቁጥርን የመስጠታቸው ውጤት አጋጣሚ ሊሆን ይችላል? ፈጽሞ የማይታሰብ ነው:: ስለሆነም የትንቢቱ ባለቤት ሁኔታዎችን እየተቆጣጠረ ተፈጻሚነትን እንዲያገኙ ለማድረግ በቁጥጥርና በመምራት ላይ መሆኑን ያሳየናል:: ዘመኑን መርምሮ ለሚያስተውልና ወደ እግዚአብሔር ለሚጠጋ ሁሉ እንግዲህ ጥቅሙ እዚህ ላይ ነው:: ጌታም እናንተ በቃሌ ብትኖሩ

በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፣ እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል ያለው ቃል እውነተኛ የሚሆነው እዚህ ላይ ነው:: ማለትም የትንቢቱን ቃል መርምሮ በእውነቱ መጽናት:: የ666 ትንቢት እርግጠኛ መሆኑን የሚያይ ሁሉ ሌሎቹን የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች እንዴት ሊንቃቸው ይችላል? የሚንቃቸው ከሆነ መንፈሳዊ ባርነት ውስጥ መኖሩን ያሳያል:: ነጻ የሚያወጣውን ፍጹሙን ሕግ ተመልክቶ የሚጸናበት እንጂ ሰምቶ የሚረሳ ያልሆነ በሥራው የተባረከ ይሆናል የተባለውም እውነት ይህ ነው:: ያዕ.1:25:: ነጻ መውጣት ማለት በተረዱት እውነት ጸንቶ መኖር ነው::

ታዲያ አውሬውና ኮምፒዩተሩ እንዴት ይገናኛሉ? ሰዎች ለምን ኮምፒዩተሩን አውሬው ብለው ሰየሙት? አጋጣሚ ይሆን? ፍጹም ሊሆን አይችልም:: አውሬው የሚለው የዕብራይስጡ ቃል ትንታኔ 666ትን፤ ኮምፒዩተር የሚለው የእንግሊዝኛው ቃል ትንታኔ 666ትን ከሰጠ የአውሬው የስሙ ቁጥር 666 ከሆነ ከኮምፒዩተሩ ጋር ከፍተኛና የተጣጣመ ግንኙነት እንዳለው የማይታበል ሐቅ ነው:: ምክንያቱም ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ዛሬ በዓለማችን ላይ ያሉት ትናንሽና ታላላቅ ኮምፒዩተሮች በጣም የተወሳሰቡና የተሳሰሩ ከመሆናቸው የተነሳ ለአውሬው የሚያስገኙት ኃይል እንደአምላክ የሚሰገድለት ሆኖ እንዲገዛ ስለሚያደርጉት ነው:: ሆኖም ሚስጢራዊ ነገሮች እንደተጠበቁ ሆነው ነው::

ቀደም ብሎ የልዕለ-ኮምፒዩተር የማስላት ችሎታ ተተንትኗል:: ይህም በሰኮንድ ውስጥ እስከ 250000000 ትዕዛዛትን መፈጸም ነው:: ይህ አሠራር ከሰው አእምሮ በላይ ነው:: ሰዎች ይህ ችሎታ ያለውን ኮምፒዩተር የሰራው ሰው ማን እንደሆነ ፈልጉ በማግኘት የዚህ ዓይነት ኮምፒዩተራዊ ጭንቅላት ማግኘት ስለሚችሉበት ሁኔታ ለማወቅ መጣራቸውና ለመሆንም መፈለጋቸው ፈጽሞ የማይቀር ነው:: በዚህ ጊዜ ነው የሰው ልጆች ወደ አውሬው ቁጥር በጥድፊያ የሚሮጡት (ስ. ይ.):: ምክንያቱም ሰው ጥቅምን ስለሚፈልግ ነው:: መጽሐፍ ቅዱሳችንን ስናጠና አውሬው እንቆቅልሽ ፈቺ ሆኖ ለዓለም ህዝብ እንደሚቀርብ ይናገራል:: ዳን. 8:23:: ታዲያ ሰው ብዙ ወራት የሚወስድበትን ሥራ በሰኮንዶች ውስጥ በጥራትና በፍጥነት የሚሠራለትንና የሚጠቅመውን ነገር ካገኘ እንዴት ወደ ኋላ ይመለሳል:: በልቼ ልሙት በማለት ራሱን ይሰጣል እንጂ:: እንግዲህ ባለ አእምሮ መሆን የሚያስፈልገው እዚህ ላይ ነው:: ራዕይ 13:18::







በጨረር የሚነበበው 666
በሰዎች ግንባር ላይ




he "666 System" is here

ግንባራቸው ላይ 666 የተጻፈባቸው ሰዎች




Triple Identification System



ከዋናው ኮምፒዩተር ጋር በመያያዝ ሰዎች የሚታወቁባቸው 3 ዘዴዎች (ግንባር ላይ፣ እጅ ላይና በድምጽ ውስጥ)

እግዚአብሔር በተለያዩ ዘመናት ብዙ ህልውናዎችን ተጠቅሟል:: ከተጠቀመባቸውም ውስጥ ህያዋን የሆኑ መላዕክት፣ ሰዎችና እንስሳት፣ ግዑዛን ውኖች፣ በራሪ ወፎች፣ በቤተመቅደስ በሚያገለግሉ ግዑዝ በሆኑ ቱሚምና ኡሪም:በዳካዎች፣ ቢላዎች፣ መቅደስ (ታቦት) ወዘተ የመሳሰሉት ይገኛሉ:: ዛሬም ቢሆን ጌታ እግዚአብሔር መኪኖችን፣ ሳተላይቶችን፣ ኮምፒዩተሮችን፣ ወረቀቶችን ወዘተ ይጠቀማል:: እርሱ በሰው ባህል ቋንቋና ፖለቲካም ይጠቀማል:: ሰው ለሚገለገልበት ቁሳዊም ሆነ መንፈሳዊ ጥቅማ ጥቅሞች መሠረቱ እግዚአብሔር ነው:: ሰዎች በጉውን በማጣመም ለክፋት ተጠቀሙበት እንጂ መልካም በሆኑ ነገሮች ሁሉ እንዲጠቀሙ ፈቃድ የሰጠ እግዚአብሔር ነው:: ሰይጣንም በማታለልና በማጭበርበር ነገሮችን ለራሱ ክብር በመጠምዘዝ ይጠቀምባቸዋል:: የኮምፒዩተር መሣሪያ አሠራር ሙሉ በሙሉ ግልጥ ሆኖ ባይታየንም እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በሰጠው የእውቀት ፀጋ እንደተሠራ እናምናለን:: ዳን. 12:4:: ይህንኑ መሣሪያ ደግሞ ክፉው አውሬ ሰዎችን ሊያስትበት እንደሚችል ልናስብ እንችላለን:: ሰው የሚጠቀምበት ቁሳዊ ነገር ሁሉ ክብርን ለእግዚአብሔር ማስገኘት ይኖርበታል:: ሰውም ያለው እውቀት ሁሉ እግዚአብሔር ከሰጠው ቁሳዊና ነፍሳዊ መጠቀሚያ ያገኘው ነው:: ስለሆነም በራሴ ጉልበት የሰራሁት ነው ቢል ልክ ናቡከደነጾር እንደሆነበት የያዘውን ሁሉ በውርደት መልቀቁ የማይቀር ነው:: ዳን. 4:28-33:: የወደፊቱም የአውሬው ዕድል ፊንታ ይሔው ነው:: ራዕይ 19:19-20::

## ሰይጣንና ኮምፒዩተር

ኮምፒዩተር በአሁኑ ጊዜ ለዓለም ኅብረተሰብ እየሰጠ ካለው ግልጋሎት አኳያ ከሰይጣን ጋር አያይዞ ማቅረብ እጅግ ከባድ ሊሆን ይችላል:: ሆኖም ለምርምርና ለህይወት የሚባለውን ማድመጡ የሚታየውን ማንበቡ ጠቃሚ ስለሚሆን ልብን ሰፋ ማድረጉ መልካም ነው:: ቀደም ብሎ ክህደት በሚለው የክፍል ሁለት ጽሑፍ ውስጥ ስለ ሰይጣንና የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ግንኙነት ጥቂት ነገር መጠቀሱን እንገነዘባለን:: ሰይጣን ታማኝና ውብ ፍጡር መሆኑን የተረዱ መስሏቸው ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ለሰይጣን የሸጡ ሰዎች ሞልተዋል:: ከዚህም የተነሳ የሰይጣን ሙሉ ባርኮት፣ ንፁህ ክፋት፣ እኛ አምላኮቻችሁ ነን፣ የገሃነም አውራ ጉዳና፣ አውሬው 666፣ የሰይጣን ኮከብ፣ በሰይጣን አገልግሎት ላይ ያሉ ነገሥታት፣ የወሲብ ሞራል አጥፊዎች፣ ስሜ ሌጊዎን ነው፣ ኢየሱስን ካደው እርሱ አሳች ነው፣ ሞትን ማምለክ ወዘተ ለተሰኙ ልዩ ልዩ ሃሣቦችና ልምምዶች ራሳቸውን በመስጠት ሰይጣንን በማምለክ ላይ ይገኛሉ::[23] (ሲ.ይ.) አውሬው ስሙ 666 ከሆነ የዚህ ሐሰተኛ ሥልጣን ሰጪ ደግመ ዘንዶው (የቀደመው እባብ) ከሆነ ሰይጣን ኮምፒዩተርን በደንብ ይጠቀምበታል ማለት ነው:: ራዕይ 13:14-16::






JUDAS PRIEST ROCK GROUP . . . accused in suicide case.
ሰዎችን ወደ ተሻለው ዓለም ለማሸጋገር
የተሻለው ዘዴ ራስን ማጥፋት ነው በማለት
ሲያደፋፍሩ የተከሰሱት የሮክ ሙዚቃ አባላት

በአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ እምነት መሠረት ሰይጣን ማለት መልካም እንጂ ክፉ እንዳይደለ እንገነዘባለን:: የሰይጣንን ማንነት ከኮምፒዩተር ጋር ለማያያዝ የተለያዩ እርምጃዎች በመወሰድ ላይ ይገኛሉ:: ከእነዚህም ውስጥ የመጀመሪያው ሰይጣንን የኮምፒዩተርን እንቀሳቃሽ ሠራተኞች የሚረዳ ወይም የሚቆጣጠር አድርጐ ሥልጣን መስጠት ይሆናል:: ይህም ማለት በኮምፒዩተሮች አሠራር ወይም ሠራተኞች ላይ ችግር ከመፈጠሩ በፊት መመሪያ የሚሰጥ ማለት ነው:: ይህንንም ሰይጣን የተሰኘውን የኮምፒዩተር አሠራር ለመጀመሪያ ጊዜ የፈለሰፈው ዳን ፋርመር በመባል የታወቀው ሰው ነው:: (ሲ.ይ.)

በ ወደ ተሻለው ዓለም መሸጋገሪያ ብቸኛ ዘዴ «ራስን ማጥፋት ነው» አሁኑኑ አድርጉት ባዩ የሮክ ሙዚቃ ተጫዋች ኦዚ ኦስቦርን



# *U.S.A.*

## Devilish Test of Security

Satan is coming to the Internet—and may create havoc on computer networks around the world.

The devilish software, released April 5, searches for hidden flaws in computer networks that make them vulnerable to intruders. The tool could be used by pranksters or serious espionage agents to penetrate the computer networks of large corporations, small business—or even military and government installations.


That is not its intended use. Satan was designed to help computer network administrators plug security holes before the hackers find them.

But intruders will find Satan an easy to-use, automated and powerful tool




Pictured is Dan Farmer, author of "Satan" computer security program.

The coming war:
Computer vs. computer.
ኮምፒዩተራዊ የእርስ በርስ ጦርነት




Supercomputer Progress

በሁለተኛ ደረጃ ሰይጣን የመላዕክት አለቃ ሆኖ ሲኖር ሳለ ብሎ መናገር ፍጹም ስህተት መሆኑን የማይቀበሉና የሰው ልጆች ሁሉ ነፍስ ጥፋት ተጠያቂው ሰይጣን አለመሆኑን በአጽንኦት የሚናገሩ ሰዎች (የሰይጣን ወኪሎች) መነሳታቸው ነው። እነዚህ ወኪሎች የተሸጠ ዕቃ ፈጽሞ እንደማይመለስና በገዢው እጅ ሲገባ ሙሉ ጥንቃቄ እንደሚያደርግለት በማስተማር ሰዎች ሁሉ ሙሉ በሙሉ ሊጠነቀቁላቸው ላማንችለው ሰይጣን ራሳቸውን እንዲሸጡ ያደፋፍራሉ።







ሰውን አእምሮ የሚያነበው ኮምፒዩተር



Surveillance: When will man's thoughts be controlled?









ፖል አንባር

## የአእምሮ ጎዳና በኮምፒዩተር!

«የሰው ልቡን የወፍ ወንዱን የሚያውቅ የለም» ሲባል ነበር የምንሰማው። ስራችን ብለው የተጨነቁበት ተመራማሪዎች ግን ከአመታት ጥናታና ዘገባ በኋላ በእይታ ብቻ የወፍ ወንዱን ከሴቷ መለየት ከቻሉ ሰንብተዋል። ይሆናል ተብሎ የማይገመተው የሰው ልብን ሰርስሮ ገብቶ ምን እንደሚያስብ መገንዘብ ነበር። አሁን ግን በሳይንስ እድገት እየተበረገደ ነው።



ሳይንቲስት ሄይንዝ ብሩማን

## 3.4 666 የታየባቸው ዕቃዎችና ሁኔታዎች

ቀደም ባሉት የተለያዩ ርዕሶች ለየት ባለ መልኩ የ666 በዓለም ላይ ያለው ወቅታዊ እንቅስቃሴ ምን እንደሚመስል በጥቂቱ ተመልክተናል:: በዚህ ንዑስ ርዕስ ደግሞ ዘርዘር ባለ መልኩ የ666 ሂደት ምን እንደሚመስል እናያለን:: በ2ኛ ተሰ. 2:6-7 የአመጽ ሚስጢር አሁን ይሠራልና ሲል የአውሬው አሠራር ድብቅ መሆኑን በግልጽ ያሳየናል:: ድብቅ የሆነበትም ምክንያት የአመጽ ሥራው ከታወቀበት በእውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን እንዳይፈርስበት ነው:: ኤፌ. 3:10:: ሰይጣንና አውሬው ሥራቸውን በሚስጢር ከሚያካሂዱባቸው አበይት መሣሪያዎች ውስጥ ዋነኛው የቁጥር 666 ስርጭትና በዓለም ሰዎች ዘንድ እውቅናና ተቀባይነትን ማግኘት ነው:: እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጉም 666 ታየ ማለት ከበስተኋላው አውሬው በዓለም ለመታየት በዝግጅት ላይ ነው ማለት ነው:: ክርስቶስ ኢየሱስ መንፈሳዊ ጽልመት በምድሪቱ ላይ ለ400 ዓመታት ወድቆ በነበረበት ጊዜ ድሬን ይዞ ብቅ እንዳለ ሁሉ አውሬውም ዓለም ግራ በተጋባችበት ወቅት አንድ ጊዜያዊ በረከት ይዞላት እንደሚመጣ ይታሰባል:: የዓለም ህዝብ ጉጉት ከፍተኛ ነውና:: በአሁኑ ጊዜ የ666 አሠራር ከኮምፒዩተር ጋር የተያያዘ ነው:: የዓለምም ህዝብ ስለዚህ ቁጥር ያውቃል:: የቁጥሩ ስም ደግሞ ኮምፒዩተር ከተባለው ስም ጋር የተያያዘ ስለሆነ በአሁኑ ጊዜ የሚታወቀው በመልካም ነው:: 666ትን አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር ማንም በክፉ አይጠረጥርም:: ደግሞም አብዛኛው የዓለም ህዝብ እውነትንም ሆነ ውሸትን እንዳያስተውል አእምሮው ስለተያዘ ከነገሮች በስተኋላ ያለውን ዓላማ ለማየት ይቸግረዋል:: 2ኛቆሮ. 4:4:: እንግዲህ አውሬው ራሱን ከመግለጡ በፊት በተለያዩ ምልክቶችና በ666 ራሱን በተባባሪዎቹ በኩል ይገልጻል::

### የ666 ስርጭት

በአሁኑ ጊዜ 666 ቁጥር በብዙ ዓይነት ዕቃዎችና ሁኔታዎች ለዓለም ህዝብ በመታየት ላይ ይገኛል:: ከታየባቸውም ነገሮች ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው::

- በጃኬቶች(ራሺያ)
- በሳሙና
- በአንሶላ
- በብርድ ልብሶች
- በገጠር ውሃ መቆፈሪያ ሞተር
- በቴፕሪኮርደር
- በመኪና ዓይነ
- በቴፕ አልማዝ (ጃፓን)
- በደረሰኞች (አሜሪካ)
- በምርጫ አገልግሎት መስጫ ካርዶች
- በላጺስ
- በልጆች አልጀብራ መጻህፍት
- በራንግለር ቫጅ (ታግ)
- በባትሪ ድንጋይ
- በባትሪ ድንጋይ ቀፎ
- በፒጃማ
- በትራክት (ሱን)
- በትራክተር (አሜሪካ)
- በቦርሳና በሱሪ ዚፕ
- በስፖርት ልብሶች



- በFFF የእግሊዝኛ ፊደል 6ኛው ቁጥር ኤፍ ነው:: 3ቱ ሲከታተሉ 666 ነው የማይሆንም አለ:: (ሲ.ይ.)
- በፎጣ
- ኦሜን ቪዲዮ ካሴት (ፊልም)
- በሎተሪ ቲኬቶች (እስራኤል)
- በሽሚዞች (ቻይና) (ሲ.ይ.)
- በመኪና ታርጋ (ሲ.ይ.)
- በጠረጴዛ ልብስ
- በቁልፎች
- በጫማዎች (ጣሊያን)
- በሞዴል 304 ሱፐር ማርኬት ኮምፒዩተር
- በቴሌፎን ኦኘሬተሮች ስልክ
- በአዳዲስ ጫማ
- በሰዓት
- በቦርሳዎች
- በእጅ ጓንቶች
- በከሰል ማዕድን ማውጫ መሣሪያ (ቪርጂኒያ)
- በሻይ ማሸጊያ ካርቶን

ይህ ፊልም በቪዲዮ የሚታይ ሆኖ በሆሊውድ ፊልም አሳታሚ ድርጅት የሚዘጋጅና ለ6 ሰዓታት የሚታይ ነው:: በፊልሙ ውስጥ ስለ ዓለም መጨረሻው ጦርነትና ስለ አምባገነኑ መሪ ተርኮ ትርኢቱን በ666 ይዘጋል::

- <u>በእርሳሶች</u>: በ1968 ዓ.ም. ከምሥራቅ ጀርመን ሲዳር ከተባለ እንጨት ተሰርተው ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ እርሳሶች በሙሉ 666 ተጽፎባቸው ነበር:: በቻይና እርሳሶችም ላይ ታይቷል::

- <u>ተሽከርካሪ መኪኖች</u>: ንብረትነታቸው የአረብ የሆኑ ተሽከርካሪ መኪኖች በ1973 ዓ.ም. በኢየሩሳሌም ከተማ በታዩበት ወቅት ቀዳሚ የታርጋ ቁጥራቸው 666 ነበር::


- <u>በመጽሔቶች</u>: ቻይና ስፖርት በመባል ይታወቅ በነበረው መጽሔት 666 ቁጥር በጨረር በተከበበ ነጸብራቅ ተጽፎ ታይቷል::

- <u>በመርከብ</u>: እ.ኤ.አ. በ1975 ዓ.ም. የስዊዝ ቦይ ሲከፈት ለመጀመሪያ ጊዜ ያለፈችው መርከብ የጎን ቁጥሯ 666 ነበር:: (ሲ.ይ.)

- <u>አውቶሞቢሎች</u>: እ.ኤ.አ. በ1979 ዓ.ም. በፍሊንት (ሚቺገን) የተመረቱ አውቶሞቢሎች የመለያ ቁጥራቸው 666 ነበር::

- <u>በማስመሪያዎች</u>: በ1979 ዓ.ም. በአሜሪካ ይመረቱ በነበሩ ላይ 666 ታይቶባቸዋል::


ኮ አይ ኑር ስፖጀኔ ኮሽፕሩሚስሎሽ ዛሽዲ የሚታወቅ በቼኮስሎቫኪያ ሕግ መሠረት የተቋቋመና ፣ ፐራግ ቼኮስሎቫኮ የሆነ ኩባንያ ከዚህ በታችየተመለከተው በኢትዮጵያ ወ... ብቸኛ ባለቤትና ተጠቃሚ ነው።



- በወዛደር እጅ ውስጥ (በግሪክ) በ1980ዎቹ መጀመሪያ ላይ በኮምፒዩተር ክፍል ይሰራ የነበረው ሰው በእጁ ውስጥ 666 ነበር:: ይህ ሰው የጌታን እራት ሊወስድ ወደሚያመልክበት ቤተ ክርስቲያን በሔደ ጊዜ የጌታን እራት ሊወስድ ሲሞክር እንዳቃተውና ቁጥሩ እንዳለበት ታውቆ ሥርዓቱን መውሰድ እንደማይችል ተነግሮት እንደነበረ ይሰማል::
- በመኪና ቲኬት(ግሪክ) ይህ ቲኬት ሌሎች ከሚሸጡበት ዋጋ በጣም ዝቅተኛ የሆነና ሰዎችንም እንደሚስብ ይነገራል:: ሆኖም በጣም ጠንካራ አቋም ያላቸው ክርስቲያኖች ቲኬቱን እንደተቃወሙ ናዘኢኮኖሚስትን የተሰኘው መጽሔት ገልጿል::
- በባንክ ካርድ (አውስትራሊያ)
- አዝ ሌ ቲፍ ኢን ዘ ናይት ይህ የቪዲዮ ፊልም ሲሆን 666 ቁጥር ሊታተምባቸው ሲሉ ሰዎች የሚደርስባቸውን ስቃይ ያሳያል::
- በሽምቅ ተዋጊዎች ስም በፓሪስ የሚገኙ ሽምቅ ተዋጊዎች ስማቸውን ሲጠየቁ 666 እንደሆነ መግለጻቸው ተሰምቷል::
- በሚስጢር የጦር ኃይል የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ካርተር የሚስጢር የፀጥታ ኃይላቸው 666ን ይጠቀሙ ነበር::
- በአስቂኝ ስዕሎች (በካርቱን) በተደረገው የዱላ ቅብብሎሽ ጨዋታ ከብዙ ሩጫ በኋላ በአሸናፊነት የገባው ስፖርተኛ መለያ ቁጥሩ 666 ነበር:: ይህም የወደፊቱ ህብረተሰብ መመሪያ ቁጥር 666 መሆኑን ለማሳየት ነው::
- ኤፍ ደብልዩ ኤስ (F.W.S) ይህ በክብ ውስጥ 666ትን ጽፎ በሦስቱ የቁጥሩ ዜሮዎች ውስጥ ሦስቱ ፊደሎች ተጽፈዋል:: ይህም የወደፊቱ ዓለም (ዘ ኒው ወርልድ ሲስተም) መመሪያ 666 መሆኑን ለማመልከት ነው:: (ሽፋን ስእል)
- ዓለም አቀፍ የምርት መለያ ኮድ(U.P.C) ይህ ኮድ በሚመረቱ ዕቃዎች ሁሉ ላይ የሚደረግ ነው:: ወደታች የተሰመሩ መስመሮችንና ከሥራቸው የተጻፉ ቁጥሮችን ያመለክታል:: የተጻፉት ቁጥሮች ዕቃው የተመረተበትን ቦታ (ቀበሌ፣ ክፍተኛ፣ ክ.ሃገር)በተጨማሪም የማንኛውም ዕቃ ዓለም አቀፋዊ መለያ ቁጥር የሆነውን 666 ያመለክታሉ:: በዓለም ያሉ ዕቃዎች በሙሉ በቁጥር በፍጹም አይመሳሰሉም:: እያንዳንዱ ዕቃ የራሱ ኮድ አለው:: ለሰውም እንዲሁ ዓይነት መለያ ቁጥር ይኖረዋል:: (ሽፋን ስእል ይ)



- በኮህ አይ ኑር፣ ናሮድኒ ፖድኒክ ኩባንያ አርማ
አርማውን (ስዩ) ኩባንያው 666 ቁጥርን ለጠፍጣፋ ብረታ ብረቶች፣ ለአሉሚኒየምና ለስሉይድ ዕቃዎች፣ ለትናንሽ ሲንቴቲክ፣ ለእንጨትና ለቀንድ ዕቃዎች፣ ለኤሌክትሪክ ለመርፌ፣ ለጫማ ማሠሪያ፣ ለባልና ሚስት ቁልፎች፣ ለቀበቶዎች፣ ለቤትና ለኮርቻ፣ ለልብስ ሰፊዎች፣ ለማጥበቂያ መሣሪያዎች፣ ለቢሮና ለጽሕፈት ለሚያገለግሉ፣ ለስዕል ስፒሎች፣ ለኮት መስቀያ፣ ለጃንጥላ፣ ለሰንሰለት፣ ወዙተ ለሚሰጡ ዕቃዎች፣ ለሲጋራ ማጨሻና ለሌሎችም ዕቃዎች የ666ትን አርማ እንደሚጠቀም ይገልጻል::



በስዊዝ ካናል የታየው የግብጽ የጦር መርከብ (ቀስቱ ያለበት 666 ነው)

d. June 5, 1975 (AP) "Surrounded by a swarm of small craft, the Egyptian Navy Destroyer er 6,' with President Sadat aboard, enters the Suez Canal at Port Said and thus re-opens the canal ommercial shipping. . . ." (AP Wirephoto) On the bow was the nnmber 666.

- በሐሰተኛው ነቢይ ካባ:

በሶርያ ምድረበዳ ዘመናዊ በሆነ ቤተ መንግሥት ውስጥ የሚኖር ልዑል አለ ይባላል:: ይህ ሰው በሚሰራቸው ተዓምራዊ ነገሮች ዝነኛ ና እውቅ በመሆኑ ከፊሎቹ ክርስቲያኖች የሆኑ 3 ሳይንቲስቶች ሊጎበኙት ይሔዳሉ:: ግለሰቡ አንዳንድ የማሳሳቻ ተዓምራትን ካደረገ በኋላ ራሱን ከመጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ ጋር በማስተካከል ወደፊት ለሚመጣው የዓለም መሢህ መንገድ ጠራጊ መሆኑን ገልጾላቸዋል:: በተጨማሪም ከእርሱ በኋላ የሚመጣው መሢሁ ከእርሱ በጣም የከበረና የጫማውን ጠፍር እንኳን ሊፈታ እንደማይችል አስታውቋቸዋል:: በመጨረሻም ካባውን ገለጥ ሲያደርግ በውስጥ በኩል 666 ተጽፎ ታይቷል::

## በኃይማኖተኞቹ ስብሰባና ውሣኔ

በክርስትና ጥላ ሥር ከተሰባሰቡት ኃይማኖታዊ ድርጅቶች የተወሰኑት በግንቦት ወር 1985 ዓ.ም. ባደረጉት ስብሰባ 2ኛ ቆሮ. 6:14-15 እና 1ኛ ቆሮ. 6:5-16 ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲወጣ በመስማማት በነሐሴ ወር ከ666 ጋር በተያያዘ የሚከተለውን የጨው ቃል ኪዳን በማድረግ ይወስናሉ:: ውሣኔያቸውም:

- የ666 ምልክት የሌለበት ደብዳቤ ወደ ፖስታ ቤት ሊላክ እንደማይችል::
- ማንም የ666 ቁጥር ምልክት የሌለው በቢሮ ሥራቸው ተሳታፊ እንደማይሆን
- ወላጆቹ 666ን ካልተቀበሉ ልጆቻቸው በየትኛውም ት/ቤት ሊማሩ እንደማይሉ
- 666 ያላቸው ብቻ የጦር መሣሪያ በመግዛትና በመሸጥ ሊጠቀሙ እንደሚችሉ
- 666ን ያልተቀበለ ማንም ሰው መሬት አልምቶ ተጠቃሚ ሊሆን እንደማይችል::
- 666 የሌለው ማንም ሰው በባንክ ገንዘብ ማስቀመጥም ሆነ ማውጣት እንደማይችል
- ቁጥሩ የሌለው በትራንስፖርት የመጓጓዝ መብት እንደማይኖረው
- ማንኛውም ተሽከርካሪ 666ትን በሚያንቀሳቅሰው ድርጅት ቁጥጥር ሥር መዋል እንዳለበት
- ያለ 666 ማንኛውም እሽግ ዕቃ ወደ ተለያዩ የዓለም ክፍሎች እንዳይንቀሳቀስ
- ዓለም በሙሉ አንድ ዓይነት የገንዘብ ምንዛሪ እንዲኖረው
- የዓለም ቤተ ክርስቲያናት በሙሉ ፀሎታቸው አንድ ቀን እንዲሆን የመሳሰሉት ናቸው
- የድርጅቱ መሪ ከ666 አሠራር ጋር በተያያዘ ድህነት ፈጽሞ እንደሚጠፋና ሰው ሁሉ እኩል እንደሚሆን፣ ያለ 666 መመሪያ እንስሳትን ማደን፣ ወፎችንና አሦችን ሁሉ በማጥመድ ከባህርና ከወንዞች ማናቸውንም ዓይነት ጥቅማ ጥቅሞች የማግኘት ሥልጣን እንደሚከለከል በዕለቱ ተናግረዋል:: በመጨረሻም መሪው ያለ 666 ማንም በድርጅቱ ያለ ሠራተኛ እምነት ሊጣልበት እንደማይችል፣ ቁጥሩ ካለው ግን ከአባቶችና ከኃይማኖት መሪዎች ጋር ኃይማኖታዊ ቅዱስ ሥርዓቶችን ሊፈጽም እንደሚችል ገልጸዋል::





## ትኩረት


እስካሁን ካየናቸው የ666 እንቅስቃሴዎች ውስጥ በዓይነቱ ከላይ እንደተጠቀሰው የኃይማኖቶቹ ውሣኔ ለራዕይ 13:16-18 ትንቢት የቀረበ ግልጽ ትዕይንት ያለ አይመስለኝም:: ምክንያቱም ብዙውን የሰው ልጅ መገልገያ የሚከለክልና ሰዎች የግድ ወደ 666 እንዲሮጡ የሚያደርግ ነው:: ያለ 666 ሰው ከባህሩና ከየብሱ መጠቀም ካልቻለ የግድ በቀኝ እጁ ወይም በግምባሩ ላይ ቁጥሩን (ምልክቱን) መቀበል ይኖርበታል:: ይህ ውሣኔ በ1980ዎቹ አጋማሽ ከተወሰነ ተግባራዊነቱ እጅግ እየፈጠነ መሆኑን መረዳት ይቻላል:: ሆኖም ሥራው እንደ 2ኛ ተሰ. 2:6-7 በሚስጢር ይሰራል ማለት ነው:: ይህ ከሆነ የአውሬው መገለጥና ከእርሱ አስቀድሞ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ መቃረቡን ልብ ልንል ያሻል:: ከፍተኛ ትኩረት ልንሰጠው የሚገባው ሌላው ነገር እነዚህ ሰዎች በክርስትና ጥላ ሥር ሆነው መጽሐፍ ቅዱስ አጥብቆ ለሚቃወመው ለ666 ተገዢ መሆናቸው ነው:: ይህ በግልጽ የሚያሳየን የጌታ መምጫና የቅዱሳንም ወደ ሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም መሰብሰቢያ ጊዜ እጅግ በመፍጠን ላይ መሆኑን ነው:: ጌታ ኢየሱስ በሉቃስ 21:31 እና ማቴ. 24:33 ላይ እናንተ ደግሞ ይህንን ሁሉ ስታዩ ቤዛችሁ በደጅ እንደቀረበ እወቁ እንዳለ በወቅቱ ከሚታዩ ዓቢይ ነገሮች ውስጥ አንዱ 666 ነው:: ስለሆነም ጌታን የተቀበልን ነቃ ልንል ያልተቀበልን ደግሞ በእውነተኛ ንሰሃ ከሰይጣን ልጅነት ወደ እግዚአብሔር ልጅነት ልንመጣ (ዮሐ. 1:12-13) ይገባል:: የጌታ ምጽዓት ምህረትን ብቻ ሳይሆን ፍርድንም ያካትታል:: የራስ ጥቅምና ክብር ሰዎችን ከጣላቸው ታላላቅ መቅሰፍቶች ውስጥ ዋነኛው ነው:: እኛ ለራሳችን የምናመቻቸው እግዚአብሔር ካዘጋጀልን ጥቅም ጋር የሚቃረነው እንቅስቃሴ ምንም ዘለቄታዊ ፋይዳ የለውም:: ይህ ሂደት ለጠቢቡ ሰለሞን፣ ለኔሮ፣ ለናቡከደነጾርና ለነሂትለርም አልጠቀማቸውም:: የሚጠቅመው ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር መጣበቁ ነው:: ስለሆነም በዓለማውያን ዘንድ እየደለበ ካለው ሃብትና ብልጽግና ጋር አንጣበቅ ሆኖም እየሰለሰለች ካለችው እውነት ጋር ግን እንቆራኝ:: በአሁኑ ጊዜ እውነት ሰልስላ ልትበጠስ ወይም ልትቀበር የደረሰች ትመስላለች:: ሆኖም እውነት ትሰለስላለች እንጂ አትበጠስም:: ለሦስት ቀን ብትቀበርም በኋላ የተጫናትን ሁሉ ፈነቃቅላ ትወጣለች:: እውነት ሥርቻ አትፈልግም እንዲሉ እውነትን መኖር ከባድ ቢሆንም መፍራት አያስፈልግም:: ሐሰት ካከበረው ለጊዜው እውነት ያዋረደው ሰው ይሻላል:: ሐሰትን ልንከተል ፈጽሞ አይገባም:: ምክንያቱም ሐሰት እያደር ይቀልላልና:: እውነትና ውኃ እያደር ይጠራል የተባለው ሁልጊዜ ልክ ስለሆነ ነው:: ሲያወላውል ቀረ ባጉል የተባለው እንዳይደርስብን ምኞት ብቻ መንግሥተ ሰማያትን ስለማያስገኝ በተቻለ መጠን እምነታችንን ልንፈትን ይገባል:: ጌታም ደግሞ ወደ እውነት ሁሉ ሊመራን ይችላል::

### 3.5 የ666 ማንነት

በዓለም ላይ ያሉ ብዙ ተመራማሪዎች፣ የሥነ ልቡና ሰዎች፣ የኃይማኖት መሪዎች፣ ወዘተ ቀደም ብሎ የተመለከትነውን አውሬ ማንነት



ለይቶ ለማውጣት ብዙ ሙከራዎች አድርገዋል:: የቀሩት ደግሞ ልባቸው በናፍቆት ተሞልቶ በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ:: ለይተን አውቀነዋል ባዮች በስምም እስከ መጥራት ደርሰዋል:: የአንዳንዶቹ ሃሣብ መላ ምት ብቻ ሆኖ በመቅረት ሲወድቅ የቀሩት ደግሞ ገና በጥበቃ ላይ ይገኛል:: ለመሆኑ ይህ አውሬ (666) የተባለው ሐሣዊ መሢህ ማን ይሆን? በምድርስ ላይ ይገኝ ይሆን? የተለያዩ ሰዎችስ ምን ይላሉ? የአውሬው ማንነት ሙሉ በሙሉ እስካልተገለጠ ድረስ ይህ ነው ብሎ ለማውጣት ለብዙዎች የሚቸግር ሊሆን ይችላል:: የአውሬው አመጣጥና አሠራር ከሞላ ጐደል ልክ እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው:: ባልተጠበቀ ሰዓት ብቅ በማለት ሰዎችን በማስደነቅ መሳብ ዓላማው ነው:: እንግዲህ አሁንና ባለፉት ዘመናት የነበሩ ልዩ ልዩ ግለሰቦችና ቡድኖች የአውሬውን ማንነት እንደሚከተለው ሊገልጡት ሞክረዋል:: እስቲ እንመልከታቸው::





### 1. አስቆሮቱ ይሁዳ

በቀድሞ ዘመን የነበሩት የሥነ መለኮት ሰዎች ሰይጣን በውስጡ ተገልጦበት ይሁዳ መምጣቱ አይቀርም ያሉ ነበሩ::[23]

### 2. ታላቁ ወንድም

በዓይነቱ ፀረ-ክርስቶሳዊ አቋም ያለውን ሰው የሚመስል «ታላቁ ወንድማችን» በሚል ቅጽል ስም የሚጠራ በአሜሪካ እንዳለ በ1984 ዓ.ም. በዓለም የኖቤል ሽልማት አሸናፊ የሆኑት ጆርጅ ኦርዌል በጽሑፋቸው አስታውቀዋል:: ይህ ሰው ዘመናዊውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ሁሉን ለራሱ ለመቆጣጠር ከዓለም ህዝብ ፍጹማዊ መታዘዝን የሚፈልግ ነው:: ይህ ሰው ሰዎችን ጨካኞች ለማድረግ ሊቆጣጠርባቸው የሚያስችሉት፣ የሰዎችን የንግግር ድምጽ ሊለዩ የሚችሉ መሣሪያዎች፣ በቁጥጥር ሥር ያለ ሰው ለማምለጥ ሲሞክር ፖሊሶችን ሊያነቁ የሚችሉ በወንጀለኛው እጅ ሰዓት ማሰሪያ ቦታ ላይ የሚደረጉ ኤሌክትሪካዊ ሽዋሊያዎችና የእጅ ጌጦች

(በሜክሲኮ እየተሰራበት ያለ ነው)፤ በሰው ሠራሽ ተቀምጦ በሰማይ ላ
ካለው ሳተላይት ጋር ግንኙነት ያለው መቆጣጠሪያ መሣሪያ፣ ሊጠቀ
የሚችል ሰው መሆኑ ታውቋል።[24] ይህ ሳተላይት 24 ሰዓት ሙሉ በዓለ
ሕዝብ ላይ የሚያተኩር ስለሆነ የሁሉንም እንቅስቃሴ ሊቆጣጠር ይችላል።
ዴቪድ ዌበርም ከዓለም ሕዝብ አጠራጠሩ ሊቆጋ የሚችል ማን
እንደማይኖር የገለጹት ከዚህ ተሉታው አሔድ ነው። ዌበር ይህንን አውሬ
የሚጠቀምበትን ሳተላይት ሁሉን የሚያይ ኤሌክትሪካል ዓይን ብለውታ
(ስይ)።[25] ሆኖም ይህ«ታላቅ ወንድም» በመባል የሚጠራው ሰው መኖ
ታወቀ እንጂ ሙሉ መጠሪያ ስሙ አልተገለጸም።






K=66 I=54 S=114 S=114 I=54 N=84 G=42 E=30 R=108
ድምር 666 ይሰጣል። ትክክለኛውን የስም ስፔሊንግ ወሳኙ ግን ባለስሙ ይሆናል።[25.1]

4. **ጐርባቾቭ (GORVACHOV)**

እንዳንድ ደራሲያን የክርስቶስ ተቃዋሚ የራሺያው ፕሬዚዳንት ጐርባቾቭ ነው የሚሉ ነበሩ። ለዚህም ያቀረቡት ማስረጃ የስሙን ስሌት ደምሮ 666 ማምጣት ነው።

G=42 O=90 R=108 V=132 A=6 C=18 H=48 O=90 V=132
ድምሩ 666 ይመጣል።

5. **ጌታው ሜይቴሪያ(ሎርድ ሜይቴሪያ)**

የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ወደፊት ዓለምን በመንፈሳዊ ነገር የሚመራው ሜይቴሪያ ነው ይላሉ። ሜይቴሪያ በአሁኑ ጊዜ በሎንደን ከተማ በዓለም ላይ ለመንገስ በመዘጋጀት ላይ እንደሆነ ይነገርለታል። እንደሚባለው የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ሜይቴሪያ ክርስቲያኖች ክርስቶስ፣ አይሁዶች መሢሁ፣ ቡዲስቶች 5ኛው ቡድሃና የሂንዱ ተከታዮች ክሪሽና ብለው የሚጠሩት እንደሆነ ዘመናይ (አ.ዘ.እ) ያስተምራሉ። ሜይቴሪያ ሲመጣ ሁሉን አንድ በማድረግ ስለሚቆጣጠር የሦስተኛውን የዓለም ጦርነት እንደሚያስቀር ይታመናል።[26]

6. **ሮም (አውሮጳ)**

ይህ አመለካከት 666 ግለሰብን ሳይሆን በንግድ ኤኮኖሚ የተሳሰሩ አገሮችን አንድነት የሚያመለክት ነው። በክርስቶስ ኢየሱስ የመጀመሪያ ምጽዓት (ከ0 እስከ 34 ዓ.ም.) ሮም የሜዲትራኒያንን አካባቢ አገሮች (ሞሮኮን፣ ስፔይንን፣ አልጀሪያን፣ ጣሊያንን፣ ቡልጋሪያን፣ ቤልግሬድን፣ መቄዶንያን፣ ቱርክን፣ ቆጵሮስን፣ ሶሪያን፣ ኢራቅን፣ ሊባኖስን፣ እስራኤልን፣ ዮርዳኖስን፣ ግብጽን፣ ቱኒሲያን፣ ቀርጤስን፣ ግሪክን አልባኒያን፣ ዩጐዝላቪያን፣ ከፊል ሳውዲ ዓረቢያን ወዘተ) ትገዛ ነበር። በአሁኑ ጊዜ እነዚህና ሌሎችም አገሮች ከአውሮጳ ማኅበረሰብ አገሮች ጋር ግንኙነት ስላላቸው 666 ወደፊት የሚታደሰውና ትንሣኤ በማግኘት የሚመጣው ሮም (የአውሮጳ ህብረት) ነው የሚል ሃሣብ ነው።[27] በአሁኑ ጊዜ የእስራኤል ከአውሮጳ ማኅበረሰብ ጋር ያላት ግንኙነትና መቀራረብ እየጨመረ በመሄዱ በዳን. 9:27 እንደተተነበየው ስምምነቱን ልትጀምር ትችላለች ይባላል። ይህ ሃሣብ እንደ ጀርመኑ ቻንስለር ሄልሙት ኮል አነጋገር ለእስራኤል ጥቅም እንደሆነና አውሮጳውያንም ወደ እስራኤል ያላቸው አዎንታዊ ዝንባሌ መልካም ነገር ሊፈጥር እንደሚችል ያመለክታል።[28]

7. **ለቢ ሜናኬም ሜንዴል ሽሃሰን**

ይህ ሰው በአሁኑ ጊዜ በኒውዮርክ ከተማ የሚገኝ ሲሆን የክርስትናንና የአይሁድን እምነት ተከታዮችን በማስተባበር የሚመራ

ነው:: በእስራኤል ከሚገኙት ኃይለኛና ታላላቅ እንቅስቃሴዎች ውስጥ አንዱ የሆነው የሐሲዲክ እንቅስቃሴ አባላት ባልታወቀ ጊዜ መሢሐቸው ወደ እነርሱ ሊመጣ እንደሆነ በማሰብ የተለያዩ ዝግጅቶችን በማድረግ ላይ ይገኛሉ:: ከዝግጅታቸውም ውስጥ ጥቂቶቹ ለሚመጣው መሢህ ተዘጋጁ፣ የመቤዣችሁ ጊዜ አሁን ቀርቧል የተሰኙ የቅስት ጽሑፎችንና ንግግሮችን ለህዝቡ ማሰራጨትና የመሳሰሉት ይገኛሉ:: በተጨማሪም መሢሃቸውን ለመቀበል ከኢጣሊያ፣ ከጀርመን፣ ከዩናይትድ ስቴትስና ከምዕራብ አውሮጳ የመጡ የእምነቱ ተከታዮች ጨርቃቸውን እስከመጣል ድረስ መሢሃቸውን ለመቀበል በዝግጅት ላይ መሆናቸው ተገልጿል::[29]

## 8. ሳሜን ሲ

ሲ እስካሁን ከተጠቀሱትና ወደፊት ከሚጠቀሱት ፀረ-ክርስቶሳውያን ተዘጋቢዎች ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የ666 ባለቤት ሊሆን እንደሚችል ይገመታል:: ምክንያቱም ዊክሊ ወርልድ ኒውስ የተባለው ጋዜጣ በሐምሌ 1994 ዓ.ም. ስለ ሲ ይዘት የወጣው ተዓምር አዘል ሐተታ የብዙ ታላላቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ሥነ መለኮታውያንን በማነጋገሩና ሐሣብ ላይ በመጣሉ ነው:: ስለ ሲ ከተጻፉት ንባባት ውስጥ ዋነኞቹ አረመኔ ፍጡር መሆኑ፣ 2000 ዓመት ከማለቁ በፊት በሰው ዘር ላይ የመጨረሻ የሞት ሽረት ጥቃቱን እንደሚፈጽም፤ ሰይጣናዊ ሥልጣኑ ለእያንዳንዱ የሰው ልጅ የስቃይ መንስኤ እንደሚሆን፤ በሰው ልጅ ተመስሎ የተፈጠረ ዲያብሎስ መሆኑ መገለጹ፤ ባጠቃላይ የሰውን ዘር የአምላክን እውነተኛ ልጆች ጨምሮ ከመዳፉ ሳያስገባ ፈጽሞ እረፍት እንደማይኖረው መገለጻቸውና የመሳሰሉት ናቸው:: ሲ ብቸኛና ሚስጢረኛ ነው:: ከፖለቲካው መድረክ እንደ ወካይ የለሽ ዲፕሎማት በመካከለኛ ምሥራቅ ችግሮች ላይ ከመጋረጃ በስተጀርባ ፅኑዕ ሚና እንዳለው ይታወቃል:: ሳሜን ሲ እ. ኤ.አ. በ1958 ዓ.ም. በሮም ከተማ ሲወለድ በስዕሉ ላይ እንደሚታየው ግንባሩ ላይ 666 ተጽፎበት ነበር:: በ1991 ዓ.ም. ወደ ኢየሩሳሌም መጓዙ ይነገራል:: በ1986 ዓ.ም. አስጸያፊ ሩካቤ ተፈጽሞባት ተተልትላ ለሞተችው እናቱ መንስኤ ሲ እንደሆነ ይጠረጠራል:: የሳሜን ሲን ረቂቅ አሠራር ለህዝብ ከገለጹት ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁር የሆኑት ዶ/ር ጂን ሚካኤል ማርኩይት፣ ፎቶግራፉን በማሳየትና ስለ ሲ ጥብቅ ክትትል በማድረግ ላይ ያሰው ሞሳድ በመባል የሚታወቀው የእስራኤል የፀጥታ ጥበቃ ኃይል፤ ለፀጥታ ኃይሉ ፎቶግራፉን በመስጠት የተባበሩት የተለያዩ የኃይማኖት መሪም ይገኛሉ:: ሲ በጣም ኃብታም ሚሊዬነር ከመሆኑም የተነሳ እስከ 60,000,000 (ስድሣ ሚሊየን) ዶላር በ50 የባንክ ሂሣብ ሰነዶች ማስቀመጡ ተገልጿል:: በመጨረሻም አውሬው ሊሆን ይችላል የሚል ከፍተኛ ጥርጣሬ ያመጣው:: በሐይማኖቱ መሪ ማስታወሻ ውስጥ «ከዓለም ፍጻሜ በፊት የሚከሰተው ፀረ-ኢየሱስ በምድር ላይ ነው:: ስሙም ሲ ይባላል» የሚል ጽሑፍ መገኘቱ፤ በሮም ከተማ መወለዱና በዳን. 9:27 የተነገረውን ትንቢት ለመፈጸም ወደ እስራኤል መምጣቱ ወዘተ ብሏል::[30]





## 9. ናምሩድ

የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ ወደ ኋላ መለስ ብለን ስናይ በምድር ላይ ኃያል አዳኝ ስለነበረው የኩሽ ልጅ ታሪክ እናነባለን:: የናምሩድ ግዛት ደግሞ በሰናኦር አገር በባቢሎንና በሌሎችም እንደነበር ተገልጿል:: ዘፍ. 10:8-10:: ከኖኅ የጥፋት ውኃ በኋላ የእግዚአብሔርን ቁጣ ለማነሳሳት የመጀመሪያዎቹ ሰዎች የናምሩድ ከተማ የሰናኦር ነዋሪዎች ነበሩ:: በሰናኦር ምድር ካረፉ በኋላ ሸክላ በመሥራት ራሱ ወደ ሰማይ የሚደርስን ህንጻ በማሰራት ስማቸውን ለማስጠራት እርምጃ ወስደዋል:: ጌታም እጅግ ተቆጥቶ ወደ ምድር በመውረድ ሃሳባቸውን ከልክሎ ቋንቋቸውን በመደበላለቅ ከተማይቱም እስከዛሬ ባቢሎን(ኢራቅ) በመባል ትጠራለች::

ናምሩድ የመጀመሪያው ፀረ-ክርስቶስ (አውሬ) እንደሆነ ይነገራል:: ታሪክን ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንመረምር የናምሩድ የልደት በዓል በጥንት ሮማውያን ዘንድ በዲሴምበር 25 ይከበራል:: ሮም በጥንት አጠራር ሳተርናሊያ ትባል ነበር:: ይህም በከለዳውያን አጠራር በናምሩድ ቋንቋ ሳተርን STUR (ስቱር) ተብሎ ይጠራ ነበር:: ይህ ስም አጠራር ደግሞ በዕብራይስጡ የፊደል ትንታኔና ዋጋ አሰጣጥ S=60 T=400 U=6 R=200 ሲሆን የስሙ ቁጥር ድምር 666 ይሰጣል::[31] ይህ መንፈስ አስቀድሞ ካለ ፍጻሜው እስኪሆን ድረስ መንፈሱ ይደጋገማል ማለት ነው:: ስለሆነም የናምሩድ አሠራር ባቢሎን ዛሬም (ነገም) እንደሚኖርና አውሬው ከባቢሎን ሊነሳ እንደሚችል ማሰብ ይቻላል::

## 10. አንቲከስ 4ኛው (ANTIOCHUSIV)

ሶሪያዊ የነበረው አንቲከስ በዘመኑ የአይሁዶችን ዘር በማጥፋት ወደ አህዛብነት ለመለወጥ የጣረ በኢየሩሳሌም መቅደስ የአሳማ መስዋዕት ያቀረበ፣ ግዝረትን በመከልከል የብሉይ ኪዳንንም መጻህፍት ያጠፋ መሪ ነበር:: በተጨማሪም ለራሱ የእግዚአብሔር መገለጥ (God Manifest) የተሰኘውን ማዕረግ በመስጠት ሊመለክ የሞከረ ፀረ-ክርስቶስ ነበር:: የዚህ ሰው የእግዚአብሔር መገለጥ የተሰኘው ስም የግሪክ ምትኩ ኤፒፋኒያ ( EPIPHANEIA) ሲሆን በግሪኩ አልፋቤት የስሙ ቁጥር ድምር 666 ይሰጣል::[32]

## 11. ቄሳር ኔሮ

ኔሮ በዘመኑ የታወቀ የክርስቲያኖች አሳዳጅ መሪ ነበር:: ቅዱሳንን እንደ ችቦ በማቃጠል ለአትክልት ሥፍራው እንደ መብራት ይጠቀም ነበር:: ለተራቡ አንበሶች መዝናኛ እንዲሆኑ ከማድረጉም ባሻገር እርስ

በርስ በሰይፍ እንዲተራረዱ አድርጓቸዋል:: በሕዝብ በዓላት ላይ በችካል አስሮ ቅዱሳንን በእሳት አሰቃይቷል:: ኔሮ የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ንሮንክርስ ሲሆን (NRONKRS) የስሙ ቁጥር 666 ይሰጣል:: N=50 R=200 O=6 N=50 K=100 R=200 S=60 =666[33]

## 12. የ1962ቱ ህጻን

ጂን ዲክሰን በመባል የታወቀችው አንዳንዶች እንደሚሏት ፈረንሳዊቱ ጠንቋይ ወይም ክርስቲያን ተንባይ እ.ኤ.አ. በየካቲት ወር 1962 ዓ.ም. ከማለዳው 1 ሰዓት ዓለምን በከፍተኛ ደረጃ የሚያንቀሳቅሰው ሕጻን በመካከለኛ ምሥራቅ ተወልዷል ብላ በመገለጥ ተናግራ ነበር::[34] መገለጡ ልክ ወይም ስህተት ሊሆን ይችላል ልክ ከሆነ ታሪክ ይገልጠዋል::

## 13. የካባላውያኑ ሉሪያና ዜቪ

የጉዳናው ጋዜጣ «ዓለምን ለጥፋት ለመዳረግ በልዩ ሚስጢር የተያዘው የ«666» የካባላ-ጉድ» በሚል ርዕስ ያወጣው ጽሑፍ በጥልቅ ጥናታዊ ዘገባ የቀረበ ሲሆን ባጭሩ የሚከተለው ነው:: ከአይሁድ ዝርያዎች ውስጥ የካቫላውያን ረቂቅ እምነት ዕንቅስቃሴ አለ:: የእነዚህ ዝርያዎች አቋምና አስተምህሮ ፍጹም ፀረ-መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሠይጣናዊ ነው:: በየዘመኑ የተነሱ የተለያዩ መሪዎቻቸው ግማሾቹ በምድር የቀሩት ደግሞ በሲኦል እንዳሉ ይናገራሉ:: የካባላውያን አይሁዶች ረቂቅ እምነት መመሪያ 666 ሲሆን ባህሪውንም ከሚቀጥሉት የመሪዎቻቸው ባህሪ መግለጫዎችና አስተምህሮት መረዳት ይቻላል:: ከታወቁት መሪዎቻቸው አንዱ <u>ሻባቱ ዜቪ</u> ይገኛል:: ዜቪ ኃጢአትን መፈጸም ቅድስና እንደሆነ ያስተምራል:: እንዲሁም የማንኛውም አይሁዳዊ ተግባር ኃጢአት መሥራት መሆኑን ገልጿል:: ኢሣ.53 ስለ በደላችን ቆሰለ የሚለውን ስለጌታ የተነገረውን ትንቢት የሚተረጉመው ክርስቶስ (መሢሁ) ከቅድስና ወደ ኃጢአተኝነት ተሰወጠ በማለት ነው:: እርሱ ኃይማኖቱን ከአይሁድነት ወደ እስልምና መሰወጡን ለማስረገጥ ማንኛውም የእስራኤል ንጉሥ የመጀመሪያ እምነቱን ትቶ ወደ አረማዊነት ካልተሰወጠ ጻድቅ መሆን አይችልም በማለት ያስተምራል:: በተጨማሪም የሙሴን በፈርኦን ቤት መኖር ወደ ኃጢአተኛነት እንደመለወጥና በኋላ ሕዝብን ለማዳን ለመመረጥ ሁኔታዎችን እንደሚያመቻች ይገልጣል:: በመጨረሻም ዜቪ ሰዎች እምነታቸውን በመተው ወደ ኃጢአት መውረድ እንዳለባቸው በመምከር <u>የተከሰከሰውን እንድናደርግ የፈቀደልን የተባረከ ይሁን</u> በማለት ተከታዮቹን ባርኳል:: ተከታዮቹ ዝሙት ይፈጽማሉ፤ የሻማ በዓል ተብሎ በሚጠራው የአይሁድ በዓል ላይ ሻማ በማቀጣጠልና ሚስቶቻቸውን በመለዋወጥ ዝሙት ፈጽመዋል::



### <u>የዜቪ አስተምህሮት (ዶክትሪን)</u>

1. መሢሃቸው ወደ ጥልቅ መውረዱን ይገልጻል::
2. እምነታቸው ራሱን ላልሰጠ ሰው ፈጽሞ አይገለጽም ሚስጢር ነው::
3. ሕግን ለመፈጸም ተቃራኒውን ማድረግ ያሻል ይላል:: ለምሳሌ አትግደልን በግደል፤ አታመንዝርን በአመንዝር፣ አትዋሽን በዋሽ ሉሪያ በመባል የታወቀው ሌላው መሪያቸው ደግሞ የተለያዩ አህዛብና ማህበረሰብ ላይ ከፍተኛ እልቂትና ውድቀት ካልደረሰ የመሢሁ መንግስት አይከሰትም በማለት ያስተምራል:: ይህንንም ለማፋጠን አህዛብን እንደሸክላ በመሰባበርና ከፍተኛ ድቀት በማድረስ ማገዝ አሰብን ይላል:: አይሁዶች በመላው ዓለም የተበተኑት ኃጢአት ስለሰሩ በቅጣት ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ነው ይላል:: በተጨማሪም የአይሁድ መዳንና እንደገና መገንባት የሚመጣው ኃጢአት በመስራት ነው በማለት ያስተምራል::[35]

የካባላውያን እንቅስቃሴ የአውሬውን አስከፊ ባህሪ በደንብ እንደሚገልጽ መረዳት ይቻላል:: ከዚህ ቀደም የተመለከትናቸው የተለያዩ ክህደቶች እንደዚህ እንቅስቃሴ ዓይን ያወጡ አልነበሩም:: ይህ እንቅስቃሴ እንደ አውሬው ሕግጋትንና ዘመናትን ለመለወጥ ፈቃድ አለው:: አውሬው እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔር የሆነውን ሁሉ አይወድም ስለሆነም አውሬውን ከመካከላቸው እንዲወጣ ያደርገው ይሆን? ሉሪያና ዜቪስ ባለ 666 አውሬ ሆነው ይነሱ ይሆን? አውሬውን እንደ ቡድንና ድርጅት የማይቀበሉ የኃይማኖት ክፍሎች ባለ 666ቱ ሰው አይሁዳዊ ነው ይላሉ::[36] ከዓለም ክፍሎች በአንዱ በአይሁዳዊነቱ ይወሰድና ጊዜው ሲደርስ የ7ቱን ዓመት ቃል ኪዳን ሊፈጽም ወደ እስራኤል መምጣቱ አይቀርም ይባላል:: ታዲያ እንደ ሊ ያለውና የካባላውያኑ ወደ እስራኤል መከማቸት የአውሬውን መምጣት ያፋጥነው ይሆን? በተጨማሪም በአሁኑ ወቅት እስራኤላውያን በከፍተኛ ውጥረት ውስጥ መሆናቸው የመሢሃቸውን መገለጥ እጅግ እንዲናፍቁት ያስገድዳቸዋል:: ዳሩ ምን ዋጋ አለው ጅብ ከሄደ ... እንደተባለው ሆነባቸው እንጂ::

አይሁዶች ስቀለው ስቀለው በማለት ትላንት የናቁትን ጌታ ኢየሱስ፣ ለ2000 ዓመታት ያህል ፈልገውታል:: ሆኖም አላገኙትም:: በአንጻሩ ግን የኦሪትን ህግ አጥፊ የሆኑ ካባላውያን በመካከላቸው ተነሱ ትላንትም አላዩም ዛሬም ማየት አልቻሉም የአህዛብ የመዳን ሙላት እስበኪሆን መታወራቸው ይቀጥላል:: ምክንያቱም ደሙ በእኛና በልጆቻችን ይሁን በማለት ራሳቸውን ስለረገሙ ነው:: አሁን እውነተኛውን መሢህ ይፈልጋሉ የሚያገኙት ግን ከብዙ ስቃይ በኋላ ነው:: ከእውነተኛው ክርስቶስ በፊት ብዙ ሐሰተኞች ላይሰለጥኑባቸው አይቀርም:: በተለይ አውሬው ብዙ ያውካቸዋል:: ራዕይ 12:: እውነተኛው ክርስቶስ መስኗቸው ገና ሐሰተኛውን ይቀበሉታል:: ዳን. 9:27:: ስለሆነም የተጻፈውና እየሆነ ያለው ነገር ለትምህርታችንና ለጥንቃቄአችን እንዲሆንልን ያሻል:: <u>ሲሳይ ያሰቀበት አንበጣ ከድንጋይ ላይ ያርፋል</u> እንደተባለ እውነተኛውን ጌታ ንቀንና ቸል ብለን እንደ አይሁዶች አጓጉል እምነት ላይ እንዳንወድቅ::

## 14. የሎስ አንጀለሱ 666

በክርስቲያኑ ኅብረተሰብ «የዲያብሎስ ገጽታ» በመባል የሚታወቅ የ666 ዋሻ በአሜሪካ ሎስ አንጀለስ ከተማ ይገኛል:: ይህ ዋሻ የ666 ተከታዮች እንደ ጸ/ቤትና ለመሰብሰቢያ የሚጠቀሙበት ባለ 6 ፎቅ ህንጻ ነው:: ፎቁ ሙሉ በሙሉ ጥቁርና ምንም መብራት ያልገባበት ሲሆን እስከ 200,000 ያህል ሰዎችን የሚያስተናግድ ሦስት ትላልቅና ስድስት መለስተኛ የመሰብሰቢያ አዳራሾች አሉት:: በዚህ ዋና ጽ/ቤታቸው ግድግዳዎች ላይ እጅግ አስፈሪና አስደንጋጭ ስዕሎች ያሉት ሲሆን የመሰብሰቢያ አዳራሾቻቸው በሙሉ መብራት የሌለባቸው ጨለማ ናቸው:: ሆኖም ሰው ሲገባ እየረገጠ እንዲራመድባቸው በወርቃማ ቀብ ተስለው የተዘጋጁ መስቀሎች በወለሎቹ ላይ ይገኛሉ:: ተመሳሳይ የሚረገጡ መስቀሎች በየአዳራሾቹ በሮች ላይም ተስለው ይገኛሉ:: የ666 አባላት እጅግ ከበርቴዎች ከመሆናቸው የተነሳ ለኃይማኖቱ ማስፋፊያና ለ666 ህንጻ ማሰሪያ እያንዳንዱ አባል ቢያንስ በወር 10 ሺህ ዶላር ማዋጣት አለበት:: የኃይማኖቱ አንቀሳቃሾችና አባላት ድኃ ሰው በመካከላቸው እንዲገባ ፈጽሞ አይፈቅዱም:: ከዚህ የገንዘብ አቅማቸው በመነሳት ሊገዙት የማይችሉት ምንም ነገር ሊኖር እንደማይችል ሊያስቡ ይችላሉ::[37] ለመሆኑ እነዚህ ሰዎች የህንጻቸውን ርዝመት ለምን በ6 ፎቅ ወሰኑት? ለምን 6 አነስተኛ አዳራሾች ኖራቸው? ለምንስ 6ቱም ፎቅ ጥቁርና ክፍሎቹ ጨለማ ሆኑ? በጨለማ አዳራሾች ውስጥ የሚያበሩ ወርቅማ መስቀሎችን አስቀምጠው ለምን ይራመዱባቸዋል? ይህ በቀጥታ ፀረ-ክርስቶሳዊ እንቅስቃሴ መሆኑን ያመለክተናል:: ለመሆኑ የዚህ እንቅስቃሴ ጀማሪ፣ አንቀሳቃሽና ተጠሪ ማን ይሆን? አውሬው ከዚህ ቡድን /የኃይማኖት ድርጅት/ ውስጥ ይወጣ ይሆን? አንባቢና አስተዋይ ይመርምረው:: ዳን. 9:2:: ትኩረት ከ666 ጋር ግንኙነት ያላቸው በአብዛኛው ክፉዎች፣ ሃብታሞች፣ አዲስ ነገር አፍላቂዎች ሩህሩህ መሣዮች ፀረ-መጽሐፍ ቅዱሳውያንና ወደ እስራኤል አትኳሪዎች መሆናቸው ግንዛቤ ያግኙ::

## 15. የጥልቁ ሰይጣን መሪ

በ666 የጥልቁ ሰይጣን ምትሃታዊ ፍቅር ጉድ ሆንኩ በሚል ተከታታይ ሳምንታትና ወራት ከ15 ጊዜ በላይ በ«የፍቅር ማኅደር» ጋዜጣ ላይ ስለ 666ና አባላቱ አሰቃቂ አሠራር ዘርዘር ባለ መልኩ ታሪኩ ከተፈጸመበት ግለሰብ ምስክርነት ቀርቧል:: በታሪኩ ውስጥ የተጠቀሰው ግለሰብ የ666 አባል ከነበሩት አንዱ በአንዲት ህጻን ልጅ ላይ በግዳጅ ይፈጽም የነበረውን የወሲብ ፈቃድ ለመበቀል ሄዶ ሲታገል ራሱ ተሸንፎ የደረሰበትን ስቃይና ያጋጠመው ልዩ ልዩ ፈተና በጋዜጣው ውስጥ ተጽፏል:: ግለሰቡ ከተማረከ በኋላ በስብሰባ ላይ ንግግር ያደርግ የነበረው የ666 አባል የስብሰባ መሪ «አሁን መንፈስ ትሞላላችሁ የምትሞሉትም መንፈስ ፈጣሪያችሁን



የምታገለግሉበት ራሳችሁን የምትጠቀሙበት ይሆናል፣ በዕፀ በለሷ ላይ የነበረው መንፈስ አዳም ዕፀ በለሷን ሲበላ ሁሉን ነገር እንዲያውቅ እንዲሁም ክፉና ደጉን እንዲለይ እንዳደረገችው ሁሉ ዛሬም እናንተ የምትሞሉት መንፈስ ሁሉን ነገር እንድታውቁ ያደርጋችኋል:: በተለይ በጠላቶቻችሁ ላይ ሥልጣን ይሰጣችኋል:: የዚህ ዓለም ሁሉ በረከት ትሆናላችሁ:: ድህነት ከእናንተ በንኖ ይጠፋል:: ስለዚህ ፈቃደኞች ከሆናችሁ መንፈሱን ለመቀበል ተዘጋጁ» በማለት የፈቃደኝነት ጥያቄ እንዳቀረበ ገልጿል:: ፈቃደኝነታቸውንም ከገለጡለት በኋላ ወደ ሌላ ጨለማ ክፍል ይሄዳሉ:: በክፍሉም ውስጥ የነበሩት 5ቱ በከፍተኛ ድምጽ በመጮህ በልዩ ዓይነት ቋንቋ ይነጋገራሉ፣ እርስ በርስ እጅ ይጫጫናሉ፣ ግማሾቹም ይወድቃሉ:: የ10 ዓመቷን ልጅ ከወሲብ ስቃይ ሊያስጥላት ሄዶ የነበረውም እንደ ኤሌክትሪክ ንዝረት ይሰማዋል:: ከፍተኛ ሙቀት ከተሰማው በኋላ አንድ ነገር ከውስጡ ሲወጣና ራሱን ስቶ ሲዘረር ይረዳል:: ኃይልንም ይሞላሉ:: ኃይልን ከተሞሉ በኋላ ግለሰቡ በቤቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች የሚያስቡትን፣ ቤተሰቦቹ መጨነቃቸውን፣ አጐቱ በመጥፋቱ ፖሊስ ጣቢያ ማስመዝገቡን፣ ግብረሰዶም ፈጽመውበት የገረፉት ሰዎች የ10 ዓመቷን ልጅ ገድለዋት ገላዋን እያጠቧት መሆኑን፣ ያለበት ግቢ መንፈሱን የተሞሉ ሁሉ የሚገኙበት መሆኑን፣ የተሞሉትም በ666 መለያ ቁጥር በሚታወቅ የአንድ ንጉሥ መንፈስ እንደሆነ፣ የንጉሱን ሥራ እየሰራ ያለው ራሱ ሳይሆን መንፈሱ እንደሆነ፣ ንጉሡም እስረኛ መሆኑን፣ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በአንዲት ተቀጣሪ የሴት ሠራተኛ አማካኝነት የመጣችውን የ6 ዓመት ህጻን ልጅ ስምንት ሆነው እንደሚበሏት:: ሌሎችንም ብዙ ነገሮች በመገለጥ ይረዳል:: በተጨማሪም ወዲያው በግቢው ውስጥ 34 ሰዎች እንዳሉና የተሞሉትም መንፈስ የተለያየ እንደሆነ ያውቃል:: ግለሰቡ አስቀድሞ እንደተገለጠለት ከሱዳን ተሰርቃ የመጣችውን ልጅ በመካከላቸው አቁመው አንገቷ ተቆርጦ ደሟን በጆግ ቀድተው ከጠጡ በኋላ ወደየሥራቸው ይሰያያሉ::

ሀና በመባል የምትጠራው፣ አስልጣኙና ባለታሪኩ ግለሰብ ግን ወደኋላ ይቀሩና ሀና ልዩ ልዩ ነገሮችን ትነግረዋለች:: ከተነጋገሩትም ውስጥ ጥቂቶቹ ከንጉሱ ወኪሎች የሚመጣውን ትዕዛዝ እርሷ እንደምትነግረው፣ ሥራቸው ለንጉሱ (ዲያብሎስ ማለት ነው) ታዛዥ ያልሆኑትን የንጉሱን ጠላቶች (ክርስቲያኖችን ማለት ነው) አድኖ ማጥፋት፣ ንጉሱ የእስር ጊዜውን ሲጨርስ በኢትዮጵያ ሳይሆን በመላው ዓለም አብረው እንደሚነግሱ የመሳሰሉት ነበር:: ግለሰቡ ስለንጉሱ ጠላቶች ማንነት በጠየቃት ጊዜ ወደ አንድ ክፍል ገብቶ የቴሌቪዥን ስክሪን የመሰለ ትልቅ መስታወት በአንድ ነገር ላይ ተገጥሞ በዓለም ያሉትን እንቅስቃሴዎች በስክሪኑ ውስጥ እንዲመለከት ታደርገዋለች:: በስክሪኑ (በቲቪው መስታወት) ውስጥ የንጉሱን ጠላቶች የሚያሳይ ቀስት ይንቀሳቀስ ነበር:: በቀስቱ አማካኝነት የንጉሱ ጠላቶች የሆኑትን የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናትን፣ ፀሎት ቤቶችን፣ የኃይማኖት ቦታዎችን ወዘተ ይመለከታል:: ባለታሪኩ በስክሪኑ ውስጥ ቀስቱ

ከተነጣጠረባቸው ቤተ ክርስቲያናት አባላት ውስጥ አንዲት የእንጦጦ መካነ የሱስ ቤተ ክርስቲያን አባል ትገኛለች፡፡ ባለታሪኩ በስክሪኑ አማካኝነት በእውነትና በፍርሃት ተንበርክካ ትፀልይ የነበረችውን ልጅ ባየ ጊዜ የሆነ ነገር እንደወረረውና ሀናም ልጅቷ የንጉሱ ቀንደኛ ጠላት መሆኗን እርሷንም ለመያዝ በተደረገው ጥረት 5 የ666 አባላት መሞታቸውን ትገልጽለታለች፡፡ በተጨማሪም ሀና የንጉሱ (የባለ 666) ጠላት ክርስቶስ ኢየሱስ እነደሆነ ልጅቷ ከምትፀልየው ንግግር በማስረዳት ሊጎዳት የቻለ የጥልቁ አባል አለመኖሩን ታስረዳዋለች፡፡ በመጨረሻም ባለታሪኩ እርሱ ሊያጠፋት እንደሚችል ለሀና ሲነግራት ሀናም ልጅቷ ከምታገለግለው የንጉሳቸው ጠላት ስም መጠበቅ እንዳለበትና 5ቱ አባሎቻቸው የምትፀልየዋን ልጅ ለማጥፋት ባደረጉት ሙከራ በሔዱባቸውና በሞቱባቸው ክልሎች ውስጥ እንዳይገባ አስጠንቅቃው ለጊዜው ይለያያሉ፡፡ (ስይ)[38]

ያየነው ነገር ሁላችንንም ቢያስገርመንም ቢያስደነግጠንም ያየሁት ነገር ከሌሎች ይልቅ በእኔ አይምሮ አንድ ነገር እንዳስብ አደረገኝ፡፡ መንፈሱን፡፡ የወደቀችውን ቤት ሌሎች እየደጋገፉ ሊያስነሷት የእኔ ትኩረት ግን ድርባዋ ላይ ከዚህ በታችም ልክት የተደረገባት ልጅ ላይ ሆነ፡፡

## በ666 የጥልቋ ሰይጣን ምትሃታዊ ፍቅር ጉድ ሆነች

ካለፈው የቀጠለ




666



የ666 አባላት ከጥልቁ ሰይጣን ጋር ያላቸው ግንኙነት



ባለታሪኩ ኃይሉን ከተሞላ በኋላ በሰውነቱ ውስጥ ኃይለኛ መንፈስ እየሰረፀ መሆኑን ይረዳል፡፡ አንድ ቀን ከሀና ጋር ሳሉ እፍ ባለችበት ጊዜ ራሱን ስቶ ይወድቃል፡፡ ከዚያም በምድር ላይ ያሉ ጠንቋዮች እንዴት እንደሚሰሩም ይመለከታል፡፡ ይኸውም አንድ ጠንቋይ በርቀት የአምልኮ ልብሱን ለብሶ የተለየ ስጦታ የያዙ እናቶች በዙሪያው ቆመው ሳሉ ባለታሪኩና ሀና ካሉበት ሥፍራ የባለውቃቢው መንፈስ በመጋረጃ ውስጥ ተቀምጦ ወደ ሚዘይረው ጠንቋይ ሄዶ መንፈሱ ሲያርፍበትና ሲዋሃደው ለተሰበሰቡት ሰዎች ለችግሮቻቸው መፍትሄ ሲሰጥ ነበር፡፡ ከዚያም መንፈሱ ይህንን ከሰራ በኋላ ሀናና ባለታሪኩ ወዳሉበት ይመጣል፡፡ ከዚህ የመናፍስት አሠራር ጋር በተያያዘ ሰዎች ሞተው ከተቀበሩ በኋላ አካሉ ከመቃብር ወጥቶ ከተቆራረጠና ከተፈጨ በኋላ ለመድኃኒትነት ተግባር እንደሚውል፣ የዘመኑ ቴክኖሎጂ ያፈራቸው እንደ ጥይትና መድፍ የመሳሰሉት የጦር መሣሪያዎች ሊያጠቃቸው የማይችሉ ወደ ታች ወደ ምድር መግባትና በአየር ላይ ሊበሩ የሚችሉ ስጋውያን መናፍስት ተብለው የሚጠሩ እንዳሉ እንዲሁም በአሁኑ ጊዜ በምድር ላይ የሚገኙ ጥቅማጥቅሞች መንፈሱ ባረፈባቸው ሰዎች አማካይነት እንደሚመረቱም ተያይዞ ተገልጧል፡፡ ባለ ታሪኩ ወደ ታችኛው ምድር ገብቶ ሲወጣ ግራ እጁን በያዘ ጊዜ በአየር የመብረርና የመሰወር ችሎታ እንዳገኘ ወደ ምድር ሲወጣ አንዲት ኤደን የምትባልን ልጅ አግኝቶ እርሷ ወደ ቤት ስትገባ ማንም ሳያየው ተሰውሮ ገብቶ ክብረ ንጽህናዋን ለመውሰድ ልጅቷ ስትነቃና ስትጮህ ቤተሰቦቿ ሲመጡ እንደተሰወረና በፖሊስ ክትትል ሲደረግበት፣ ቤተሰቦቿም ሊያገኙት እንዳልቻሉ እንደሚሰወርባቸው ታሪኩ ያብራራል፡፡[39] ይህ የ666 አባል ከጥልቅ ሲወጣ አለቃው ከልጃገረድ ጋር ካልሆነ በስተቀር ወሲብ እንዳይፈጽም በተሰጠው መመሪያ መሠረት የ16 ዓመት ወጣት የሆነችውን ኤደንን በወሲብ ለመገናኘት በወሰዳቸው የሌሊት እርምጃዎች በልጅቷና በቤተሰቧ የደረሰው ስቃይ ለአእምሮ የሚከብድና የሚያሳዝን ነው፡፡ ዳሩ ምን መፍትሔ አለው፣ ልጅቷም ሆነች ቤተሰቦቿ የዚህን ክፉ አሰራር ማክሸፊያ መሣሪያ ባለመያዛቸው በዚህ መከራ ማለፋቸው የግድ ነበር፡፡ ቀደም ብሎ እንዳነበብነው የ666 አባላት ሊያጠቁት የማይችሉትን የንጉሣቸው አለቃና የበላይ የሆነው የጌታ ኢየሱስን ስም በአስመሳይና ስማዊ (ኖሚናል) በሆነ መልኩ ብቻ ሳይሆን ልባዊና እውነተኛ በሆነ የዳግም ልደት ሥልጣንን በመቀበልና በማምለክ ስሙን ተጠቅመውበት ቢሆን እጅግ አስደናቂ ሰላምና ዕረፍት ውስጥ በገቡ ነበር፡፡ የዚህ ታሪክ አንባቢያን ለመሆኑ በጌታ በክርስቶስ ኢየሱስ መለኮታዊ ስም ሙሉ በሙሉ መጠቀም የሚያስችለንን መለኮታዊ የልጅነት ሥልጣን ተቀብለን ይሆን? አሁንም ሆነ በኋላ በ70ኛው ሱባኤ (7ቱ ዓመት መከራ) ለሚገለጸው የአውሬው የክፉ አሠራር መድኃኒቱ የጌታን ስም በዳግም ልደት ሥርዓት አልፎ መጠቀም መቻል ብቻ ነው፡፡ የልጅቷ አባት በልጁ የሆነውን ክፉ በተመለከተ ጊዜ አማትቦ የፈጣሪን ስም ሲጠራ የጥልቁ አለቃ ስቆበት ነበር፡፡ ምክንያቱም ባለ ታሪኩ እንደገለጸው አባቷ ለኃይማኖት ግድ የሌለው ሆኖ ሳለ በችግሩ ጊዜ ፈጣሪን በመጥራቱ ነበር፡፡

ባለ ታሪኩ የልጅቷን ከአባቷ ጋር ሄዶ መተኛት ሲያይ ተስፋ በቆረጠ ጊዜ የጥልቁ አባቱ ሲያጽናናው ስለ 6 ቁጥር የጠቀሰውን ልብ እንድንል ያስፈልጋል:: ልጅቷ ለጊዜው ያመለጠችው ቢመስለውም ያ ዕለት ሌደን ከመኪና አደጋ የተረፈችበት 6ኛው ቀን መሆኑን፣ የተወለደችው በ6ኛ ወር መሆኑን፣ 6 ዓመት እስኪሞላት ድረስ ህመምተኛ መሆኗን፣ የወንድ አያቷ የገጽ ቁጥር 6 መሆኑን፣ የሴት አያቷ ግራ እጅ 6 ጣት ማብቀሉን፣ ገልጾለት ቀጥሎ በ6ኛው ሰዓት ቀጠሮ እንዲይዝ መንገሩ፣ ከተሰበረው አምፑል ጋር በተያያዘ ደግሞ ስብርባሪውን ሰብስቦ 6 ጊዜ በአለግሮኛ 6 ጊዜ በመግሮኛ 6 ጊዜ በአጠጊሮኛ አጋጥሞ 666 ትዱል ሲደግምበት እንደበፊቱ እንደሚሆን ይነግረዋል:: ይህ 6 ቁጥር የያዘው ሚስጢር ከመናፍስት አሠራር ጋር ምን ያህል ቁርኝት እንዳለው ልብ ልንል ያሻል::[40] ሳሌም ኪርባን በጻፈውም «666» በተሰኘው መጽሐፍ የአውሬውን የስም ቁጥር ሲገልጸው 666 ከተወለደበት ቀን ሰዓትና ወር ጋር የተያያዘ መሆኑን ከአውሬው እናት ባገኘው ምሥክርነት አስታውቋል::

ምርኮኛ የነበረው ምሥክርነቱን በመቀጠል 666 በአንዳንድ አገሮች ለሚገኙ ለጦር ባለሥልጣኖች ማዕረግ፣ በጭማቂ ጣሳዎች፣ በሲዲ ዕቃዎች፣ በኮምፒዩተር መፍቻ ቁልፎች፣ በትላልቅ ቤቶች በሚገኙ መጋረጃዎች፣ በነጠላ ጫማ ላይ በሚገኙ የቢራቢሮ ሥዕሎች፣ በካራቴ ማስተማሪያ ት/ቤቶች በራፍ ላይ በሚለጠፉ አርማዎች ላይ፣ በኮንጐ ላስቲክ ጫማዎች ላይ፣ ማለፍ ክልክል ነው የሚል ጽሑፍ በተጻፈባቸው ዓለም አቀፍ አርማዎች፣ በሞተሮችና ትራንስፎርመሮች ላይ 666እንደሚጻፍና ለዚህም መሪ መንፈስ እንዳለው ገልጿል:: በተጨማሪም ባለ ታሪኩን በተደጋጋሚ በተለያዩ ቦታዎች ይገጥሙት የነበሩትም መላዕክት (ልዩ ፍጥረታት) ቁጥር 6 ነበር:: ባለታሪኩ አባል በነበረበት ጊዜ ብዙ አስደናቂና አሳዛኝ ነገሮች ገጥመውታል:: ከእነዚህም ውስጥ ለ666 መንፈስ አለቃ እንደሚገባ ሲታዘዝ ባለመቻሉ መንፈሱ ከእርሱ መለየቱ ወደ ተለያዩ አገሮች ለጥፋት ተግባር ሊልኩት ሲያስቡ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቶ ለማምለጥ ሲሞክር ታክሲ ውስጥ ገብቶ ሲሸሽ አብረውት የነበሩት ሁሉ የ666 አባላት ሆኖ ሲያገኛቸው፣ ሊያመልጣት የፈለገው ሀና ባልጠበቀው ሁኔታ ቀድማው ፊቱ ስትመጣ፣ ተይዞና ተገድዶ ወደ ኬኒያ አገር ሲሄድ፣ ከዚህ የሰይጣን አገልጋይነት ነጻ መውጣት ሲናፍቅ ከኅብረተሰቡ ጋር ተቀላቅሎ ጤናማ ህይወትን መምራት ሲፈልግ ሆኖም አለመቻሉ፣ ያለፍላጐት በመጨነቅ የህጻንን ልጅ ሥጋ በህይወት ሳለች ከሰውነቷ ላይ በመቁረጥ እንዲበላ መገደድና ህጻኗ ስጋዋ ሲቆራረጥና ስትሰቃይ ሌሎች ስጋዋን እየበሉ ሲደሰቱና ሲስቁ ሲያይ የመንፈሱ መታወክ፣ የሰውን ደም እስከመጠጣት መድረሱና የመሳሰሉት ይገኛሉ:: በተጨማሪም በሰዎች ላይ ያለፈቃዳቸው የተለያየ ዓይነት ስቃይ ሲደርስባቸው ሰዎች እንደ እንቅልፍ ዕረፍት፣ ነጻነት ሰብአዊ ማንነት የሚጠይቀውን ሲፈልጉ ማግኘት አለመቻላቸውን፣ ሰዎች ሆነው ሳለ በከተማ ይኖሩ የነበሩ ከህዝብ ተለይተው በድቅድቅ ጨለማ ወደ ጫካ ውስጥ በመግባት ከጅቦች ጋር ወሲብ ሲፈጽሙ፣ ሰዎች ናቸው ሲባል ጅብ (አውሬ) አውሬ ናቸው ሲባል እንደ ሰው ሲለዋወጡና እጅግ አጸያፊ የሆነን ሩካቤ ሲፈጽሙ ማየትና የሥጋ ዝምድና ያላቸው ሰዎችም በግብረ-



ወሲብ መተፋፈር እንዳሌለባቸው ሲደፋፈሩና ርምጃ ሲወስዱ ተመልክቷል::[41]

አንባቢያን ከ«ፍቅር ማጎደር» የተገኙትን የተለያዩ የ666 ገጽታዎች በዳን. 8:23 እና ራዕይ 13:5-6 ከተጠቀሰው እውነት ጋር በማነጻጸር ሰናይ አውሬው በደጅ መሆኑን እንገነዘባለን:: ለመሆኑ እነዚህ የ666 አባላት ይህ የሚያንቀሳቅሳቸው ሥጋዊ መንፈስ የት እንዳለ ያውቁት ይሆን? እነዚህ በሰው ልጅ ህይወት አሰቃቂ ገቢር የሚፈጽሙ ክፋዎች ቁጥራቸው እየበዛ ከሄደ በምድር ላይ የሚኖሩና ክርስቶሳዊ መከላከያ መድኃኒት የሌላቸው ሰዎች ስቃያቸው ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል መረዳት የሚያዳግት አይመስለኝም:: ሰው አእምሮውን መቆጣጠርና መምራት እስከማይችል ድረስ ተጽዕኖ የሚደረግበት ከሆነ የሰው የውስጥ ማንነቱ ሰላምን ዕረፍትንና እርካታን እየናፈቀ ማግኘት እስከማይችልበት ራሱን ሲሰቃይ ማየቱ ምንኛ ዘግናኝ ነገር ነው! ባለታሪኩ በኬኒያ በነበረበት ጊዜ በአንድ ግቢ ውስጥ ያገኛት የ666 አባል የልጅቷን ሥጋ በህይወት ሳለች በሰላ ቢላዋ ግራና ቀኛን እየቆረጠች ስትበላ ባያት ጊዜ አላስችል ብሎት ሴትየዋን በያዘው ሰይፍ ገድሏታል:: ከገደላትም በኋላ በስቃይ ደሟን እየጠጣ ሰውነቷን አገላብጦ ሲያያት በሰውነቷ ላይ በርካታ የ666 ንቅሳት ተደርጐባታል:: ጀርባዋን ገልበጥ አድርጐ ሲያያት ደግሞ ከትከሻዋ አካባቢ ጀምሮ በትልቁ 666 የሚል ተጽፎ ነበር::[42] በተጨማሪም አስቀድሞ ወደ ሌላ ክፍል ገብቶ በነበረበት ወቅት 15 ሰዎች ግማሽ የሞቱና በህይወት ያሉ ቁልቁል ተዘቅዝቀው ተሰቅለው ሳለ ግማሾቹ ከመቀመጫቸው፣ ከጉንጫቸውና ብልታቸው ተቆርጦ ሲወሰድና ደማቸው ሲጠጣ ተመልክቷል:: ባለታሪኩ በዚህ ሁኔታ ተጨንቆ ሳለ ነበር የ666 አባላት ከነበሩት አንዷ ሴት የነገው ተረኛ በማለት ከፍተኛ ሽብርና የንግግር ፍርሃት የለቀቀችበት::

ትኩረት ከዚህ ታሪክ የምናገኘው እውነት አለ:: ይኸውም የ666 አባላት ያለባቸውን ስቃይ ነው:: በታማኝነት ቢታዘዙ ሰይጣን አለቃቸው በቃኝ- ረካሁ የማይል የተለያየ ኢ-ሰብዓዊ ሥራውን የሚያሰራቸው ይሆናል:: ታማኝ ባይሆኑ ደግሞ እግዚአብሔር ለዓላማው ነጥቆ ካልታደጋቸው በቀር በቅድሚያ ተሰቅለው እንደተሰቃዩት በምድር ነፍሳቸው ከተለየችም በኋላ በሲኦልና በገሃነም ያሰቃያቸዋል:: ጠላት ይቀባል ጥላት ይለዋል ይህ ነው:: ስለሆነም አካሄዱ እንደ እግዚአብሔር ቃል ነው ወይስ አይደለም ብሎ ራስን መመርመር ከዚያም መስተካከል ያስፈልጋል:: ይህም የጠረጠረ ቤቱን አጠረ እንደተባለ ህይወትን ከሚመጣው ክፉ ሁሉ ለመከለል ያስችላል::

## 16. ዴቪድ አይኬ

አይኬ እ.ኤ.አ. በ1997 ዓ.ም. ዓለምን አድናለሁ ብሎ ወደ መካከለኛ ምሥራቅ የመጣ ሰው ነበር:: ይህ ሰው ዓለም በ1991 ዓ.ም. በታላላቅ መቅሰፍቶች ስለምትታወክ ላድናት ይገባል ባይ ነበር:: ነገ ይነሳ ይሆን?

እንግዲህ ሐሰተኛው ክርስቶስ (አውሬው) በዘመናችን ማነው የሚለውን ጥያቄ የተለያዩ ገፀባህሪያትንና ቡድኖችን በውስጣቸው ያሉትንም መሪዎች ለማየት ሞክረናል:: ቀደም ብሎ የተጠቀሱት ገፀ-ባህሪያት በሙሉ የ666ቱ አውሬ ላይሆኑ ይችላሉ:: ምክንያቱም አውሬው በቀጥታየሚታወቀው ሲገለጽና በተተነበየው መልክ ሲታይ ብቻ ስለሆነ ነው:: ከተጠቀሱት አንዱ ሆኖ ሊመጣ ይችላል:: በቀደመው ዘመን ኖረው አውሬው እንደሆኑ ስማቸው የተጠቀሰው ሰዎች በዘመናቸው ሊመጣ ያለው አውሬ መንፈስ ሰርቶባቸው ሊሆን ይችላል:: በአንድ ወቅት በክፉ መንፈስ ተሞልቶ የነበረ ሰው ሲሞት ይኖርበት የነበረው አጋንንት ለቅቆት ሌላ ሰው ውስጥ በመግባት እንደ ቀደመው ሰው ፍጹም ተመሣሣይ የሆነ ሥራን እንደሠራ ከታሪክ ይነበባል:: በዚህ ሁኔታ ቀድሞ የነበረው መንፈስ በስጋ በሌላ ጊዜ ሊገለጥ ይችላል ማለት ነው:: የ666ን ማንነት አጥርቶ ለማወቅ ወሳኙ ነገር ወደፊት የሚሆነውን በጥብቅ መከታተል ነው:: አንዳንዶችም 666 /አውሬው/ ሰብአዊ ማንነት ሳይሆን ድርጅት ነው የሚሉ አሉ::

## 3.6 666 ዘመን ማየል

የአንድ ነገር ምንነት ለአንድ ማንነት የከበረና ዋጋ ያለው ሆኖ ከታየ ያንን ነገር በተለያዩ መንገዶች ማሳወቁና በሁኔታዎች ሁሉ መግለጹ የባለቤቱ ጥረት ይሆናል:: ተወዳጅ ነገር አብልጦ በሁሉ ዘንድ እንዲታወቅ ይፈለጋል:: ቁጥር 666 ለአውሬው ስሙ እንደሆነ ሁሉ ስሙን ማግነን ይኖርበታል:: ለዚህም በሁኔታዎች ሁሉ ይህንን ስሙን ማስተዋወቅና ማሳወጅ ይኖርበታል:: ይህንንም ከሚከተሉት ተጨማሪ ዕይታዎች አውሬው ምን ያህል ቁጥሩን በፍጥነት እየገለጸው እንደሆነ ማየት ይቻላል:: ከዚህም የተነሳ ይህ ዘመን የ666 ቁጥር ዘመን ነው ወደ ማለት ሰዎችን እንዳመጣቸው ይታያል::[43]


- ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ውቅያኖስ የተላከችው የማትሰጥም መርከብ ስሟ ታይታኒክ በግሪክ ግዙፍ ማለት ነው:: የ666 ቁጥር ዋጋ አላት::
- ለመጀመሪያ ጊዜ ጨረቃ ላይ ያረፉት የ3ቱ ጠፈረተኞች ስም የእያንዳንዱ የስማቸው ፊደላት 6 ነበር::
- ከህዋ 6 የቴሌቪዥን ማስተላለፊያ መስመሮች ተበጅተው ነበር::
- የጨረቃ ጉዞ 6 ቀን ወስዶ ነበር::
- ወደ ህዋ የመጠቀው መንኮራኩር 6 ክፍሎች ነበሩት::
- የዚህ የአፖሎ በረራ በ6 ሚሊዮን ፓውንድ ይተመን ነበር::
- መንኮራኩሩ የምድርን ስበት አሸንፎ ወደ ህዋ ለመምጠቅ በሰኮንድ 6 ማይልስ መብረር ነበረበት::
- መንኮራኩሩ በጨረቃ ላይ ለማረፍ የቻለው በ6ኛው የበረራ ክፍልፋይ ላይ ነው::
- የጨረቃ ላይ ስበት የምድር 1/6ኛ ነው::
- ጠፈርተኞቹ ወደ ምድር የተመለሱት ከሳምንቱ በ6ኛው ቀን ነው::
- የተመለሱበት መሣሪያ ክብደቱ 6 ቶን ነበር::



- አንዋር ሳዳት ስዊዝ ካናልን የከፈቱት ጥቅምት 6 ነበር:: የጦር መርከባቸውም ስም «October 6» ትባል ነበር:: ከዚህ ቀን ጀምሮ ቁጥር 666 በኤኮኖሚው ዘርፍ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ማሳየት ጀምሯል::
- ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የዓለም የኤሌክትሪክ ገንዘብ አጠቃቀም ሥርዓት ቀዳሚ ቁጥር 666 እንደሚሆን ተሰማ::
- የጄኔራል ሞተርስ ድርጅቶች ዋና መ/ቤት 666 ቁጥርን መያዝና 1976 ዓ.ም. የ666 ቁጥር ዘመን መሆኑን መናገራቸው::
- የፊልም አምራች ድርጅቶችም 1976ን የ666 ዘመን ነው ማለታቸው::
- ዶክተር ጃክ ቫን ኢምፔ የተባሉት ሰው 666 በልዕለ-ኮምፒዩተር አማካይነት የዓለምን ህዝብ እንደሚቆጣጠር መግለጣቸው...::
- ዊሊያም ጋሪሰን የተባሉት ሰው ደግሞ ልዕለ-ኮምፒዩተሩ የዘመኑ የወርቅ ጥጃ መሆኑን ተናግረዋል::
- ወደፊት ለሰዎች የሚሰጠው ቁጥር በጨረር ኃይል ወደ ሰውነት በ1/1000000000ኛ ሰከንድ ውስጥ በፍጥነት እንደሚሰራጭ ታውቋል::
- ቀጥሎ የተዘረዘሩት በABC...Z ትንታኔ የፊደሎቹ ቁጥሮች ሲደመሩ 666 መስጠታቸው::[44]

1. DEVIL & SHEOL=666
2. NRONKS=666
3. PEOPLE & SIN=666
4. DEVIL and DRAGON=666
5. MARK OF BEAST=666
6. COMPUTER=666
7. BAR CODE OF U.P.C. MARK IS 666
8. LUCIFER and HELL=666
9. BIRDS OF FIRE=666
10. NEW PORT=666

ታዲያ ከላይ የተዘረዘሩት ትዕይንቶች በአጋጣሚ የተደረጉ ይሆን? ሊሆን አይችልም:: ለክብሩ ቀን የናፈቀው አውሬውና አበሮቹ በስውር የሚያፋጥኑት እንቅስቃሴ ነው:: ይህ ከሆነ እንግዲህ አውሬውም በደጅ ነው:: የቤተ ክርስቲያንም የመነጠቅ እንዲሁም የጌታ መምጫ የአውሬውም የፍርድ ጊዜ በደጅ ነው ማለት ነው::




J.C. Penney Card issued in 1980




## 3.7 ስለ 666 የሚነሱ ጥያቄዎች


666ትን በተመለከተ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ሰዎች ብዙ ጥያቄዎችን ይነሳሉ:: ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ይህ ቁጥር በሰው ላይ ተጽእኖ ያደርሳል አያደርስም? ቁጥሩ ያለበትን ዕቃ ልጠቀምበት እችላለሁ ወይስ አልችልም? ይህ ቁጥር ምሳሌያዊ ንግግር ነው ወይስ እውነት ይሆን? ምን ማድረግ አለብኝ? የመሳሰሉት ናቸው:: የመጽ. ቅዱስ ሰዎች ከላይ ለተጠቀሱት ጥያቄዎች የተለያዩ መልሶችን አቅርበዋል:: አንዳንዶቹ ዓለማውያን እኔ እስካመንኩበት ድረስ ምንም ሊያደርገኝ አይችልም ሲሉ ሌሎች ደግሞ በእከሌ የደረሰበትስ? ነገር በማለት የሆነውን አሉታዊ (ክፉ) ተጽዕኖ ሲጠቅሱ ይስተዋላል:: ቁጥሩ ባለበት ዕቃ የመጠቀሙን ነገር በተመለከተም ከላይ ከተጠቀሰው ሃሣብ እምብዛም የራቀ ሃሣብ የለም:: በቁጥሩ ሳያምኑ በመኪና ታርጋቸውና ሞተር ላይ ተጠቅመውበት ችግር ላይ የወደቁ እንዳሉ በአንደርቢ ዓይነት በቤታቸው የዕቃ መገለባበጥ ችግር የገጠማቸውና አባላቱ ሆነው ሳለ ብዙ ስቃይ የደረሰባቸው እንዳሉ ወቅታዊው ታሪክ ይመሰክራል:: የሚሆነውን ነገር እያዩ መቀበልና ማመን አለመቻል ከክህደት ተለይቶ አይታይም:: ቁጥሩ ምሳሌያዊ ነው እንጂ በተግባር የሚታይና በነባራዊው ዓለም የሚገለጽ አይደለም ለሚሉ ሰዎች አሁንም መልሱ ቀደም ብሎ በዕይታ 666 ውስጥ የተጠቀሰውን መመልከት ነው::

ስለ 666 በዕቃዎች ላይ መውጣትና በንብረቶቹ ስለመጠቀም ግን አንድ ልብ ሊባልበት የሚገባ እውነት አለ:: ይኸውም የሳይንስና የሐይማኖት፣ የሐይማኖትና የባሕል፣ የባሕልና የሳይንስ ... ግንኙነት በጣም በመቀራረብ ላይ መሆኑን ነው:: ይህም ማለት እግዚአብሔር በዳን. 12:4 ላይ በመጨረሻው ዘመን እውቀት እንደሚበዛ በተናገረው መሠረት ዛሬ ኮምፒዩተርና ሌሎች አስደናቂ ግኝቶች ወደ አለማችን ወጥተዋል:: እግዚአብሔር እውቀት ይሰጣል ለሰዎች ጥቅም ይውል ዘንድ ጥበብንም ይገልጣል:: ሰው አምራች ከሆነ በኋላ ግን እግዚአብሔር ጥበብና እውቀት ሰጥቶኝ ይህንን ሰራሁ ብሎ እግዚአብሔርን አያከብርበትም:: ስለሆነም ሰው የእውቀትና የጥበብ ባለቤት ለሆነው ለእግዚአብሔር ክብር እስካልሰጠ ድረስ ሰይጣን የዚህ ዓለም ገዢ እንደመሆኑ ኮምፒዩተሩን እኔ ሰራሁት ብሎ አምላክነቱን በመግለጥ ይብለጠለጥበታል:: ተከታዮቹም እርሱ ሰራው ብለው ያከብሩታል:: ሆኖም ግን ሰይጣን እግዚአብሔር በሰራው ነገር ላይ በማጭበርበር ሊከበርበት ይጥራል እንጂ የራሱ የሆነ ነገር የለውም:: ሰይጣን አዳምንና ሔዋንን ሊሰለጥንባቸው የቻለው በማጭበርበር እንደነበር ዛሬም በረቀቀ ዘዴ በማታለል ይገዛል::


ቁጥሩ ያለበትን ዕቃ ከመጠቀምና ካለመጠቀምም አኳያ አንባቢያን ሊይዙት የሚገባ እውነት አለ:: በአንድ ዕቃ ላይ 666 ተጽፏል ማለት ፍቺው ያ ንብረት ከሦስቱ በአንዱ ወይም በሁሉም ዓይነት ኮምፒዩተሮች ተመዝግቧል ማለት ነው:: በቀላሉ ዕቃው ከስርቆትና ከአደጋ ለመጠበቅ በሚችልበት ሁኔታ ውስጥ ተመዝግቧል ነው:: ስለሆነም ይህንን ዕቃ



Arab-owned car in Jerusalem bearing on its license the prefix "666" (All Arab-owned vehicles must be pre with "666" in order that Israel may quickly identify enemy in the event of war.) This depicts the "666 System" Israel.



በቻይና የተሠራው ሸሚዝ






Financial and government institutions in U.S. and abroad are utilizing variations of this horizontal logo "666."

በአሜሪካ የሚገኙ አንዳንድ የገንዘብ ነክ ተቋሞች ይህንን አርማ ይጠቀማሉ



## 3.8 የ1997 ዓ.ም. መረጃዎች

ቀደም ባሉት ገፆችና ምዕራፎች 666 በተለያዩ መልኮች በመታየት ላይ እንደሆነ ተመልክተናል:: ቀጥሎ ደግሞ የ666 አጠቃቀም የት እንደደረሰ እንመለከታለን::

ቀደም ባሉት ገፆች 666ን በሰው ግንባርና በእጅ ላይ ለመስጠት በእንስሳት እንደተሞከረና ውጤታማ እንደሆነ ወደፊት ግን በሰው ላይ ለመሞከር ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ለማመልከት ሞክሬያለሁ በአሁኑ ወቅት ደግሞ በቀጥታ በራዕይ 13÷16-18 እንደተፃፈው በሞንዴክስ የገንዘብ አጠቃቀም ስርዓት(System) ምን እርምጃ እየተወሰደ እንደሆነ ከዌብ ሳይት " www.google.com " የተገኘውን መረጃ እንመለከታለን::

### መታወቂያ ካርድ

በቀድሞ ዘመናት ሰዎች ማንነታቸውና የማን ወገን መሆናቸው እንዲታወቅ በሰውነታቸው ላይ ምልክት ይደረግ ነበር:: አንድ ሰው ወደ ማናቸውም ቦታ ቢሄድ ምልክቱ በሰውነቱ ላይ ስላለ ተለይቶ ይታወቅ ነበር:: በዚያን ጊዜ የተጀመረው የመለያ ምልክት ጉዳይ እያደገ ሄዶ ቀደም ባሉት ዓመታት በወረቀት (በካርድ) ግልጋሎት ሲሰጥ ቆይቷል:: የቀድሞው ካርድ የግለሰቡን አገር ፣ ከተማ፣ ቀበሌ፣ ወረዳ የመታወቂያ ቁጥሩንና ስሙን ወዘተ ይይዝ ነበር:: ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ግን የመታወቂያው ጠቃቀም ረቀቅ ብሎ በመሄድ ፣ከተራ መታወቂያ ካርድነት

ወጥቶ ወደ ክሬዲት ካርድና ማስተር ካርድ ብሎም ወደ ፕላቲኒየም ካርድ ደረጃ ደርሷል:: እነዚህ ካርዶች ብዙ ዓይነት ናቸው :: ግለሰቡን በብዙ አቅጣጫ ይጠቅሙታል:: ስለ ግለሰቡ ያለውን መረጃ ፣በባንክ ያለውን ገንዘብ መጠንና ስለ እርሱ የሚፈለገውን ዝርዝር መረጃዎችን ያቀርባል::

## የገንዘብ አያያዝ ሲስተም

በዓለማችን በዓይነት መነገድ ከተካሄደበት ከጥንት ዘመን ጀምሮ ሰዎች ንብረትን ( ገንዘብን) የሚለዋወጡባቸው መልኮች እንደየሃገሩና ሕብረተሰቡ ሲለዋወጥ ቆይቷል:: ሰው ሲነግድ ውሎ ያገኘውን ገንዘብ ይዞ ወደ ቤቱ ሲመለስ ወርሮ- በሌዎች (ማጅራት-መቺዎችና ዘራፊዎች የነገደበትን ገንዘብ በመዝረፍ ሙልጭ አድርገው ሲወስዱበት ባዶ እጁን ከመቅረቱም ባሻገር ህይወቱን ያጣበት ጊዜያት ነበሩ:: ከእነዚህም ግድያዎች፣ ዝርፊያዎች፣ ሁከቶችና ሰላም ማጣት የተነሣ ነጻ ለመውጣት ሰው አማራጭ መፍትሄዎችን ሲፈልግ ኖሯል:: ከእነዚህም የተለያዩ አማራጮች ውስጥ መሬት ቆፍሮ ፣ (በልዩ ምስጢራዊ) ቦታ ገንዘቡን ማስቀመጥ አንዱ ነበር:: ለምሣሌ በአሜሪካ ይጠቀሙበት ከነበረው ገንዘብ አያያዝ ሲስተሞች አንዱ ትልቅ ሣጥን ሰርቶ የመጀመሪያውን መሣቢያ (drawer) ቀጥሎም አልፎ ወደ ግራ(ቀኝ) ሌላ መሣቢያ ቀጥሎም ወደ ውስጥ ገንዘብ የሚቀመጥበት ቦታ ማመቻቸት ነበር:: በመቀጠልም ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ እስካሁን በተለያየ መልኩ ግልጋሎት እየሰጠ ያለውን ባንክ የመጠቀም ስርዓት ተጀምሯል:: አዎን ሰዎች ሁሉ የሠሩበትን ገንዘብ ወደ ባንክ ወስደው አስቆጥረው ደረሰኝ



በመቀበል ገንዘባቸውን በባንክ ማስቀመጣቸው ችግሩን በመጠኑ ቢቀንሰውም ፈፅሞ ሊያጠፋው አልቻለም:: ስለሆነም ሌላ የተሻለ ዘዴ መፈለጉ አስገዳጅ ሆኗል:: ይኸውም እያንዳንዱ ሰው ያለ ገንዘብ እንዲገኝ ማድረግ ነው:: ይህም ስርዓት « ገንዘብ አልባው ስርዓተ ማህበር (ሎሮቋሻ ቁስቋቋ መቄሰሽስቋቨ) ይባላል::

## ገንዘብ አልባው ስርዓተ ማህበር ( ገስማ)

ገንዘብ አልባው ስርዓተ ማህበር ማለት ብርን፣ ሩፒን ፣ ዩሮን ወይም ዶላርን በእጅ ይዞ ሣይገበያዩ ገንዘቡ በባንክ ወይም በሌላ ስርዓት ሥር ሆኖ በካርድ አጠቃቀም ስርዓት(ሎሮቈሳሽቃሽ መቨቋቋስቂ ) ብቻ መጠቀም ማለት ነው:: ለምሳሌ: በቀድሞው ዘመን ( አሁንም) አንድ ሰው ዕቃ ለመገብየት ገበያ ቢሄድ የሚፈልጋቸውን ዕቃዎች ከገዛ በኋላ ዋጋውን ገንዘብ ወይንም ብር ቆጥሮ ይከፍል ነበር የካርድ ሲስተም ግን ይህንን ያስቀራል፣ ይህም ሲሆን ሰው ገንዘብ ይዟል ተብሎ ለመዝረፍ አደጋ አይጣልበትም ማለት ነው::

የካርድ ሲስተም ማለት በሚሊዮን ወይም በቢሊዮን የሚቆጠሩ መረጃዎችን በውስጡ የሚይዝና ከመገበያየት አልፎ ሕይወትንም ለማስጠበቅ እስኪቻል ድረስ ጥቅም እንዲሰጥ ተድርጎ የተዘጋጀ ነው:: ይህ ሲስተም በአሜሪካና በሌሎችም ያደጉ ሀገሮች ጥቅም መስጠት ከጀመረ አመታት አልፈዋል:: ለምሣሌ አንድ ሰው 10 ሚሊዮን ብር/ዶላር/ በባንክ አለው እንበል ያለው ብር በሙሉ በኤሌክትሮኒክስ ካርድ ውስጥ ይመዘገባል:: ግለሰቡ የሚፈለገውን ንብረት ከገዛ በኋላ ያለውን ኤሌክትሮኒክስ ካርድ በተዘጋጀው

ማሽን ውስጥ ሲያሳልፈው ሊከፍል ያለውን ገንዘብ ይቀንስና ቀሪውን ካርድ ውስጥ እንዳለ ይተውለታል:: ይህ ማለት የመገበያያ ሲስተሙ በባንኮች ውስጥ ለውስጥ ነው የሚሆነው:: ግለሰቡ ገንዘብ ይዞ በመዞር ከሚመጣው ማናቸውም ዓይነት አደጋ ተጠብቋል ማለት ነው:: ካርዱ ቢጠፋና በሌላ ሰው ቢገኝ መክፈቻ ቁልፍ ቁጥሩን(Pin-Number) የሚያውቀው ግለሰቡ ብቻ ስለሆነ ያገኘው ሰው ሊጠቀምበት አይችልም:: በዚህ ሲስተም በመጠቀም ህብረተሰቡ ገንዘብ በእጁ ሳይዝ በካርድ ብቻ ይጠቀማል ማለት ነው:: በቀድሞ ጊዜያት ጥቅም መስጠት ከቻሉት የካርድ ዓይነቶች ውስጥ ያለ ኤሌክትሮኒክስ የሚሰራው ካርድ፣ ማስተር ካርድ ፣ ክሬዲት ካርድና ፕላቲኒየም ካርድ ወዘተ ይገኛሉ:: ሆኖም ግን እነዚህ ካርዶች ጥራት ያለውን አገልግሎት ከመስጠት አንፃር አነስተኛ ነቀፌታ ስለሚታይባቸው የተሻለ ዓይነት የገንዘብና የራስ ማንነት መቆጣጠሪያ ካርዲንግ ሲስተም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል:: ከዚህም በመነሣት ሞንዴክስ ኢንተርናሽናል በመባል የሚታወቅ ሲስተም ተዘርግቷል::

ዓለም አቀፋዊው የሞንዴክስ ካርድ(Mondex International)

ስለ የሞንዴክስ ዝርዝር ነገሮች ከማየታችን በፊት የቃሉን ትርጉም መመልከቱ ይጠቅማል::

MONDEX ማለት ባጭሩ Money on your hand ማለት ሲሆን ዘርዘር ባለ መልኩ ደግሞ MON = Monetary ሲሆን - Dex = Dexter = Right-hand side ማለት ነው:: የዌብስተር



ኢንሳይክሎፒዲያ ዲክሽነሪም MONDEX ማለት Monetary Dexter እንደሆነ በማሣየት Monetary ከገንዘብ ጋር የተያያዘና Dexter ደግሞ በቀኝ እጅ የመሆንን ሁኔታ እንደሚያመለክት ይገልጻል:: አጠቃላይ ትርጉሙ በቀኝ እጅ ላይ ያለ ሃብት( ገንዘብ ) ማለት ይሆናል:: በሌላ አነጋገር ሞንዴክስን ሰይጣን ከገንዘብ በስተኋላ ሆኖ ሌሎች አምላኮች( gods) ተቆጣጣሪ የሆኑበትን ረቂቅ አሠራር አመልካች ነው የሚሉም አሉ::

ባዮ-ቺፕ(Bio-Chip)

ሞንዴክስ ከላይ የተጠቀሱት ዓይነት ትርጉም ቢኖረውም በሌላ መልኩ የዚህን ዓይነት የገንዘብ አጠቃቀም ሲስተም የዘረጋው ኩባንያም ነው:: ሞንዴክስ የገንዘብ አልባውን ስርዓተ ማህበር ለመመስረት ታጥቆ የተነሣ ኩባንያ ነው:: ይህንንም ለማካሄድ ከሃያ የሚበልጡ አገሮች ጋር ግንኙነት አድርጓል:: የሞንዴክስ ኩባንያ ሲስተሙን ለመዘርጋት የሚጠቀመው በሞቶሮላ ኩባንያ ነው:: የሞቶሮላ ኩባንያ የሞንዴክስ ኩባንያ የሚጠቀምባቸውን ማይክሮቺፕስ (ባዮ-ቺፕስ) ያመርታል:: እነዚህ ባዮ-ቺፕ በመባል የሚታወቁት መሣሪያዎች ኤሌክትሪካዊ በሆነ መንገድ ከሰውነት ጋር በተያያዘ መልኩ የሚሠሩ ናቸው:: እያንዳንዱ ባዮ-ቺፕ 7 ሚሊ ሜትር ቁመትና 0.75 ሚ/ሜትር ስፋት ያላቸውና አጠቃላይ መጠናቸው የሩዝን ቅንጣት( መጠን) የያዙ ናቸው:: ባዮ-ቺፕስ ግልጋሎት መስጠት የሚችሉት በሰው አካል ክፍል ውስጥ ሲቀመጡ ብቻ ነው:: በባዮ-ቺፖች ውስጥ

ሊቲየም በመባል የሚታወቅ ባትሪ አለ ፣ ይህ ረቂቅ ባትሪ የሚሰራው የሰው ሰውነት የሙቀት መጠን (ቴምፐሬቸር) በሚለዋወጥበት ወቅት ነው:: ለምሣሌ BT 952000 በመባል የሚታወቀው በዶክተር ካርል ሳንደርስ የተመረተው ባዮ-ቺፕ በ17 የአዲሱ ዓለም ስርዓት ስብሰባዎች ላይ ማብራሪያ ተሰጥቶበታል:: ማብራሪያውም ባዮ-ቺፕ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሰውን ማንነትና የኢኮኖሚን ስርዓት በአግባብ ከመጠቀም አንፃር ግልጋሎት እንዲሰጥ ስለማድረግ ነው:: የሞንዴክስን ስማርት ካርድ በትክክል ስራ ላይ ለማዋል ከፍተኛ ዋጋ ተከፍሏል::

## የሞንዴክስ ባዮ-ቺፕ (ቬሪ-ቺፕ) ሲስተም አጠቃቀም ስርጭት

የገንዘብ አልባውን ሲስተም አጠቃቀም በተግባር ለመተርጎም በከፍተኛ ደረጃ በኦንታሪዮ፣ በካናዳ፣ በእንግሊዝና በአሜሪካ ሙከራ ተደርጓል:: በካናዳ የሚገኙት ባንኮች በሙሉ በሞንዴክስ ሲስተም ለመጠቀም ፈርመዋል:: ይህንን አሰራር በመላው ዓለም ለማስረፅ ዕቅድ የወጣው እ.ኤ.አ. በ1998 ዓ.ም. ነው:: በአሁኑ ወቅት የካናዳውያን ዓለም አቀፍ ንግድ ባንክ ገንዘብ አልባ የሆነውን ስርዓት ከመጠቀም አንፃር ሞዴል( ምሣሌ) እንዲሆኑ በብራምተን( ኦንታሪዮ) ከተማዎች ቅርንጫፎችን አቋቁመዋል::

በሃያ አገሮች የሚገኙ ከ250 የሚበልጡ ድርጅቶች የሞንዴክስ ባዮ-ቺፕ ሲስተምን ለመጠቀም ፈቅደዋል:: ከዚህም የተነሣ ሲስተሙን ወደ አገራቸው ለማስገባት በዝግጅት ላይ ናቸው:: አንዳንዶቹም ጀምረዋል:: የሞንዴክስን ሲስተም ለመጠቀም



ከወሰኑት አገሮች ውስጥ ዩናይትድ ኪንግደም(እንግሊዝ)፣ ካናዳ፣ አሜሪካ ፣አውስትራሊያ፣ኒውዚላንድ፣እስራኤል፣ሆንግኮንግ፣ቻይና፣ ኢንዶኔዢያ፣ማካው፣ማሌዥያ፣ፊሊፒንስ፣ሲንጋፖር፣ታይላንድ ፣ህንድ፣ታይዋን፣ስሪላንካ፣ኰስታሪካ፣ ጉዋቲማላ፣ ኒካራጉዋ፣ ፓናማ፣ሆንዱራስ፣ኤልሳልቫዶርና ብራዚል ይገኛል:: ወደፊት ባዮ-ቺፕስን ለአባል አገሮች ለማዳረስ በከፍተኛ ደረጃና በብዛት ባዮ-ቺፖች መመረት አለባቸው:: ስለሆነም ባዮ-ቺፖቹን ለማሰራጨት ሞቶሮላና ሞንዴክስ ኩባንያዎች በቅንጅት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ እስከ 1,000,000,000 ( አንድ ቢሊዮን) ባዩቺፖች ማምረት ይኖርባቸዋል:: በአሁኑ ጊዜ ካለፈው ዓመት ጀምሮ እነዚህ ባዮ-ቺፖች መመረት ጀምረዋል:: የባዮ-ቺፖች መመረት ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ሴፕቴምበር ኢለቨን ( Sept.11) የአሜሪካው አለማአቀፍ የንግድ ማዕከል ጥቃት ከደረሰበት በኋላ ነው::

## የባዮ-ቺፖች ማስቀመጫ ( የቬሪ ቺፕስ) ትክክለኛ ቦታ ( Biochips & Verchips)

ባዮ-ቺፑን ያዘጋጁት ኩባንያዎች ስለሚቀመጥበት ተስማሚ ቦታ ጥናት አድርገዋል:: ይህንንም ጥናት ሲያደርጉ ተስማሚው ቦታ የሰው ሰውነት መሆኑንን አረጋግጠዋል:: ባዮ-ቺፑን እንደ ክሬዲትና ማስተር ካርዶች በቦርሣ ውስጥ መያዝ አይቻልም:: ምክንያቱም ከሰውነት የደምና የአካል ሙቀት ጋር በተያያዘ መልኩ ስለሚሠራ ነው:: ሣይንቲስቶች

ጥናት አድርገው ተስማሚውን ቦታ ለማግኘት ከ1.5 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወስደባቸዋል:: ባዮ-ቺፑ በካርድ ውስጥ የሚደረግ ከሆነ የመቆረጥ፣ የመሠረቅና የመጥፋት እንዲሁም መረጃ ዘግቦ የመያዝ አቅሙ ሊጠፋ ወይም ደግሞ በአንድና በሁለት ዓመታት ጊዜ ውስጥ አገልግሎቱ ሊያበቃ (expire) ስለሚችል እንዲሁም የትክክለኛው የገንዘብ አጠቃቀም አደጋ ሊገጥመው እንደሚችል ተረጋግጧል:: ከዚህም በመነሣት ብቸኛውና አስተማማኝ የባዮ-ቺፕ መቀመጫ ስፍራ በመርፌ መልክ በመወጋት ለስለስ በሚለው የሰውነት ክፍል በቀኝ እጅ ጀርባ ወይም በግንባር (አንጎል) ውስጥ ከፀጉር መብቀያ ሥር መደረግ እንዳለበት ተጠንቷል:: ይህ ባዮ(ቤሪ) ቺፕ በሰውነት ውስጥ ሲቀበር እስከ 20 (ሃያ) ዓመታት ያህል መቆየት ይችላል::


ይህ ስፍራ የተመረጠው በቀላሉ ሊገኝ የማይችልበት ቦታ ስለሆነ ነው:: ሆኖም ግን ይህ ባዮ-ቺፕ በቀዶ ጥገና ወይም በሌላ ምክንያት ከአካል ተለይቶ ቢወጣ መሣሪያው ( ባዮ-ቺፑ) ፈንድቶ ግለሰቡ ሊቲየም በተባለው ኬሚካል ሊጎዳ ይችላል:: ዶ/ር ሳንደር ሊቲየምን መጠቀም አጥብቀው ተቃውመውታል:: ዓለምአቀፋዊው የብክለት ተከላካይ ባለስልጣን ( Global Positioning System= GPS) እርዳታና ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚችል መረጃዎች ይጠቁማሉ::

ይህ የባዮ-ቺፕ የገንዘብ መቆጣጠሪያ ዘዴ በዓይነቱ አዲስና የበለጠ ጥቅም ሰጭ ከመሆኑ የተነሣ ቀደም ብሎና አሁን




ከፍተኛ ጥቅም እየሰጡ ያሉትን ልዩ ልዩ የካርዶች አጠቀቀም የሚያስወግድና የሚተካ ይመስላል:: የቀድሞዎቹ ካርዶች በኪስ (በቦርሣ) ውስጥ የሚያዙ በመሆናቸው በቀላሉ ሊጠፉ ይችሉ ነበር:: በዚህ ስርዓት (ባዮ-ቺፕ ሲስተም) በጣም ሃብታም የሆኑ ግለሰቦች መጠቀም ጀምረዋል:: በሌሎች ታፍኖ ከመወሰድና ከመሰረቅ ሊጠብቃቸው እንደሚችልም ተረጋግጧል:: ባዮ-ቺፑን በሚጠቀሙበት ጊዜ ግልጋሎት የሚሰጣቸው እንደ "በርቀት መቆጣጠሪያ መሣሪያ =Remote Control " ሆኖ እየተከናወነ ስላለው ሁነት ለባለስልጣናት መረጃ በማቀበል ነው:: ስለሆነም ባዮ-ቺፑን ለመቀበል ሰው ሁሉ ከፍተኛ መነሳሳት ጀምሯል:: በአሁኑ ጊዜወደ 7000 (ሰባት ሺ) የሚደርሱ ቺፖች ሲሸጡ ከ1000 የሚበልጡ ደግሞ በሰው ሰውነት ውስጥ ተቀብረዋል:: በተጨማሪም ሜክሲኮአውያን ልጆችን ከአፈና ለመከላከል ባዮ-ቺፖች ግሩም እንደሆኑ በስፔይን የሚገኘው የባጃ ክለብ ለመግዛት ባዮ-ቺፑን እንደተጠቀሙ ተዘግቧል:: በራዕይ 13፥16-18 ተፈፀመ ማለት ነው:: ክብር ለእግዚአብሔር መዳን ለሰው ልጆች ይሁን አሜን::

በመርፌ መልክ ( Syringe-Injection ) በቆዳ (በግምባር) ውስጥ የሚቀመጠው ባዮ-ቺፕ ይህንን ይመስላል:: ( ሲ.ይ)



ልዩ ልዩ ዓይነት የሞንደክስ ካርዶች






ክርስቲያናዊ (ቤተ ክርስቲያናዊ ምላሽ)

በዮሐንስ ራዕይ ውስጥ ከበድ ብለው ከተጠቀሱትና የቅርብ ክትትል እንዲሁም ምርመራ ከሚጠይቁ ጥቅሶች ውስጥ አንዱ በ13፥18 ላይ የተጠቀሰው ነው።ቃሉም «ጥበብ በዚህ አለ፣ አዕምሮ ያለው

የአውሬውን ቁጥር ይቁጠረው፣ ቁጥሩም 666 ነው» የሚለው ነው:: ጥበብ በዚህ አለ አዕምሮ ያለው የአውሬውን ቁጥር ይቁጠረው ይላል ለምን አዕምሮ ያለው ተባለ? ጥበቡስ ምንድር ነው?

መፅሐፍ ቅዱስ አንተ ታካች ወደ ገብረጉንዳን ሂድ፣ መንገድዋንም ተመልክተህ ጠቢብ ሁን (ምሣ6:1) በታካች ሰው እርሻ አዕምሮ በጎደለው ሰው ወይን ቦታ አለፍሁ፣ እነሆ ሁሉ እሾህ ሞልቶበታል፣ ፊቱንም ሳማ ሸፍኖታል፣ የድንጋዩም ቅጥር ፈርሶአል::.. እንግዲህ ድህነትህ እንደ ወንበዴ፣ ችጋርህም ሰይፍ እንደታጠቀ ሰው ይመጣብሃል:( ምሣ 24÷30-34) ይላል::

የአሁን ዘመን በሉቃስ 21÷34 እንደተጠቀሰው እጅግ የመባከኛና ልብ የሚከብድበት ዘመን ነው:: የሰው ልጅ የሚሄድበት የእውቀት ፍለጋ መስመር እጅግ ብዙ ስለሆነና ወደ አዕምሮ የሚገባውና ሰውንም የሚቆጣጠረው ( Internalization) ስርዓት በአመዛኙ ከአቅም በላይ ስለሆነ ወደ እግዚአብሔር ቃል በጥንቃቄ ቀርቦና አጥንቶ ባለአዕምሮና አስተዋይ መሆን የቸገረበት ዘመን ነው:: ይህም ደግሞ በክፉ ሃይላት ተፈላጊ ነው:: በትንቢቱ እንደተነገረው ሰው እንደ ሣጥናዔል ምቾት የሚፈልግበት ጊዜ ነው:: የሰው የአዕምሮው የመያዝና የመማር አቅሙ ከጊዜ ከሁኔታና ከቦታ የተነሣ ውሱን ነው:: በዚህ በሰው ውሱንነት ላይ ጥልቅ የሠይጣን ውጊያ ተካሂዶበት ( ራዕይ2:24) አብልጦ ካልጠነከረና ከብበ ከሚለበልበው የሣማ ሕይወት ካላመለጠ ወደሚብሰው ለብላቢ ሕይወት መዝለቁ የማይቀር ነው::



ዛሬ የሰው አዕምሮ በምን ተሞልቷል? ብለን ብንጠይቅ ብዙ ማለት ይቻላል:: እግዚአብሔር የለም! ወይም ሰው እግዚአብሔር ነው! ባይነት ሲያልና ገሃነም የለም፣ ሰው በነፍስ ሽክርክሪት( ደጋግሞ በተለያዩ መልኮች ይወለድና) ዘለዓለም ይኖራል፣ አጋንንት ወደ ቅድስና ይለወጣሉ፣ ሰው ከግዑዝ ነገር ብቻ የተፈጠረ ነው፣ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም:: ክፉ የሚባል የለም ሁሉ መልካም ነው፣ ኢየሱስ ከሠማይ አይመጣም ፣ በምድር የለም የሞቱም ሁሉ ይድናሉ፣ ቅጣት የለም፣ ሰው አንዴ ሞቶ አይቀርም ደጋግሞ ይነሣና አዲስ አካል ይለብሣል፣ ብቸኛው እውቀት ዘመናዊው ሣይንስ ነው! ወዘተ.. የሚሉ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የማይሄዱና የማይስማሙ እውነት መሣይ አሳሳች እውቀቶች በተለይ በተማሩ ሰዎች አዕምሮ ውስጥ አሉ:: በተለይ ሣይንስ እያደገ በመጣ ቁጥር የሚከሰቱ አንዳንድ ግኝቶች ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ስለሚጣረሱና የሰውን አዕምሮ ስለሚበክሉ ሰው በከፍተኛ ጥንቃቄ ካልተጓዘ ባለአዕምሮ ሆኖ ወደ እግዚአብሔር ጥበብ ይደርሣል ማለት ዘበት ሊሆን ይችላል::

በአንድ ግለሰብ( አማኝ) ውስጥ ተጠራሽ ( ርስ በርሱ የሚጋጭ) እውቀት ካለ ሰው በሚኖረውና በሚያደርገው ነገር ወይም ልምምድ ዳተኛና ተጠራጣሪ ይሆናል:: ያመነበትን በሙሉ ሃይሉ ለመደገፍ ያላመነበትን ለመቃወም ሃይል የሌለው ሽባ ይሆናል:: ከዚህም የተነሣ ከአማኝነቱ ይልቅ ወደ ከሃዲነቱ ያዘነብላል:: ከዚህም የተነሣ ከመጨረሻው አስጨናቂ ዘመን ጎራ ይገባና ሰው የአምልኮት መልክ ያለው ከዳተኛ ይሆናል( 2ኛጢሞ3:1-9 ) ሰው እውነት እስከሌለው ድረስ የሐሰት ወዳጅ መሆኑ አይቀርም፣ ይህም ከሆነ ሰው ባሪያ

ነው ማለት ነው( ዮሐ8÷32 ):: ስለሆነም በለፀጉ በተባሉት አገሮች የኖሩትን ስናይ አስቀድሞ ጠንካራና ታማኝ የነበሩ አማኞች ጌታን ትተው ወደ ዓለም በመሄድ ከሃዲ የሆኑት ከእውነት ስለተፋቱ ነው:: ከእውነት የተለያየ ሰው ደግሞ አዕምሮውን ከሚወርር ማናቸውም ድብቅና ግልፅ ክፉ ኃይል ራሱን የሚከላከልበት ኃይል አይኖረውም:: ስለሆነም ወደ መፅሃፍ ቅዱስ ተመለስ ( Back to the Bible) እየተባለ የሚሰበክለት ትውልድ ቶሎ ካልታዘዘ በስተቀር የ666 ትን ሚስጥር የሚረዳበትን አዕምሮ ያገኛል ማለት ዘበት ነው::

የ666 ትንቢት መፈፀም እውነት እስከሆነ ድረስ የክርስቶስ ነን የምንል ሁሉ ቸልተኛና ፈራጅ መሆናችንን ትተንና ራስን እንደልዩ አዋቂ ባለመቁጠር ራሳችን ኖረን ከጌታ በነፃ የተቀበልነውን እውነት ላላወቁ ጎረቤቶቻችን ልናስረዳቸው ይገባል:: እውነቱንም ልናሳውቃቸውና ልንፀልይላቸው ይጠበቅብናል::

ከኃላፊነትና ከተጠያቂነት ለመሸሽ ብሎ ለ666 ከነባራዊ ዕውነት በራቀ መልኩ ትርጉም በመስጠት በመተርጎምና የሰውን አዐምሮ ማጨለም ክርስቲያናዊነት አይደለም:: ይህ እንደበለዓም በዚህ ዓለም ሃብት ፍቅር ታውሮ የነብይነቱን ሚና መጣል ነው:: ይህ ለአማኝ አይገባም:: ማንኛውም ክርስቲያን ነኝ ባይ አማኝ ሁሉ ቃሉ ለሚጠይቀው ሁሉ አወንታዊ ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል:: ኃይል ከጠፋ ኃይልን ስጠኝ እንደ ነብዩ በለዓም ዓይኖቼን ክፈት ብሎ መጸለይና ኃይልን መቀበል እንጂ በፍቅረ ንዋይና ክብር ታውሮ ዓይኗ የተከፈተውን አህያ መደብደብ መንፈሣዊነት አይደለም::



የራዕይ 13:18ቱ 666 በባዮ-ቺፕና( ማይክሮ ቺፕ) ውስጥ ሆኖ እንደተተነበየው ወደ ምድሪቱ ነዋሪዎች መጥቷል:: የቁጥሩ ስርዓት አጠቃቀም ወደ አገራችንም ሊመጣ ይችላል:: ሣይንቲስቱ እንዳጠኑት ለቺፑ መቀመጫነት ከግራ እጅ ይልቅ የቀኝ እጅ የበለጠ አመቺ መሆኑን ማረጋገጣቸው እጅግ ሊደንቀን ይገባል:: ምክንያቱም ትንቢቱ የሚለው ሰዎች በቀኝ እጃቸው ቁጥሩ/ምልክቱን እንዲቀበሉ ያደርጋል ስለሚል ነዋ! በ2ኛተሰ2÷6-7 እንደተጠቀሰው የአመፅ ኃይል( አውሬው) የሚሰራው በሚስጥር ነው:: በአሁኑ ጊዜ ላይ በየዕቃዎቹ ላይ የምናየው UPC = Universal Production Code ) ላይ 666 ቁጥር አለ:: ሆኖም ግን ይህ ቁጥር በሚስጥር ነው የጠቀሱት ለምን? ሌሎች ከ18 ዲጂት የማይበልጡ ቁጥሮች በገሀድ ሲነበቡ 666 ትን በስውር( በኮድ መልክ) ማስቀመጥ ለምን አስፈለገ? አዎን አመፅ በሚስጥር ወደ ዓለም ሁሉ እንዲሰራጭ ነው:: 666 ግልፅ ሆኖ ከተፃፈ ክርስቲያኑ ነቅቶ ሊቃወም ስለሚችል ነው:: ይህ ጥበብ ይመርመር? መሞትህ ካልቀረና ከሞት በኋላ ወደ እግዚአብሔር ፍርድ መቅረብህ ካልቀረ ያንተ(ያንቺ) በዶክተርነትህ(ሽ) በኤጲስ ቆጶስነትህና በክቡርነትህ፣ በዝነኝነትህ በአገር አቀፍም ሆነ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ባገኘ ኸው(ሽው) ፕሮፌሰርነትሽ(ህ) ታዋቂ ሆነህ ስትሞት(ች) ሁሉን የምትጥለው(ጥይው) ከሆነ ዛሬ ፈጣሪህን በማጣጣልህ በኩራት ንግግርና ድርጊት መመላለስህ ምን ይጠቅምሃል? (ሻል)? እንኳን ሚሊኒየር ቢሊኒየር ሃብታም ብትሆን እውነተኛ ፈጣሪህን(ሽን) መካዱ ሞት ካልቀረ ጥቅሙ ምንድነው? በዓለም ያለውን ሃብት ሁሉ አንዱ ቢጠቀልለው ሙሉ በሙሉ ወዳላየው መንፈሣዊ ዓለም

መሄዱና መጠየቁ የማይቀር ከሆነ ነገ ከማፈር ዛሬ እውነትን ለመያዝ መሮጥ አይበጅም? ያለ ጥያቄ ይበጃል !

ስለ ባዮ-ቺፕ ተጨማሪ መረጃዎች ( http:// www.av1611.org/666.html)

ሰዎች በወቅቱ እየተጠቀሙባቸው ያሉት የተለያዩ ዓይነት ካርዶች በመተውና በማስወገድ ወደ አዲሱ በቀኝ እጅና በግምባር ላይ ስለሚሰጠው የባዮ-ቺፕ መታወቂያ እንደሚጓዙ ብዙ መረጃዎች በመውጣት ላይ ይገኛሉ:: ባዮቺፖቹ=ችን ባለመቀበል ለመግፋት መሞከር በብዛት አይታይም፣ አማራጮችም እየተወገዱ ነው:: ከነዚህም ውስጥ ዋነኞቹ:


- ❖ እ.ኤ.አ. ከ1974 ዓ.ም. ወዲህ አዲስና እንግዳ የሆነ ምልክት በምርት ውጤቶች ላይ መታየት ጀምሮአል:: ይህም የ « UPC » ( ዓለም አቀፍ የምርት መለያ ቁጥር) ምልክት ነው:: በዚህም ኮድ 3 የተደበቁ ቁጥሮች አሉ እነርሱም 666 ናቸው:: በተጨማሪም FH ከምልክቱ ስር ይታያል F=«ለ»Forhead H=«ለ» Hand የቆሙ ናቸው:: ይህም UPC ከቁስ ወደ ሰውነት ሊሸጋገር መሆኑን የሚያሳይ ነው:: (

General Interest-Literature & Arts-Art
ISBN 0-8361-9254-0

F H







በግልጽ ዓይናችን የማይታዩት ሶስቱ 666 እና FH ( ሲይ)

- ❖ አምኒ ተብሎ በሚጠራ የሰኔ 1991 (እ.ኤ.አ) መፅሔት ( ገፅ. 59) ላይ አንድ አስደናቂ ዓረፍተ ነገር ተፅፎአል:: ፅሁፉም ገንዘብና ( Cash) የክሬዲት ካርድ አገልግሎት በፍጥነት ያረጃል ያከትማል የሚል ነው:: በተጨማሪም የኢንፎርሜሽን ዊክ ፅሁፍ ( ኦክቶበር 11 1993 ) በሽፋኑ ላይ በድፍረት ገንዘብ አልባውን (Cashless ) ህብረተሰብ በካርድ ውስጥ.. « በአሜሪካ «ገንዘብ አልባዋ ህብረተሰብ በመሆን ላይ ናት » በማለት ገልጧል ( ገፅ 4 )::
- ❖ « ልዩ መስህብና ጥቅም ሰጭ የሆኑ ካርዶች( Smart Cards) መጠቀም አስቀድሞ በልብ ወለድ መልክ ታይቶና ተሰምቶ የነበረውን አሁን ወደ ገሃድ እናመጣዋለን» የሚለው የኒውስ ዊክ መፅሄት( ጁላይ 31 1989 ገፅ 54) ደግሞ ሌላው መረጃ ነው:: ኒውስ ዊክ እንደዘገበው እነዚህን ልዩ ካርዶች መጠቀም ከካሽ (ገንዘብ) ከመጠቀም ይልቅ የተሻለ መሆኑን ከካሊፎርኒያ መረጃዎች አመልክቷል:: ማንኛውም ወደፈለገው መደብር( ግሮሰሪ)፣ ጋዝ ማደያ፣ታክሲ ክፍያ፣ ፈጣን ምግብ..) ሲሄድ ሣንቲምና ገንዘብ(ካሽ) ይዞ

አይሄድም:: በግንባርና በእጁ ያለው ቺፕ ብቻ ይሆናል:: የራም ምርመራ ድርጅት ፕሬዚዳንት የሆኑትም ሮብበርት ሚኪንሊም « ስለ ገንዘብ አልባው ህብረተሰብ ሰምታችኋል ከጥቂት ጊዜ በኋላ ይታያል» ብለዋል::

እነዚህ ካርዶች ከሚሰጡአቸው ጥቅሞች ውስጥ ዋነኞቹ ግለሰቦችን መከታተል የአስመስሎ መቅረፅን (Forgery) እንቅስቃሴ ለመከታተልና ለብሔራዊ መታወቂያነት ግልጋሎት መስጠት ናቸው::

እነዚህ ካርዶች ከመጠቀም አንፃር የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ቢን ክሊንተን ለህዝቦቻቸው በቴሌቪዥን አጠንክረው ተናግረዋል:: በተለይም « ለህዝብ ቅድሚያ መስጠት » በሚለው አጀንዳቸው ጋር አያያዘው ስለ ብሔራዊ የጤና እንክብካቤ ካርድ አጠቃቀም ሲናገሩ «ያለ ይቅርታና ያለ ምክንያት (No exceptions! No Excuses, Everbody ) ሁሉም ወንድና ሴት አዋቂዎችም ልጆችም ካርድ መቀበል አለባቸው» (All Americans will Carry Smart Cards ) በማለት ተናግረዋል::

አሁን ቢሆን እነዚህን ካርዶች( ስለ ገንዘብ« ስለጤንነትና ስለ ማንነት ሙሉ መረጃ የያዙት ቢጠፉና ቢሰረቁ ምን መደረግ አለበት የሚለው ጥያቄ በከፍተኛ ደረጃ አነጋጋሪ ሆኗል:: መፍትሄ ተደርጎ የተገኘው ሌላ የተለየ ነገር ከእያንዳንዱ ግለሰብ አካል ጋር የተጣበቀ ID ማዘጋጀት ነው::ይህም መታወቂያ ባዮ-ችፕ ይሆናል:: ይህ ባዮ-ቺፕ ወደፊት በዓለም ላይ በሚደረገው መገበያየት ፈጣንና ጥራት



ያለውን ግልጋሎት የሚሰጥ ነው:: ዘዴው ከጣት አሻራ ጋር የተያያዘና ከሰውነት ክፍሎች ጋር ግንኙነት ያለው ነው:: ይህም ባዮ ሜትሪክ ሴንሰር ይባላል:: (ከተመ.7) ይህ አሰራር ከፍተኛው የቴክኖሎጂ የስራ ውጤትና እጅግ የተሻሻለው የመገበያያ የመጠበቂያ መንገድ ይሆናል:: ለሁሉም ግዳጅ ይሆናል:: ይህ አሰራር በሰው ከመሞከሩ በፊት በስፔይን ውስጥ በውሾችና በአይጦች ቆዳ ውስጥ ተሞክሮ ስራ ላይ ውሏል:: በተጨማሪም ይኸው ሲስተም በኔዘርላንድስ፣ ኖርዌይ፣ በፖርቱጋል ፣በታላቋ ብሪታንያ፣ በቤልጀየም፣ በኤርላንድ፣ በኒዮርክና በካሊፎርኒያ ጥቅም በመስጠት ላይ ይገኛል:: ልጆች ተሰርቀው እንዳይሸጡ. ታፍነው አደጋ እንዳይደርስባቸው ለመቆጣጠር ይጠቅማል::

- ከ1991 እ.ኤ.አ. ዓ.ም. በፊት የአሜሪካ መንግስት የአገሩ የቴሌኮሙኒኬሽን ሲስተም ( FTS) FTS 2000 በሚል ለነዋሪው 25,000,000,000 ( ሃያ አምስት ቢሊየን ዶላር) በሚወስድ ግንባታ ሁሉም የአገሩ ኮምፒዩተርና ቴሌፎን ከዋናው ኮምፒዩተር አሠራር (NetWork) ጋር እንዲያያዝ የሚል ሕግ አውጥቷል:: ይህ እየተከናወነ ነው:: ሲስተሙ ከተዘረጋ ማንም ሊገዛ ወይም ሊሸጥ እንዳይችል ለማድረግ የሚቸግር አይደለም:: እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ 25 1994 ዓ.ም. ቢል ክሊንተን « በ2000 ዓመት የመማሪያ ክፍሎችን፣ ክሊኒኮችን፣ ቤተመፃህፍትና ሆስፒታሎችን ከዋናው የአሜሪካ ብሔራዊ ማስታወቂያ አሰራር ጋር በማያያዝ ከግል ባለሃብቶች ጋር መስራት ይኖርብናል» ሲሉ የሚያመለክተው ሁሉንም ሰው ለመቆጣጠር እንዲያመች

ታስቦ እንደሆነ ይነበባል ::( ከተመ ገፅ 7) የቢል ክሊንተን ረዳት የነበሩትን ፕሬዚዳንት አልጎር « ፈጣን የሆነና በኤሌክትሮኒክስ ለብሔረሰባችን ጥቅም የሚሰጥ ሲስተም መዘርጋት ይኖርበታል.. ይህንንም በ1994 ዓ.ም ተግባራዊ ማድረግ ይኖርብናል የሚል ሃሳብ ሰንዝረው ነበር አያያዙ ዋዛ የሌለበት (Serious ) ነው:: ስለሆነም በአልጎር አነጋገር መሠረት በአዮዋ፣ ሚኒሰታ፣ኒው ሜክሲኮ፣ ኦሃዮ፣ፔንስልቫንያ፣በቴክሳስና በዮሚንግ ሙከራዎች በመደረግ ላይ ይገኛሉ::

## ምን ያህል ወደ 666 አሰራር ቀርበናል?

የ666 ትን አሰራር መፋጠንና መቅረብ ከሚያመለክቱን የምድሪቱ ትዕይንቶች ውስጥ አንዱ የአውሮጳ ማህበር አንድነት ምስረታ መፋጠንና አንዳንድ ውሳኔዎቻቸው ነው:: በእነርሱም አካባቢ ለማመን የሚቸግር ፈጣን እድገት አለ:: ይህ ማህበር አንድ ዓይነት መለያ ምልክትን ለመጠቀም« አንድ ግለሰብ የአውሮጳ ማህበር (EC)አርማ ምልክት ከሌለው መግዛትም ሆነ መሸጥ አይችልም» በማለት ወስነዋል::(Standardization News, Feb.1991 P.30:.)

## ትኩረት የሚሹ የማስተዋል ጥያቄዎች

1. ከዛሬ 1990 ዓመታት በፊት የዚህ ቁጥር/ምልክት አጠቃቀም እንደሚመጣ በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ተነግሯል፣ ትንቢት ደግሞ ከእግዚአብሔር ነው:: ይህ



ሲፈፀም ስናይ በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ተወልደን የእግዚአብሔር ልጅነትን ስልጣን ያገኘን አማኞች ምን እናስባለን?
2. ይህ ትንቢት እውነት ነው ውሸት? ሌሎችስ ትንቢቶች መፈፀማቸው ይቀራል?
3. እውነትን አውቆና ተረድቶ ተገቢውን የአክብሮት ምላሽ አለመስጠት ከተጠያቂነት ነፃ ያደርጋል? እውነትን መግፋት በ2ተሰ2፥9-11 እንደተጠቀሰው ለአውሬው (ለሐሰተኛው ክርስቶስ) አልፎ መሠጠትን እንደሚያመጣ ተገንዝበዋል::
4. ሰምቶ እንዳልሰሙ መሆን በማቴ25፥5 ከተጠቀሰው እንቅልፋምነት በምን ይለያል?
5. ስለ ባዮ-ቺፕ አጠቃቀም ልዩ ልዩ ዓይነት ጠበብት ምን አሉ? የዚህ መፅሐፍ አንባቢስ? በግልህ(ሽ) ምን ምላሽ ሰጠህ(ሽ)

ካለፉት 70 ዓመታት ወዲህ እስከ 1993 እ.ኤ.አ. የ666 ቁጥር ጉዳይ እያደገ መምጣቱ ለጥቂቶቻችን ግልፅ ሣይሆን የቀረ አይመስለኝም:: የዛሬ 2000 ዓመታት ገደማ የቁጥሩ ባለቤት እንደሚመጣ ባለቤቱ ማን እንደሆነ፣ ከቅዱሣን ጋር የሚኖረው አሉታዊና አጥፊ ግንኙነት ምን እንደሚሆን በክርስቶስ ያመኑትን እንደሚያርድ (ራዕይ 13፥10) ፣ የእርሱ ቤተክርስቲያን የተባለችው ቤተ ሰይጣንም በጌታ ቅዱሳንና በነቢያቱ ደም እንደምትሰክር (ራዕይ17፥5-6፣ 18፥24፣ 16፥6 ) በመጨረሻም አውሬውም ሆነ ጋለሞታይቱ በክርስቶስና በአብ ፅድቅ ውሣኔ እንደሚፈረድባቸውና እንደሚጠፉ ትንቢት

ተነግሯል:: ካለፉት 70 ዓመታት ወዲህ ይህ ቁጥር ዝም ብሎ በተለያዩ ዕቃዎች ላይ በመታየት መልክ ብቻ (በፀጥታ) ነበር የመጣው:: ካለፉት አሰርት ዓመታት ወዲህ ግን ( በተለይም ከ2000 ወዲህ በግልፅ በፅሁፎች ተደግፎ መውጣት ጀምሯል::

ይህ የሚያመለክተን እግዚአብሄር የወሰነውን « ዘመን » በማምጣት ላይ መሆኑን ነው:: (ራዕይ 11:171-18 ) ይህ ዘመን ለሁለት ተግባራት ይመጣል:: የመጀመሪያው ለእውነት ፣ ለፅድቅና ለፍትህ ከመቆማቸው የተነሣ እንገቶቻቸው የተቆረጡትን፣ ብዙ የተሰቃዩቱንና የሚሰቃዩትን ሊያሳርፍና ክቡር ዋጋ ሊሰጥ (ሊፈርድላቸው) ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ምድርን የሚያጠፉትን( ያጠፉአትን) ሊያጠፋ ነው:: ምድርን ያጠፋ ማለት ምን ማለት ነው:: በአስተሳሰባቸው፣ በፍልስፍናቸው፣ በምርምራቸው፣ በእውቀታቸው፣ እውነተኛውን ሥነመለኮት በማጣመማቸው በአምልኮ መልካቸው( በተሳሳተ ሃይማኖታቸው) በአስመሣይ እምነታቸው (Compromisers) በግልሙትናቸው፣ በፈጠሩት አንድነት እውነተኛይቱን ቤተ ክርስቲያን በኃጢያታቸው፣ በሥልጣናቸው አስገድደው በማበላሸታቸው፣ በዓለም በተካሄደው ርኩሰት ዋነኛ መነሻና አስፋፊ በመሆን የምድርን ነዋሪዎች ያበላሹ ሁሉ ምድርን አጥፍተዋል:: ብዙ ሰዎች የሥላሴን ትምህርት አበላሽተዋል፣ሰው እግዚአብሔር ነው ብለዋል፣ መፅሐፍ ቅዱስ ውሸት ነው፣ የእግዚብሔር ቃል አይደለም ብለዋል:: በረቀቀ መንገድ ከመፅሐፍ ቅዱስ ሃሳብ በመቀንጨብና አጣምሞ በመተርጎም ኢየሱስ አይመጣም በማለት ሰዎችን ከቅድስና አርቀዋል:: በሣይንሱ፣ በስነ ልቡናው፣ በህክምና ሙያው፣ በቴክኖሎጂው በማመካኘት ሰዎች ከፈሪሃ እግዚአብሔር እንዲርቁ



አድርገዋል:: ሰዎች ደፋሮች፣ኩሩዎች፣ ትዕቢተኞች እንዲሆን ሲያደርጉና በኃጢያት ውስጥ ሲሰጥሙ ይህ ምድርን ማጥፋት ነው::

መቼም ለእውነት ፈላጊ ያመነበትን፣ የተባለውን የሚያረጋግጥለት ሲያገኝ በታላቅ አክብሮትና በመርመር ይቀበለዋል እንጂ ነፃ የሚወጣበትን. የኃይል ምንጭ የሚሆንለትን እውነት በቸልታ ሊመለከተው አይገባም:: እውነት ከማስረጃ ጋር ወደ ሰው ሕይወት ሲመጣ እውነቱን ተቀብሎ እየታዘዙ መኖር እንዲችል ኃይልን ይፈጥርለታል:: ይህም ኃይል ከሚሰጣቸው ነገሮች አንዱ ማስተዋል ነው:: ጌታ ክርስቶስ በፍካሬ ኢየሱስ ከተናገራቸው እውነቶች ውስጥ አንዱ በማቴ 24:15 ላይ የተጠቀሰው ነው:: ጌታ .. አንባቢው ያስተውል ብሏል ማንበብ ብቻውን መፅሐፍ ቅዱስን ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ብቻውን ማንበልበል ማስተዋል ካልታከለበት ምን ዋጋ አለው:: በአሁኑ ጊዜ ባለ 666 ቱ ሐሰተኛ ክርስቶስ በምድራችን ላይ እንዴት በሚስጥር እየሰራ እንደሆነ ማስተዋልን ሊያስገኝ የሚችል ንባብና መረጃ ማንበብና ማየት እስኪሰለች ሞልቷል:: ታዲያ ይኼ የእንቅልፍ ሸልብታ የወደቀባቸው ወገኖች ምን ሆነው ይሆን? አንዳንዶቹ መስማትም አይፈልጉም፣ ሸብር ወይም ጭንቀት ፈጣሪነት አድርገው ስለሚወስዱት ነው:: የቀሩትም ከጥቅም ጋር አያይዘውታል፣ ሌሎችም ይፈራሉ አንዳንዶችም ገና በማጥናት ላይ ናቸው:: አስቀድሞ የባዮ-ቺፕ አካል ክፍል የሆነው የሌቲየም ጋር ግንኙነት የነበራቸው ሰው ዶ/ር ሳንደርስ ወደ ክርስትና ዕምነት መጥተው የ666 ትን ሁኔታ ካጠኑ በኋላ አቋማቸውን በመለወጥ ማስጠንቀቂያ የሚሆን ሴሚናር በመስጠት ላይ ይገኛሉ:: ስለሆነም የ666 አሠራር

ከሦስት ዓመት ወዲህ በግለጽ ሥራውን ጀምሮአል:: (http://legalminds.lp.findlaw.com ) ሰው እውነት ሲበራለት የእግዚአብሔር ርዳታ መሆኑን ተረድቶ የእርቀ-እግዚአብሔር ርምጃ ሊወስድ ይገባል:: እንግዲህ ህይወት ይኼ ነው:: መፅሐፍ ቅዱስ የማያስተውል ህዝብ (ግለሰብ) ይገለበጣል( ይጠፋል) ይላል:: ስለሆነም ስለ 666 የተፃፈውንና ወቅታዊውን ሁነት በማየት ጥብቅ ፀሎት ወደ ጌታ ኢየሱስ እናድርግ:: እውነት ያለውና በእውነቱ ቀድሶ ወደ እውነት ሁሉ የሚመራው እግዚአብሔር አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከመንፈስና ሥጋችን ጋር ይሁን! አሜን::



## ክፍል 4

## መጥኔአዊ ኢላማ

ይህ ክፍል ቀደም ብሎ የተጻፈውን ያነበቡ ሰዎች ሊወስዱት በሚገባቸው እርምጃ ላይ ያተኩራል:: የአውሬውን ረቂቅ አሠራር የተመለከተ አንባቢ እንደ ልብ ወለድ ንባብ ዝም ብሎ አድንቆ ሲያልፈው አይገባም:: ይህ ጽሑፍ እኔን ይመለከተኛል ወይስ አይመለከተኝም? በማለት ሊጠይቅ በመቀጠልም ለጥያቄው በራሱ መልስ ሲያገኝ ከዚያም አቋም ሊወስድ ይገባል:: ሰዎች ለአውሬው ገባሪዎች የሚሆኑት በተለያየ ዓይነት መንገድ ነው:: በሚታይም ሆነ በማይታይ መልኩ ተገዢ መሆን ይኖራል:: ቀደም ብሎ ስለ አውሬው ፍጻሜ እንዳነበብነው የዚህ ክፉ ተከታዮች የሆኑ ሁሉ ዕድላቸው በአውሬው እንደደረሰው ዓይነት እንደሚሆን የማያጠራጥር ነው:: ስለሆነም የዚህ መጽሐፍ አንባብያን በሙሉ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ስያሜዎች በየትኛው ክፍል ውስጥ እንደተፈረጁ ራሳቸውን መስታወት ፊት እንዳለ ገጽታ ሊያዩትና ጌታን ሊያመሰግኑ ወይም ንስሀ በመግባት አካሄዳቸውን ሊያስተካክሉ ይገባል:: ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ማንነቶች በየትኛው ውስጥ ነው ያለኸው?

### 4.1 አረማዊ?

አረማዊ ማለት በኦሪትም ሆነ በወንጌል የማያምን እምነትና ርህራሄ የሌለው ሰው ነው::[1] በዚህ ክፍል ያለ ሰው ከመንፈሳዊው ዓለም ለሚወረወረው ተምዘግዛጊ መንፈሳዊ ሚሳኤል መከላከያ የሌለው ነው:: ውስጣዊ መንፈሱ ላይ ኃጢአት የተባለው የሰይጣን (የሞት) መውጊያ ስለተቀመጠበት ክፉ ኃይላትን ወደ ራሱ ለጉዳቱ ይስባል እንጂ ማራቅ አይችልም:: ምክንያቱም ስላልዳነ ብቻ ነው:: መዳን ማለት ዳግም ከመንፈስ ቅዱስ በመወለድ ለሰይጣንና ለክፉ መላዕክቱ ከተዘጋጀው የዘላለም ቅጣት ኃይል መከለል፣ መሰወርና መጠበቅ ነው:: የመዳን መንገድ ደግሞ ክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ ነው:: ይህም ቃል በሐዋርያት ሥራ 4:12 ውስጥ <u>መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ከሰማይ በታች ለሰዎች የተሰጠ ከኢየሱስ ስም ሌላ የለምና</u> የሚለው ነው:: ሰው ከእግዚአብሔር ወገን ነው ወይስ ከሰይጣን? ተብሎ ለሚጠየቀው ጥያቄ ትክክለኛው መልስ በእውነተኛው አዳኝ በክርስቶስ ማመኑ ከእግዚአብሔር ወገን ያደርገዋል የሚል ነው:: እምነት ሲባል ደግሞ የሞተ የእውቀትና የአጋንንት እምነት ማለት አይደለም:: አጋንንት ኢየሱስ ጌታቸውና ተበቃያቸው እንደሆነና በኃጢአት ሥራቸውም ሳይተባበራቸው እንዳሸነፋቸው ያውቃሉ:: ወደፊትም ከሰማይ ወደ ምድር መጥቶ ወደ ጥልቅ እንደሚጥላቸው ያውቃሉ ያምናሉም:: የዚህ ዓይነት እምነት የሞተ ወይም አጋንንታዊ ይባላል:: በአንጻሩ ግን <u>ህያው እምነት</u> ማለት በክርስቶስ ኢየሱስ አምላክነት ጌትነት፣ ፈጣሪነት፣ በደሙ ከኃጢአት የሚያነጻ፣ የሞተ፣ የተቀበረ፣ የተነሳና አሁን በሰማይ በአብ ዘንድ ያለ የሚመጣና ቅዱሳኑን የሚወስድ ኃጢአተኞችን

የሚቀጣ፣ የነገስታት ንጉስ፣ የጌቶች ጌታ የአለቆች አለቃ መሆኑን የሚያውቅ፣ የሚያምንና ክርስቶስን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ተቀብሎ በኑሮው ጌታውን የሚገልጽ ማለት ነው:: እንደዚህ የማይኖር ማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር ሁሉ አረማዊ ይባላል:: አረማዊ ሁሉ ደግሞ የአውሬው ተገዢ እንደሚሆን ይመን:: ምክንያቱም የክርስቶስ የሆነ መንፈሳዊ መከላከያ እስካሌለባቸው ድረስ ሊሰለጥንባቸው ሥልጣን ተሰጥቶታል:: ራዕይ 13:5-10::

## 4.2 ከያኒ?

ከያኒ ማንኛውም ብልህ፣ ጠቢብ፣ ብልሃተኛ፣ ሥራ አዋቂ፣ አንጥረኛ፣ ባለመኪና ፈጣሪ፣ ሃኪም፣ መሐንዲስ፣ ፈላስፋ፣ በፍጥረት ሥራ የሚራቀቅ ምሁር፣ የሚጠራበት የጥቅል ስም ነው::2 መጽሐፍ ቅዱሳችን እውቀት እንደሚያስታብይ ይናገራል:: በዘመኑ ያሉ እጅግ የተራቀቀ የእውቀትና የተግባር ችሎታ ያላቸው ሳይንቲስቶች፣ ፕሮፌሰሮች፣ ዶክተሮች፣ ሃብታም ነጋዴዎች፣ ምሁራን፣ ኬሚስቶች፣ ቀማሚዎች፣ ፈጣሪዎች፣ የሥነ ልቡና ተመራማሪዎች፣ አብራሪዎች፣ ልዩ ልዩ ሂሣባዊ መኪኖችን አምራቾች፣ ኢ-ክርስቶሳዊ-ሃይማኖታውያን ወዘተ ከከያኒ ክፍል ይመደባሉ:: ይህ ችሎታቸው አስታብዮአቸው እውነተኛውን ፈጣሪ እንዲንቁተ አድርጓቸው ከሆነ ወደዱም ጠሉ ለሐሰተኛው ክርስቶስ ተገዢ ከመሆን ፈጽሞ አያመልጡም:: በዚህ ዓለም ሞት በኃጢአት ያልወጋውና ያላንከባለለው ከያኒ ይገኛል? ለሞት ተንበርክኮ እጁን ያልሰጠ ፕሮፌሰር የቱ ነው? የትኛው ሳይንቲስት፣ የጠፈር ተመራማሪ ነው ሞትን ያሸነፈ? ከክርስቶስ በቀር ማንም አይገኝም:: ባለ 666ቱ ሃሣዊ መሢህ ራሱ የዲያብሎስ መሣሪያ ነው:: ስራውም መግደል ነው:: ራዕይ 6:1:: ስጊዜው ጠቃሚ መስሎ ለዓለም ህዝብ መቅረቡ ሰዎችን በቁጥጥሩ ሥር እስኪያደርግ ድረስ ነው:: እርሱ የሚያንጠባጥባቸው ብዙ ባቄላዎች አሉት::

አንድ ጊዜ አንድ የአሳማዎች እረኛ አሳማዎቹን ቄራ ውስጥ አስገብቶ ሊያርዳቸው ቢፈልግ በሙሉ ያምጹበታል:: በኋላ በብብቱ ሥር ባቄላ የሞላበት ከረጢት ይዞ እያንጠባጠበላቸው ይሄድ ጀመር:: አሳማዎቹ ባቄላውን እየተሻሙ ሲበሉ ከቆዩ በኋላ ቀና ሲሉ አሳማ አርቢው መታረጃ ቄራ ውስጥ እንዳስገባቸው ተረዱ:: ከዚህ በኋላ ማምለጥ አልቻሉም:: ዛሬም የሰይጣን ሥላሴዎች (ዘንዶው--ሰይጣን፣ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ራዕይ 16:13) ሰዎችን የህይወት መጥፊያ ቄራ (ከእግዚአብሔር መራቅ) ውስጥ ለማስገባት የሚያንጠባጥቧቸው መንፈሳዊ የኃጢአት ባቄላዎች መርካት፣ በዝርፊያና በውንብድና መደሰት፣ ማጭበርበር፣ በቁሳቁሳዊ ነገር ብቻ መወሰን፣ መብላት መጠጣት መዝፈን፣ ደም በማፍሰስ መርካት፣ የሰው ሥጋ መብላት ወዘተ ናቸው:: ከያኒያን ከየትኛው ፈርጅ ነን፣ ከያኒ ሆኖ ክርስቶስን አምኖና ተቀብሎ በመኖር ውስጥ ወይስ ከያኒ ሆኖ አረማዊ ህይወት ውስጥ? እንግዲህ ራስን የመመርመር ጥቅም እዚህ ላይ ነው:: በራዕይ 13:18 ላይ ጥበብ በዚህ አለ የተባለውም ረጂነቱ እዚህ ላይ ነው:: ከያኒነት ከእውነተኛው የክርስቶስ



ህይወት የሚያርቅ ከሆነ 100% መክሰር ነው:: እንግዲህ ከው ቤት ሔጄ በድንገት፣ ቋንጣ ጠብሼ ለመብላት፣ ወድቄ ነበር በእሳት ላይ፣ ሥጋ ሥጋዬን ሳይ:: የተባለው የዘለሰኛው ምክር ለክፉና ለጉዳት እንዳይሆንብን እንጠንቀቅ:: የዚህ ዓለም ኑሮ ቢደላ አጥጋቢነቱ እዚሁ ምድር ላይ ብቻ ነው:: ተጠግቦ ቢበላም እንኳን ቋንጣ የመብላት ያህል ነው:: ውጤቱም ዘላለማዊ እሳት ላይ መውደቅ ነው:: ጌታ ኢየሱስ ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል በማለት ከዛሬ 2000 ዓመታት አስቀድሞ ተናግሯል:: ለሥጋ የተረፈው ለነፍስ የጐደለው ልንሆን አይገባም::

ትክክለኛ ከያኒ በሰው መንፈስ፣ ነፍስና ሥጋ መካከል ያለውን ግንኙነትና ልዩነት፣ ስለራሱ የውስጥና የውጪ ሰውነት አፈጣጠር በጌታ ኢየሱስ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ በኩል አውቆና ተረድቶ ፈጣሪውን በማመን የሚኖር ነው:: ይህም ብቻ አይደለም፤ እውነተኛ ከያኒ የጥበብና የመገለጥ ምንጭ የእግዚአብሔር መንፈስ መሆኑን አውቆና ተረድቶ ከሃሊ-ኩሉ (ከሁሉ በላይ) በሆነው ፈጣሪው ፊት ራሱን ትሁት አድርጐ የሚኖር፣ ስለተሰጠውም እውቀት ክብርን ለፈጣሪው በመስጠትና በማምለክ የሚኖር ነው:: ከዚህ የራቀ ከያኒነት ከአጋንንት ራዕይና መገለጥ እምብዛም የተለየ አይሆንም ውጤቱም መታለል ነው:: ስለሆነም ህይወት ሳታመልጥ፣ የለቅሶ አበባ ጉንጉን ሳይሰራለት፣ የሞት ጉድጓድ ሳይቆፈርለት፣ ደረት ሳይደቃለት፣ ፀጉር ሳይነጭለት፣ አጥንቱም የአፈርና የምስጥ ወዳጅ ሳይሆን አሁንና ዛሬ ፈጣሪን ማሰብ እጅግ የተሻለ ነው:: ይህ ካልሆነ በአውሬው ዕጣ ክፍል መመደብ ቁርጥ ነው:: መክ. 12፤1-2

## 4.3 ተምኔታዊ?

ተምኔታዊ ማለት ምኞተኛ ማለት ነው:: ህያው ፍጡር ሁሉ ለክፉ አልተፈጠረም:: በኋላ ክፉ መንፈስ ገባበትና ራሱም ለራሱም ክፉ ሆነ እንጂ:: ሆኖም ሰው ክፉ ሆኖ ሳለ መልካምን ምኞት ይመኛል:: ሉቃስ 11:11:: ለራሱ፣ ለቅርብና ለሩቅ ዘመዶቹ ሰው መልካምን ይመኛል:: አንዳንድ ተፈላጊ ነገሮች በምኞትና በጥረት ሊገኙ ቢችሉም በአውሬው ከሚመጣ መከራ መዳን ግን በምኞትና በናፍቆት ሳይሆን ከእውነተኛው ፈጣሪ ከእግዚአብሔር ጋር የመንፈስ ዕርቅ በማድረግ ብቻ ይገኛል:: ተምኔት ብቻ ሰውን በፍጹም ወደ ደህንነትና መንግሥተ ሰማያት አያመጣም:: ሰው ለመዳን ከጌታው ከኢየሱስ ጋር ታርቆ የሰውን መንፈስ ከገደለው ኃጢአት ነጻ መውጣት አለበት:: ያን ጊዜ የሚመኘው ምኞትና ፍላጐት በሚጸልየው ፀሎት ወደ ጌታው ሲያርግለት ብቻ የልቡን መሻት ያገኛል:: ስለሆነም ተምኔታውያን በእውነተኛ ምኞት ወደ እግዚአብሔር በተሳሳተ ምኞት ደግሞ ወደ አውሬው መቅረብ እንዳለ ልብ ሊሉት ይገባል:: ምኞት መልካም ነበር ጣጣው ባልነበር የተባለውን ልብ ይሏል::

## 4.4 አዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ? (አ.ዘ.እ.)

የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ሲባል ዋነኛ መለያቸው ሰው አምላክ ነው፤ ከሰው ሌላ ሊመለክ የሚገባ ማንነት የለም፤ «የሰው 3ኛ ዓይን ሲከፈት ሰው መለኮት መሆኑን ይገነዘባል፤ የሚል አቋም ያለው ዓለም አቀፋዊና ሰይጣናዊ እንቅስቃሴ ነው። የአ.ዘ.እ. አባላት ትምህርታቸው፣ ልምምዳቸው፣ ኃይላቸው፣ መገለጣቸው ወዘተ ሁሉ በአብዛኛው አዲስ ነው። በሐዋ. 17 ላይ ስማቸው የተጠቀሰው አቴናውያን አዲስ ነገርን ከመናገርና ከመስማት በቀር በሌላ ጉዳይ አይውሉም ነበር። (ቁ. 21) ተብሎ የተጻፈው ታሪክ ዓይነት ናቸው። ልብ ይባል። አቴናውያን አዲስን ነገር ለማግኘት ሲፈላሰፉ የቀደመውን እውነት ጥለው ነበር። ደግነቱ ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ በኩል አዲስ ነገር አቅርቦ ከፊሎቹን ለደህንነት አበቃቸው እንጂ ወደ አጋንንት አሠራርም ሊሔዱ እንደሚችሉ መገመት አያዳግትም። ሰው አዲስ ነገርን ሲፈልግ በቀደመው እውነት ላይ ቆሞ እንጂ የበፊቱን እየቀበረና እየጣለ መሆን የለበትም። የያዕቆብ ወንድም ይሁዳ ያገለግል በነበረበት ዘመን የነበሩት መናፍቃን የሐሰት ትምህርታቸውን እያሾለኩ በማስገባት (ቁ. 4) የአምላካችንን ፀጋ በሴሰኝነት ይለውጡ እንደነበር ይናገራል። የገላትያ ክርስቲያኖች የጳውሎስን ጤናማ ትምህርት በአዲስ እውቀት ለወጡት፣ ፈጥነውም ተወሰዱ (1:6) ይሁዳ አዲስ እውቀት ሰዎችን ከቀደመው እውነት የሚለይ ክፉ ሰይፍ መሆኑን አውቆ አንድ ጊዜ ስለተሰጠ ኃይማኖት እንዲጋደሉ (ቁ. 3)፣ ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ኃይማኖታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ (ለማሳደግ) ትጉ ይላቸዋል። ይህ የሚያመለክተን የቀደመው ኃይማኖታቸው በሐሣቡም ሆነ በንግግሩ በድርጊቱም እንደ ጥላ ከማይለዋወጠው ከእግዚአብሔር ዘላለማዊና ጽኑ እውነት መውጣቱን ነው። ስለሆነም ሰዎች በትምህርት ነፋስ እየተፍገመገሙ ወዲያና ወዲህ መንሳፈፍ እንደሌለባቸው ሆኖም በቀደመው በጌታ እውነት ላይ መጽናታቸው አስፈላጊና አማራጭ የሌለው የህይወት መመሪያቸው መሆን እንዳለበት እንገነዘባለን።

መንፈሳዊ ሥፍራን በመልቀቅ ወዲያና ወዲህ በማለት ብዙ ሰዎች አደጋ ውስጥ እንደወደቁ ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ መጥቀስ ይቻላል። ለዚህም በአሜሪካ ያሉትን አማኞች አመሠራረትና ሂደት መመልከቱ ለአብነት በቂ ሊሆን ይችላል። አሜሪካ በኮሎምቦስ ከተገኘችበት ጊዜ አንስቶ ህዝቡ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ፣ ህገ መንግሥቱም ሆነ ዩኒቨርሲቲዎቹ የአሜሪካ ህዝብ መመሪያ የተመሠረተው በክርስትና መርህ ላይ እንደሆነ ያምናል። በቀድሞ ዘመን የነበሩት የአሜሪካ መንግሥታት በአንዱ በእግዚአብሔር እንደሚያምኑ፣ ማንም የእግዚአብሔርን መኖር፣ የአዲስንና የብሉይን ኪዳናት፣ የክርስትናን ኃይማኖት የሚክድ መኖር እንደሌለበት ወዘተ ያውቁ ነበር።[3]

ቀጥሎ ስማቸውና ንግግራቸው በሠንጠረዡ ውስጥ የተመለከተው የአሜሪካ ፕሬዚዳንቶችና የህዝቡ አቋም ለመጽሐፍ ቅዱስና ለመለኮታዊው እግዚአብሔር የነበራቸውን አክብሮት ያስረዱናል።[4]



| ደረጃ | ኘሬዚደንት | የነበሩት ጊዜ | ያቀረቡት ትግግር |
|---|---|---|---|
| የመጀመሪያው ኘሬዚደንት | ጆርጅ ዋሽንግተን | 1732-1799 | ያለ እግዚአብሔር ዓለምን በትክክል ማስተዳደር አይቻልም። |
| 3ኛው | ቶማስ ጃፈርሰን | 1743-1826 | የተቀደሰ መጽሐፍ የተሻሉ ዜጐችን አባቶችንና ባሎችን ይሰራል። |
| 6ኛው | ዮሐንስ ኩንሲ አዳምስ | 1767-1848 | የዓለምን ትኩረት የሳበ የመጀመሪያውና ብቸኛው መጽሐፍ |
| 7ኛው | እንድርያስ ጃክሰን | 1767-1845 | ሪፐብሊካችን ያረፈበት ደንጊያ መጽሐፍ ቅዱስ ነው |
| 18ኛው | ኡሊሲስ ኤስ ግራንት | 1822-1885 | በዓለም ውስጥ ለተካሔደው ሥልጣኔ መሠረቱ የመጽሐፍ ቅዱስ መልካም ተጽዕኖ ነው። መጽሐፉም የወደፊት መመሪያችን ሊሆን ይገባል። |
| 28ኛው | ውድሮው ዊልሰን | 1856-1924 | አንድ ሰው በዓለም ሲኖር ካጣቸው ታላላቅ ነገሮች ውስጥ የመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ ይሆናል። |

እነዚህ ፕሬዚዳንቶች በነበሩባቸው ዘመናት የእግዚአብሔርና የመጽሐፍ ቅዱስ ጉዳይ ታላቅ አክብሮትና ተቀባይነት ነበረው። ሆኖም ከ1962 ዓ.ም. ጀምሮ በአሜሪካውያን ህገ መንግሥት ላይ ለውጥ መደረግ ሲጀመር የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥት መለያየት ተቀባይነቱ ከፍ እያለ ሄደ። ብዙ ክርስቲያኖች መንግሥት ይሰራ የነበረውን መከታተል አቆሙ ስለሆነም ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ለህጻናት መጽሐፍ ቅዱስ ሥነ ልቡናን ይጐዳል ብሎ ስላመነበት በት/ቤቶች እንዳይተላለፍ ታገደ። በ1980 አስርቱ ትዕዛዛት ከመንግሥት ት/ቤቶች ተሰረዙ። በፍርድ ቤቱ ውሣኔ ምክንያት ኃይማኖት (መጽሐፍ ቅዱስና ፀሎት) ከት/ቤት ወጣ። ውጤቱም እጅግ አስፈሪና አደገኛ ኖኗል። ግድያ፣ ውርጃ፣ የግዳጅ ወሲብ፣ የአጋንንት ረቂቅ አሠራር በአገሪቱ ላይ ሰፍኗል። የአብዛኛው ህዝብ ባህሪ ወደ አውሬነት ተለውጧል። የኤች አይ ቪ ቫይረስ ተሸካሚ ከሆኑ ዝንጀሮዎች ጋር አወስቦ መፈጸም፣[5] [illegible] ቀስቃሽ የሆኑ ፎቶዎችና ስዕሎች (ፎርኖግራፊ) በስፋት በገበያ ላይ መዋልና የሰይጣንን አለመኖር አምኖ መቀበል እየተስፋፋ መጥቷል። የሕዝቡም አእምሮ ከመጽሐፍ ቅዱስ እየራቀ ስለሔደ 31% የሚሆኑት ህዝቦች ሰይጣን ማለት ሃሣብ ብቻ መሆኑንና አለመኖሩንም ሲቀበሉ 49% ደግሞ ሃሣቡን ተቃውመውታል። 26% የሚሆኑት ግን ስለ ሰይጣን አናውቅም በማለት ለቀረበላቸው ጥያቄ መልስ ሰጥተዋል። በተጨማሪም ትክክለኛውን ኃይማኖት ማንም ሊያረጋግጠው አይችልም የሚለውን ሃሣብ 40% የሚሆኑት ወጣቶች ሲደግፉት 34% የማይስማሙ

መሆናቸውንና 26% ደግሞ የሚያውቁ መሆናቸውን ገልጸዋል::[6] ይህ የሚያመለክተው ህዝቡ ምን ያህል ከመጽ. ቅ. እውነት መራቁንና ወደ ክህደት መግባቱን ነው::

ጽንስ ማስወረድ ህጋዊነት እያገኘ መጥቷል:: አንዲት ሴት በተሳሳተ ወሲብ ብትጸንስ በውርጃ ልትረዳ እንደሚገባ ማደፋፈሪያ ይሰጣል:: ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ይቃወማል:: ኤር. 1:5-7:: ይህም ብቻ አይደለም፤ መጽሐፍ ቅዱስ ከት/ቤቶች እንዲርቅ ከተደረገ በኋላ ሰዎች እንዴት ከአጋንንት ጋር ኅብረት እንደሚያደርጉ፣ ወጣቶች እንዴት ለክፉ ነገር አልፈው እንደሚሰጡ፣ ህጻናት እንዴት የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ኃይማኖት ብቻ መማር እንዳለባቸው የሚያስገድድ ሁኔታ መመቻቸቱ እያየለ መጥቷል::[8] ዘመናዊው የሥነ ልቡና እውቀት በህዝቡ ህይወት እየሰረጸ እንዲሔድ፣ የህጻናት ተቆጣጣሪ የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ እንዲሆን፣ ህጻናት ክርስቶስን እያገለገሉ ማደግ እንዳሌለባቸው፣ ልጆች እንደ እግዚአብሔር መከበር እንዳለባቸው፣ ልጆችን ሊመራቸው የሚገባው መንፈስ እንደሆነ ህብረተሰቡ እንዲያውቅ ማድረግ፣ ልጆች በወሲብ ንቁ መሆን እንዳለባቸው እንዲያውቁ፣ ከሞት በኋላ በድጋሚ በሌላ ህልውና መልክ መፈጠር ዳግማዊ ትስግውት (REINCARNATION) እንዳለ ህዝቡ እንዲቀበል ማደፋፈር፣ ወጣቶች ከመታዘዝ እንዲያምጹ መነሳሳት እንዲደረግ፣ ወዘተ በህዝቡ አእምሮ ውስጥ እንዲሰርጽ እየተደረገ እንደሆነ ይነበባል::[9]

አዲስ ነገርን ለማግኘት መመኘት በፍጻሜ የሚያመጣው ከላይ የተጠቀሰውን አይነት አደጋ ነው:: ሰይጣን እግዚአብሔር የሰጠውን ክብር ትቶ ሌላ አዲስ ነገር ሲመኝ የባሰ ውርደት ውስጥ ወደቀ:: መናፍስቱም የእርሱን ሃሣብ ሲከተሉ ይባስ ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ወደቁ:: ከነጻነት ወደ እስራት ገቡ:: አዳምና ሔዋንም እንደ እግዚአብሔር ስናውቅ አዲስ ነገርን እናገኛለን ብለው ሲያስቡ ቀድሞ የነበራቸውን ታላቅ ክብር አጡ:: ኢሳ.14:12-14፣ ሕዝ. 28:11-18፣ ራዕይ 12:1-5፣ ዘፍ. 3:1-24:: ዛሬም ያለው ነገም የሚመጣው የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ውጤቱ ውርደት እንደሚሆን ምንም ጥርምር ሊኖረን አይገባም:: አንባቢ ሆይ ከአዲሱ ዘመን እንቅስቃቂ ክፍል ነህ? የዓለምንም ሆነ የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ወደ ኋላ መለስ ብሎ በምናባዊ-ዕይታ መቃኘት ያሻል:: ለእውነት ፈላጊና መርማሪ የእውነት ጌታ እውነትን ይገልጣል:: ቆርኔሌዎስና ኒቆዲሞስ እውነትን ይፈልጉ ነበር:: በኋላ እግዚአብሔር እውነትን አስጨብጧቸዋል:: ዮሐ. 3:1-8፣ የሐዋ. 10:: የቆረጠ አመለጠ ነውና ከዚህ የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ከተባለ ረቂቅ የአውሬው መሣሪያ ለማምለጥ መቁረጥ ያስፈልጋል:: ለመቁረጥ ደግሞ መመርመር ያሻል:: ይህ የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ በረቀቀ መልኩ ወደ ቤተ ክርስቲያን እየገባም ስለሆነ ቅዱሳን ሊጠነቀቁ ይገባቸዋል:: ለምሣሌ ራሳቸውን መንፈስ ነን፣ ድኃ ልንሆን አይገባም፣ ከሥጋ ወጥተን በመንፈስ መብረር እንችላለን፣ በፈለግነው ጊዜና ሰዓት በመንፈስ ሆነን ከመንፈሳዊ ኃይላት ጋር መገናኘት እንችላለን የሚሉ ክርስቲያን ነን ባይ የቤተ ክርስቲያን አባላትም ቢሆኑ የአዲሱ ዘመን እነቅስቃሴ መንፈሳዊ ማኖ እንዳስነካቸው ልብ ሊሉ ይገባል::



በተጨማሪም በ16ኛው ክፍለ ዘመን የነበረው ማርቲን ሉተር የፕሮቴስታንትን ተሃድሶ ሲያመጣ የከፈለው ዋጋ ቀላል አልነበረም:: ዛሬ ግን በመላው ዓለም ተሰራጭተው ያሉት የክርስቶስን አምላክነትና የሥላሴን አስተምህሮ የሚክዱት የሞርሞንስና የይሆዋ ምስክሮች አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የመጡት ከፕሮቴስታንት አባላት ነበር::[10] እንግዲህ እንቅስቃሴው ከካቶሊክ ወደ ፕሮቴስታንት ቀጥሎ ወደ ይሆዋ ምስክሮች ከሆነ ቀጥሎስ? ወደ ፍርድ መገሰጫው ወደ አዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ የማይሆንበት ምንም ምክንያት የለም:: ይሔ ሁሉ አዲስን ነገር ለማግኘት የሚደረግ መሻት ነው:: እንግዲህ አዲስ ነገርን ለማግኘት የሚደረገው ዘመቻ ቀላል ልጓም እንዳይደለ ልብ ልንል ይገባል:: የለመደ ልብ ቶሎ አይጠፋም::

## 4.5 <u>መሰቃዊ?</u>

መሰቃዊ ማለት ያየውንም የሰማውንም የሚንቅ ትዕቢተኛ ሻካራ የሆነ ንግግር ያለበት ሰው ነው:: ያልመረመረውን፣ ደግሞ ደጋግሞ ያላየውን፣ የማያውቀውን ነገር ለማጣጣል፣ ሌላውም እንዳይቀበል ለማድረግ ትዕቢት የሞላበትን ንግግር አቅራቢ ነው:: የዚህ ዓይነት ሰው ወይ ክፉ መናፍስት አሉበት ካልሆነም የተፈጥሮ ክፋት ስለተጠናወተው አጋንንትን በከፍተኛ አክብሮት ለመሳብ የተመቻቸ ሰው ነው:: እነዚህም ከአውሬው ማምለጫ መንገድ የላቸውም:: ቶሎ ብለው በክቡር የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ነጽተው ህይወታቸውን ካላስተካከሉ በቀር::

## 4.6 <u>ዘንገሊል?</u>

በሬዲዮ፣ በቲቪ፣ በመጻህፍት፣ በመጽሔቶች፣ በሰው በሚታይና በማይታይ መንገድ ሰውም ሆነ እግዚአብሔር ሲናገረው በምድራዊ ጥቅም ብቻ ስለተያዘ እውነት የማይገባው ሞኝ ማለት ነው:: የዚህ ዓይነት ሰው በየኃይማኖት ድርጅቶቹ ሊኖር ይችላል:: እውነትን እየተማረ ወደ ነጻነት ክብር ሊደርስ የማይችል ሰው ነው 2ኛጢሞ. 3:6-7:: ጳውሎስ ወደ ቤቶች ሾልከው እየገቡ <u>ሐጢአታቸው የተከመረባቸውን በልዩ ልዩ ምኞትም የሚወሰዱትን ሁልጊዜም እየተማሩ እውነትን ወደ ማወቅ ሊደርሱ ከቶ የማይችሉትን ሞኞችን ሴቶች የሚማርኩ</u> ሲል ለመግለጽ የፈለገውን እውነት ፈልቅቀን ልናገኝ እንደሚገባን ነው:: ሞኝ (ዘንገሊል)፣ ኃጢአቱ የተከመረበት፣ የተለያዩ ተናጋሪዎች በመጡ ቁጥር አብሮ የሚነፍስ እንደ ተጐታች ሪሞርኬ ያለ ማለት ነው:: ኃጢአቱና ምኞቱ በህይወቱ ላይ ተጽዕኖ ስለሚያሳድርበት የሚነገረውን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ስለሚንቀውና ስለማይቀበለው ወደ እውነት መድረስ ያዳግተዋል:: እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች በቀላሉ ለአውሬው ተገዢ ይሆናሉ ምክንያቱም ለሆዳቸው እንጂ ለእውነት ስለማይኖሩ መከላከያም ስለሌላቸው ነው:: በህይወትህ ዘንገሊልነት ይታይብሃል? ህይወትህን ለጌታ ስጥ የጌታ መንፈስ ቅዱስ ከዘንገሊልነት ተፅዕኖ አርነት ያወጣሃል:: ዮሐ. 16፣13፤ 8፣32፤ 6፣63፤ 17፣17::

## 4.7 መሃል ሰፋሪ?

አንድ ጊዜ የዝንጀሮ ሠርግ ይሆናል:: ሠረገኞቹ ሙሽሮቹን ይዘው ወደ ቤት ሲገቡ ቤቱ ጠባቸው ነበር:: በጊዜው ውጪ ባሉትና ውስጥ ባሉት መካከል የዘፈን ውድድር ይደረጋል:: ያሸነፉ ልዩ ሽልማት ይታደሉ ስለነበር፣ ለማሸነፍ ሲጣጣሩ አንደኛይቱ ዝንጀሮ በመስኮቱ ጉበንና መቃን መካከል ተቀምጣ ወደ ውጪም ወደ ውስጥም እየተመለከተች ትዘፍን ነበር:: ይህንንም ያደረገችው የውስጦቹ ካሸነፉ ወደ እነርሱ የውጪዎቹ ካሸነፉ ደግሞ ወደ ውጪዎቹ እደባለቃለሁ የሚል አቋም በውስጧ ስለያዘች ነበር:: አንዳንድ ክርስቲያኖችም ከዚህ ያልተለየ ህይወት ይኖራሉ:: በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ሲመቻቸው ይቀጥላሉ ሳይመቻቸው ደግሞ ወደ ዓለም ለመሔድ ያሰፈሰፈ ልብ አላቸው:: የዚህ ዓይነቱም ክርስትና ከጌታ ፍርድ አያስመልጥም:: ይህ <u>ልጓም ለቀቆ ቼቼ</u> ዓይነት ህይወት ነው:: ስለሆነም <u>ሲያወላውል ቀረ ባጉል</u> እንደተባለ እንዳይሆን ለጌታ ህይወትን ቶሎ ማስረከብ ነው:: የሚጠራጠር ሰው ከጌታ አንዳች አያገኝምና:: ያዕ. 1:7-8:: የዚህ ዓይነት ሰዎች ከሐሰተኛው ክርስቶስ ረቂቅም ሆነ ግልጽ አሠራር አያመልጡም ለመማረክም የተመቻቸ ህይወት አላቸው::

## 4.8 ቅይጣዊ?

ይህ ጊዜ ዘመነ ባቢሎናዊነት የሰለጠነበት ወቅት ነው:: ሰው ልዩና ቅዱስ የሆነውን ፈጣሪውን መስሎ ከመኖር ይልቅ ተቀላቅሎና ተመሳስሎ መኀዝን ሲመርጥ ቅይጥ ህይወት ይባላል:: ቅይጣዊነት (ሲንክሬቲዝም) ሁሉንም ኃይማኖት ፀንሶና አርግዞ መኀዝ ነው:: ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል እንደተባለ አቋም ሳይዙ የሁሉንም ኃይማኖት ቀነጫጭቦ የጋራ የሆነውንና ለሰው የሚስማማውን ከእግዚአብሔር እውነት ጋር የሚጋጭን ኃይማኖታዊ አቋም መያዝ ነው:: ይህ አቋም ለጊዜው የሚጥም ይምሰል እንጂ ሁሉም የየራሱን ሲያበላልጥ እየተነካከሱ መኀዝን ማምጣቱ የማይቀር ነው:: በዘፍ.11:4-6 ስናነብብ ራሳቸውን ከፍ ለማድረግ ባሰቡ ጊዜ ጌታ ተቆጥቶባቸው ከሰማይ ወርዶ ቋንቋቸውን እንደደበላለቀባቸው ዓይነት ፈጽሞ አይስማሙም:: ስለሆነም አንድ ሰው የዘላለምን ህይወት ከመረጠ ጌታ ኢየሱስን ብቻ አምኖ መቀበል እንጂ ከሁሉም ተስማምቼ እኳዛለሁ ማለት አይችልም:: ይህ አቋም ለአውሬው ያመቻል:: መፍትሔው ወይም ሰይጣንን (ለፍርድ) ወይ እግዚአብሔርን (ለህይወት) መምረጥ ብቻ ነው::

## 4.9 ፈሪ?

ሰውን የሚያስፈራው ብዙ ነገር አለ:: ከእነዚህም ውስጥ ባል፣ ሚስት፣ ቤተሰብ፣ ፖለቲካ፣ ስልጣን፣ ወላጅ፣ ከሥራ መውጣት፣ ስደት፣ ጓደኛ፣ እጮኛ ወዘተ ይገኛሉ:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም ሰውን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዳይገባ ከሚከለክሉት ክስተቶች አንዱ ፍርሃት እንደሆነ ተገልጿል:: ጌታ ኢየሱስም እንግዲህ አትፍሯቸው በማለት ተናገረ:: ማቴ. 10፣26 ወደ እውነት መቅረብ በጣም ያስፈራል:: ሆኖም



ይቻላል:: ፍርሃት ቅጣት አለው:: ሰው ስለ መፍራት ሲያስብ የፍርሃቱን አቅጣጫ መመዘን ይኖርበታል:: የሰይጣን ኃይል፣ ጨለማ፣ አጋንንት፣ አጋንንት የገቡባቸው ሰዎች፣ የፖለቲካ ሰዎች፣ እብዶች፣ ወዘተ የማስፈራት ባህሪ አላቸው:: ሆኖም ከእነዚህ ይልቅ መፈራትና መከበር የሚገባው ሌላ አለ:: እርሱም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ሰው በማናቸውም ዓይነት ሁኔታ ይሁን የሚገባው ክብር ሊሰጠው ይገባል:: ከጉልበተኝነትና ከኃይለኝነት አኳያ ግን ሰው ሊፈራ አይገባውም:: ምክንያቱም የሚያስፈራችሁና የሚያስደነግጣችሁ እርሱ (የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር) ይሁን ተብሎ ስለተጻፈ ነው:: ኢሳ. 8:13:: በራዕይ 13:10 ላይ በአውሬው የግዛት ዘመን የሚኖሩ ሰዎች ከመፍራታቸው የተነሳ 666ን ሲቀበሉና ጌታን ሲክዱ ይታያል:: መፍራት አንድ ትልቅ ክፉ ነገርን በሰው ህይወት ይፈጥራል:: ይኸውም አለማመንንና አለመቀበልን ነው:: ራዕይ 21:8:: መጽሐፍ ቅዱስ የሚፈሩ ሁሉ እድላቸው በዲን በሚቃጠል በእሣት ባህር ነው ይላል:: የትኛው ይመረጣል፤ የአውሬው ወገን ሆኖ ለጊዜው በምድር ተደላድሎ ኖሮ በኋላ በዘላለም እሣት መቃጠል ወይስ ለወራት ወይም ለ3½ ዓመታት በአውሬው ተሰቃይቶና በ666 ሰይፍ ተቆርጦ የዘላለምን መንግሥት መውረስ? ይህ ጥያቄ ካሁኑ ሊጤንና ምላሽ ሊያገኝ ያሻል ምክንያቱም የመዳን ቀን አሁን ስለሆነ ነው:: 2ኛ ቆሮ. 5:2:: ለሰው ልጅ ክብሩ ወይም ውርደቱ የተቀመጠው ልቡ (አስተሳሰቡ) ላይ ነው:: ልቡን ለፈጣሪው ከሰጠ ጌታ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ይሰጠዋል:: ይህ ኃይል ደግሞ በጽድቅ ኖሮ ለእውነት እንዲሞት ይረዳዋል:: ይህ ከፈጣሪው የመጣው ኃይል ነበር ጌታ ኢየሱስን በመስቀል ላይ ስለሰዎች ኃጢአትና ስለጽድቅ እንዲሞት ያደረገው ስለሆነም ፍርሃትን ጌታ አድርጐ ተሸማቅቆ ከመኖር ይልቅ ፍርሃትን አስወጥቶ ጽድቅ በሞላበት ድፍረት ሲያመላልስ ለሚችለው ለጌታ ኢየሱስ ሁለንተናን መስጠት ነው::

## 4.10 ፖለቲከኛ?

ፖለቲካ የአስተዳደርና የነገራት ዘዴ ነው:: እውነተኛው ፖለቲካ ሰው በምድር ሲኖር ራሱን አብዝቶ እንዳይጠቅም ከሌላው እንዳይበዘብዝና ሌላውን እንዳይጐዳ እንዳይመዘብር፣ ጉቦ እንዳይቀበል፣ እንዳይዋሽ፣ በሰነድ እንዳያጭበረብር፣ ድሃን እንዳይጨቁን፣ ጥፋተኛው ነጻ ነህ ጻድቁን ኃጢአተኛ ነህ እንዳይል ያዛል:: ጆርጅ ዋሽንግተን እንዳሉት የእውነተኛ ፖለቲካ ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስና እግዚአብሔር ናቸው:: ሆኖም የተመረዘና የተበረዘ ፖለቲካ ግን ሌላ ነው:: የዚህ ዓይነቱ ፖለቲካ የሰዎችን መብትና ነጻነት ይጻረራል:: ፍትህ አያስገኝም:: ማንም የፖለቲካ ሰው ነኝ ብሎ ቢያመካኝና ከእግዚአብሔር እውነት ቢርቅ ከፍርድ ነጻ አይሆንም:: ስለሆነም ከሐሰተኛው ክርስቶስ ወጥመድ አያመልጥም:: ነቢዩ ዳንኤል ወደ ባቢሎን ተማርኮ በሄደ ወቅት ከናቡከደነጾር ቀጥሎ 3ኛ ገዢ ነበር:: ሆኖም የሚያረክሰው ነገር በመጣ ጊዜ ራሱን ጠበቀ:: እውነተኛ ፖለቲከኛ ምን ጊዜም ለእውነት ይቆማል:: አታምልክ የሚል ተጽዕኖ ቢደርስበት ግን ይህ ውሸት ነውና አይስማማም:: ዳን.6:: የፖለቲካ አስተዳዳሪዎች ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እውነት እስካልተመለሱ ድረስ እድል ፋንታቸው ከአውሬው ጋር ሊሆን እንደሚችል ልብ ሊሉ ይገባል::

## 4:11 ኃይማኖታዊ?

በዚህ ርዕስ ሥር ኃይማኖታዊ ሲባል ክርስቶስ ኢየሱስ ፈጣሪና ጌታ መሆኑን የማይቀበሉ ሁሉና በክርስትና ስማዊና ሙት ህይወት ውስጥ የሚኖሩትን የሚጨምር ይሆናል:: በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ 6000 ያህል ኃይማኖቶች እንዳሉ ይነገራል:: ለመሆኑ እነዚህ ሁሉ ሰውን ወደ ዘላለማዊው ቤት ያስገቡት ይሆን? መጽሐፍ ቅዱስ ግን በሩ አንድ እንደሆነና ያም በር አንዱ ክርስቶስ ኢየሱስ እንደሆነ በግልጽ ያስቀምጣል:: ዮሐ. 10:7-10 ወደ እውነተኛው ሰማያዊ አባት ለመድረስ መንገዱ አንድ እንጂ 6000 አይደለም:: ዮሐ. 14:6 በሰፊው መንገድ ብዙ በጠባቡ ግን ጥቂት ሰዎች እንደሚሔዱበት የዛሬ 2000 ዓመት አካባቢ የተነገረው እውነት ትላንት ዛሬ ነገም ተግባራዊነቱ ያው ነው:: ቃሉ ፈጽሞ አይለወጥም:: ስለዚህ ማንኛ ውም አንባቢ ሰው ሁሉ የፈለገውን ማመንና ማምለክ ይችላል የሚለውን አጉል ፍልስፍና ወደ ጐን በመተው ጠባቡን በር (መንገድ) ፈልጐ ሊይዝ ይገባዋል:: እንግዲህ ሰውን ወደ ሰማያዊ ቤቱ የሚያስገባው በክርስቶስ ኢየሱስ አምኖ የሚኖረው በክርስቶስም የሚሰራው ህይወት እንጂ ማንኛ ውም ዓይነት ኃይማኖት እንዳይደለ ልብ ሊል ይገባል:: የፈለጉትን ማመን ይቻላል የሚለው አቋም አዝማሚያው ወደ ክህደት ነው::

## 4.12 ከሃዲ?

ሰው ለረጅም ጊዜ ክርስቶስን አምኖ ከቆየ በኋላ ፊተኞችም ኋለኞች ይሆናሉ፤ እንደተባለ ጌታን ክዶ ወደ ዓለም ሊሄድ ይችላል:: በኋላም የክፉ ኃይላት ሊሰለጥኑበት ወይም በእግዚአብሔር ምህረት ለተወሰነ ጊዜ ሊቆይ ይችላል:: የዚህ ዓይነቱን ሰው ደግሞ ወደ ንስሀ መመለስ እንደሚያስቸግርም መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል:: ዕብ. 6:4-8:: የዚህ ዓይነት ሰዎች ቶሎ በንሰሀ ካልተመለሱ የንስሃው በር ከተዘጋ ፍጻሜያቸው እሣት ነው:: ቁ.8:: የከሃዲ ዓይነቱ የተለያየ ነው:: አንዳንዱ እንደ ጴጥሮስ ዙሪያውን የፈተና ኃይል ከብቦት ስለሚያስጨንቀው በተደጋጋሚ ጌታን የሚክድ አለ:: ሆኖም ግን ሳይወድድ በተጽዕኖ ስለሚሆንበት በንስሀ ሊመለስ ይችላል:: ሌላው ግን ይህንን ዓለም ወድዶ ጌታን አናንቆ ደሙን ረግጦና ቅዱስ መንፈሱን አክፋፍቶ የሚሄድ ነው:: ዕብ. 10:26-29:: 2ኛ ጢሞ. 2:13:: ያለ አምልኮ ዝም ብሎ እኖራለሁ ባይና ከእርሱ በላይ ፈጣሪና ገዢ መኖሩን የማይቀበለውም ከሃዲ ነው:: ከሃዲ ቶሎ ወደ ክርስቶስ ካልተመለሰ እድል ፈንታው ከአውሬው ጋር ይሆናል ማለት ነው::

## 4:13 መናፍስት ጠሪ? ጠንቋይ? ሟርተኛ?

ማንኛውም ከመንፈስ ቅዱስ ውጪ የሆነ ልዕለ ተፈጥሯዊ ወይም መንፈሳዊ ልምምድ ሁሉ የሚፈረጀው ከገሃነም ደጆች ክፍል ነው:: ዓለማችን እጅግ በጣም ብዙ በሆኑ የጥንቆላ፣ የሟርት፣ የመተት መጻህፍትና አጋንንታዊ ልምምዶች እየተሞላች ነው:: ከመናፍስት ጋር በተያያዘ ብዙ ዓይነት ጠቃሚ መሰል ነገሮችን የሚሰሩ ሁሉ ከእግዚአሔር መንግሥት ውጪ ናቸው:: በመናፍስት አሠራር ሃብታም የሚያደርጉ፣ <u>ጥቁርና ነጭ አስማት</u> የሚሰሩ፣ መዳፍና ግንባር አንባቢዎች፣ ሙታን



ሳቢዎች፣ በመናፍስት በሽታ አስለቃቂዎችና በሽታ ፈጣሪዎች፣ አስማታዊ መድኃኒት ቀማሚዎች፣ መገለጥ ሰጪዎች፣ የጠፋ ነገረ አስገኚዎች፣ ትክክለኛና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ከምድር በታች ያሉ ጥቅማ ጥቅም አመልካቾች፣ ኮከብ ቆጣሪዎች፣ ወዘተ ከክርስቶስ ት/ት ጋር ስለማይስማሙ የአውሬው አገልጋዮች መሆናቸው የማይቀር ነው:: ስለሆነም ካሁኑ ሊያስቡበት ይገባል::

## 4.14 ቤተ ክርስቲያን?

ቤተ ክርስቲያን ማለት የተሰበከላቸውን እውነተኛ ወንጌል ሰምተው በክርስቶስ ኢየሱስ አዳኝነትና ጌትነት አምነው በመቀበል እንዲሁም ንሰሀ በመግባት በኃጢአታቸው አዝነው ተናዘውና ከኃጢአት ርቀው ትክክለኛውን ህይወት የሚኖሩ ቅዱሳን ማለት ነው:: እነዚህ ሰዎች አስቀድሞ በህይወታቸው ተሞልቶ የነበረው ኃጢአት በሰው ሰራሽ ሳሙናና ውኃ ሳይሆን በክርስቶስ ክቡር ደም ታጥቦላቸዋል:: ከሰይጣን ልጅነት ወደ እግዚአብሔር ልጅነት ተሸጋግረዋል:: ከተቀበሉትና ከታተሙበት መንፈስ አኳያ የእግዚአብሔር ልጆች ተብሎ የመጠራትን መብትና ሥልጣንን ያገኙ ናቸው:: ዮሐ. 1:12-13፤ 1ኛ ዮሐ. 3:8-10:: ሮሜ 8:16:: ምክንያቱም ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣን ሰጣቸው የሚለው ቃል ፈጽሞ የታመነና ሊዋሽ የማይችል ስለሆነ ነው:: የእግዚአብሔር ልጅ የመሆን ሥልጣን ራሱ ጌታ እግዚአብሔር በስላሴ አሠራሩ የሚፈጽመው እንጂ ሰው ሙሉ በሙሉ መርምሮ ሊያገኘው የሚችል ነገር አይደለም:: እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን ማለት ከሰይጣን ተገዢነት ነጻ የወጣና የዲያብሎስና የክፉ የሠራዊቱ ጠላት የሆነ አካል ማንነት ማለት ነው::

ቤተ ክርስቲያን ከመንፈሳዊ ኃይላት ጋር ትዋጋለች:: በሰማይ ውስጥ ከዲያብሎስ ቀጥሎ ሥልጣን ያላቸው የክፉ ሠራዊት አሉ:: ከቃሉ፣ ከክርስቶስ ደምና ከስሙ ባገኙት ኃይልና ሥልጣን እነዚህን መንፈሳዊ ኃይላት ይጋጠማሉ:: ኤፌ. 6:12-18:: እነርሱ በጾምና በፀሎት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይዘጋጃሉ:: ድል የሚሰጣቸው ከቃሉ፣ ከስሙና ከፀሎት በስተኋላ ያለው መለኮታዊው እግዚአብሔር ነው:: ሆኖም ቤ/ ክ. ሲባል የአምልኮት መልክ ኖሯቸው እንቅስቃሴያቸው የሞተውን፣ ለብ ብለው የተተፉትን፣ ፍሬ አልባ ሆነው ከወይኑ ግንድ ተቆርጠው ፍሬያቸው በክፉ የሚገልጣቸውን አይጨምርም:: መጽሐፍ ቅዱስ ለሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን «ስም አለህ ሞተህማል» (ራዕይ 3:2) ኤፌሶንን ደግሞ «አንተ የምትተኛ ንቃ ከሙታንም ተነሳ» በማለት ሲጽፍ (ኤፌ. 5:16-17) በወቅቱ ያሉበትን ሁኔታ ማመልከቱና ንሰሀ ካልገቡ ጌታ መቅረዙን ሊያነሳ መሆኑን ማስጠንቀቁ ነበር:: ጳውሎስ የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል በማለት ሲጽፍ (2ኛ ጢሞ. 3:5) ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖራቸው የሚገባው ህብረት ውል እንደጠፋባቸው ያሳያል:: እንደ እነዚህ ዓይነት ቤተ ክርስቲያናት ከዓለማውያን ያልተሻሉ ናቸው:: የሃይማኖትን መልክ ብቻ ይዘው የሚጓዙና በዳግም ልደት አሠራር እንደኒቆዲሞስ ያልተለወጡ እስከሆነ ድረስ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ኅብረት የለውም::

አንድ ሰው አውሬውን በትክክል መቃወም የሚችለው ሥልጣንን ከእግዚአብሔር ሲቀበል ብቻ ነው:: ሥልጣን ከኃይል ይበልጣል:: እግዚአብሔር የሁሉ ገዢና የበላይ ነው:: እርሱ ብቻ በክፉ ኃይላት ላይ ድልን ሊያቀዳጅ የሚችል ኃይልን እንዲሁም ሥልጣንን መስጠት ይችላል:: ሆኖም ይህንን ሥልጣን ለመቀበል ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር ወደ ቤተ ክርስቲያን ክልል መግባት ይኖርበታል:: ወደ ቤተ ክርስቲያን ክልል መግባት ማለት እሁድ ወይም ሌላ ቀን ወደ ቤተ መቅደስ ሄዶ መመለስ፣ እንደ ሽርሽር ፀሎት ቤት ሄዶ ዝማሬ ማዳመጥ፣ በግል ቤት ቁጭ ብሎ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ገጾችን ማንበብ፣ በሺህ የሚቆጠሩ ማምለኪያ ህንጻዎችን ማሰራት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ (ዩኒቨርሲቲ) ገብቶ በማስተርስ ወይም በድግሪ ተመርቆ መውጣት፣ እውቅ ሰባኪ መሆን፣ ወዘተ ብቻ ላይሆን ይችላል:: ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባት ማለት ወደ ክርስቶስ አካል ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቆ መቀላቀል የሰማዩን ርስት መያዣ መንፈስ ቅዱስ መቀበል ማለት ነው:: ለዚህም ማረጋገጫ ፍሬዎች በግለሰቡ ህይወት መታየት አለባቸው:: ከሚታዩትም ፍሬዎች ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው:: አንድ ሰው ወደ ክርስቶስ አካል ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ አሠራር ሲቀላቀል ህይወቱ ዘወትር የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ይናፍቃል:: ያነብባል:: ያጠናል:: ቃሉንም ሲያነብብ ታላቅ ደስታና ሐሴት ይሰማዋል:: ኤር. 16:15-16፤ 1ኛ ጴጥ.2:1-5:: እርሱ ያገኘውን ታላቅ ደስታ ለሌሎች ሰዎች ይመሰክራል:: አስቀድሞ ይናፍቃቸውና ያደርጋቸው ከነበሩት የኃጢአት ልምምዶች ፍጹም ይለያል፣ ይጠላቸዋል:: ህይወቱ ይለወጣል:: 1ኛ ዮሐ. 3:8-10:: ዘወትር ቃሉን ስለሚመገብ በመንፈሳዊ ህይወቱ ያድጋል:: በምድር ያለውን በመጠን በመጠቀም ሃሣቡ በሰማያዊ ነገሮች ላይ ይጣበቃል:: ቆላ. 3:1-3:: እውነተኛ አማኞችን ይቀርባል:: ወንበሩና መንገዱ ከኃጢአተኞች ጋር አይሆንም:: በዚህ ዓይነት መንገድ የሚኖር ሁሉ ክርስቲያን ነኝ ቢል አልተሳሳተም:: ይህ ሰው ስሙ በህይወት መዝገብ ተጽፏል:: የእግዚአብሔርም ልጅነት ሥልጣን አለው:: በዚህ እውነት ከፀና የአውሬው ተሳታፊ አይሆንም:: በአውሬውና በተከታዮቹ ከሚደርሰው ክፉ ዕድል ፈንታ ማምለጫው ብቸኛ መንገድ በእውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ክልል ውስጥ መግባት ነው::

ራሳችንን <u>የዳግመኛ ልደት ቤተ ክርስቲያን</u> አባል አድርገን የምንቆጥር ሁሉ ለራሳችን ከፍተኛ ትኩረት ልንሰጥ ይገባል:: ጌታ ኢየሱስ ፊተኞች ኋለኞች ኋለኞችም ፊተኞች ይሆናሉ እንዳለ ትንቢቱ እንዳይፈጸምብን እንትጋ:: ህይወት እንደ ተንከባካቢው ነው:: ልቅ ካደረግነው ኃጢአትን ለማንገሥ ያነሳሳናል:: ሐዋርያው ጳውሎስ ለምኞቱ እንድትታዘዙ <u>በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገስ</u> ያለው ያለ እውቀት አይደለም:: በአንድ አማኝ ህይወት ኃጢአት ሊነግሥ ይችላል ይህም ሲሆን ያንን ሰው ኃጢአት ይገዛዋል፣ ይቆጣጠረዋል፣ ይሰለጥንበታል ማለት ነው:: ሰው በኃጢአት አረንቋ ውስጥ ተዘፍቆ መንግሥተ ሰማያትን እንደገባው 100% ሊመኝና ሊናፍቅ ይችላል:: ማንም አይከለክለውም:: ተመኘ ማለት ግን አገኘ ማለት አይደለም:: <u>ሰው ደግሞ ምኞቱን ኃይማኖቱ አድርጐ ሊቀበል አይገባውም</u>:: አንዳንድ ሰዎች ምኞታቸው በመልካም ነገር ላይ የጠነከረ ስለሆነ ያንን የሚቃረን ስብከት ሲሰሙ ነገሩ እንደዚህ ይሆንን ብሎ



እውነትን ከመመርመርና ከመያዝ ይልቅ ምኞታቸው ስለ ተገጨባቸው ብቻ የሚቆጡ አሉ:: ምኞት ሲጠነክር የጽድቅ ጠላት መሆኑ አይዘንጋ:: ሰውነታችንን የአመጻ የጦር ዕቃ አድርገን እያቀረብን በፀጋ ድኛለሁ በሚል የተሳሳተ ግላዊ መመሪያ ውስጥ ብንገኝ የኃጢአታችንን ዋጋ እንደምንቀበል አንዘንጋ:: ሮሜ 6:22-23:: መለወጥ አንድ ነገር ሲሆን አለመለወጥ ደግሞ ሌላ ነገር ነው:: ሁለቱም ተቃራኒዎች ናቸው:: ሰውነት ለጽድቅ የጦር ዕቃነት እንጂ የአመጻ የጦር ዕቃ ሆኖ ሊቀርብ አይገባውም:: ምክንያቱም ሞት የሆነው ዋጋው ስለሚከተለው ነው:: ሞትም ከእግዘአብሕር ተለይቶ ለዘላለም በስቃይ መኖር ነው:: ማንም በክርስቶስ ቢሆን ኩነኔ የለበትም ሲባል ስላለፈው በደሉ መወገድ እንጂ ስለወደፊቱ ኃጢአት መሥራቱ ጭምርም ማለት አይደለም:: ሮሜ 6:1-2:: ትላንት በክርስቶስ የተወገደልኝ ኃጢአቴ ለነገውም በደሌ ዋስትና ነው በሚል የተሳሳተ መርህ ወደ ኃጢአት መንገድ ራስን በማታለል ወደ ከፍተኛ ዲያብሎሳዊ ወጥመድ ውስጥ መክተት ነው:: ስለሆነም ማንም በቤተ ክርስቲያን ክልል ውስጥ አለሁ የሚል ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ሊኖራት ስለሚገባው የመንግስተ ሰማያት መግቢያ ባህሪይ ጠንቅቆ ሊያውቅ ይገባዋል::

<u>የአገልጋይ መጠኑ</u>

ቤተ ክርስቲያንን ከክፉ አሠራር ለመጠበቅ የቤተ ክርስቲያን ሎሪዎች ሊያልፉበት የሚገባ ከፍተኛ ሚና አለ:: ይኸውም አባላትን ከመንከባከብ አኳያ ነው:: <u>የሁላቀፋዊነት</u> እንቅስቃሴ እየገነነ በሄደበት በአሁኑ ወቅት ካለፉት ጊዜያት ይልቅ አሁንና ወደፊት የቤተ ክርስቲያን አመራር ስልት ጥራት የሞላበት ሊሆን ያሻል:: በተለያዩ ጊዜያት ከተለያዩ አገሮች ሚሽነሪዎችና መሰሎቻቸው ወደ ኢትዮጵያ ገብተዋል:: ዛሬም እየገቡ ነው:: ነገም እንዲሁ:: ከገቡትም ውስጥ ጥቂቶቹ አንድ አባል በአንድ አጥቢያ ሊወሰን አይገባም፣ ክርስቶስ በሁሉ ስለሆነ አንድም አባል የሁሉ ነው:: ዲኖሚኔሽን ቤተ-እምነት (የአብያተ ክርስቲያናት ወቅታዊ ስም አጠራር) አያስፈልግም:: አንድ አባል በሁሉም ቦታ እየገባ በነጻነት ማገልገልና መገልገል ይችላል፤ ወዘተ የሚለውን መርህ የሚከተሉ ናቸው:: ከዚህም መስተጋብር የተነሳ ብዙ ምዕመናን ስለ ቤተ ክርስቲያን አመሠራረትናአመራር፣ ስለ ወንጌል ሥርጭት ጥበብ፣ ስለነፍሳት እንክብካቤ በቂ እውቀትና ተግባር አዘል ሥልጠና ሳይሰጣቸው ጌታን በተቀበሉ በሦስትና በአራት ወራት ውስጥ ገና አዲስ ክርስቲያን ሳሉ ለአገልግሎት ሲሰማሩ ይታያል:: ለጌታ ቅንዓት አላቸው:: ሆኖም እንደ እስራኤላውያን ቅንዓታቸው በእውቀት የቀና አይደለም:: በእውቀት አይቅኑ እንጂ ለእግዚአብሔር እንዲቀኑ እመሰክርላቸዋለሁ:: የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውን ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም ተብሎ እንደተጻፈ. ሲሆን ዛሬ ይታያል ሮሜ 10:2-3:: እስራኤላውያን ለጌታ የቀኑ መስሏቸው ጌታቸውን እንደገደሉ ዛሬም የጌታን ቤተ ክርስቲያን የመሰረቱና ያገለገሉ መስሏቸው የአውሬውን ቤተ ክርስቲያን መሥራቾችና አስፋፊዎች እውነተኛይቱን ቤተ ክር. ግን አፍራሾች እንዳይበዙ ያስፈራል:: በተግባርም ታይቷል::

አንድ አገልጋይ ጌታን ለማገልገል ሲነሳ ሊያተኩርባቸው የሚገቡ ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ እርሱ በራሱ ላይ ሊያተኩር ካልቻለ ግን መሪዎች ሊፈትሹት ይገባል፡፡ ለዚህ ሥርዓት የማይገዛ ራሱንም የማይመረምር ከሆነ ግን ቢያገለግል የማይገባ ዘር ዘርቶ ክፉና መራራ ነገር እንደሚያጭድና እንደሚያሳጭድ ልብ ሊል ይገባዋል፡፡ አንድ ሰው ለአገልግሎት ሲነሳ በራሱ ፈጽሞ ሊንቀሳቀስ አይገባውም፤ ራሱንም ሊያስማራ አይገባውም፡፡ እንኳን እርሱ ጌታ ኢየሱስም አሰማሪ ነበረውና፤ ጌታ የራሱን ፈቃድ ሊያደርግ አልመጣም የአባቱን እንጂ፡፡ ዮሐ. 4:34፡፡ ማንም ሰው በራሱ ፍጹም አይደለም፡፡ የእኔ ተቆጣጣሪና መሪ 100% መንፈስ ቅዱስ ነው ካለ ሰው አያስፈልገኝም፤ ሌላ ጓደኛ ሊስለኝ፣ ሊያርመኝ አያስፈልገኝም ማለቱ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሔዋን መመሪያ ነበር፡፡ ሔዋን አዳምን አማክራ ቢሆን ኖሮ ላትወድቅ ትችል ነበር፡፡ በመንፈስ ከመናፍስት ጋር ተራክባ ለመመራት ሞከረች ውጤቱም እንደምናውቀው ሆነ፡፡ ዛሬም ቢሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊም ሆነ ሰዋዊ መመሪያ አያስፈልገንም በመንፈሳዊ ዓለም ውስጥ ስለገባን መመሪያችን መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው የሚሉ እየበዙ መጥተዋል፡፡ መንፈስ ቅዱስ እንደዚህ ባለ መንገድ ብቻ አይመራም፡፡ ለዚህም «መንፈስ» የሚለውን ቃል ፍቺና ተግባራዊነት በማጤን መመርመር ያሻል፡፡ አንድ አገልጋይ በጌታ ህዝብ ፊት ቆሞ ራሱ ደርቆ ሌሎችም ላይ መንፈሳዊ ድርቀት ከመጨመሩ ስቶም ከማሳቱ፣ ወድቆም ከመጣሉ፣ ተዋርዶም ከማዋረዱ፣ ፈርዶም ሳይፈረድበት በፊት በስርዓት በቤተ ክርስቲያን አመራርና ቁጥጥር ውስጥ ቢያንስ ለ3½ ዓመታት ማደጉን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ራሱን ለቤተ ክርስቲያን አመራር ማስገዛት የግዱ ነው፡፡ እንኳን ከቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባህልና ሥርዓት ርቆ ይቅርና በውስጡም እንኳን አድጕ የተዋጣለት አገልጋይ መሆን የሚቸግርበት ሁኔታ አለ፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ ቲቶንና ሌሎች አገልጋዮችን የመዘነበትን ሚዛን በጥንቃቄ መፈተሸ ለታማኝ አገልጋይነት እጅግ ይጠቅማል፡፡ 2ኛ ቆሮ. 8:15-22፡፡ ጳውሎስ የቆሮንቶስን ምዕመናን ለቲቶና ለተባባሪዎቹ ከመስጠቱ በፊት ቲቶንና አብሮት ያለውን አገልጋይ መዝኗቸውና ፈትኗቸው ነበር፡፡ ብዙ ጊዜ በብዙ ነገር መርምረን ትጉ እንደሆነ ያገኘነውን ... እንልካለን ሲል የወሰደውን የጥንቃቄ እርምጃ አገልጋይም ሆነ የአገልጋይ መራጭና አሰማሪ ልብ ሊሉት እንዲሁም ሊተገብሩት የሚገባ እውነት ነው፡፡ ቲቶ ለጥቂት ጊዜ በጥቂት ነገሮች አኳያ ብቻ አልተመረመረም፤ ብዙ ጊዜ በብዙ ነገር እንጂ፡፡ የቲቶ አነሳስ፣ አካሄድ እድገት፣ ለራሱ ክብር ሳይሆን ለጌታና ለምዕመናን ህይወት፣ ለገንዘብ ሳይሆን ለአገልግሎት፣ ራሱን በራሱ በመምረጥ ሳይሆን በመመረጥ የተገኘ አገልጋይ ነበር፡፡ ጢሞቴዎስም ቢሆን ለአገልግሎት ሳይላክና እጅ ሳይጫንበት በፊት ጳውሎስ በተለያየ አቅጣጫ አገላብጦ መርምሮታል፡፡ 2ኛጢሞ. 1:3-7፡፡ ጢሞቴዎስ የእንባና የእምነት ስጦታ ያለው ሰው መሆኑ ተረጋግጦ ነበር፡፡ መዳን የሚገኝባቸው የጥበብ አዘል መጻህፍት ወዳጅ መሆኑ ተፈትሾ ነበር እጅ የተጫነለትና የተጸለየለት፡፡ ጢሞቴዎስ ከራሱ ኑሮ ይልቅ ለእግዚአብሔር ህዝብ ኑሮ የሚጨነቅ በምዕመናንንም የተፈተነ ነበር፡፡ ፊልጵ. 2:19-24፡፡ በተጨማሪም አፍሮዲጡ በነፍሱ የተወራረደና በጌታ የጐደለውን ሥራ



ለመሙላት የተሰጠ ሰው መሆኑን አውቆ ጳውሎስ ሲልከው ይታያል፡፡ ቁ. 25-30፡፡ ጳውሎስ ሐዋርያ ነው፡፡ ለጌታ ሥራና ለምዕመኑ እጅግ የሚጠነቀቅ ታላቅ ሰው ነው፡፡ ማንንም አገልጋይ በስሜት ስለተቀጣጠለና ስለዘለለ አይቶ የመንፈስን ሳይሆን የስሜትን መመዘኛ ተጠቅሞ አገልጋዮችን ሲል፤ አይታይም፡፡ ያሰማራቸው ፈትኖ ነበር፡፡ ዛሬስ ወደ ጌታ ሥራ የሚሰማሩና ጥሪ አለኝ የሚሉ አገልጋዮች በዚህ መስፈርት ውስጥ ራሳቸውን ማስቀመጥ የለባቸውም? እኔን ማንም አይቆጣጠረኝም መንፈስ ቅዱስ አይስትም እኔም ድምጹን ስሰማ አልስትም፤ ስለሆነም አልሳሳትም በሚል ትምክህታዊ መመሪያ ተይዘው መጓዛቸው ምን ያህል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው? ለመኖርና ለመሞት ወዘተ ጊዜ እንዳለው ሁሉ በጌታ ዳግም ለመወለድ፣ ለማደግ፣ ለመገልገል፣ እጅ ለመጫን፣ በአገልግሎትም ለመሰማራት እንዲሁ ጊዜ አለው፡፡ ስለሆነም በተለይ ለማገልገል ጊዜን እንጠብቅ፡፡

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የአገልጋዮችን ሁሉ መንፈሳዊና ሌላውንም ጤንነት መመዘን ይኖርባቸዋል፡፡ ሐዋ. 20:28-30፡፡ የጌታ ህዝብ ጠባቂዎች እረኞች ናቸው፡፡ ከሆኑም የመጨረሻዋን የነፍስ ዋጋ እስኪከፍሉ ድረስ ጊዜን፣ ቦታን፣ ገንዘብን፣ እውቀትን፣ አመራርንና አስተዳደርን በመጠቀም የጌታን ህዝብ ሊጠብቁት ይገባል፡፡ መንጋ ተጠበቀ የሚባለው በድብቅም ሆነ በግልጽ ባልተፈቀደለት (ባልተፈተነ) አገልጋይ ምዕመኑ እንዳልተገለገለ ሲረጋገጥ እንዲሁም በቤ/ክ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ደቀ መዝሙር ሲሆን ነው፡፡ ክርስቶስ ኢየሱስ አንዲትን ነፍስ ወደ አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚልካት ያቺ ነፍስ አምናና ተጠምቃ ደቀ መዝሙር (የኢየሱስ ተማሪና ጌታን መስላ የምትኖር) እንድትሆን ነው፡፡ ሆኖም ግን ያቺ ነፍስ ጤናማነታቸው ባልተመረመሩና ባልታወቁ አገልጋዮች የምትገለገል ከሆነ ከየዓይነቱ በመማር እስከመሰናከል የምትደርስና ተናጋሪዎችን በማወዳደር አንዱ ወደ አንዱ አንዱ ወደ ሌላው የምትንከራተት ከሆነ ተጠብቃለች ማለት አይቻልም፡፡ ስለሆነም ለአንዲት አጥቢያ በተሰጠች ነፍስ ላይ ተናጋሪ ሁሉ መሰልጠን አይኖርበትም፡፡ ምክንያቱም ይህ አሠራር ለጋለሞታይቱ (ምድራዊ ወዳዲቱ) ቤተ ክርስቲያንና ለአውሬው ተከታይነት ሁኔታን ስለሚያመቻች ነው፡፡ ወደ ከፍተኛው የአውሬው አሳሳችነት ሳንሔድ ግን ከወዲሁ ሊተኮርባቸው የሚገቡ ብዙ እንቅስቃሴዎች መኖራቸው ልብ ሊባል ይገባል፡፡

አንድን አገልጋይ የመፈተን ኃላፊነት የመሪዎች ድርሻ ብቻ አይደለም፡፡ የቤተ ክርስቲያን አባላትም በዚህ ጉዳይ ላይ ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡ ምንም እንኳን በእውቀትና በመንፈሳዊ አሠራር የተወሰኑ ምዕመናን በቂ መረዳት ባይኖራቸውም ከመሪዎቻቸው በሚያገኙት ትንሽ ሥልጠና ሊጠነቀቁና እርምጃ ሊወስዱ ይችላሉ፡፡ ራሳቸው ክፉና ደጉን የመመርመር መንፈስ አላቸው፡፡ ቃሉን፣ መንፈስ ቅዱስንና የአካባቢ ወገኖቻቸውንም መጠቀም ይችላሉ፡፡ አንድን አገልጋይ ሲያዩ ለአንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ለረጅም ጊዜ ስለ ህይወቱ ማጥናት ከመሪዎቻቸው በመጠየቅ ሊረዱ ያሻል፡፡ ማንነቱን ለማያውቁትና በበቂ መሪዎች ላልተመሰከረለት አገልጋይ ራሳቸውን መስጠት የለባቸውም፡፡ ምክንያቱም በዚህ መንገድ ያለፉ ሰዎች ብዙ ስለተጐዱ ነው፡፡ ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት ብለው ክፉ መንፈስ

ተጠናውቷቸዋል:: የፀሎትን፣ የቃል ንባብንና የቅዱሳንን ኅብረት እስከመጣል ደርሰዋል:: ክቡር የሆነውን የፀጋ ስጦታ አጠቃቀም ውሸትና ማጭበርበሪያ ነው እስከማለትና ጌታን እስከመጠራጠር ደርሰዋል:: ለመፈወስ ተስፋ አድርገው ሔደው ተፈውሳችኋል! ተብሎ ተነግሮላቸው ፈውሱን ሲያጡት ለማረጋገጥ በተመለሱ ጊዜ ከእምነትና(ሽ) ማነስ! ነው ተብለው ተኮንነዋል:: አብያተ ክርስቲያናት ታማኝ አገልጋዮቻቸውን አጥተዋል:: ስለሆነም አገልጋዮችም ራሳቸውን ያስመርምሩ፣ መሪዎችና ምዕመናንም ይመርምሩአቸው:: ይህ ካልሆነ <u>ይበጃል ያሉት ኩል አይን አጠፋ</u> የተባለው በቤተ ክርስቲያን ላይ እንዳይደርስ ያሰጋል:: ምዕመናን ምንም ያህል መንፈሳዊ እውቀቱ ቢኖራቸው የቤተ ክ. የመሪን ድምጽ የግድ መስማት ይገባቸዋል:: ፕሬዚዳንት ሆኖ የተመረጠ ሁሉ ንጉስም ሲሆን በሁሉ ነገሩ የሁሉ በላይ አይደለም:: በእውቀት በችሎታ በልምምድ የሚበልጡት አሉ:: ሆኖም ስልጣን ስላለው የሚያወጣቸው መመሪያዎች ይተገበራሉ:: ሥልጣን ከእግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች እስከተሰጠበት ድረስ ለእውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች መገዛት ይበጃል:: ሆኖም አባት መከልከሉ አይቀርም:: ልጅ ባይጥመውም የአባትን ድምጽ ይሰማል በዚህም ይጠቀማል::

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለ 666 የተተነበየውንና ትላንትናና ዛሬ የተፈጸመውን ተመልክተናል:: በመጽ. ቅዱስ ውስጥ የተጻፈው እውነት ተግባራዊነቱ ታይቶአል:: በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያልተጠቀሱ ሌሎች ብዙ አሉ:: መጽሐፉን ስናነብብ አንድ ልብ ልንለው የሚገባ እውነት አለ ይኸውም የክርስቶስ መምጫና የቤተ ክ. መነጠቂያ ጊዜ እጅግ ቅርብ መሆኑን ነው:: ይህም ሊሆን የሚችለው የዚህ ዓለም ፍጻሜ ግልጽና የቅርብ ምልክት የአውሬው መገለጥ ነው:: በ2ኛ ተሰ. 2:3 ላይ የተነገረው ክህደት ዓይን ባወጣ መልኩ በምድራችን አለ:: ከ6000 በላይ ኃይማኖቶች መኖራቸው በቂ ማስረጃ ነው:: "ክህደቱ" የተባለው ከመጣ ዘመናት አልፈዋል:: የመጨረሻውና ከፍተኛው ክህደት ግን አውሬው ሲገለጥ የሚሆን ነው:: ከክህደት ቀጥሎ ሐሰተኛው ክርስቶስ ይመጣል:: ይህ ባለ 666ቱ አውሬ ከመጣ ደግሞ በምድር ላይ መሥራት የሚችለው 7 ዓመታት ብቻ ነው:: ቀጥሎም ጌታ ኢየሱስ ከሰማይ ከቅዱሳኑ ጋር ይመጣና በአርማጌዶን ጦርነት ፍጻሜውን ያደር.ጋል:: ቀጥሎም የሺሁ ዓመት ይቀጥላል::

የዚህ ዓለም ፍጻሜ እጅግ መቅረቡ ለሁላችንም ታይቶናል? የተሰሎንቄ ቅዱሳን የጌታ ቀን ቀርቧል ብለው ተናውጠው በነበሩበት ጊዜ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው የክህደቱን መምጣትና የአውሬውን መገለጥ እንዲጠባበቁ ነበር:: ዛሬ ይህ ትንቢት በአይናችን ሊፈጸም ቻለ ክህደቶች እጅግ ብዙ 666 ቁጥር ለአይናችን እስኪሰለችን መታየት ጀመረ:: ይህ የሚያመለክተን አውሬው በደጀ መሆኑን ነው:: ስለሆነም የጌታን መምጣትና የእኛን መነጠቅ በልዩ አትኩሮትና አክብሮት ልንከታተለውና ልንጠብቀው ይገባል::



ያ ቆፍጣና ጀግና ስመ ገናናው

ፈዘዘ ደከመ ድው አለው ምነው እንደተባለ ፉተኝነታችንን ማጠንከር ትተን ደብቶን መንፈሳዊ አዙሪት እንዳይመጣብን ነቃ ልንል ይገባል :: አንተ የምትተኛ ንቃ ከሙታንም ተነሳ የተባለው ለክርስቲያን ተብሎው ነበርና:: ክርስቲያናዊ ወኔአችን ሙት ሊሆን አይገባም:: ጌታን ብንተው ልንተው ብንከደው ልንካ አጥብቀን ብንይዘው ልንያዝ ነውና::

እርምጃህ ይፋጠን ጉዞህ እንዳይርቅ

ፀሐይዋ ሳትጠልቅ ሳታዘቀዝቅ እንደተባለ የጀመርነውን የክርስትና ህይወት ዳሩ እናድርስ ያልጀመርን ከሆነ ደግሞ ቶሎ ውርደት ሳይመጣ እንጀምር ዘመኑን በጥንቃቄ ለመረመረ ሰው ከ70 ያህል የዓለም ፍጻሜ ምልክቶች ውስጥ እነዚህ ሁለቱ ክህደትና የ666 (የአውሬው መኖር ምልክቶች) መታየታቸው ለጌታ ምጽዓትና ለቤተ ክ. መነጠቅ እጅግ ቅርብ ምልክቶች ናቸው::

ኤልያስ አካሔዱን ከጌታ ጋር አድርጐ ወደ ሰማይ እንደተወሰደ እኛም ለመነጠቅ የጌታ የዘወትር ፀጋ ከሁላችን ጋር ይሁን:: አሜን!

<u>ምሳሌአዊ ምክሮች</u>

(ከመጽሐፉ መልዕክት ጋር የተያያዙ)

- የተጠገነ እጅ እንደቀድሞ አይሆንም (በተለያየ እምነትና እውቀት የተበረዘ አእምሮ እንደ መጽሐፍ ቅዱሱ እምነት የጠራ እውነት ስለማይሆን እንዳትወድቅ ተጠንቀቅ)::
- ተመረቅሁ ብለህ ከተረገመ አትዋል (በእውቀትና ተኩራርተህ የፈጣሪህ ጠላት አትሁን)
- ባዶ ሆድ ጆሮ የለውም (አእምሮው በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ያልተሞላ ለሐሰት ትረት-የተጋለጠ ነው)
- ወርቅን ለማግኘት ወርቅን ይዞ መነሳት (ላልተመረመረ ማንነት ራስን መስጠት ወደ ክብር አያመጣም)
- ስድብ ከአካል ቁስል የላቀ ያምማል (ጌታ ኢየሱስን ትቶ ወደ አውሬው መጠጋት እግዚአብሔርን መስደብ ነው)
- እንደ ርግብ ገብቶ እንደ እባብ ይናደፋል (የሐሰት ትምህርት ባህሪ ይህ ነው)
- ሲሳይ ያለቀበት አንበጣ ከድንጋይ ላይ ያርፋል (የዞንገሊል ትርፉ ጉዳት ነው

- ባፍዋ ማር ያለባት ንብ በጅራቷ መርዝ አለባት (ክፉና ተንኮለኛ አገልጋዮች እንዲሁ ይቀርባሉ)
- መሬት ሲያረጅ መጭ ያበቅላል (አስቀድሞ በጌታ የጋለ ሕይወት የነበራቸው ጌታን ሲተው በሕይወታቸው ኃጢአት ሲበዛና ሲታይ)
- ይበጃል ያሉት ኩል ዓይን አጠፋ (በአውሬውና በሐሰተኞች የሚጠቀሙ ሁሉ ፍጻሜያቸው መንፈሳዊ እውርነትና ሞት ነው)
- ሰውን አትመኑ አብዷል ዘመኑ (መጽሐፍ ቅዱስንና መንፈስ ቅዱስን ታምኖ የሚጓዝ ሰው ሕይወቱ በዋስትና የተጠበቀ ነው)
- ሰማይ ላይ ጤፍ ይወቃል ቢሉ እብቁ ዓይኔ ገባ አለ (በውሸት ላይ ውሸት እየተጨመረ ይሄዳል)
- ዝንጀሮና አርበኛ ገደሉን አይቀቅም (የትጉ መመሪያ በቃሉና በመንፈስ ቅዱስ በታማኝ አገልጋዮቹም ራስን መጠበቅ ነው)
- በቅርብ ያልመለሰ እረኛ ሲሮጥ ይውላል (ቀድሞን ነበር እንጂ አልሞ መደቆስ አሁን ምን ያደርጋል ድስትን ጥዶ ማልቀስ)
- ጽድቁ ቀርቶ በውል በኮነነኝ (የአውሬው ተከታዮች ዘላቂ መፍትሄ የላቸውም)
- ሣቅ ሲበዛ ለቅሶ ይሆናል (ዘመኑ ለደስታ እንጂ ለጾም ፀሎት ስለማያነሳሳ ለድል እንደ ዳንኤልና ነህምያ ልናዝን ይገባል)

የሰማነውንና ያነበብነውን በብረት መቀነት ለመቋጠር በነፍስ ገበና ለሚኖር የጌታ ፀጋና ኃይል ይብዛልን:: አሜን!!!



## ፍታቴ ቃላት

(በእንግሊዘኛው ፊደላት ቅደም ተከተል)

መለኮት ነኝ፣ አምላክ ነኝ ብሎ ማሰብና ለመሆን መጣር

ክፉ ውቃቢ፣ ክፉ መንፈስ

ቋጡ፣ ፀባየ ክፉ፣ ደምልሶ ብርንዶ ጉርሶ አጥንት ከስክሶ የሚኖር፣ የሚያድንና የሚታደን በረኸኛ፣ የሰውና የእንስሳ ደመኛ

ክርስቶስ እስኪመጣና መንግሥት ለልዑል ቅዱሳን እስከሚሰጥበት ጊዜ ድረስ የዓለም መንግሥታት በምድር ገዢነት የሚሰለጥኑበትና እስራኤላውያን፣ አሦራውያን፣ ባቢሎናውያን፣ የሜዶንና የፋርስ መንግሥታት፣ የግሪክ የሮም መንግሥታት የእግዚአብሔርን ህዝብ ክፉኛ አሰቃይተዋል:: ጌታ ሲመጣና አውሬውን ሐሰተኛውን ነቢይና ዲያብሎስን ሲቆጣጠራቸው የአህዛብ ዘመን ያበቃል:: ራዕይ 11:15፤ ራዕይ 19:11-21፤ ዳን. 8:23::

ኤ የሚባለው ፊደል ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው አባ ከተሰኘው ፊደል ነው:: ትርጉሙም አባት ወይም ሰው ማለት ነው:: የአባ የመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥር ደግሞ 6 ነው:: ስለሆነም ለኮምፒዩተር ትንታኔ አሠራር A=6, B=12, C=18, D=24 ... Z$156 እያለ ይቀጥላል:: የመጀመሪያው ከፍተኛው የሁሉ አባት እኔ ነኝ ለማለት ይሆን?

ለጊዜው ሥራ ላይ ያልዋለ ወደፊት የሚሰራበት ጉልበት፣ የተከማቸ ጉልበት

እየጣ፣ የማንነትና የኃይማኖት ጥራት እንዳይኖር በመቀላቀል እንዲኖር የሚደረግ ቅስቀሳ

ትርጉም፣ ፍቺ፣ ትንቢት፣ ሚስጢር

ከአንዱ ወደ ሌላው በብዛት መሔድ

ትርጉም፣ ፍቺ

በወቅቱ ያለውን የስርቆትና ዝርፊያ አመጽ ለማስወገድ ሲባል

ማንኛውንም ገንዘብ ነክ፣ የቼክ ልውውጥ አስወግዶ በእጅ ወይም በግምባር ላይ ባለው መታወቂያ ምልክትና በኮምፒዩተር ብቻ ተፈላጊውን ንብረት

| | |
|---|---|
| | ለማግኘት የሚደረግ ልውውጥ ሥርዓት ገበያ ነው:: በገንዘብ መግዛትና መሸጥ አይቻልም:: (ገጽ 43) |
| ግለአማሉታዊነት | ከሌሎች ይልቅ ሁኔታዎች ወደ ራስ እንዲያተኩሩ ማድረግ፣ ራስን ማጽነን:: |
| ግልሙትና | ብቻውን የሚኖር ወንድ (ሴት)፣ ባል (ሚስት) አልባ መሆን (ከሣቴ ብርሃን ተሰማ) ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር መኖርን ጠልተው ጌታ ሲተዋቸው የዲያብሎስ (የአውሬው) ወዳጅ ሲሆኑ |
| ሁላቀፋዊነት | የኃይማኖት፣ የፖለቲካና የኤኮኖሚ ሥርዓት ሂደቶች ሁሉ አንድ ወጥ በሆነ መርህ መካሄድ አለባቸው የሚል ርዕዮት |
| ሁነት | የአንድ ነገር ሆኖ መገኘት፣ ትዕይንት፣ ክስተት |
| ሕላዌ-ምጡቅ | ማንም ሊቀርበው በማይችል ድንቅ ብርሃን የሚኖረውና ካሉት ማንነቶች የሚበልጥ ማንነት ያለው እግዚአብሔር ከሰው መረዳት በላይ የሚኖር ፈጣሪ አውሬውም ራሱን እነደ ህላዊ ምጡቅ (ትራንሴንዳንት) ይቆጥራል |
| የህይወት ሽክርክሪት | የሰው በመሞት ከሥጋው መለየትና በድጋሜ መንፈሱ በሌላ መልክ ተወልዶ ወደ ምድርና ሌላ ዓለም ሄዶ ይኖራል፣ ይፈጠራል የሚል አመለካከት ያላቸው መናፍቃዊ የኃይማኖት ሰርፎች የሚጠቀሙበት ቃል፣ የነፍስ ትስብዕት በመባልም ይጠራል:: |
| ጀሜ | ወህኒ ቤት፣ እስር ቤት |
| ክህደት | ከትክክለኛው የህይወት እምነትና ተግባር መውጣት፣ ከእውነት ማፈንገጥ፣ ከእውነተኛው የህይወት ኃይማኖት መራቅ |
| ልዕለ-ተፈጥሯዊ | ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ማንነት፣ ልዑል እግዚአብሔርን ያመለክታል:: |
| ልዩ ወንጌል | ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮት ጋር የማይስማማ መናፍቃውያን የሚሰብኩት ወንጌል ገላ. 1:6 |
| መካነ-ጣኦት | ፌጕር ወይም አፍን እንደመቃብር ከፍቶ በከፍተኛ የዛር መንፈስ መጮህ (ጋድስ አፍ ዘ ኒው ኤጅ ሙቭመንት የሚለውን የቪዲዮ ካሴት ይመልከቱ) |
| መስፍ | ብረት ለማሸል ሲታሰብ ከጋለ በኋላ እንደ ማረሻና ቢላዋ ተደግፎ የሚቀጠቀጥበት ትክል ወይም ከባድ ተንቀሳቃሽ ብረት |



| | |
|---|---|
| መቅረዝ | የመብራት (የኩራዝ፣ ሻማ) ማስቀመጫ በአ.ኪ. የቤተ ክርስቲያን መገኛ ቦታ ምሳሌ ነው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን |
| መጠራ | ዒላማ ማነጣጠሪያ፣ የተተከለ ማነጣጠሪያ |
| መጥኔ(መጠኔ) | የሚያበረታ፣ ኃይል የሚሰጥ (መጥኔ ይስጥህ እንዲሉ) |
| መጦዝ | ከፍተኛ የእድገት ደረጃ ላይ መድረስ |
| ሚስት (የበጉ) | የብሉይና የአዲስ ኪዳን እንዲሁም የመከራው ዘመን ቅዱሳንና 144000 አይሁዶች ሆነው ከክርስቶስ ጋር በሺሁ ዓመት መጀመሪያ ወደ ምድር ሲመጡ የሚሰጣቸው ስም |
| ማጽነን | አጉልቶ ማለየት፣ ማክረር |
| ማየዊ ትውልድ | ውሃ አፍሳሽ ትውልድ ሲሆን በቀጥታ የአዲሱ ዘመን እንስቃሴን የኮከብ ቆጠራ ስራ የሚያሳይ |
| ማስገበር | ለአንድ ሁኔታ ወይም ማንነት እንዲገዛ ማድረግ |
| ምናብ | በሐሳብ ማየት ወይም መመልከት |
| ነጭና ጥቁር አስማት | በአጋንንት የተሞሉ ሰዎች ሌሎችን በነጭ አስማት ለመጥቀም በጥቁር አስማተ ለመጉዳት የሚጠቀሙበት ዘዴ |
| ነፍስ-ትስብዕት | ደጋግሞ የሰው ነፍስ በስጋ ይወለዳል የሚል የኑፋቄ ትምህርት |
| ኔፍሊማውያን | ቁመታቸው 3 ሜትር የሚደርስ በዘፍ. 6 ውስጥ እንደተጠቀሱት ዓይነት ሰዎች የሰውን ዝርያ አስወግዶ ልዕለ ተፈጥሯዊ የሆኑ በመናፍስት የተሞሉ ሰዎችን በምድር የመግለጽ ሰይጣናዊ ሂደት |
| ንባባት | ጽሁፎች |
| ርቱዕ | ቀጥተኛ፣ ግራ ቀኝ የማይል |
| ሳንትሪክ-ኹወእቦ | አወስቦ፣ የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አባላት በክፉ መናፍስት ከተሞሉ በኋላ የሚፈጽሙት የወሲብ ርኩሰት |
| ተጻብኦ | የጦርነት ፍትወት፣ ከፍተኛ (የጋለ) ፍትወት |
| ቺፕ | በኮምፒዩተር አካል ውስጥ በጣም ትንሽ የሆነ ብዙ የተቀናበሩ ውስብስብ የኤሌክትሪክ መስመሮችን የያዘ እንደ ሂሣባዊ ስሌቶችን ለመሥራትና መረጃዎችን ለመጥጠት ሌሎችንም የኮምፒዩተር ክፍሎች ለመቆጣጠር የሚረዳ የኮ. ዋነኛ ክፍል ነው:: |

| | |
|---|---|
| ውስጥ-ሂያጆች | የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አባላት አስቀድሞ በምድር የነበሩ በኋላ ግን ሞተው ወደ ላይ ያረጉ የሰዎች ነፍሳት በአንድ ወቅት ተመልሰው በሰው ውስጥ በመግባት ይኖራሉ:: እነርሱንም የውስጥ ሂያጆች (ተራማጆች) ይሏቸዋል:: በመሠረቱ አጋንንት ገብተው ሲኖሩባቸው የሰጡት ትርጉም እንጂ የሰዎች መንፈስ (ነፍስ) ይህንን አያደርጉም:: |
| ዘውታሪ | ሳያቋርጡ ለአንድ ማንነት (ለእግዚአብሔር ወይም ለሰይጣን) ተሰጥቶ ሳያቋርጡ መመላለስ:: |



<u>ምህጻረ-ቃላት</u>

| | |
|---|---|
| • እ.ኤ.አ. | እንደ አውሮጳውያን ዘመን አቆጣጠር |
| • እ.ኢ.አ. | እንደ ኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር |
| • ከተመ | ከላይ የተጠቀሰው መረጃ (መጽሔት፣ መጽሐፍ፣ ጋዜጣ ... ቀጥሎ ቁጥሮች ከተጻፉ ገጾችን ለማመልከት ነው) |
| • ክክልበ | ከክርስቶስ ልደት በፊት |
| • ኮ | ኮምፒዩተር |
| • መጽ. ቅ. | መጽሐፍ ቅዱስ |
| • መን.ቅ. | መንፈስ ቅዱስ |
| • ስይ | ስዕሉን ይመልከቱ |
| • መ.ቃ.ይ. | መዝገበ ቃላት ይመልከቱ |
| • ት③ት | ትምህርት |
| • ቤ③ክ. | ቤተ ክርስቲያን |
| • ገ. | ገጽ |
| • ገአሕ | ገንዘብ አልባው ሕብረተሰብ |
| • አ.ኪ.. | አዲስ ኪዳን |
| • አ.ዘ.እ. | አዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ |
| • N.A. | New Age |
| • PP | Pages |
| • UPC | Universal Prodction Code (ዓለም አቀፍ የምርት መለያ ኮድ) |

## ዋቢ መጻህፍት

## ክፍል አንድ


1. Finis Jennings Dake, Dake's Annotated Reference Bible, (Georgia: Dake Bible Sales, Inc. 1961) p. 41NT.
2. A.O-Schnabel, Has God Spoken; (San Diego: Leation Life Pablishers, 1974) p.1
3. ከተመ. ገ. 39-48.
4. ን . ገ. 76-94.
5. Josh, Mc Dowell, Evidence that Demands a Verdict (California: Here is Life Publishers, Inc., 1972) p. 19-21.
6. ከተመ. ገ. 21.
7. Dake NT. p. 243.
8. ከተመ. ገ. 241 (ኢ.ኪ.)
9. KJV. 2ኛ ተሰ.2:1-3::
10. ህያው ቃል ን.
11. Texe Marrs, Book of N.A. Cults & Religious (Austin, Texas: Living Truth Publishers, 1990) pp. 46-48.
12. Texe Marrs, Mystery Mark of the New Age (Illinoise: Good News Publishers, 1988) pp. 56-75.
13. ከተመ. (Ibid)
14. Texe Marrs, Book of ...

141 ዕለተ ሰንበት አዲስ አበባ ታህሳስ 17 ቀን 1986 ገ. 6

14.2 Texe Marrs Ravaged by the New Age.

15. በራሪ ወረቀት
16. አዲስ ዘመን ጋዜጣ አዲስ አበባ-ጥር 3/1986.
17. Don E. Stanton, Alert, (Secundurabad: Maranath Revival Crusade Publishers, 1993) pp. 28.
18. Ibid. p. 27.
19. Stanton. pp. 7-11.
20. Ibid. pp. 21-22
21. ሸት. ከኮምፒውተር የተገኘ.


### ክፍል 2 ፍካሬ 666


1. Dake. NT. p. 307.
2. Ed. F. Vallowe, Biblical Mathematics (Georgia: Vallowe Evangelistic Association, 1995) pp. 13-14.
3. Ibid
4. Dake. NT. p. 279.
5. Herbert, Vander Lugt, There's a New Day Coming (New York: Zonderran Bible Publishers, 1983) pp. 28-29.





6. ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ=ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ (አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት አ.አ. 1948) ገ. 239
7. Taxe Marrs, Mystery ...
8. Radio Bible Class, What can we know about the End Times (Grand Rapids: Thomas Nelso Inc. 1996) pp. 10-11.
9. Theodore H. Epp, The Times of The Gentiles (Lincoln: Back To The Bible Publication, 1969) pp.56-57.
10. Dake's NT. p. 310.
11. Lugt. p. 46.
12. Lugt. pp. 48-50
13. Dake's NT. p. 874.
14. Richard W. D-Hann, Israel and The Nations in Prophecy. (Grand Rapids Michigan: Zondervan Publishing House, 1968) pp. 38-39.
15. Hal Lindsay, The Late Great Planet Earth (Grand Rapids: Zondervan Publishing House, 1970) p.94.
16. ከተመ. ገ. 93-94.
17. Berry Smith, Warning (New Zealand: Wright and Carman Upper Hutt, 1980) pp. 15-18.
18. ከተመ. ገ. 26.
19. Midnight Call Magazine, Midight Call Inc., W. Colimbia, Oct. 1996. No. P.
20. " " " " " " " " Dec. 1994. p.15
21. Jogn Mac. Arthur, The Future of Israel (California: Word of Grace Communication, 1985) pp. 15-17.
22. Dake's NT. p. 309.
23. Warning. pp. 35-36.
24. Salem Kirban, Guide To Survival (Illinoise: Tyndale House Publishers, 1968) p. 151.
25. News From Israel Midnight Call Inc. W. Columbia. July, 1995, p. 19.


### ክፍል 3= ዕይታ 666


1. Warning. p. 23.
2. Mystery... pp. 56-75.
3. ንጉሱ አጥናፉ ኮምፒዩተር ካሮስ የኮምፒዩተር አገልግሎት 1985. ገ. 9.

4. ከተመ. ገ. 45.
5. ከተመ. ገ. 8.
6. Donald D. Spencer. The Isslustrated Computer Dictionary. 3rd Ed (New Delhi: Universal Book Stall. 1986) p.
7. Salem Kirban. Satan's Mark Exposed (Chattanooge) USA: AMG Publishers, 1978) p. 133.
8. Mary, Stewart Relfe, When Your Money Fails, Montgomery, (Alabama: Ministries Inc., 1981) pp. 44-48.
9. Dr. David Webber, 666 The Mark Isready (Dklahoma: Midnight Call Ministries) p. 93
10. ኮምፒዩተር. ገ. 9
11. አዲስ ዘመን:: አዲስ አበባ፣ ሚያዝያ 20፣ 1983. ገ. 5.
12. ግምማ ሰይፉ ብታምኑም ባታምኑም (ትርጉም) (ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ: 1982) ገ. 19-20::
13. Popular Science Magazine. GM Corp. Canada, 1994, p. 28.
14. 666 ... pp. 14-15.
15. Texe Marrs-Mega Force (Srgns & Wonders of the Coming Chaos) (Living Truth Publishers. Austin Texas, 1988) pp. 97-98.
16. ትንግርት ታምቤክ ኢንተርናሽናል አዲስ አበባ ሐምሌ-ነሐሴ 1985፣ እትም 02 ገ. 33-34::
17. ምስክር መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አዲስ አበባ ጥቅምት 1989፣ ገ. 22-23::
18. ትንግርት ታምቤክ ኢንተርናሽናል አዲስ አበባ ህዳር 1986 እትም 04. ገ. 11::
19. Mega Force. (ከተመገ)
20. አዲስ ዘመን ኢ.አ. የካቲት 15 1989. ገ. 7::
21. 666... pp. 50-63.
22. Alert. No. 58. pp. 3-16.






23. Guide To Surrival: pp. 153-154.
24. Mega Force. pp. 78-79.
25. 666 ... p. 22.
25.1 Relfe. p. 168.
26. Mystery ... pp. 57-60.
27. News From Israel. Feb. 1995, pp. 23-24.
28. " " " June, 1993, P. 17.
29. " " " Jan., 1993, p. 25.
30. " " " May, 1992, pp. 16-17.
31. ሳይኮሎጂ ጋዜጣ አዲስ አበባ 1ኛ ዓመት ቁ. 2 1988. ገ. 1፣ 6-7::
32. ጉዳናው አዲስ አበባ 1ኛ ዓመት ቁ. 30፣ 1986. ገ. 1፣4::
33. Relfe. p. 164.
34. ከተመ.
35. ከተመ. ገ. 164-165::
36. Warning. p. 24.
37. ጉዳናው ጋዜጣ አዲስ አበባ 1ኛ ዓመት መስ. 13 1987. ገ. 3::
38. Wim Maego. 50 questions Most Frequently Asked About The Second Coming. (Columbia: Midnight Call Inc., 1980) p. 57.
39. ጉዳናው አዲስ አበባ 1ኛ ዓመት ቁ. 59 ጥቅ. 25፣ 1987. ገ. 1-2::
40. የፍቅር ማኅደር ጋዜጣ አዲስ አበባ ቁ. 106 ሚያዝያ 30 1990፣ ገ. 3 እና 7::
41. ከተመ. ቁ. 113
42. " " 117
43. Relfe ,,, " 123
44. " " 124
45. " " 130-139.
46. ((Pamphlete by Taberah World Mission, Illinois.)

## ክፍል 4 መፕኒአዊ ኢላማ



1. ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ገ. 241::
2. ከተመ. ገ. 530::
3. Jack Simpson. Good Vs. Evil (A War of the Spirits) (Satan Rosa. California: Restoration Press, 1995) p. 193-196.
4. Dake's. p. 243.
5. Simpson. pp. 217-219.
6. ከተመ. ገ. 221::
7. ን ገ. 224::
8. Texe Marrs-America Shattered, Austin, Texas, Living Truth Publishers, 1991) pp. 33.
9. መጋቢ ስዩም ገ/ጻድቅ፣ ዶ/ር አታላይ ዓለም፣ አቶ ፈቀደ ተፈራ የቤተ ክርስቲያን አመራር (አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1990) ገ. 13::
10. America-Shattered. p. 3-6.




መጋቢ ተኩ ከበደ የተወለዱት በ1948 ዓ.ም. በናዝሬት ከተማ ቢሆን የ1ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በናዝሬት ከተማ ቀ.ኃ.ሥ.ቁ. 4 ት/ቤት እና በመጽሐፍ ቅዱስ አካዳሚ ት/ቤት ተከታትለዋል፡፡ በተጨማሪም በናዝሬት አፄ ገላውዴዎስ 2ኛ ደረጃ ት/ቤትና በአዲስ አበባ ተግባረ ዕድ ት/ቤት በተለያዩ ጊዜያት ተምረዋል፡፡ በ1978 ዓ.ም. ከአ.አ ንግድ ስራ ኮሌጅ ተመርቀው ለ2 ዓመታት በኢት. እብነ በረድ ኢንዱስትሪ ከሰሩ በኋላ በ1980 [illegible] ላይ ሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልግሎት ወጥተዋል፡፡ ...ረስ በ.ኢ.ቲ.ቢ (E.T.C) የስነ መለኮት ድግሪያቸውን ያዘው በደቡብ አዲስ አበባ መሠረተ ክርስቶስ ቤተ/ክ ለ4 ዓመታት ያህል በመጋቢነት አገልግለዋል፡፡ ከዚያም በዋናው መ.ክ. ቢሮ በትምህርት ክፍል ተጠሪ ሆነው በማገልገል ላይ ሳሉ ለጥናት ወደ አሜሪካ ሄደው ከ1993 እስከ 1994 በኢንድያና ኤልካርት በAMBS ሴሚናሪ በማስተርስ ኦፍ ቲዎሎጂ እና ኢቲክስ ተመርቀው ከተመለሱ በኋላ እስካሁን በዋናው ቢሮ መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ጽ/ቤት የትምህርት ክፍል ኃላፊ ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡

መጋቢ ተኩ ጌታን በመ.ሠ.ክ.ቤ/ክ ከተቀበሉበት ከ1968 ዓ.ም. ጀምሮ ጌታ በልባቸው ካስቀመጠው ትምህርቶች ውስጥ ዋንኛው ነገረ ፍጻሜና ትንቢት ሥነ መለኮትን መመርመርና ምላሽ መስጠት ነው፡፡ ፍካሬ 666ትን ለማዘጋጀት ከ29 ዓመታት ያላነሰ ዝግጅት አድርገዋል፡፡ ስለ ነገረ ፍጻሜ ከ50 እስከ 30000 ምዕመናን በተሰበሰቡበት መድረክ ለማስተማር ጌታ ረድቷቸዋል፡፡ በተለይ በ1982 ዓ.ም. ከሾኔ አምቡርሲ ኮንፍራንስ በኋላ ብዙ በዎች በመጽሐፍ በካሴቶችና በመጽሔቶች ትምህርቱ እንዲዘጋጅላቸው በተደጋጋሚ ጠይቀዋል፡፡ እግዚአብሔር በልባቸው ካስቀመጠው ሸክምና ምዕመኑም ካቀረበው ጥያቄ በመነሳት ይህንን መጽሐፍ ለእግዚአብሔር ጉባኤ አትርበዋል፡፡ ስለሆነም በጥንቃቄ እና በማስተዋል እናንብበው፤ ከመናወጥም በተጠበቀ መንፈስ እንመርምረው፡፡ ለጌታ ምፅዐት ራሳችንን እናዘጋጃለን፡፡

በማይሳሳት መለኮታዊ ምህንድስና ሁሉን የሚቆጣጠረው ጌታ እግዚአብሔር ይመስገን፡፡ አሜን!!




በአውሬው ዘመን 666 የሌለባቸው እናቶች የታመመ ልጃቸውን እንኳን ማሳከም አስከማይችሉ ይሆናል

ዋጋው ብር 13.00